# ክፍል ፪

# ከኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር በሐራሬ ከተማ የተደረገ ቃለ መጠይቅ

***ገነት - ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ መቼና የት እንደተወለዱ፣ በማይያዝም ስለልጅነት ጊዜዎ ቢገልፁልኝ?***

***መንግሥቱ*** - የተወለድኩት ግንቦት 19፣ 1933 ነው:: ልጅ ሆኜ ሲነ ገረኝ ከነበረው እንደማስታውሰው «መንግሥቱ» የሚለው ስም የወ ጣልኝ ከፋሺስት ወረራ በኋላ ነፃነታችን በተመለሰበት ዓመት በመወ ለዴ ነው:: የተወለድኩት አዲስ አበባ ውስጥ ጊዮርጊስ አጠገብ አሁን ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በሚገኝበት አካባቢ ነው:: እንዲት አነስተኛ የጠ ላት ሥሪት የሆነች ቤት ነበረች:: እዚያ ውስጥ ነው የተወለድኩት::

አንድ ጊዜ ወላጅ አባቴ በአንድ ቃለ መጠይቅ ስለራሳቸውም ሆነ ስለኔ አሉ ተብሎ በመጽሔት የወጣውን ታሪክ እኔ አላውቀውም:: እውነት አይደለም:: አባቴ እንደዚያ ያለ ነገር ይናገራሉ ብዬም አላም ንም:: ማን ፈጥሮ እንደፃፈው አላውቅም:: እውነቱ ከዚህ የሚከተለው ነው::

የአባቴ አባት አቶ ወልዴ አያና የሸዋ ኦሮሞ ሲሆኑ፣ በግብርና የሚተዳደሩ ነበሩ:: የተወለዱትና ብዙ ጊዜ የኖሩት ፋሪ አካባቢ ልዩ ስሙ ረጂ በተባለው ቦታ ነበር:: አያቴ በወቅቱ እንደነበረው የገበሬ ሠራዊት ነፍጠኛ ነበሩ:: የአሁኖቹ ጠባብ ብሔረተኞች ሊያጥላሉት እንደሚሞክሩት የቃሉን ትርጉም ከማዛባት የሚመጣ እንጂ ነፍጠኛ ማለት ባለጠመንጃ ማለት ነው:: ነፍጥ ወይም ጠመንጃ ከሚለው የመጣ ነው:: ሌላ ምንም ትርጉም የለውም:: ነፍጥ መሣሪያው ነው:: መሣሪያውን ያነገበው ነፍጠኛ ይባላል::

አባቴ የተወለዱበትን ይህን አካባቢ ካደግሁኝ በኋላ ሄጄ አይቼ ዋለሁ:: ዛሬ ዕድሜ ተጭኗቸውና በጤናም ማጣት ግማሾቹ ሞተው አንዳንዶቹም ከሥፍራው ሄደው ነው እንጂ ከአባቴና አያቴም ጋር የነበሩ ሰዎችን በልጅነቴ እየሄድኩኝ አያቸው ነበር:: የአያቴ መሬት ነው:: የፈራረሰች ጎጆና ያርሱት የነበረውን መሬት ሁሉ አይቼዋለሁ::



አባቴ ኃይለማርያም ወልዴ፣ ለአያቴ ለወልዴ አያና የመጀመሪያ ልጅ ናቸው:: ሁለተኛው ልጃቸው አሥራት ወልዴ[6] ነው:: በዚህ ዓይነት ከቆዩ በኋላ አያቴ ታመው አረፉ:: አባቴም እዚያው እስከጣሊያን ወረራ ድረስ ቆይተው እናታቸውን ለመደገፍና ታናሽ ወንድማቸውን ለማስተማር ጥረት ያደርጉ ነበር:: ሆኖም ግን ወጣትና ከተማ ቀመስ በመሆናቸው የግብርናውን ነገር ብዙም አላወቁበትም:: ጣሊያኖች ከመጡ በኋላ የዶሮና የዕንቁላል ንግድ በጣም ደርቶ ነበር:: እሳቸውም ዶሮና ዕንቁላል እያስፈለፈሉ በገፍ በማቅረብ ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር ችለዋል:: ይሄ ነበር ያባቴ የመጀመሪያ ሥራቸው:: በዚህም ሥራ ብዙ ውጣ ውረድ ያጋጥማቸው እንደነበር አጫውተውኛል::

ጣሊያን ከተባረረ በኋላ ዘመናዊው የጦር ሠራዊት እንደገና ሲቋቋም ከመጀመሪያዎቹ ተቀጣሪዎች አንዱ ሆነው ተቀጠሩ:: ቤታቸውንም ምድር ጦር አቅራቢያ በዱሮው አውሮፕላን ማረፊያ አድርገው እዚያ ይኖሩ ጀመር:: ክፍላቸው 11ኛ ሻለቃ ነበር:: ከመጀመሪያዎቹ ተቀጣሪዎች መካከል በመሆናቸው ቁጥራቸው በአንድ ሺህ ተራ ውስጥ ነበር[7]:: «ተራ ቁጥር አንድ ማን ነው?» ብዬ ስጠይቃቸው፣ ‹ኰሎኔል አስፋው ሺ. አምዖ ናቸው› የሚሉኝ ትዝ ይለኛል:: እንግዲህ እኔ የተወለድኩት እሳቸው የግብርናውን ነገር ትተው ከተማ ከገቡ በኋላ ነው ማለት ነው::

በእናቴ በኩል ስንሄድ አያቷ፣ እናቷና አባቷ፣ ዘመዶቿ ሁሉ ተጉለቴዎች ናቸው::ይህ የሰሜን ሸዋ ክፍል መሬቱ የተበላ በመሆኑና ከብቱም በተደጋጋሚ ችግር እያለቀበት ነዋሪው «አገር ለማቅናት» እየተባለ ወዲያ፣ ወዲህ በማለት ይኖራል:: አገር በምትወረር ጊዜም የገበሬ ወታደር እየሆነ ይዘምታል:: የናቴ አያቷ ወልደአማኑኤል ጎርፍነህ ይባላሉ:: ሁለት ታላላቅ ወንድሞቻቸው አድዋ ዘምተው በጦር ሜዳ ወድቀዋል:: ወልደአማኑኤል ጎርፍነህ ራሳቸው ምዕራብ ሸዋ ውስጥ በባሻ ማዕረግ የገበሬ ሠራዊት አለቃ ሆነው እየተዘዋወሩ ፀጥታ ያስከብሩ ነበር:: ለዚህም አገልግሎታቸው በአዲስ ዓለም ወረዳ ሁለት ጋሻ መሬት ተሰጥቷቸዋል:: ይህም ከአዲስ አለም ከተማ በግምት አንድ አሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ በርጋ የሚባል ቦታ ነው:: ክሪሴና በርጋ የሚባሉ ወንዞች የሚያዋስኑት ሰም መሬት ነበር:: እዚያ ላይ ከብት እያረቡና እያሳረሱ ይኖሩ ነበር:: ሃብታም ገበሬ

---

[6] በዚምባቡዌ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩ የመንግሥቱ አጎት::

[7] የጦር ሠራዊት ቁጥራቸው 1204 ነበር::

ነበሩ:: ወንድሞቻቸውና ሌሎች ጭሰኞችም መሬታቸው ላይ አብረዋቸው ይኖሩ ነበር::

የእናቴ የመጀመሪያ የሕግ ባሏ እዚያው አዲስ ዓለም ተወልዶ ያደገ፣ ከዘመዶቿ ጋር በቅርብ የሚተዋወቅ የእነዋሪ ማርያም ቄስ ልጅ የነበረ ራሱም ዲያቆን ነው:: ኪዳኔ ተፈራ ይባላል:: ከናቴ ጋር በሕግ ተጋብተው አብረው ሲኖሩ ቆይተው በኋላ ተለያዩና እናቴ ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ርቃ ለመሄድ ተገደደች:: የተለያዩትም በቤተሰብ ግፊት ነበር:: ነገሩ እንደዚህ ነው::

የእናቴ አጎት (የአቶ ወልደአማኑኤል የመጨረሻ ልጅ) አስፋው ወልደአማኑኤል የሚባለውና የእናቴ ታናሽ ወንድም ድረስልኝ ተሰማ የሚባለው በአዲስ አለም አካባቢ አዛዥ ዘውዴ በሚባሉ የኀበዝ አለቃ ሥር የተሰባሰቡትን ተቀላቅለው ወደአርበኝነት ገቡ:: እናቴ ከጓደኞቿ ጋር በመሆን ለነኚህ አርበኞች ስንቅ ታቀብል ጀመር:: በምብና ጥይት በውሃ እንስራ አድርገው ደብቀው በማድረስ፣ መረጃ በማቀበል ይሠሩ ነበር:: ከዚህ በኋላ ይሄ ሥራዋ በጣሊያኖቹ ዘንድ ሲታወቅ እናትና አባቷን ካንድም ሁለት ጊዜ አሠሯቸው:: ቤታቸውን ሌሊት በተኙበት መጥተው አቃጠሉባቸው:: ብዙ ችግር ደረሰባቸው:: ይሄ ዝም ብሎ ወሬ ሳይሆን ክልሉና አገሬው የሚያውቀው ታሪክ ነው::

እናቴ የምትኖረው ከባሏ ቤተሰቦች ጋር ነበር:: ‹ይሄን ተግባርሽን ካላቆምሽ ላንቺም ጥሩ አይደል፣ እኛንም ታስፈጂናለሽ› በማለት ቢመክሯት ‹እምቢ› ስላለች ከባሏ ጋር አለያዩዋቸው:: በዚህ ዓይነት ነው ሁለቱ ወጣቶች የተፋቱት:: ከዚያ ወደቤተሰቦቿ ተመልሳ እዚያም ይሄንኑ ሥራዋን ትቀጥላለች:: በኋላ ነገሩ የሚያሰጋ ሲሆንና ለሷም ሆነ ለወላጆቿ ሕይወት አደገኛ እየሆነ ሲመጣ በስውር ወደአዲስ አበባ ላኳት:: አራት ኪሎ አርበኞች ሕንፃ አጠገብ ይኖሩ የነበሩት አክስቷ ወይዘሮ ታጠረች ውቤ ቤት መኖር ጀመረች:: እዚያ እያለች ነው ከአባቴ ጋር የተገናኙት:: የተጋቡት በሥርዓትና በሠርግ አይመስለኝም:: በሃገራችን በተለምዶ ሲደረግ እንደምናየው ኃይል በተመሳበት ሁኔታ፣ ማለትም በጠለፋ ነው የወሰዷት:: በዚህ ዓይነት ሲኖሩ እኔ ተወለድኩ:: እናቴ ምንም በፈቃዷ ወዳ ባታገባቸውም ለኔ በነበራት ከፍተኛ ፍቅር የተነሳ ያ ግንኙነት በግድ ወደቋሚ ትዳርነት ተለውጦ አብረው መኖራቸውን ቀጠሉ:: ከዚያ በኋላ ታናሽ እህቴ አመለወርቅ ኃይለማርያምና የሷ ተከታይ ጌታነህ ኃይለማርያም ተወለዱ::



አባቴ ውትድርናቸውን በጀመሩ ዘመን ሠራዊቱን ያሰለጥኑ ከነበሩት እንግሊዞች መሣሪያ ጥገና ተምረው ነበርና በነበረው የባለሙያ እጥረት የተነሳ በየግዜው ካንዱ ክፍል ወደሌላው እየተዘዋወሩ ይሠሩ ነበር:: ሲዳሞ ነገሌ፣ ከፋ ክፍለ ሃገር፣ ሸዋ ክፍለ ሃገር፣ ሰሜንና ምሥራቅ ሁሉ እየተዘዋወሩ ሠርተዋል:: እሳቸው በታዘዙ ቁጥር በየአገሩ ሲሄዱ እናቴም ከኔ ላለመለየት እየተከተለች ስትንከራተት ኖራለች:: እኔ ለሷ፣ እሷም ለኔ የነበረን እጅግ ከፍተኛ ፍቅር ከዚህ የመነጨ ነው:: እናት ለልጇ፣ ልጅም ለናቱ ያለው ፍቅር አጠያያቂ ባይሆንም ለሷ የነበረኝ ፍቅር ልዩ ነበር:: አባቴ ለሥራ ስለሚዘዋወሩ ብዙ ጣዕማቸውን አላውቅም:: እኔ እናቴን ነው የማውቀው:: አልፎ አልፎ አያቶቼ ጋር ከመሄዶ በስተቀር የኖርኩት ከሷ ጋር ነው::ታዲያ የእናቴ ቤተሰቦች የሷ ሁኔታ እያሳዘናቸው ከወታደር ጋር ምን ያንከራትትሻል፤ አርፈሽ ተቀመጪ እያሉ አልፎ፣ አልፎ ጣልቃ ሲገቡ አባቴ ትንሽ ሞገደኛ ቢጤ ነበሩና ‹እሷን ማስቀረት ትችላላችሁ ልጄን ግን የሚነጥቀኝ የለም› ብለው እኔን ይዘው እልም ይላሉ:: ይሄኔ እሷ እኔን ብላ ተከትላ ትመጣለች::

በመጨረሻ ኦጋዴን ከእንግሊዞች አስተዳደር ወጥታ ወደኢትዮጵያ አስተዳደር ስትመለስና ሠራዊቱ እዚያ ሲመደብ አሁንም አባቴ ወደዚያው ሄዱ:: እናቴ ግን እኛን ይዛ ድሬዳዋ ቀረች:: በ1942 ነው:: እሷ ታዲያ ደገኛ በመሆኗ የድሬዳዋን የአየር ንብረት አልተቋቋመችውም:: ወባውም ምኑም ሰውን በቀላሉ ያጠቃል:: በቀላሉ ሊድን የሚችል በሽታ ሁሉ ሰው ይገድል ነበር:: መድሃኒቱስ፣ ሕክምናውስ፣ መቼ እንደልብ ይገኛል? እና ያን ጊዜ ነው ለጥቂት ቀናት ብቻ ታማ እናቴ ያረፈችው:: ባረፈች ጊዜ ሦስቱም ልጆቿ አጠገቧ ነበርን:: የዘጠኝ አመት ልጅ ነበርኩ:: የናቴ ሞት ያደረሰብኝ ኀዘን ይህ ነው አይባልም:: ለሷ የነበረኝ ፍቅር እጅግ ከፍ ያለ ስለነበር ትዝ ባለችኝ ቁጥር አለቅስ ነበር:: በእርግጥ ዛሬ ከጊዜ መቆጠር ብዛት የማስታወሰው ገጿ እየደበዘዘ ቢሄድም ትዝታዋ አሁንም ከኔ ጋር ነው::

*ገነት - ከደጃዝማች ከበደ ተሰማ ጋር ዝምድና የላችሁም?*

***መንግሥቱ*** - እኔን ‹የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ልጅ ነው› እያሉ የሚያወሩ እንዳሉ ሰምቻለሁ:: ይህንን ከሚያወሩት መካከል አንዳንዶቹ ታሪኬን ከማንም የበለጠ በሚገባ የሚያውቁ ናቸው::

ደጃዝማች ከበደ ተሰማን የማውቃቸው ገና አራተኛ ክፍለ ጦር እንደገባን ነው:: እኔ ከዚያ በፊት ደጃዝማችን ጨርሶ አላውቃቸውም::

ከጊዜ በኋላ ልጃቸው ካሣ ከበደ ጓደኛዬ ሆኗል:: ከካሣ ጋር ቅርበታችን ያው የወንድም ቃህል ስለነበር ‹እሱ ወንድሙ ነው:: በደም አባቱ ናቸው› የተባለው ከዚህ የመጣ ሊሆን ይችላል:: ይሄ ወሬ መወራት የጀመረው ገና አራተኛ ክፍለ ጦር እያለን ነው:: እንዴት እንደሆነ ላስረዳሽ::

ያኔ ገና ሥራ መጀመራችን ነው:: ሕዝቡ በምንሰራው ሥራ ሊተባበረን ይፈልጋል:: የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ ይፈልጋል:: ሰዎች ጥቆማ ያመጡልናል:: ደብዳቤ ጽፈው ይመጣሉ:: ‹እከሌ እንደዚህ ሕዝብን በድሏል፣ እንዲህ የተባለው ባለሥልጣን እንደዚህ አድርጓል› እያሉ ያመጡልናል:: አንዳንዱ እንዲያውም ራሱ አስሮ ይዞልን የሚመጣም ነበረ:: አንዱን የራስ ልጅ እንግሊዝ አገር የተማረና ሰላሌ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበረ በገመድ ግጥም አድርገው አሥረው በመኪና ጭነው አመጡት:: «ምነው?» ሲባሉ፣ ‹ይሄ ትልቅ ሌባ ነው› አሉ:: ጄኔራል ኢሳይያስን ተማሪዎች ናቸው ይዘው አራተኛ ክፍለ ጦር ድረስ በታክሲ ያመጧቸው:: ታምኛለሽ? ጄኔራል ኢሳይያስን! እዚህ ሲጋራ ፋብሪካ አጠገብ ድንጋይ እየወረወሩ ከበው ነው የያዟቸው:: ደጃዝማች እከሌ ነው ተብሎ ተይዞ ይመጣል፤ ይግባ ነው:: ፊታውራሪ እከሌ ነው ይባላል፤ አስገባው ነው:: ሌላው ቀርቶ ለሹመት ታጭተው ልኾማቸው ጠርተናቸው የመጡ ሰዎች ታስረው አግኝተናል::

ሰዎች አጥፍተዋል ተብለው በሕዝብ እየተከሰሱ ነው የሚመጡልን:: በሐቅም፣ በቂም በቀልም ሊሆን ይቻላል:: እኛ ማንን እንደምንፈልግና እንደምናስር መስፈርት ካላበጀንለት አገሩ ሁሉ ሊታሰር ሆነ:: ስለዚህ አንድ ገደብ ይደረግለት ብለን ስብሰባ ላይ ተነሳ:: በዚያው ሰሞን ሊታሰሩ የታሰቡ የብዙ ሰዎች ስም ዝርዝር መጥቶልኝ ነበርና ስመለከት የጄኔራል ግዛው በላይነህ፣ የጄኔራል ጌታቸው ናደው፣ የአቶ ይድነቃቸው ተሰማና የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ስም አለበት:: ከነዚህ አንዳንዶቹን ስሞች ስለማውቃቸው ነገሩ ከንክኖኛል:: ጄኔራል ግዛውን በደንብ ስለማውቃቸው የወነጀሏቸው እንዲሁ ዝም ብለው እንደሆነ መረዳት አላቃተኝም::

አቶ ይድነቃቸውም ቢሆን ታዋቂ ሰው ናቸው:: በአስተዳደር ገብተው ገንዘብ አጠፋ አይባሉ፤ ሕዝብ በደሉ አይባሉ:: የሳቸው ስም ለምን እዚህ ገባ? እሳቸው ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ስፖርት ሲደክሙ የኖሩ ሰው ናቸው:: በፊፋና በሌሎችም ዓለም አቀፍ የስፖርት መድ



ረኮች በሚያደርጉት ተሳትፎ ውጪ ይሄዳሉ:: በቂ ገንዘብ ሊያገኙም ይችላሉ:: ታዲያ ገንዘብ አላቸው ተብሎ መወንጀል አለ እንዴ?

ደጃዝማች ከበደ ደግሞ ከ20 ዓመት በፊት ጡረታ የወጡ ሰው ናቸው:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ውጥንቅጥ ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰው ናቸው:: ከንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ጀምሮ በቤተመንግሥት አካባቢ ስለቆዩ የቤተመንግሥቱን ሥርዓት ጥርሳቸውን ነቅለው ያደጉበት ነው:: ስለዚህ ንጉሡ ስለሚያቀርቧቸው ሌሎች ሊነግሯቸው የማይደፍሩትን እሳቸው በግልፅ ሊናገሩ ስለሚችሉ ጃንሆይ አጠገብ ቢሆኑ ለኔ ይጠቅሙኛል ብሎ ያመጣቸው እንዳልካቸው ነው:: የግቢ ሚኒስትር አደረጋቸው:: እና ምን አድርገው ነው ብዬ ሳጣራ ኰሎኔል ደምሴ ዱሬሳ የሚባል የኛው የደርግ አባል የሆነ ሰው ወንጅሏቸው እንደሆነ ደረስኩበት:: ደምሴ ደግሞ የልጆቻቸው፣ የካሣ ጓደኛ የነበረ መሆኑን አጣራሁ:: (አባትህን ደምሴ ወንጅሏቸው ነበር ብዬ ይሄንን ጉዳይ እስከዛሬ ለካሣ አልነገርኩትም::) ተማሪ ሆኖ ካሣ ከበደ፣ ደምሴን ይረዳው ነበር:: እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የልጆቻቸው ጓደኞች የደጃዝማች ቤት እንደቤታቸው ነው:: ይወጣሉ፤ ይገባሉ:: ይረዷቸዋል:: ደምሴ በሶሺል ሳይንስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመመረቁ በፊት ገና ተማሪ እያለ ለልምምድ ሄዶ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ተመድቦ ይሠራ ነበር::

እኔ ደግሞ ከደጃዝማች ጋር ትውውቅ ባይኖረንም «የታሪክ ማስታወሻ» የሚለውን መጽሐፋቸውን አንብቤያለሁ:: እዚያ ውስጥ ስለበላይ ዘለቀ ታሪክ በዚያን ዘመን እውነቱን የፃፉ በመሆናቸው በልቤ ለሳቸው አክብሮት አለኝ::

ስብሰባው ላይ ደምሴ ብቻውን ተጋትሮ ካልታሰሩ ይላል:: ቤቱም አልተቀበለውም:: በዚህን ጊዜ «ደምሴ፣ እኚህ ሰው የቀረበባቸው ክስ ተቀባይነት የለውም:: የሚያሳስራቸው ነገር አለ ብሎ ቤቱም አላመነበትም:: አንተ ብቻህን በምታቀርበው ክርክር ያንድ ሰው ዕድል አይወሰንም» አልኩት:: ቢበሳጭም ‹እሺ› ብሎ ቁጭ አለ::

ማምሻውን ቤቱ ሄዶ ኢሕአፓን ይሁን ወይም ሌላ ወረቀት መበተን የተካነ ቡድን አነጋገረ መሰለኝ ጠዋት ስናይ አገሩ ሁሉ ወረቀት በወረቀት ሆኗል - መንግሥቱ ኃይለማርያም የከበደ ተሰማ ልጅ ነው የሚል:: በደርግ ስብሰባ ላይ ስለወረቀቱ መበተን ተነገረ::‹ይሄ ነገር ከዚህ ቤት ነው የወጣው:: እዚህ ያለነው ሁላችንም ቃልኪዳን የገባን የደም ጓደኞች ነን:: ለትልቅ ዓላማ ቆመን ብንሞትም አብረን ለመሞት

ተዘጋጅተናል:: እያንዳንዳችሁ የየራሳችሁ ፍላጎትና ቂም በቀል ሲኖራችሁ ይችላል:: እያንዳንዳችሁን ለማስደሰት ስንል ደግሞ ሰውን ያለጥፋቱ እንደ እንስሳ አናጉርም:: ከበደ ተሰማ ይታሰሩ፣ ወይስ አይታሰሩ? በሚለው እዚህ ሁላችንም ተነጋግረን የሚያሳምነን ነገር ስላላገኘንበት መቶ አሥራ ዘጠኝ ሰው ‹አይታሰሩ› ሲል፣ አንድ ተቃውሞ በዲሞክራሲ መንገድ ያለፈ ውሳኔ ነው:: ይሄን ውሳኔ አለመቀበል ብቻ ሳይሆን አልፎ ተርፎ ከተቃዋሚ ጋር ሆኖ ወረቀት መበተን ምን ማለት ነው!?› ተባለ:: በአባላቱ ተወገዘ::

*ገነት - ደምሴ መሆናቸውን በትክክል አጋልጣችሁ ተናገራችኋል ወይ?*

***መንግሥቱ*** - ዞሮ፣ ዞሮ እሱ መሆኑን ሁላችንም አውቀናል:: እኔ ደግሞ በአደባባይ ስሙን ጠርቼ ላጋልጠው አልፈለግሁም:: ደምሴ ዴሬሳ መሆኑን ግን አውቂያለሁ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይሄንን ስም ወርሻለሁ:: የደጃዝማች ከበደ ልጅ ነው እየተባለ የተወራው በዚህ ምክንያት ነው::እኔ ግን ነገሩን ትቼዋለሁ:: እንዳውም ቀልድ የሚወዱ የደርግ አባላት በጨዋታ መሐል በቀልድ የሚያነሱት ነገር ነው:: ደምሴ ያወራው ነገር እያሉ ይስቁ ነበር::

# አብዮቱ ሲፈነዳ

*ገነት - በየካቲት፣ 1966 የፈነዳው የሕዝብ ንቅናቄ ወቅት የሠራዊቱ እንቅስቃሴ እንዴት ነበር? በተለይም እርስዎ በነበሩበት በሐረር የነበረውን ሁኔታ ቢያብራሩልኝ?*

***መንግሥቱ*** - ሰኔ፣ 1966 ላይ ደርግ ከመቋቋሙ በፊት የተካሄደው የሠራዊቱ እንቅስቃሴ በሦስት ምዕራፍ የተከፈለ ነው:: በመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ መኰንኖች ያሉበት ስብስብ ዓይነት ነገር በአራተኛ ክፍለ ጦርና በመኰንኖች ክበብ አካባቢ ተጀመረ:: በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቅናቄውን ክቡር ወደሆነ ሕዝባዊ ዓላማ ለመለወጥ የፈለጉ ሰዎች በጥቂቱ ቢኖሩም ሌሎች ደግሞ የተፈጠረውን እገጭ እጓ በማዳፈን ያለው ሥርዓት የሚቀጥልበትን መንገድ የሚፈልጉ ነበሩ:: እነዚህ የሠራዊቱ አባሎች ሁኔታው እነሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ እንዲሄድ ለማድረግ የመጡ በመሆናቸው ሁሉም በዓላማና በሃሳብ አንድ ሆነው



መግባባት አልቻሉም:: የዚህ እንቅስቃሴ ተካፋዮች በሰራዊቱ ስም ብዙ ብለው ነገሩን እንዳልሆነ አድርገው ሲመለሱ በሠራዊቱ በኩል ‹ዱሮውንስ ማን ወከላቸውና በኛ ስም ተነሱ?› የሚል ጥያቄን አስነሳ:: ይህ የመጀመሪያ ዙር እንቅስቃሴ ነው::

ከዚያ በኋላ እነኰሎኔል አጥናፉ አባተ የተካፈሉበት ሁለተኛ ዙር ንቅናቄ ፈነዳ:: ይህ ንቅናቄ በነኰሎኔል ዓለማየሁ ደስታና በልጅ እንዳልካቸው መኰንን ጥበብና ሴራ እነኰሎኔል ያለምዘውድ የገቡበት ሲሆን፣ ለውጥ ለማምጣት ወይም እንቅስቃሴውን ለማጎልበት ሳይሆን ከልጅ እንዳልካቸው ጋር በተሳሰረ ተፈላላጊነትና ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነበር::

ይህ ኰሚቴ በነኰሎኔል ያለምዘውድ ቁጥጥር ሥር ሙሉ በሙሉ በመዋሉ ብዙ ሳይራመድ ፈረሰ:: ከመፍረሱ በፊት ግን ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርቦ ስለተፈጠረው ሁኔታ ይቅርታ ጠይቆ ተሰናበተ:: ከዚያ በኋላ በገዢው መደብ ተመክሮበት ለሠራዊቱ የደሞዝ ጭማሪ ተደረገ::

በዚህም ሕዝቡ ብሶቱንና ቁጣውን በተለያየ መንገድ በመግለጽ ተቃወመን:: በውነቱ ወታደራዊ ልብስ ለብሶ መሄድ እስኪያስጠላን ድረስ እንወቀስ ጀመር:: በዚህን ጊዜ በራሳችን አነሳሽነት የቀወሰንን ወጣት መኰንኖች ምስጢራዊ ግንኙነት ማድረግ ጀመርን:: ይህ የሦስተኛው ዙር እንቅስቃሴ ጥንስስ ሆነ::

የነኰሎኔል ያለምዘውድ ስብስብ የሰጠን ትምህርት ቢኖር አንዳንድ ሰዎች በሠራዊቱ ስም ተሰብስበው እነሱ የመሰላቸውን የማይረባ ነገር አከናውነው እንደሚመለሱና የሠራዊቱንም ሆነ የሕዝቡን ጥያቄ ዳር ለማድረስ ያልቻሉት ከመደብ ጀርባቸውና ለሥርዓቱ ካላቸው ታማኝነት የተነሳ እንደሆነ ነው:: ስለዚህ ካሁን በኋላ ያለው የሠራዊቱ እንቅስቃሴ ምን መሆን አለበት? በማለት ከብዙ ማውጣት ማውረድ በኋላ ከሻለቃ ያልበለጠ ማዕረግ ያላቸው መለዮ ለባሾች ብቻ የሚሳተፉበት እንዲሆን ተወሰነ:: ለራሳቸው ጥቅም ያደሩ፣ ከገዢው መደብ፣ ከመሳፍንት፣ ከመኳንንት ጋር በልዩ ልዩ መንገድ የተሳሰሩ ሰዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ያመጣሉ ብሎ ማሰብ ስሕተት ስለሆነ እነሱን እዚህ ውስጥ ማካተቱ ጥፋት ነው የሚል ውሳኔ ላይ ተደርሶ ነው ከሻለቃ ማዕረግ እንዳይበልጥ የተባለው:: ስለዚህ በሠራዊቱ ንቅናቄ ታሪክ ውስጥ አብዮታዊ ባሕሪ የያዘውና የገፋበትም ይሄ ሦስተኛው እንቅስቃሴ ሆነ::

# የእንቅስቃሴው መጀመሪያ በሐረር

በንቅናቄው የመጀመርያ ወራት ሐረር ያለነው የሠራዊት አባላት በህቡዕ እንንቀሳቀስ ነበር። ህክምና፣ ማመላለሻና መገናኛ የነበሩትን ያስተባበርነው እኔና መንገሻ ታደሰ ነበርን። በዚህ እንቅስቃሴያችን ወቅት የጦሩ አባላት የሚያሰሙትን ቅሬታ የሚያዳምጥ እነተካ ቱሉ አባል የሆኑበት ኮሚቴ ነበር። በሳምንት ሦስት ጊዜ ስብሰባ እንቀመጣለን። በዚህን ጊዜ ስለጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ የጦሩ አባላት ባቀረቡት ክስ ተበዳይ ወታደሮችን እናነጋግር ነበር። በዚህ ሽፋን ሌላ የፖለቲካ ሥራ መሥራት ጀመርን። ይሄ ተነቃብን መሰለኝ ጄኔራል ደግነህ ጉግሣ ከአዲስ አበባ ተልከው መጡብን። አመጣጣቸው የጦሩን ሁኔታ ገምግመው እንዲመለሱ ነው። የላካቸው ማን እንደሆነ በውል አላውቅም።

ጄኔራል ደግነህ ሐረር በነበሩ ጊዜ በጦሩ ዘንድ ተወዳጅነት ያተረፉ መኰንን በመሆናቸው ነገሮችን ለማለዘብ ይችላሉ ተብሎ የተመረጡም ይመስለኛል። እንደመጡ እኔን አስጠሩኝና ‹መሥሪያ ቤት መጥቼ አላናግርህም። ጊዜው ጥሩ አይደለም። ሌላ ቦታ እንገናኝ› በማለት በግል ለመነጋገር ቀጠሮ ሰጡኝ።

ስንገናኝ በወዳጅነትና በአባትነት መንፈስ ነው ያነጋገሩኝ። ‹የምትሠሩት ነገር ታውቋል። እኔ ምክር ተብዬ ነው የመጣሁት። የአባትነቴን ልምከርህ። ራስህን ጠብቅ። በኋላ እንዳትቀቀል› አሉኝ።

ከዚያ በኋላ የመጡበትን ለመፈፀም ጦሩን ለማነጋገር ፈለጉ።ጦሩ ደግሞ ‹መሣሪያ ግምጃ ቤት[8] ግቢ ካልሆነ አንሰበሰብም። ለሱውም እኛ ሳንጠራዎት እንዳይመጡ› ብሎ ላከባቸው። እኛ ግን ከጦሩ ጋር ተሰበሰብን። ጦሩ ‹ጄኔራል ደግነህ ምንድነው የሚፈልጉት?› አለና ጠየቀኝ። ሽምግሉ ተብለው እንደመጡ ተናገርኩ። በዚህ ዓይነት ጄኔራል ደግነህ ተመልሰው ሄዱ።

ከዚያ በኋላ በጄኔራል ወልደሥላሴ በረካ የሚመራ አራት ጄኔራሎች ያሉበት ቡድን መጣ። ጄኔራሎቹ ተልከው የመጡት ጦሩን ሊያነጋግሩ ነው ስለተባለ እኛ ጥያቄዎቻችንን አዘጋጅተን ለማቅረብ ስንሰናዳ ሁላችንንም ባንድነት ሳይሆን በተናጠል በየክፍላችን እየመጡ እንደሚያናግሩን ተገለፀልን።‹ወታደሩን በአንድነት አናነጋግርም› ብለው

[8] የመሣሪያ ግምጃ ቤት አዛዥ ያኔ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነበሩ።



በማግሥቱ ጠዋት ፕሮግራም እንዲያዝላቸው ትዕዛዝ ሰጥተዋል ተብሎ ተነገረን። ወዲያውም ሊያነጋግሩን የፈለጉበትን ሰዓት ፕሮግራም አውጥተው ላኩልን። ይሄም ማለት መገናኛም የራሱ ግቢ ውስጥ ተሰልፎ ይጠብቃቸዋል። ሙዚቀኛም፣ ማመላለሻም፣ መሣሪያ ግምጃ ቤትም፣ ሁሉም ተከፋፍሎ ይጠብቃቸዋል ማለት ነው። ነጥሎ ለመምታት፣ አመፀኛውን፣ ነገረኛውን፤ ቀደም፣ ቀደም የሚለውን ለመለየት ያመቻል ማለት ነው። እኛ ደግሞ ይቺ አልጣመችንም። «ስለዚህ ሠራዊቱን ማነጋገር ከፈለጉ አንድ ሆነን በአንድነት ነው እንጂ አንነጣጠልም» ብለን ቁርጠኛ ውሳኔ ወሰንን።

ትዝ ይለኛል ቀኑ ቅዳሜ ነበር። ከግቢ እንዳትወጡ ተብለናል። ይሄን ጊዜ አንድ አምስት መትረየስ የተጠመደ ጂፕ አሰልፌ ደመቀ ባንጃውን የጓዱ መሪ፣ አዳፍሬን ምክትል አደረግሁና ጄኔራሎቹ ወዳሉበት እንዲንቀሳቀሱ አደረግሁ።

እዚያ እንደደረሱ የጄኔራሎቹን አጃቢዎች እጅ ወደላይ ብለው መሣሪያ አስፈቱ። ከዚያ ደመቀ ወደነሱ ቀርቦ ወታደራዊ ሠላምታ በመስጠት ‹ጌቶቼ ሠራዊቱ ለማነጋገር ይፈልጋችኋል። መልካም ፈቃዳችሁ ይሁንና ተነስታችሁ ተከተሉን› አላቸው። ነገሩ የማስገደድ መሆኑ ግልፅ በመሆኑ እነሱም ‹እሺ› ብለው ተነስተው ላንድሮቨራቸው ውስጥ ገቡ። ከፊትና ከኋላ በመትረየስ እጀብ ስተተተተት አድርጎ እኔጋ አመጣቸው። እንደዚች ትንሽ ቢሮ አለችኝ። እዚያ እኔ ቢሮ ውስጥ አስገባና ዘጋባቸው። ከነሱ ጋር አብረው የክፍለ ጦሩም አዛዥ ጄኔራል ነጋ ተገኝ ታሰሩ።

በኋላ ለገሠ አስፋው፣ደመቀ ባንጃውና ንጉሤ ፋንታ ሆነው ሄደው ጄኔራሎቹን አነጋገሯቸው። ደመቀ ባንጃው ጥሩ ወኔ ያለውና ወታደራዊ ቁመናውና አቋሙ የሰጠ ነው። እነለገሠ ደግሞ ለማስተባበርና ለመሳሰለው ነገር ፈጣንና ቀልጣፎች ናቸው። እና ቀረቡና ‹የጦሩን ጥያቄ በመዘርዘር የተዘጋጀ ጽሑፍ አለ። እናንተ በቀጥታ ለንጉሠ ነገሥቱ ደውላችሁ ጥያቄያችንን ማስፈፀም አለባችሁ። ይሄን እንዳስፈፀማችሁ እንለቃችኋለን። የኛ ጥያቄ ይሄ ነው። ይሄንን በሥነ ሥርዓቱ እናንተ ሠራዊቱ ፊት ቀርባችሁ፣ እኛም ጥያቄያችንን አቅርበን ይዛችሁ ሁላችን እንድትሄዱ ነበር የፈለግነው። ነገር ግን እናንተ የኛን በጎ ፍላጎት ልትረዱ ስላልፈለጋችሁ በኃይል ለመጠቀም ተገደናል› አሏቸው።

እነሱም ‹ለልጅ እንዳልካቸው ጥያቄዎቻችሁን በስልክ እንነግራለን› አሉ።

‹ጦሩ የጠየቀው ለንጉሡ እንዲነገር ነው:: እኛ እንዳልካቸው የሚሰጡትን መልስ አንፈልግም› አሉ እነለገሠ::

‹ያው እኮ ነው:: ለእንዳልካቸው እንነገረውና እሱ ለንጉሡ አቅርቦ የሚሰጡትን መልስ ይነግረናል:: ዞሮ፣ ዞሮ መልሱ የሚመጣው ከንጉሡ ነው:: ይሄ ምን ችግር አለው?› ይላሉ ጄኔራሎቹ::

ይሄን ጊዜ እኔ ጋ ተመልሰው መጥተው ያሏቸውን ነገሩኝ:: «እኔም ግዴለም ለእንዳልካቸው ይነገራቸውና መልሱ ከንጉሡ ይምጣ» አልኳቸው::

ካቀረብናቸው ጥያቄዎች አንዱ በበቂ ማስረጃ አገርንና ሕዝብን በድለዋል ተብለው በሕዝብ የተከሰሱት ከሲቪልም ባለሥልጣኖች፣ ከጦሩም አለቆች እነከሌ፣ እነከሌ ይነሱልን የሚል ነበር:: ለምሳሌ፣ እነጄኔራል አበበ ገመዳ ሲታሰሩ፣ እነጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝን የመሳሰሉት ደግሞ ተረስተው ቀርተው ጭራሽ የምድር ጦር ምክትል አዛዥ ሆነው ተሾመው ቁጭ ብለዋል:: እነጄኔራል አሰፋ አያናም እንዲሁ አልተያዙምና እነሱ፣ እነሱ ይታሰሩልን ነው:: ሌሎችም የሕዝቡን በደልና የሠራዊቱን ብሶት የሚገልፁ ጥያቄዎች ነበሩ::

የንጉሡ መልስ ሲመጣ ጄኔራሎቹ ለኛ ነገሩን:: ‹በጥያቄያችሁ መሠረት አድርገናል:: ይሄን፣ ይሄን እንዲፈፀም ጃንሆይ አዘዋል:: ተቀብለዋል:: ሌላው ጊዜ የሚጠይቅና በሂደት የሚስተካከል ነገር ነው:: ወደፊት ይደረጋል ተብሏል› አሉን:: እኛም «እሺ በማታው የሬዲዮ የዜና ፕሮግራም ላይ የሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ጥያቄዎች አቅርቦ ንጉሠ ነገሥቱ በቀጥታ ውሳኔ እንደሰጡት ይገለፅልን:: ይሄን በሁለት ሰዓቱ የዜና ፕሮግራም ላይ እንጠብቃለን» አልናቸው:: እንደጠየቅነው እንደሚደረግ ነገሩን::

ያን ዕለት ገና በቀኑ ብዙ የኛ መኰንኖች እንዲታሰሩ አድርጌያለሁ:: ይሄውም ሊሆን የቻለው ከአዲስ አበባ የመጡት ጄኔራሎች ታሰሩ መባልን ሲሰሙ፣ አንዳንድ መኰንኖች ‹ለምን ታሰሩ?› ብለው ሌላ ቅስቀሳ በመጀመራቸው ነው:: የዚያው የሦስተኛ ክፍለ ጦር መኰንኖች ናቸው:: የአዲስ አበባው መንግሥትም በዚህ መሐል አንዳንድ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ጀመረ:: ለምሳሌ፣ ድሬዳዋ ያለው የመድፈኛ ጦር ‹እነዚህን ጄኔራሎች ባስቸኳይ ካለቀቃችሁ እንዘምትባችኋለን:: እናንተ ማናችሁና ነው ይሄን ያህል ከፍተኛ የጦር አለቃ ሰብስባችሁ የምታስሩት?› የሚል ነገር አሰማ:: አዛዡ ጌታቸው ባልቻ ይባል



ነበር:: እሱ ነው ማስጠንቀቂያውን የላከብን:: ‹ጄኔራሎቹን ባስቸኳይ ካላካችሁ በአየር ኃይል ትደበደባላችሁ› ብሎ ማስፈራሪያ ላከብን:: ከላይም ብርቱ ማስጠንቀቂያ ደረሰን::

‹መንግሥቱ ኃይለማርያምና አንዳንድ አባላት ምን እያደረጉ ነው?› በማለት አንዳንድ መኰንኖች መንቀሳቀስ ጀምረዋል የሚል ነገር ሲደርሰኝ፣ ‹ይሄ ነው እንዴ? በል! ሰብስብና መኰንኑን በሙሉ ጥረግና አስገባልኝ› አልኩኝ:: ሁሉም ከከተማ እየተፈለገ እቤቱ የተገኘውን፣ በጎዳና የሚሄደውን ሳይቀር ሙልጭ አድርገው አሰሩልኝ:: ሙዚቀኛ ግቢ ተወዛዋዦች ለልምምድ የሚጠቀሙበት አዳራሽ አለ እሱ ሰፋ ስለሚል እዚያ አስገቧቸው:: አንዳንዶች ታዲያ ወታደር እንደሚፈልጋቸው ሲያውቁ ለመደበቅ ሲሞክሩ ሰንዱቅ ውስጥ ሳይቀር ተደብቀው ተያዙ:: አንድ ትዝ የሚለኝ በኋላ አክሱም ላይ የሞተ ካድሬ ነበረ:: እሱ እሁን ቁም ሳጥን ውስጥ ገብቶ ተደብቆ አዳፍሬ ነው ያወጣው::

መኰንኖቹን ለመጠበቅ በኃላፊነት ንጉሤ ፋንታ ተመደበ:: ጄኔራሎቹ ጋር ደግሞ ደመቀ ባንጃውና ለገሠ ነበሩ:: በኋላ ላይ ደግሞ እኔ ራሴም ታሰርኩ:: ይሄ የሆነው እንዴት ነው ‹መኰንኖቹ ከታሰሩ በኋላ ሲፈቱ፣ መንግሥቱ ነው ያሳሰረን ማለታቸው አይቀርምና ለማስመሰል አንተንም አብረን እንስርህ› አሉኝ:: «እሺ» ብዬ ታሰርኩ:: ይሄ እንግዲህ ለማደናገር ነው::

ትንሽ ቆይቶ ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ከድሬዳዋው መድፈኛና ከሌሎችም ማስጠንቀቂያ ሲመጣ ‹ለሥራ እንፈልግዎታለን › ብለው ከታሰሩት መኰንኖች መሐል አውጥተው ወሰዱኝ:: የድሬዳዋው ጦር ነገር አሳስቧቸዋል:: እኔ ግን «ማንም አይወጋችሁም:: ተረጋጉ:: ዝም ብለው ነው:: መድፈኛ ከድሬዳዋ (ወደሐረር) አይተኩስ» ስላቸው፣ ‹ገፍቶ የመጣ እንደሆንስ?› አሉ:: «አይመጣም:: ይሄን ያህል ካሳሰባችሁ ግን ደንገጎ ላይ አንድ ሁለት መትረየስ የያዘ ጂፕ አስቀምጡ» አልኩ:: ጊዜውም መሽቶ ነበር::

ማታ ሁለት ሰዓት ላይ ሁላችንም በያለንበት ሆነን በጉጉት ዜናውን እንጠባበቅ ጀመር:: እኔ ቤቴ ነበርኩ:: እንደተባለውም ስለጥያቄያችንና ንጉሡም እንደወሰኑልን የሚገልፀው ክፍል ተነበበ:: ከዚያ ተያይዞ የተነገረው ዜና ግን ጨርሶ የሚያበሳጭ ሆነ::

‹ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ የምድር ጦር ምክትል አዛዥነትን በገዛ ፈቃዳቸው ለቀዋል› የሚል ነገር ተነገረ:: ጊዜው ማታ ነው:: ጦሩ

ከተማ በመዝናናት ላይ እያለ ዜናውንም ይከታተል ነበርና ይሄንን ሲሰማ ቁጣውን መግለፅ ጀመረ:: ጀኔራሉ የወረዱት በኛ ጥያቄ ሆኖ እንዴት በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ ተብሎ በሬዲዮ ይነገራል ተባለ:: ሐረር ቀውጢ ሆነች::

እነደመቀ ባንጃው መትረየስ የተጠመደበት ጂፕ ይዘው ሲበሩ ቤቴ መጡ:: 'እረ ጌታዬ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጪ ሊሆን ምንም አልቀረውም' ይሉኛል:: ተነስተን አብረን ወደከተማው መሐል መሄድ ስንጀምር ሌሎች ወታደሮች ደግሞ እንዲሁ በጂፕ ጠምደው ከተማ ውስጥ ይዘዋወራሉ:: 'ቁም! ማነህ?' አሉን:: ልንታኮስ ምንም አልቀረን:: ሞቅታ ይዟቸዋል:: እኛ መሆናችንን ሲያዩ በረድ አሉ:: መቼም ሠራዊቱ ጠቅላላ ከተማ የወጣ ነው የሚመስለው::

ይሄ ሁሉ ሲሆን ጀኔራሎቹ አሁንም እኔ ቢሮ ውስጥ እንደተዘጋባቸው ናቸው:: 'አየር አሳጣችሁን' ሲሏቸው፣ ጠባቂዎቹ ወታደሮች መስኮቶቹን ከፍተውላቸው እዚያ ቁጭ ብለዋል:: እኔ ቢሮ ውስጥ ሆኖ በስተምሥራቅ በኩል ያለው መስኮት ሲከፈት ፊት ለፊት ትንሽ ሜዳ ነገር አለች:: እንግዲህ ልብ በይ:: የኛ አዛዥ ጀኔራል ነጋ አብረዋቸው አሉ:: የሐረር አካዳሚ አዛዥ ጀኔራል ግዛው በላይነህ አሉ:: የሳቸው ረዳት ኩሉኔል ሙላቱ የሚባል አለ:: እነዚህ ሁሉ እኔን ያውቁኛል:: እና ቢሮዬ አጠገብ ደርሼ እነሱ ጋ ሳልገባ ሳልፍ ስል መስኮቱ ተከፍቶ ሳይ «ዝጉት እንጂ፤ ዝጉት መስኮቱን» አልኳቸው አጆበውኝ ለመጡት ወታደሮች:: ጀኔራሎቹ እንዳያዩኝ ነው:: ልብ ያላልኩት ነገር ግን እነሱ ገና ስገባ ጀምሮ በሁለተኛው መስኮት በኩል ያዩኝ ኖሯል!

ከዚያ አብረውኝ ያሉት ገብተው ለጀኔራሎቹ እንዲነግሯቸው ያልኳቸው ምንድነው «ጀኔራል ኃይሌ ከሥልጣን የወረደው በፈቃዱ ሳይሆን በአንበሳው ሦስተኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ጥያቄ መሆኑንና ከሥልጣን መውረድ ብቻ ሳይሆን በቁጥጥር ሥር መዋሉም በሦስት ሰዓቱ ዜና ወይም ዘግይቶ የደረሰን ተብሎ ባስቸኳይ በሬዲዮ ይነገርልን:: ያለበለዚያ ለሚደርሰው ነገር ኃላፊነት የለብንም» ብላችሁ ቁርጥ አድርጋችሁ ንገሯቸው አልኳቸው::

ይሄ ሲሆን ከተማ ያለው ወታደር የራሱን እንቅስቃሴ ቀጥሏል:: እኛ ሲቪል የሆነ ሰው አላሰርንም:: የጦር አለቆችን ብቻ ነው ያሰርነው:: ጦሩ በራሱ አነሳሽነት ይሄድና የሐረርጌ ክፍለ ሃገር ምክትል እንደራሴ የነበሩትን ፊታውራሪ መሐረነ ምንዳን ከቤታቸው አስነስተው



አምጥተው እዚያ ይከቷቸዋል:: ሌሎችንም፣ እነሐጂ በምባን (እየሳቁ) የመሳሰሉ ትልልቅ ነጋዴዎችና የሃገር ሽማግሌዎች ሁሉ ሰብስበው አስረዋል::ታዲያ በኋላ እንዳጣራነው አንድ ባሻ ጦና የሚባል የፖሊስ በክሰኛ ነበር:: እሱ ነው እሱ ይሄን የሚያደርገው::

እነዚህ ሰዎች መታሰራቸው ሲነገረኝ «በሉ እነኚህን ሰዎች ቶሎ ልቀቁ» አልኩ:: «ይሄ የሠራዊቱን ስም የሚያጠፋና የተነሳንበትን ዓላማ የሚያኮስስ ነው» ብዬ ተቆጣኋቸው:: ይሄ ሁሉ ሲሆን እኔ የምናገረውን ሁሉ ለካ እነኛ ጀኔራሎች ያያሉ:: ይሰማሉ:: በኔ ቤት ተደብቄያለሁ እኮ! ማንም ሰው እንዲያውቀኝ አልፈልግም ነበር::

ሬዲዮን እያዳመጥን ብዙ ቆየን:: 'የምናቀርበው ዘግይቶ የደረሰ ዜና አለን፤ ጠብቁ' ሲል ቆይቶ በመጨረሻ ዜናውን እኛ እንደጠየቅነው አድርጎ አቀረበ:: 'የሦስተኛ ክፍለ ጦር ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ቀደም ብሎ የተሰጠው ውሳኔ ታርሞ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትዕዛዝ ሜጀር ጀኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ ከሥልጣናቸው ወርደው ያለአግባብ በመበልፀግና በሥልጣን መባለግ ክስ ቀርቦባቸው ወደፊት በሚቋቋመው መርማሪ ኮሚሽን ፊት እስኪቀርቡ በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ታዟል' ሲል ጦሩ በደስታ አወካ:: ቀላዳምባ በሙሉ!

ከዚያ ወደቤቴ ሄድኩኝ:: ጀኔራሎቹም 'ለዛሬው እዚሁ ይደሩ' ተባለ:: በእውነት ራስ ሆቴልም እንዲያድሩ ማድረግ ይቻል ነበር:: ነገር ግን ሁኔታው ጥሩ አልነበረም:: ወታደሩ ጠጥቷል:: እነሱም ቢያዩ ይታዘቡናል ተባባልንና ለዚያን ዕለት እዚያው የጦር ሠፈር አደሩ:: ሌሊቱን ሐረር ሬዲዮ ጣቢያን ያዝንና ትንሽ ፕሮፓጋንዳ ቢጤ ነዛን:: ብቻ ብዙ ያዳመጠን ሰው አልነበረም:: ቢሆንም እኛ ሰሞኑን በደንብ ያዘጋጀናት ጽሁፍ ነበረች:: አስተላለፍናት:: አንድ ሕለተወርቅ መንግሥቱ የሚባል «አጋዬን አንበሳ» መጽሔት ላይ የሚጽፍ ልጅ ነበረ:: እሱ ነው ያነበበው::

በማግሥቱ ያሰብነው ሁሉ ስለተሟላ መኮንኖቹን ፈታናቸው:: በዚሁ ጊዜ ሶማሊያ በቶጎ ውጫሌ በኩል ወታደሮቿን ማንቀሳቀስ ጀምራ እኛን ለማደናበር ያደረገችውን ሙከራ አከሸፍንባት::

ይህ ድርጊት ሠራዊቱን ሲያነቃውና ልብ ሲሰጠው ከመሐከላችን ቁጥራቸው የማይናቅ ተቃዋሚዎችን አስነሳብን:: በተለይ በኔ ላይ ዓይናቸውን በክፋት የጣሉብኝ አባሎች ነበሩ:: ስለዚህ መኖሪያ ቤቴ በደጋፊ የሠራዊት አባላት ይጠበቅ ጀመረ::

ከዚያ በኋላ የኛ ውጤት ማግኘትና በነገሌ የተደረገው እንቅስቃሴ በሌሎች የጦር ክፍሎችም ንቅናቄው እየጎለበተ እንዲመጣ አደረገ::

ሥራችን ሁሉ በይሆናል ሳይሆን በደንብ የተቀናጀ ዝግጅት የነበረው ሥራ ነበር:: ለምሳሌ፣ ለገሠ አስፋው ለጀኔራሎቹ የሚሰጠውን የጦሩን ጥያቄ በደንብ አቀናብረን ሰጥተነው በደመቀ ባንጃው እየታገዘ ነው ያስፈፀመው:: በኃይል የማስፈፀሙ ነገር ቢመጣ፣ ለጌ ለፈስፈስ ያለች እንደሆነ ደመቀ ቆራጥና ወኔ ያለው በመሆኑ እሷን ያጠናክራል ተብሎ ነው አብሮ የተመደበው:: ንጉሤ ፋንታ የታሠሩትን መኰንኖች የመጠበቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል:: ሻምበል መንገሻ ደግሞ ከውጪ ሆኖ የሠራዊቱን ሁኔታ ይቆጣጠር ነበር:: ከተማውን የሚዞሩት ቃኚ ጂፖች በሙሉ በሱ የሚታዘዙ ነበሩ:: ሥነ ሥርዓት ያስከብር ነበር:: ሌሎቹም እንደዚሁ:: ይህን በመሰለ ቅንጅት የሥራ ክፍፍል ተደርጎ እንጂ በዘፈቀደ የተሠራ ነገር አልነበረም::

*ገነት - የምንመራው ሕዝባዊ ንቅናቄ ነው ካላችሁ ከሲቪሉ ለምን አልጨመራችሁም?*

**መንግሥቱ** - እኛ በመሠረቱ የጀመርነው ወታደራዊ ንቅናቄ ነው:: እንደዚህ ዓይነት ንቅናቄ ሲቪሉን ሊያካትትም ላያካትትም ይችላል:: በኛ እንቅስቃሴ ውስጥ ሠራዊቱ ሲቪሉን ሊያካትት ቀርቶ ከወታደሩም ቢሆን ከሻለቃ በላይ ያሉትን አልጨመረም:: የአመራር አካላት እንዲሳተፉ አልተፈለገም:: «ለምን?» የተባለ እንደሆነ እኛ የፈለግነው ሥር ነቀል ለውጥ ነው:: የበላይ መኰንኖቻችን በአብዛኛው የግል ሃብት ያበራከቱ፣ለራሳቸው የግል ጥቅም የሚዋትቱ፣ ካለው ሥርዓት ጋር የተሳሰሩ ሰዎች ናቸው:: እንዲህ ያለ ወደኋላው የሚጎትተው ትብትብ ያለበት ሰው አብዮታዊ ለውጥ ለማምጣት ፍላጎት ቢኖረው እንኳን በሙሉ ኃይሉ ወጥቶና ተጋልጦ ሊታገል አይችልም:: እኛ ያደረግነው ዓይነት ዐመፅና መጋፈጥ ያለበት ነገር ውስጥ ገብቶ ለመዘፈቅ ይቸገራል:: ይህ ተሞክረው ከከሸፉ ሙከራዎች የተማርነው ነው:: ወጣቶችና የጠነከረ ዓላማ ያላቸው ሰዎች ግን ለሚያምኑበት ነገር እሳት ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉ ከሻለቃ በላይ አይሁኑ የተባለበት ምክንያት ይሄ ነው::

ሲቪሉን ለማካተት አልፈለግንም:: ወታደር ከሲቪል ጋር ተቀላቅሎ የሚሠራበትም የማይሠራበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: እኛ ሲቪሉን በተመለከተ በኋላ ላይ እንጂ በመጀመሪያው እንቅስቃሴያችን ላይ እንዲገባ አልፈለግንም:: ይሄው ነው ምክንያቱ:: አልተፈለገም ነበር::



በኢትዮጵያ ትቅደም ራዕይ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመመሥረት ዓላማ ነበረን:: የፖለቲካ ፓርቲ የመመሥረት ዓላማ ነበረን:: ይሄንን ለማድረግ ዋናው ባለቤት የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ተዋናይ የሚሆንበትን መንገድ የማመቻቸት ዓላማ ነበረን:: ይህ ከመሆኑ በፊት ግን እኛ የያዝነው የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ወታደራዊ ነበር:: በዚሁ ገፍተንበታል::

ከዚያ በኋላ አዲስ አበባ ያሉ የጦሩ ክፍሎች በፈጠሩት ኮሚቴ አማካኝነት መገናኛ ብዙኃኑን በቁጥጥር ሥር አውለው የሠራዊቱን ንቅናቄ ይፋ ሲያደርጉ በሐረር ለነበርነውም ጥሪ አደረጉልን:: ‹ለተፈጠረው ሁኔታ የእኛ መልስና አቋም ምን ይሁን?› የሚል ስብሰባ ተደረገ:: ስብሰባው ሦስተኛ ክፍለ ጦር ብቻ ሳይሆን፣ የሐረርን ፖሊስና የጦር አካዳሚንም ያካተተ ነበር:: በስብሰባው ለተነሱት ጥያቄዎች ንቅናቄው በአዲስ አበባ ክፍሎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን አገር አቀፍ ስለሆነ በጥሪው መሠረት መሳተፍና የዚችን ሃገር ዕድል ከመወሰን ሌላ አማራጭ እንደማይኖር አቋም ተወሰደ:: በውክልና የሚላኩትን መኰንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች የመምረጫ ደንብና መስፈርት ተዘጋጅቶ በድምፅ ከተደገፈ በኋላ በመመሪያውና በመሥፈርቱ መሠረት ይመጥናሉ የሚባሉ ሰዎችን ስብሰባው እንዲጠቁም ተደረገ::

ከተጠቆሙት መኰንኖች አንዱ እኔ ነበርኩ:: ከጥቆማው በኋላ ከተሰብሳቢዎቹ ሁለት መኰንኖችና ሦስት ባለሌላ ማዕረጎች እንዲመረጡና ከሚሰጠው ድምፅ ሁለት ሦስተኛ ድምፅ የሚያገኙት ብቻ እንዲያልፉ ተወሰነ:: ይሄ እንግዲህ በሦስተኛ ክፍለ ጦር ክፍሎች ውስጥ ሲሆን፣ ፖሊስና ሐረር ጦር አካዳሚ በጋራ በተስማማንበት መመሪያ መሠረት በየክፍላቸው የየራሳቸውን ምርጫ አድርገው ተመራጮቻቸውን ለስብሰባው እንዲያቀርቡ ነበር::

ከመኰንኖች ምርጫ ያለማጋነን በሙሉ ድምፅ ማለት ይቻላል በመጀመሪያ ተመረጥኩ:: በሁለተኛ መኰንንና በሦስቱ ባለሌላ ማዕረጎች ምርጫ ድምፅ ተበታትኖ ሁለት ሦስተኛ ድምፅ የሚያገኝ ሰው ስለታጣ በተደጋጋሚ ተሞክሮ ሊሳካ ባለመቻሉ ትልቅ ችግር ተፈጠረ:: አንድ ቀን ሙሉ ተዋለ:: ሁኔታው አሳሳቢና አስቸኳይም ስለነበር በጊዜው የሐረር ጦር አካዳሚ አዛዥ፣ በኋላ የደርጉ ሊቀመንበር የሆኑት ብርጋዲየር ጄኔራል ተፈሪ በንቲ አንድ ሃሳብ አቀረቡ::

‹የተቀሩት ተመራጮች በደንቡ መሠረት ተገቢውን ድምፅ ማግኘት ካልቻሉና ድምፃችን በእጅጉ ከተበታተነ ሙሉ ድምፅ የሰጠነውና

ማዕረጉም ቀደምት የሆነው ሻለቃ መንግሥቱ፣ እኔን ሊረዱኝ ይችላሉ፤ የተባለውንም መስፈርት ይመጥናሉ የሚላቸውን ራሱ እንዲመርጥ ብናደርግስ?› የሚል ነበር::

የጄኔራል ተፈሪ ሃሳብ ስለተደገፈ ድምፅ እንዲሰጥበትና ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ድጋፍ ካገኘ እንዲያልፍ ተወሰነ:: ሙሉ ድምፅ አግኝቶ ፀደቀ:: በዚህን ጊዜ እኔ ተነሳሁና «በቅድሚያ እኔ ይህንን ኃላፊነት ለመ ውሰድ ፈቃደኛ መሆንና አለመሆኔን ሳትጠይቁ መረጣችሁኝ:: አሁን ደግሞ እንዴት እንደገና ሌሎችንም እኔው እንድመርጥ እንዴት ትወስና ላችሁ?» ብዬ ሌላ ውዝግብ ተነሳ:: ሆኖም ቤቱ በሙሉ በጩኸት ከባድ ተፅዕኖ ስላደረገብኝ ሃሳቡን መቀበል ግድ ሆነብኝ:: የተወሰነ ጊዜ እንዲ ሰጠኝ ጠይቄ ጦሩን ካነጋገርኩ በኋላ ከዚህ የሚከተሉትን መረጥኩ::

1. ሻለቃ ገብረየስ ወልደሃና፣
2. የሃምሣ አለቃ ደመቀ ባንጃው፣
3. የሃምሣ አለቃ ንጉሤ ፋንታ፣
4. የሃምሣ አለቃ ለገሠ አስፋው::

በዚህ ዓይነት የሦስተኛ ክፍለ ጦር ምርጫ ካለቀ በኋላ ፖሊስና አካዳሚም የራሳቸውን ተመራጮች አቀረቡ:: እነሱም ከፖሊስ ሻለቃ ተካ ቱሉና ሁለት የበታች ሹሞች፣ ከአካዳሚ ሻምበል ብርሃኑ ባይህና አንድ የበታች ሹም፤ በጠቅላላው አሥር ሰዎች የምሥራቁን መለዮ ለባሽ እንድንወክል ተመረጥን:: የቡድኑም መሪ እኔ ነበርኩ::

ከሐረር ወደአዲስ አበባ በአጣዳፊ እንድንሄድ በመወሰኑ በዚያው ዕለት ወደማታ ተነስተን ሌሊቱን ስንጓዝ አድረን በማግሥቱ ረፋዱ ላይ አዲስ አበባ ደረስን:: ማረፊያ በመፈለግና ዕቃችንን በማሳረፍ የከሰዓት በፊቱን ጊዜ ወስደን ከሰዓት በኋላ የአዲስ አበባው ጦር ወደተሰበሰበበት አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ሄድን::

# አዲስ አበባ - ደርግ ሲቋቋም

ደርግ ሲቋቋም ከየክፍላችን የተመረጥነው አዲስ አበባ ስንገባ ባንዴ አልገባንም:: ከኛ በኋላ ዘግይተው የመጡ ነበሩ:: ወደስብሰባው አዳራሽ እንደገባን ስብሰባውን የሚመራው ኰሎኔል አጥናፉ ስለነበር «የሦስተኛ ክፍለ ጦር አባሎች ነን» ብለን የተወከልንበትን ደብዳቤ ሰጠን:: በአዳራሹ ውስጥ የአዲስ አበባ ክፍሎች፣ የክብር ዘበኛና የፖሊስ



ሠራዊት ተወካዮች ብቻ ነበሩ:: የውይይቱ አጀንዳ ያለአግባብ በመበል ጸግና በሥልጣን መባለግ ከሕዝቡ ክስ የቀረበባቸው ባለሥልጣናት ስም ዝርዝር ቀርቦ ‹እነማን ይታሰሩ?› የሚል ነበር:: በውይይቱ መሠረት ውሳኔ እየተሰጠ ወታደር በመላክ ሹማምንቱ እየታደኑ ይታሰራሉ:: ጥቆማውን በማካሄድ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት የአዲስ አበባ ፖሊስና ክብር ዘበኛ ናቸው:: የተቀሩት መለዮ ለባሾች የሚጠቆሙትን ሰዎችም ሆነ ጥፋታቸውን በውል የሚያውቁ አይመስሉም::

ትንሽ የመደናበር ሁኔታና የሥርዓት መጉደል ይታይ ነበር:: የውይይቱ አያያዝና የአሠራሩም ዘይቤ በአንድ ሃገርና በሰዎች ዕድል ላይ ለመወሰን የሚያስችልና የሚመጥን ሁኔታ አይታይበትም ነበር:: አደናጋሪና አሳሳቢ ሁኔታ ስላየንበት እኛ የምሥራቁ ጦር ተወካዮች ገብተን ብንቀመጥም ከመሳተፍ ተቆጠብን::

ይሄ በሌሎቹ ተሳታፊዎች ታይቶ ኖሮ ‹ሦስተኛ ክፍለ ጦሮች ምነው ዝም አላችሁ? ለምንድነው ሃሳብ የማታቀርቡት? የማትናገሩትስ ለምንድነው?› የሚል ጥያቄ ከቤቱ ተወረወረ:: በዚህን ጊዜ ተነሳሁና በመጀመሪያ ደረጃ የተሰበሰብነው ሰዎች መላውን የአገሪቱን የጦር ኃይል የማንወክል መሆኑን ካመለከትኩ በኋላ «ለመሆኑ ለምን ዓላማ ነው የተሰበሰብነው? ሰው ለማሠር ከሆነ የተሰበሰብነው ይሄንን ግልጽ አድርጉልን በማለት ጀመርኩ:: አያይዤም «ይህን የመሰለ ታላቅ ውሳኔ ስትሰጡ የአሠራራችሁ ዘይቤ ብዙ ሥርዓትና ደምብ የሚጎለው ነው:; ስለሚታሠሩት ሰዎች በደልና ጥፋት በበኩላችን የምናውቀው ነገር የለም:: አገር በድለዋል የሚባሉትን ማሰር አንድ ነገር ነው:: ከዚያ ባለፈ ለመሆኑ ዓላማችን ምን ለማድረግ ነው? ዓላማችንና ግባችን ግልፅ ካልሆነ ለመሳተፍ አይቻለንም» ብዬ ሌሎች ብዙ ጉዳዮችንም ያቀፈ ሰፋ ያለ አስተያዬት ሰጠሁና የኛን (የምሥራቁን ጦር) አቋም ግልፅ አደረግሁ:: ተሰብሳቢዎቹ ያቀረብኩትን ሃሳብና ሂስ ካዳመጡ በኋላ ሃሳቤን ደግፈው በዚህ ዓይነት ቀኑን ሙሉ ስንወያይ ዋልን:: ከዚያ ጊዜው በመምሸቱ የዕለቱ ስብሰባ ተበተነ::

በነጋታው በፊት ያልመጡ ተወካዮች ሁሉ በተከታታይ አዲስ አበባ ገብተው ኖሮ እየገቡ ቦታቸውን ሲይዙ ምልዓተ ጉባዔ ሆነ:: ስብ ሰባው ሲከፈት ‹ትላንት ሻለቃ መንግሥቱ ያቀረቡት ጥያቄ መልስ ሳያገኝ እኛ በፊት በጀመርነው ሁኔታ መቀጠል የለብንም› የሚል ነገር በተከታታይ በተለያዩ ተወካዮች ቀረበ:: በዚህን ጊዜ ኰሎኔል አጥናፉ እሱን የተቃወምኩት መስሎት በስጨት አለና ‹አሁን ምን ይሁን ነው

የምትሉት?› አለና ሥራውንም፣ አመራር መስጠቱንም ትቶ ቁጭ ሲል ሁላችንም ተፋጠጥን። በዚህን ጊዜ አንድ መኰንን ብድግ ይልና‹የምናደርገው ከጠፋንና መፋጠጥ ከሆነ ሻለቃ መንግሥቱ ስላቀረቧቸው ጥያቄዎችና ሃሳቦች ራሳቸው መፍትሔውን ይስጡን› ይላል።

ከዚያ በኋላ ነገሮች መልክ እየያዙ እንዲመጡ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ወደማቋቋምና ወደሰው ምርጫ ሄድን። ይህም በወግና በሥርዓት መሆን አለበት አልኩና ፎርማሊቲውን አስረዳሁ። «መጀመሪያ አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል። ከዚያ ወደዋናው ምርጫ እንሄዳለን» ስል፣ አንዳንዶቹ ‹ሻለቃ መንግሥቱ ይሁን› አሉ። ነገሩ የገባቸው ‹አይሆንም› አሉና እነኰሎኔል ፋንታ እና እንዳለ ተመረጡ። በመሐል ዕረፍት ሆኖ እደጅ ቆመን እያወራን ተስፋዬ ገብረኪዳን ‹ይሄ ነገር አንተው ላይ ሳይጫን አይቀርም› አለኝ። «ሊሆን አይችልም» አልኩት።

ከዕረፍት መልስ ለሚመረጠው ሰው የሚሰጠውን ስያሜ በተመለከተ «ፕሬዝዳንት» ከማለት ይልቅ «ሊቀመንበር» ቢባል ይሻላል የሚል ሃሳብ ቀረበና ተቀባይነት አገኘ።

እኔ አጥናፉ እንዲመረጥ ግፊት አድርጌያለሁ። አጥናፉ በመጀመሪያው ስብሰባችን ላይ «ሰዎች ይታሰሩ ሲባል እኛ ማን ሆነን? ምንስ ዓላማ ይዘን ነው ሰው ለማሠር የተነሳነው? መጀመሪያ ይሄ በግልፅ ይቀመጥና ከዚያ ቀስ እያልን ያሰብነውን ለመሥራት እንችላለን» ስል እሱን የተቃወምኩት መስሎት ትንሽ ቅር ብሎት ስለነበር በኋላ ምርጫ ተደርጎ እኔ ስመረጥ እሱ ለኔ እጅ አላወጣም። እኔ የተመረጥኩት በ98 በመቶ ድምፅ ሲሆን፣ እሱ ሲመረጥ በ99 በመቶ ድምፅ ነበር። ምክንያቱም ለሱ እኔ እጄን አውጥቼለታለሁ።እሱ እኔን አልደገፈኝም። እኔ ግን «ያለሱ አልሠራም» ብዬ እሱ ምክትል እንዲሆን መርጬዋለሁ። የሱ ቅሬታ እንግዲህ መንግሥቱ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር መጥቶ ከኔ ይበልጥ ታዋቂ ሆነ በሚል ነገር ይመስለኛል። በእውነቱ ለብዙ ጊዜ ርቆኝ ለመጠጋት እየተቸገረ በኔ ትግል ነበር አብረን ለመሥራት የተሞከረው።

የደርጉ ሊቃነመናብርት ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደዋና ፀሐፊ ምርጫ ስንሄድ እኔ «የንቅናቄውን መሪ መርጣችኋል። ምክትሉን መርጣችኋል። ዋና ፀሐፊ ማለት አቀናባሪ ማለት ነው። ቀኝ እጅ ነው። ወጥ ቤት ነው (ይሄንኑ ቃል ነው የተጠቀምኩት)። አሁንም የሚሸከመውን ኃላፊነት አይታችሁ ጥንቃቄ የተመላበት ምርጫ ማድረግ ይገባችኋል» አልኩኝ። በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ ተነሳና ‹ሻለቃ መንግሥቱ



ራሳቸው ፀሐፊውን እንዲመርጡ ለምን አንፈቅድላቸውም? ይሄንን ለሳቸው እንተወው› አለ። ቤቱ በዚህ ተስማማ። ኰሎኔል አጥናፉ ‹በአንተ በኩል ማን አለ?› ሲለኝ ገብረየስ ወልደሐና አልኩት። እሱ ሆነ። ገብረየስ የአስተዳደር መኰንን ነበር። መረጃ ውስጥም ሠርቷል። ጽሑፍ ማቀነባበር ልዩ ስጦታው ነው። ትጉህና ታታሪ ሠራተኛ ነው። በምርጫዬ አላሳፈረኝም።

*ገነት - እስቲ ስለደርግ አባላት ትንሽ ይንገሩኝ?*

***መንግሥቱ*** - በመጀመሪያዎቹ የአስተባባሪው ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የተሳተፍነው ቁጥራችን 170 ነበር። እኔ ከተመረጥኩ በኋላ እያንዳንዱ አባል የተወከለበትን ደብዳቤ ያምጣ ተባለ። አንዳንዶቹ ማንም ሳይወክላቸው እንዲሁ ጎራ ብለው ከኛ ጋር ተቀላቅለው ነበርና ማቅረብ ያልቻሉት ተነቅሰው ተባረሩ። ከዚያ በኋላ የቀረነው 120 አባላት ነበርን። ይህ ትክክለኛ ቁጥራችን ነው።

እያንዳንዳችን ለንቅናቄው መሳካት የየበኩላችንን አበርክተናል። በአዲስ አበባ ለነበረው ትግል አጥናፉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። ለዚህ የተሰጠው ክሬዲት የሚገባው ነው። እኔም አውቅለታለሁ። በአብዮቱ ፍንዳታ አካባቢ በዲፕሎማው ፕሮግራም የሕግ ትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያኔ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) ይማር ነበር።

በኤርትራ የወታደሩን ትግል ፈር ያስያዙትና የሚያንቀሳቅሱት እነነሲቡ ታዬ ነበሩ።ፍሰሐ ደስታ አጋፋሪ ነው። ከአብዮቱ በፊት ፖለቲካ ውስጥ ብዙ የማይገባ ሰው ቢሆንም፣ ከማንም ያላነሰ አስተዋፅዖ አድርጓል። ነገሩ ሁሉ እየጋለ መጥቶ ውጥረት በበዛበኝ ወቅት አንዳንድ ቀልዶችን በመናገር ፊቴን የሚያፈካው ሰው ነበረ። ሻለቃ አሥራት ደስታ የጋዜጠኝነት ትምህርት አሜሪካን አገር ተምሮ የመጣ ነበር። ፀጣም፣ በጣም ችኩል ሰው ነበር። ለአስተባባሪው ኮሚቴ «ደርግ» የሚለውን ስያሜ የሰጠው ናደው ዘካርያስ ነው።

ከንጉሡ መውረድ በፊት የነበሩት ጥቂት ወራት እጅግ ፈታኝና አደገኛ ነበሩ። ስንቶች ሊያጠፉን ዶልተው ነበር። ልጅ እንዳልካቸውም አልተኙልንም። እኛ አራተኛ ክፍለ ጦር ተሰብስበን ውለን ወደየሆቴላችን ሄደን ነው የምናድረው። አንዳንዴ ከሌሊቱ ስድስት፣ ሰባት ሰዓት ነው የምንመለሰው። አንዲት ኡዚ አለችኝ። እሷው ነች። ሌላ ጥበቃ የለኝም። ሊገድሉኝ ይችሉ ነበር።

ከልጅ እንዳልካቸው ካቢኔ ጋር አገናኝ መኰንናችን (ሳይዘን) የነበረው ሻለቃ ሲሣይ ሀብቴ ነበር:: ሰባት አባላት ያሉበት የደርግ ኮሚቴ ተቋቁሞ በሚኒስትሮቹ ስብሰባ ላይ ይገኝ ነበር:: እንዳልካቸው ‹ሁለት መንግሥት ከሚሆን ሌላ ዘዴ ለምን አይፈለግም?› ይላሉ የሚል ነገር ሰማን:: አንድ የሚሊቴሪ ፖሊስ፣ ሻለቃ ተጫኔ የሚባል የደርግ አባል ነበር:: የእንዳልካቸው ዘመድ ኖሯል:: ሌላ ደግሞ በዛብህ የሚባል ትግሬ፣ ከምድር ጦር መሐንዲስ ክፍል ሻምበል ሺፈራው የሚባል፣ የንጉሡ አጃቢዎች ኃላፊ ኰሎኔል ጣሰው ሞጆ የሚባል:: እነኚህ ሁሉ እኛን ለማጥፋት ይደልታሉ::

በዚህ መሐል ኃይሉ ያዴሳ የሚባል ለናደው ዘካርያስ ይመጣና አንድ ነገር ሹክ ይላል:: ‹መንግሥቱ ኃይለማርያምን ዛሬውኑ ከዚህ ቦታ ዞር አድርጉት› የሚል ነገር ተሰማ:: ከዚያ በኋላ አራተኛ ክፍለ ጦር ገብተን ቆለፍን::

*ገነት - ይሄ ሁሉ ሲሆን ጃንሆይ ምን ይሉ ነበር?*

***መንግሥቱ*** - ጃንሆይ ያ ሁሉ ሰው ካጠገባቸው እየተያዘ ሲታሰር አልተቃወሙም ነበር:: ታሳሪዎቹን ባለሥልጣኖች በተመለከተ ንጉሡ ከእንዳልካቸው ጋር ከሞላ ጎደል አንድ የጋራ አቋም የያዙና የተግባቡ ይመስላል:: ሁለቱም የሕዝቡን ጥያቄ ከማስተናገድ የተለየ ምርጫ የለም የሚል ውሳኔ ላይ ደርሰዋል:: እነኚህ ሰዎች ባለፈው የአገዛዝ ዘመናችን ተቀባይነት በነበራቸው ጊዜ አገልግለዋል:: ተጠቅመዋል:: አሁን ያለንበት ወቅት ደግሞ እነሱን የተፋ ወቅት ነው:: ስለዚህ ዘውዱን ለማዳን እኛም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ልንከተለው የሚገባው ስልት ከነኚህ ሰዎች ጋር መቆም አይደለም:: እነኚህን በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች ሕዝብ ጠልቷቸዋል:: እነሱን ለማዳን ዕድሉ የጠበበ ነው:: መሄድ አለባቸው ነው የእንዳልካቸው ፖለቲካ:: ጃንሆይም ይሄንን ተቀብለውታል::

ነገር ግን ጃንሆይ ከቤተመንግሥት አካባቢ የሚወሰዱትን ቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ ረዳቶቻቸውን በተመለከተ ተመሳሳይ ሁኔታ አላሳዩም:: ለምሳሌ፣ ንጉሣውያን ቤተሰቦቹን በክብር ይዘናቸው እያሉ ትንሽ ገደብ ያለፈ መቅበጥ ሲያሳዩ እንዲታሠሩ ወስነን ወህኒ በወረዱ ጊዜ ጃንሆይ ‹ለምንድነው?› ብለዋል:: የልጅ ልጃቸው ሪር አድሚራል እስክንድር ሲታሠሩ ‹የት ሄደ?› ብለዋል:: የእልፍኝ አስከልካያቸው ጄኔራል አሰፋ ሲወሰዱም ‹ለምንድነው እሱን ደግሞ የምትወስዱብን?



ምን አደረገ ነው የምትሉት? እሱን ተዉት:: ያለበለዚያ እኛንም እሰሩን› ብለዋል:: እኛም «በቃ ተዉ» ብለን ሲይዟቸው ቤተመንግሥት የሄዱትን ወታደሮች መለስናቸው:: ማታውኑ ጄኔራሉ አገር ደህና ብለው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ የክብር ዘበኛ ወታደሮች ሄደው ያዟቸው:: ጠዋት ጃንሆይ ሲጠይቁ ‹አዬ እሳቸውንም ማታ ወታደሮች ከቤታቸው ወሰዷቸው› ተብሎ ተነገራቸው::

ንጉሡ ከሥልጣን የወረዱ ዕለት ደበላ ዲንሳ በደርጉ የተዘጋጀውን ጽሑፍ ይዞ ሄዶ እንዲያነብ ወደቤተመንግሥት የተላከው ቡድን መሪ ሆኖ ሄደ:: ለንጉሡ ቅርብ ከሆኑት ሰዎች መካከል ዘመዳቸው ራስ እምሩ እንዲገኙ ወስነን ስለነበር እሳቸውም ተገኝተዋል::

ሌሊቱን ጥበቃው ተጠናክሮ ነበር ያደረው:: በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በሒልተን ሆቴል፣ በቤተ መንግሥቱ ዙሪያና በፍልውሃ አካባቢ በብረት ለበስ፣ በታንክና በእግረኛ ሠራዊት በደንብ አድርጎ የተማገረ ጥበቃ ተደርጓል:: በሥራ ክፍፍላችን መሠረት እኔ ከአዋጅ አርቃቂው ኮሚቴ ጋር ነበር የምሠራው:: የከተማውን ቁጥጥርና ጥበቃ ጄኔራል አማን ራሳቸው ከተስፋዬ ገብረኪዳን ጋር በመሆን ሌሊቱን እየተዘዋወሩ ሲቆጣጠሩ ነበር ያደሩት:: በበነጋው የሚፈጠር ነገር ካለ ወታደራዊው ዘመቻ በነሱ ኃላፊነት ሥር ነበር::

ንጉሡ ከወረዱ በኋላ ከቤተመንግሥት ሲወጡ ደርግ ሆን ብሎ ሰዎች ተሰብስበው እንዲጠብቁና ‹ሌባ! ሌባ!› እያሉ እንዲጮኹ አድርጓል የሚባለው ሐሜት ከእውነት የራቀ ነው::በእርግጥ ሰው ተሰብስቦ ነበር:: ልክ በጥሪ እንደቀሰቀሱት ቢጤ ነው የወጣው፣ ‹ሌባ! ሌባ!› እያለ እየጮኸ:: ግን እኛ አዘጋጅተነው አይደለም:: በዚያን ወቅት በየጊዜው አንድ ነገር ይፈጠራል:: ሕዝቡ ሬዲዮው ላይ ተጣብቆ ነው የሚውለው:: ያን ዕለት ደግሞ የዓመት በዓል ማግሥት ነበር:: የእንቁጣጣሽ ለት ማታ የወሎን ረሃብ ፊልም አሳይተናል:: ስለዚህ አንድ ነገር ይመጣል ብሎ በመገመት ወደዚያ አካባቢ ወሬ ለማነፍነፍ የመጣ ሕዝብ ነው::

# ጃንሆይ በእስር ላይ

*ገነት - ጃንሆይ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ኑሯቸው እንዴት ነበር? እስር ላይ እያሉ እርስዎ አግኝተዋቸው ያውቃሉ?*

*መንግሥቱ* - በመጀመሪያ ነገር የነበሩበት ቦታ እስር ቤት ሊባል የሚገባው አይደለም:: መጀመሪያ አራተኛ ክፍለ ጦር፣ በኋላም ታላቁ ቤተመንግሥት እያሉ በጥሩ ሁኔታ ተይዘው ነው የቆዩት:: እኛ ሥራችንን የጀመርነው አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ስለሆነ ለጥበቃው፣ ለደህንነታቸው ሲባል፣ ከሥልጣን ሲወርዱ በቀጥታ እዚያ እንዲመጡ አደረግን:: ንጉሡን በቁጥጥር ሥር ማዋል አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ባይሆንም፣ ሥልጣን አይኑራቸው፣ እንደልባቸው ያሻቸውን አይስሩ እንጂ በአክብሮት ይዘን ነው ያቆየናቸው:: አሽከሮቻቸው እያገለገሏቸው ከቤተ መንግሥት የሚመጣ ምግብ እየቀረበላቸው፣ ጤናቸው እየተጠበቀ ከቤተሰቦቻቸው የፈለጉትን ‹እከሊት ትምጣ፣ እከሌ ይምጣ› እያሉ ሲያዙ፣ እየሄዱ እያነጋገሯቸው ነው:: እንዲያውም ልዕልት ተናኘ ወርቅን ‹ከኛ ጋር ትቀመጥ› ስላሉ፣ «ይቀመጡላቸው» ብለን ፈቅደንላቸዋል::

ከአራተኛ ክፍለ ጦር ወጥተን ጃንሆይ ይሠሩበት ከነበረው ታላቁ ቤተመንግሥት ከገባን በኋላ ቢሯችንን የሳቸው ጽህፈት ቤት የነበረው ውስጥ አደረግን:: ለሳቸው መኖሪያ ዱሮ አፄ ሚኒልክ አሠርተውት ይኖሩበት የነበረው ትልቅ አሮጌ የእንጨት ፎቅ ቤት ሥር የነበረ አንድ መለስተኛ ጥሩ ቪላ ተዘጋጀላቸው:: ይህ ቤት ከቤተመንግሥቱ በስተሰሜን ራቅ ብሎ ይገኛል:: የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለስብሰባ ከሚቀመጥበት ቤት በስተኋላ ነው:: በስተደቡብ በኩል ከፀሎት ቤታቸው በታች ዱሮ የበጅሮንድ (የገንዘብ ቤት ወይም ግምጃ ቤት) የነበረበት አጠገብ ጥሩ፣ ጥሩ አትክልቶችና አበቦች የተተከሉበት መናፈሻ አለ:: ዱሮ እጅ ለመንሳት ወይም አቤት ለማለት ወደንጉሡ ለሚመጣው ሰው ማረፊያ እንዲሆኑ ተብለው ከድንጋይ ተጠርበው የተሠሩ አጫጭር መቀመጫዎች ተተክለውበታል:: የጥላ ዛፎች አሉበት:: ያንን ቦታ እንደልብ ለመዘዋወር እንዲያስችላቸውና ከሰው ዓይንም ሰወር እንዲል በጣም ሰፋ ተደርጎና ወደላይም ከፍ ተደርጎ በቆርቆሮ ታጠረ:: እዚህ ውስጥ ነበር የሚናፈሱት:: ከዚህ ከተከለለላቸው ቦታ ውጪ በቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ሌላ ቦታ አይሄዱም ነበር::እዚያ



በቆዩበት ጊዜ የቀዶ ጥገናው ሕክምና የተደረገላቸው ጊዜ ብቻ አንድ ጊዜ ከቤተ መንግሥቱ ከመውጣታቸው በስተቀር ጨርሶ ወጥተው አያውቁም:: ማንም አያያቸውም ነበር:: ማንም እሳቸው ጋ አይገባም:: የምናያቸው ሰዎች የተወሰንን ነበርን:: ከቤተሰቦቻቸው መካከል ራሳቸው እገሌ ይምጣልኝ ሲሉ ተፈቅዶላቸው ከሚገቡ የንጉሣውያን ቤተሰብ፣ ጤናቸውንና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በየዕለቱ ለመከታተል ከተመደቡ ሰዎች በስተቀር ማንም አይገባም:: የደርግ አባላትም ቢሆኑ ማንም አይገባም::

ከሥልጣን ከመውረዳቸው በፊትና በኋላ በጠቅላላው ያነጋገርኳቸው ሦስቴ ወይም አራቴ ቢሆን ነው:: ብቻዬን ሳይሆን ከኰሎኔል አጥናፉ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ጥቂት የደርግ አባሎች ጋር:: በመጀመሪያ የሄድነው አራተኛ ክፍለ ጦር እንደደረሱ ከሌሎች ጓዶቻችን ጋር ሆነን ነው:: እኔ ቀርቤ በአክብሮት አነጋገርኳቸው:: «ግርማዊ ሆይ፣ እዚህ እንድትሆኑ ያደረግነው አሁን ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ችግር ምክንያት ለርስዎ ደህንነት ጥበቃ ሲባል ነው:: እና መቼም እንደኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ባይሆንም የሚያስፈልግዎ ነገር እንደማይጎድልብዎ ተስፋ አደርጋለሁ::በጎደለ ነገር ይጠይቁ»ብያቸው፣ አስገብተናቸው ነው የወጣነው::

ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደዚሁ እኔና ኰሎኔል አጥናፉ ልናያቸው ሄድን:: «ግርማዊ ሆይ» እያልን የሚገባቸውን ክብር ሳንነፍግ ነው ያነጋገርናቸው:: ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ምን እንደሚያስቡ ለማወቅ ስጠይቃቸው የተረዳሁት ኢትዮጵያን ከፍተኛ ቦታ ላይ አድርሻታለሁ ብለው እንደሚያስቡ ነው:: እሳቸው የነበሩበትን ሥርዓት ለማስታወስ «ጉልታዊ-ሥርዓት» ብዬ ስናገር ‹ጉልታዊ ሥርዓት አትበል:: ጉልታዊውን ሥርዓት ከደመሰስነው ጊዜ የለውም› ነው ያሉኝ:: ይህንን ማለታቸው የመጃጀት አይደለም:: በዕድሜያቸው ይሸምግሉ እንጂ አንዳንዶች እንደሚያወሩት ጃጅተው፣ ራሳቸውን የሳቱ ሰው አልነበሩም:: እውነት ነው በዘመናቸው የፖለቲካ ሥልጣናቸውን አማክለውታል:: በሳቸው አስተሳሰብ ጉልታዊው ሥርዓት የዱሮው የነምኒልክና ከሳቸውም በፊት የነበረው ነው:: በምኒልክ ጊዜ እያንዳንዱ የክልል መስፍን ወይም ባላባት በያለበት አገር በሕዝቡ፣ በሃብቱ፣ በንብረቱ ፈላጭ ቆራጭ ነው:: ሿሚ ሻሪ ነው:: የበላይ የለበትም:: አቤቱታ የለም፣ ፍርድ የለም:: ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት ቢኖር ዓመታዊ ግብር መክፈልና አስፈላጊ ሲሆን፣ ጦርነት

ሲመጣ፣ ክተት ሲባል ሠራዊቱን ይዞ ይዘምታል:: ከዚህ በስተቀር እያንዳንዱ በክልሉ በራሱ አፄ ነው:: ይሄንን አስቀርተውታል:: ስለዚህ በጃንሆይ አስተሳሰብ ትልታዊው ሥርዓት ካበቃለት ቆይቷል::

በኔ አስተያየት ጃንሆይን ውድቀት ላይ የጣላቸው ከሕዝባቸው መራቃቸው ነው:: የዘመኑ መሪዎች ክልል ይጎበኛሉ:: ግለሰብ ቤት ድረስ እየሄዱ የሕዝባቸውን የልብ ትርታ ያዳምጣሉ::ሃሳብ ይቀበላሉ:: ሃሳብ ይሰጣሉ:: እኛጋ እንዲህ አይነት ነገር አልተለመደም:: በባህላችንም ንጉሡን እንደፈጣሪ ነው የምናየው:: እና እንደዚህ ዓይነት ነገር በመኖሩ ከሕዝቡ ርቀው በመኖራቸው ምክንያት ሰው ስለሳቸው ያለውን አስተያየትና ግምት አያውቁትም ማለት ይቻላል:: አንዳንድ ነገር ሲነገራቸው ‹እንዴት ሆኖ? ከየት ነው እንዲህ ያለውን ፈጥራችሁ የምታወሩት?!› ነበር የሚሉት:: አንዳንድ ነገር ስለሕዝቡ የኑሮ ደረጃ፣ ስለችግሩ እንኳን ሲነገራቸው ‹ኢትዮጵያን የት ታውቋትና?!› ነው የሚሉት::

ሌላው የገረመኝ አስተያየታቸው የሃገራቸው ሕዝብ ለምንም ነገር የበቃ ነው ብለው አይገምቱም:: ከበፊቱ የተለየ አካሄድ ያስፈልገዋል ብለው አያስቡም:: ስለሰውጥ ስናነሳባቸው፣ ‹እናንተ ይሄን ውጪ ሄዳችሁ የቀላወጣችሁትን ነገር አምጥታችሁ ነው እዚህ የምትናገሩት:: ይሄንን ሕዝብ አለማወቅና አለመረዳት ነው› አሉን::

ልክ መጽሐፋቸው ላይ እንደፃፉት ‹አንድን የሁለት ወር ሕፃን ቅቤ ነው የምታውጠው ወይስ ሙዳ ሥጋ ነው የምታጎርሰው?› እንደ ዚህ ዓይነት ነገር ነው የሚናገሩት:: ሽማግሌ በመሆናቸው በዚያ ሁኔታ ስሜታቸውን መንካት ስለማያስፈልግ እንዲያው በምን የሃሳብ ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅና ስለሃገራቸው የቱን ያህል እንደሚገነዘቡ ለመረዳት ያህል እንጂ ክርክር ልገጥማቸው አልነበረም ያነጋገርኳቸው::

*ገነት - ማን መሆንዎን ያውቀዋል?*

***መንግሥቱ*** - በሳቸው ግምት አብዮቱን የቀሰቀሱትና አገሪቱን በመምራት ላይ ያሉት ጄኔራል አማን ናቸው::‹ጃኒናር አማን የታለ? መጥቶ ያነጋግረኝ› ነው የሚሉት እንጂ ‹ሻለቃ መንግሥቱ› ብለው አያውቁም:: እኛም ጄኔራል አማን ሲሉ፣ ጄኔራል አማንን እናቀርብላቸው ነበር:: ልዕልት እከሌን ሲሉም፣ «ይምጡላቸው» ነበር የምንለው እንጂ ከልክለን አናውቅም::



ከቤተመንግሥት አውጥተን አራተኛ ክፍለ ጦር በጥሩ ሁኔታ ወደተዘጋጀ ማረፊያ ስንወስዳቸው ሕዝቡ ‹ሌባ! ሌባ!› እያለ ሲጮህ እኔ የታዘብኩት ነገር አለ:: እኚህ ሰው ከጥቂት ጊዜ በፊት በመንገድ ሲያልፉ መሬት ላይ እየተደፋ የሚሰግድላቸው ሰው ዛሬ ደግሞ እንደዚህ ሲላቸው ይሄ ራሱን የቻለ ትምህርት ይሰጣል:: ጊዜና ሰው ተለዋዋጭ ነው:: ጊዜ ሲያዘነብል፣ ሰውም ይለወጣል::

*ገነት - እሳቸውስ ምን አሉ?*

***መንግሥቱ*** - ምንም አላሉም::ዝም ነው ያሉት::ብዙ አይናገሩም:: ከዚያ በፊት ግን እዚያው አራተኛ ክፍለ ጦር እንዳለን ነው:: እሳቸውም ከሥልጣን ገና አልወረዱም:: ብዙ ገንዘብ በአውሮፓ ባንክ ጄኔቭ እንዳላቸው ይነገራል:: በቢሊዮን ነው ተብሎ እንዳውም በአኃዝ የቀ ረበልን 12 ቢሊዮን ነው ተብሎ ነው:: እኔ በበኩሌ ይህን ያህል ገንዘብ ይኖራቸዋል የሚለውን አላመንኩም:: በሳቸው የአገዛዝ ዘመን በጠቅላላ የነበረው የኢትዮጵያ ባጀት ቢደመር እንኳን ሳነፃፅረው እኚህ ሰው እንዴት አድርገው ይህን ያህል ብር ያስቀምጣሉ? ብዬ ነበር:: ባንድ በኩል ግን ምንም ገንዘብ የላቸውም ብዬ ማመንም አልቻልኩም:: የነበ ርንበት ሁኔታ ደግሞ እጅግ አሳሳቢ ነበር:: ካዝናው ፈጽሞ ባዶ ነው:: ምንም ነገር የለም:: የወሎ ረሃብ በጣም አስቃቂ ነበር:: ጠላቶቻችን አሰፍስፈው ሲገኙ እኛ ግን ወታደር ለመመልመልም ሆነ መሣሪያ ለመግዛት ምንም አልነበረንም:: መምህራኑ፣ ሠራተኛው፣ ሁሉም ደሞዝ ጠያቂ ነው:: የምንከፍለው ነገር የለም:: ከየት ይምጣ?

ተነሳንና ጃንሆይ ዘንድ ሄድን:: «ገንዘብ አለዎት ይባላል:: ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ይሄ ነው:: ችግሩ ይሄን ይመስላል:: ይሄ ገንዘብ ውጪ አገር ቀርቶ የማንም ሲሳይ ከሚሆን የሚወደንና የምን ወደው ለሚሉት ሕዝብዎ ቢቸሩት» ብለን ብንጠይቃቸው፣ ‹ከኢትዮጵያ ሕዝብ ደብቀን ያስቀመጥነው ገንዘብ የለንም› ብለው በጥሞና መለሱልን:: በአጠገባቸው የነበሩት ሴት ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ግን አካኪ ዘራፍ አሉብን:: ተቆጡ:: እኛም በእርጋታ ጃንሆይን «ግርማዊ ሆይ! እስቲ ያስቡበት፤ እኛ አይደለንም ይህን ጥያቄ ያቀረብነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ግርማዊነትዎ በስደቱ ዘመንም ይሁን ወደኋላ ጊዜ ምናልባት ላንድ ክፉ ቀን ብለው ለራስዎም ባይሆን ለአገር ያስቀመጡት ገንዘብ ካለ ብለን ነው:: ሕዝቡ በውጪ ለኢትዮጵያ ብለው ገንዘብ አላስቀመጡም ብሎ ለማመን ስለሚቸገር

ነው:: እርስዎ ያመዛዝኑት» ብዬ ሌሎች አባሎችን አስወጥቼ እኔ ብቻ አነጋግሬያቸው ወጣሁ::

*ገነት - ልዕልት ተናኘ ምን ብለው ነው የተቆጡት?*

*መንግሥቱ* - ‹እንዴ! ቢኖረንስ? እንዘረፋለን እንዴ? እኛም እኮ ልጆች አሉን:: እናወርሳለን:: ለልጆቻችን እንሰጣለን:: ቢያስፈልግ ጠበቃ ገዝተን እንሟገታለን› አሉ:: በቁጣ ነው:: እንዴት ተደፍረን፣ እንዴት ተጠይቀን ነው አነጋገራቸው::

እኔ ደግሞ ከልዕልት ተናኘ የምጠብቀው የአነጋገር ዘይቤ እንደ ዚህ አልነበረም:: የንጉሥ ልጅ እንደመሆናቸው መጠን ሥነ ሥርዓት ያላቸው፣ የተማሩ ነበር የሚመስሉኝ:: የሚናገሩትን ነገር ከማንነታ ቸው አንፃር አመዛዝነው የሚናገሩ፣ እንዲህ ያለ ነገር ነበር የምጠብ ቀው:: እሳቸው ግን ንግግራቸው፣ አለባበሳቸው ሁሉ ተራ፣ እንዳው ዝም ብለው ከጥርሳቸው የፈለጉትን ነበር የሚወረውሩት::

ከዚያ በኋላ በሌላ ጊዜ ልዑል ራስ እምሩ በታዛቢነትም በአማላጅ ነትም በተገኙበት፣ሌሎቹም ልዕልታትና ልዑላን ባሉበት እንደገና ሰፋ ባለ ዝግጅት ማስረጃ ይዘን ለመጠየቅ ወሰንን:: ስንመክርበት፣ ‹ቆይ እስቲ መጀመሪያ ነገር እኚህ ሰው ገንዘብ አላቸው ወይም የላቸውም ለማለት አንድ አይነት መርቺያ ወይም መሟገቻ ፍንጭ ያስፈልገናል› ተባለ:: ማስረጃ ፍለጋ ተሯሯጥን:: አውሮፓ ሰው ላክንና ባንኩን ጠየ ቅን:: የሃገራችንን ብሔራዊ ባንክ ጠየቅን:: የባንኩ ገዢ አቶ ተፈራ ደግፌ ነበሩ:: «ንጉሡ ይሁኑ ሌላ ሰው ገንዘብ ለማስቀመጥ ምን ዓይነት ፎርማሊቲ ይጠየቃል? በምን መልክና ዘዴ ነው?» ብለን ጠየቅናቸው የባንኩ ገዢ ‹እኔ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብሔራዊ ባንክን ማስተዳደር እንጂ ሌላ በምስጢር ስለሚቀመጥ ገንዘብ የማውቀው ነገር የለም:: መኖሩንም አላውቅም:: የንጉሡን ገንዘብ አቀማመጥ በተመለከተ ምንም ግንኙነት የለኝም:: የማውቀውም ነገር የለም› የሚል መልስ ሰጡኝ::

«ተዉ ግድየለዎትም፣ የምንጠይቅዎትን ባይነግሩን እሳቸውንም አይረዱ፤ ራስዎንም አይረዱ:: እዚህ ቦታ ላይ ለብዙ ዓመታት ተቀም ጠው የሠሩ ሰው ነዎት:: እንዴት አያውቁም? ይሄ ገንዘብ እርግጠኛ ነኝ የማንም ሲሳይ ሆኖ ነው የሚቀረው::የሕዝብ ባለውለታ ይሆናሉ:: እርዱን እንጂ» ስላቸው፣ ‹እኔ በውነቱ የማውቀው ነገር የለም:: ከኢት ዮጵያ ሕዝብ ተደብቆ የተቀመጠ ገንዘብ ቢኖራቸው የሳቸው የግል ገንዘብ ሊሆን አይችልም:: የሕዝብ ገንዘብ ነው ማለት ነው:: ስለዚህ



እኔም በኢትዮጵያዊነቴ ይመለከተኛል:: ነገር ግን እንዲህ ያለውን ነገር ለማድረግ ቢያስቡ ለኔ የሚያማክሩበት ምንም ምክንያት የለም:: እዚህ ላይ አትሞኙ:: እኔኮ የአንድ ሥራ መስክ ኃላፊ ነኝ እንጂ የንጉሣዊ ቤተሰብ አባል አይደለሁም:: እኔ እንዴት ምስጢር ተካፋይ መሆን እችላለሁ? ለዚያውም በርግጥ ገንዘብ አስቀምጠው ከሆነ እኔ ቀርቶ ልጆቻቸውም የሚያውቁ አይመስለኝም› አሉኝ::

ሰውዬው ካነጋገራቸው አሳመኑኝ:: ከዚህ በላይ የንጉሡ ገንዘብ ያለበትን ታውቃለህ ብሎ ሰውዬውን መፈተን አስፈላጊ አለመሆኑን ከውይይታችን ግንዛቤ አገኘሁ::

ዛሬ የስዊስ ባንኮች የዛሬ 50 ዓመታት ገደማ ከአይሁዳውያን የዘ ረፉትን ገንዘብ አፍንጫቸውን ተይዘው ሲከፍሉ፣ ያን ጊዜ ለኛ እንኳን ገንዘብ ሊሰጡን ምንም ነገር፣ ምንም ዓይነት ፍንጭ አልሰጡንም:: ከንጉሡ ጋር ያላቸው ውለታና ምስጢር በምንም ዓይነት አይገለጥም:: ምንም ነገር አይገለጥም:: ለነገሩ ለኛ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም መሪዎች እንደዚሁ ነው የሆነው:: ለምሳሌ፣ የግብፁ ንጉሥ ፋሩቅ ያሸሹትን ሃብት እነኮሎኔል ጋማል አብደል ናስር ለማስመለስ ብዙ ጥረው ሳይሳካ ላቸው ቀርቷል:: እነሱን ሁሉ (ግብፆቹን) ሄደን እስከመጠየቅ ደርሰ ናል:: «ምንድነው ያጋጠማችሁ ችግር» በማለት::

እና ምንም ሳይሳካልን ቀረ:: ቤተመንግሥት የነበረው የንጉሡ የግል ካዝና እንዲመረመር ተደረገ:: ሲከፈት በጣም ልዩ በሆነ ረቂቅ ሥራ የተሠራ የቆዳ ቦርሳ ተገኘ::ያ የቆዳ ቦርሳ የተቆለፈ ነው:: ቁልፉ የለም:: ቁልፉ የት እንደሆነ አንድ ውስጥ አዋቂ የሆነ ሰው ጠቆመን::

*ገነት – ማን?*

*መንግሥቱ* - አይ ስም እንኳን አልነግርሽም:: በጣም ጠንካራ ግን ትንሽና ረቂቅ በወርቅ የተሠራች ቁልፍ ነች:: ይቺን ቁልፍ እሳቸው በእጃቸው ላይ እንደቀለበት አስረዋታል::

*ገነት - እውነት ነው ማለት ነው ለለቀለበታቸው?*

*መንግሥቱ* - አዎን:: እጃቸው ላይ አድርገዋታል:: እሱን ለመጠ የቅ ስሄድ ነው ለሁለተኛ ጊዜ ያየኋቸው:: «ቀለበትዎን ስጡን» አልኳ ቸው፣ ‹እሺ› አሉና ሰጡን::

*ገነት - «እሺ» አሉ?*

መንግሥቱ - አዎን፤ ግን መጀመሪያ ‹ለምንድነው?› አሉ:: «ይመ ለስልዎታል፤ቁልፋን እንፈልገዋለን» አልኳቸው:: ‹በምን አወቃችሁት?› አሉ:: «ግርማዊ ሆይ! ይሄን ማወቅ ይገዳል እንዴ? ይከብዳል እንዴ?» አልኳቸው::

‹ውሰዱ› አሉ::

«እንመልስልዎታለን::»

‹እንዳሻችሁ› አሉ:: ወሰድንና ከፈትን:: እኔ እንኳን ሲከፈት በቦ ታው አልነበርኩም:: ሰው ነው የላኩት:: ሲከፈት ቦርሳው ውስጥ ልዩ የሆኑ የባንክ ሰነዶች ተገኙ:: ተፈራ ደግፌም ይሄንን (የባንክ ሰነዶች መሆናቸውን) አልካዱም:: ነገር ግን በጣም የተመሰጠሩ በኮድ የተፃፉ ነገሮች ነበሩ:: እኔ እንደሚመስለኝ ያስቀመጡት ገንዘብ የገቢና የወጪ ዝርዝር (የባንክ ስቴትመንት) ሳይሆን አይቀርም:: ግን መፍታት አልተቻለም:: ጄኔቭ ሰው ተልኮ ‹ይሄ ምን ማለት ነው?› ቢባል፣ መልሱ ‹አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበናል (No Comment)› ሆነ::

እንግዲህ ይሄን ሁሉ ነገር ካደረግን በኋላ ይቺን ፍንጭ ይዘንና ልዑል ራስ እምሩንና ሌሎቹንም ልዕልቶች ይዘን እንደገና በቤተሰባ ቸው ፊት ልንጠይቃቸው ሄድን:: ልዕልት ሣራም፣ የልጅ ልጆቹም ነበሩ::

በቤተሰቡ ፊት ልንጠይቅ የተነሳንበትም ምክንያት አለን:: የልዑል መኮንን ልጆች አንዳንዶቹ ‹እኛ ገንዘብ መቀመጡን አናውቅም:: አልተነገረንም:: በኛ ስም የተቀመጠ ነገር ካለ ይሰጥ› ብለዋል የሚል ነገር ስለሰማን ነው:: እንግዲህ ምናልባት ልጆቹ የሚሉት ነገር ይኖር ይሆናል:: ፊት ለፊት ሲገጣጠሙ የቤተሰብ ገበና ሊወጣ ይችላል ብለን ነው::

ታዲያ ሁሉንም አሰባሰብንና አሁንም በአክብሮት «ግርማዊ ሆይ! አገሪቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ትገኛለች:: ሕዝቡም በዚህ ዓይነት ችግር ላይ ይገኛል::የመንግሥት ግምጃ ቤትና ባንክ ባዶ ነው:: ሕዝቡ አሁንም በረሃብ እየሞተ ነው:: ሶማሊያና ሌሎች ጠላቶቻችን አሰፍስ ፈው ከበውናል:: እና ከማንም በላይ የደከሙላትን ሃገርዎን የሚያድ ኑበት ጊዜ አሁን ነው:: በዚህ ችሮታዎ ደግሞ በሕዝቡ ላይ የሚያሳድ ሩት በጎ ተፅዕኖ ሌላ ታሪክዎንም የሚያሳምር ነው:: እኛ ፍንጭ አግኝተናል:: ይሄ የባንክ ሰነድ ነው:: ባንክም ሄደን ያገኘነው ግንዛቤ አለ:: አሁንም በድጋሚ የማሳስብዎት ይሄ ገንዘብ በውጪ ባክና



ከሚቀር ሕዝቡ ይጠቀምበት» በሚል አክብሮት በተመላው ጥንቃቄ ተናገርኩ:: ይሄን ጊዜ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ቱግ አሉ::

‹እንዴ! ገንዘብ ቢኖረንስ? እንዘረፋለን እንዴ? እኛስ ልጆች የሉንም እንዴ? ልጆቻችን ምን እንዲሆኑ ነው?!› አሉ:: ይሄንን ሲሉ ገንዘብ እንደተቀመጠ ማመናቸው ነው:: አይደለም እንዴ? አድሚት አደረጉ ማለት ነው::

ይሄኔ «ምናለበት ታዲያ? የናንተም ልጆች ሌላው ሕዝብ እን ደሆነው ይሆናሉዋ! ይሄ ገንዘብ ብቻ ነው እንዴ ሕይወታቸው? ኢትዮጵያ አገራቸው ናት:: መጀመሪያ'ኮ ኢትዮጵያ መኖር አለባት» የሚል መልስ ሰጠኋቸው::

ራስ እምሩ ይሄን ጊዜ ‹ቆይ እስቲ እንደማመጥ እንጂ› አሉ:: ልዕልት ተናኘ ግን አሁንም ወደኛ እየተመለከቱ ‹አይቻልም! አይቻ ልም! ልትዘርፉን አትችሉም:: ልትነጥቁን አትችሉም:: ቢያስፈልግ ጠበቃ ከውጪ ገዝተን እንሟገታለን› አሉ::

‹ቆይ እስቲ አንቺ› አሉ ንጉሡ::

ከዚያ ደግሞ ልዕልት ሣራ ጀመሩ:: ልክ እንደተራ ሴቶች ነው ንግግራቸው (በመሠረቱ ልዕልት ሣራን የሚያገባቸው ነገር የለም):: እኔ እንዳው በጣም ነው የሚገርመኝ:: ንጉሡ አልታደሉም:: ቤተሰብ አላፈሩም:: ልጅ አልወጣላቸውም::

ልጆቹ ይሄን ጊዜ ተነሱና ትልቁ፣ ልዑል ወሰንሰገድ ነው ትዝ ይለኛል:: ‹እንዴ! አንቺ ምን ያገባሻልና ነው? ምን የምታውቂው ነገር አለ? ለልጆቻችን እናወርሳለን ለምትሉት እኛ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ ምንም የምንፈልገው ነገር የለም:: ያለ ነገር ካለ በኛ አይሳበብ አውጡና ስጡ:: እኔ በበኩሌ ለኔ ያሰባችሁልኝ ነገር ካለ አሁኑኑ እንድትሰጡ እፈልጋለሁ› አለ:: እንግዲህ እናትና ልጅ ተጣሉ:: ታናሽ ወንድሙ ደግሞ በጣም ትሁትና አይንአፋር ነው:: እንደገባ ንጉሡን እጅ እነሳለሁ ብሎ ጎንበስ ሲል የለበሰው ኮት ጠበብ ያለ ነበር ቁልፎቹ ጧ! ብለው ተበጠሱ:: ትልቁ ግን በደንብም ሠላም አላላቸው::

በዚህን ጊዜ ራስ እምሩን አንድ ነገር በሉ ብዬ በዓይኔ ጠቀስኳ ቸው:: እሳቸውም ‹መቼም እኔ ገንዘብ አለ፣ የለም የሚለው ነገር ውስጥ ለመግባት ሳይሆን ገንዘብ አለ የሚለው ነገር በሕዝብ ውስጥ የተሰራጨ ወሬ ነው:: ስለዚህ መልስ መስጠት አስፈላጊ ይመስለኛል:: እንደተባለው ደግሞ እውነት ገንዘብ ካለ ካገራችን የበለጠ ነገር የለም::

ይሄ ደግሞ ለግርማዊነትዎ በኔ አንደበት የሚነገር አይደለም። ያለው ችግር አንድና ሁለት የለውም (ያን ጊዜ ገና የወሎውን ረሃብ ፊልም አላሳየንም)። እና አንድ ነገር ይደረግና ቁርጡ ይነገር› አሉ።

እሳቸውም ራስ እምሩን በመገርመም አዩና ‹እኛ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ደብቀን ያስቀመጥነው ነገር የለም ብለን አንዴ ነግረናችኋል። ይሄ የመጨረሻ ቃላችን ነው። ከዚህ ሌላ ምንም የምናደርገው ወይም የምንናገረው ነገር የለም። ማስረጃ ስለምትሉት ይሄ የያዛችሁት ሰነድ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ባንክ የሰጣችሁ ሌላ ማስረጃ ካለ አምጡትና እንየው› አሉ።

«እሺ፤ ታዲያ ይሄ ሰነድ የምንድነው?»

‹እሱን ለናንተ መንገር አስፈላጊ አይደለም።›

«ሊነግሩን አይፈልጉም?»

‹አዎን። አስፈላጊ አይደለም።›

እንግዲህ የተቻለውን ሁሉ ሞከርን።ኮሎኔል አጥናፉም የበኩሉን ተናገረ። ምንም እንደማይሆን ገባን። ከዚያ በኋላ እምቢ ማለታቸውን ለሕዝቡ ይፋ አደረግን። ይህም በሕዝቡ ላይ መጥፎ ስሜት አሳደረ።

ወደተነሳሁበት ልመለስና እሳቸውን ከሥልጣን ስናወርድ ያወረ ድናቸው ለመጣልና ለማዋረድ ወይም ለመግደል አይደለም። የወቅቱን ሁኔታዎች፣ የወሎ ረሃብ ያሳደረውን ስሜት፣ የሕዝቡን ምሬትና ባጠ ቃላይ ለለውጥ የነበረውን ፍላጎት ማስታወስ ያስፈልጋል። ንጉሡን ከሥልጣን በማውረዳችን የደረሰ ተቃውሞ የለም- ከሥርዓቱ ተጠቃ ሚዎች በስተቀር (እነሱስ ስንት ናቸው?)- ይሄ ከመሆኑ በፊትም ብዙ የተወያየንበት መሆኑን ቀደም ብዬ ጠቅሻለሁ። «ምን ዓይነት መንግ ሥት? ሕዝቡስ የሚቀበለው ገንቢ እርምጃ ምንድነው?» የሚባለውን ነገር ሁሉ አብስለን ተወያይተንበታል። ለሳቸውስ ምን ዓይነት ቦታ? ይሄን ሁሉ እየተወያየን ነው እንጂ የምንወስነው እንዳው በአንድ ሰው ፍላጎት ብቻ የሚደረግ ነገር አልነበረም። ንጉሡን መግደል ያህል ግዙፍ ነገር ወይም ሌላ ከባድ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን ሥልጣን እንደነ በረኝ ተደርጎ ሲነገር ይገርመኛል። ይሄንን መቼም ከደርግ አባላትና ከውስጥ አዋቂዎች መረዳት ይቻላል።

እኛ ንጉሡ አጠገብ እንኳን ስንቀርብ በግል አንቀርብም። ምክንያ ቱም ‹ከንጉሡ ጋራ ምን አላቸው? ምን አሉት? ደግሞ ምናልባትም በገንዘብ? ...› ይሄን የመሳሰለ ነገር ሁሉ አለ የሚል ነገርም ስለሚነሳ እርስ በርሳችንም ስለምንፈራራ እኔ ብቻዬን ሳይሆን ከሰው ጋራ ነበር



የማነጋግራቸው። ራስ እምሩንም እንዲገኙ ያደረግነው ሕዝቡ እን ዲያምንና እውነት እንደሆነ እንዲረዳ በእማኝነት ነው። ሰዎቹን ቁጭ አድርገን ስናበቃ፣ ስንነጋገር በካሜራና በድምፅ ተቀርጿል። ውሸታቸ ውን ነው እንዳይባል እማኝ እያደረግን ነው። ባጭሩ ምንም ነገር ብቻችንን እንደማናደርግ ነው።

ገንዘቡን በተመለከተ እምቢ ማለታቸውን ይፋ ስናደርግ ሕዝቡ ተቆጣ። ከዚያ የሆነው ሁሉ የሚታወቅ ነው። ከዚያ ከወረዱ በኋላ ጤናቸው እየተበላሸ ሄደ። በአንድ ጊዜ ተለወጡ። ምናልባት የደረሰባ ቸው ነገር ሾክ ያድርጋቸው፣ ብቸኝነት ይሰማቸው፣ መቼም ብዙ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በሌላ ጊዜ ስናነጋግራቸው እንዳው ትንሽ የመሳት ነገር ተመልክተናል። ለምሳሌ፣ የሌሉትን፤ ዱሮ፣ ዱሮ የሞቱትን ሰዎች (እነጄኔራል ደጎልን) ሁሉ እያነሱ ይጠይቃሉ። «አ! እኚህ ሰው ... እስቲ ሐኪሞች ይምጡና ይጎብኟቸው» አልን። ሐኪሞ ቻቸው እነፕሮፌሰር አሥራት እየመጡ ያዩዋቸው ነበር።

ከዚያ በኋላ የእስር ቤት ጥበቃ ኮሚቴ የሚባል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አለ። የንጉሠ ነገሥቱ ጥበቃ ኮሚቴ የሚባል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አለ። ኃላፊ አለው። ለኛ በየጊዜው ጤናቸውና ሁኔታቸውን በተመለከተ ሪፖርት ይደረግልናል። ከዚህ በተረፈ እሳቸውን የምናነ ጋግርበት ጊዜና ሰዓት አልነበረንም። ‹ገንዘብም የለኝም› ብለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሊደረግላቸው የሚችለው ነገር ሁሉ ያለማሰለስ ይደረጋል። እኔን እዚያ የሚያመላልሰኝ ምክንያት የለም። እኔም ሆንኩ አጥናፉ አላየናቸውም። ደግሞ ማንም ሰው የሚሄድ የለም። አንዱ ቀባጣሪ ‹ሐኪም ቤት መጥተው ሲያነጋግሯቸው ምንትስ ብለው፤ እን ደዚህ ብለው› አሉ እያለ የፃፈውን አይቼ በጣም ገርሞኛል። እሳቸው ከዚያ ግቢ ወጥተው አያውቁም። ሐኪሞች ከነሙሉ ዕቃቸው መጥ ተው ነው የሚያክሟቸው እንጂ ንጉሡ ከቤተመንግሥት ወጥተው አያውቁም። እስከመጨረሻው። ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ደግሞ እንዳ ያቸው አድርጎ ጽፏል። ዳዊትን ዓይነት ሰው ቀርቶ ከደርግ አባሎች እንኳን የሚሄድ ሰው የለም። ጥበቃው ጥብቅ ነው። ግንኙነትም የለም።

የንጉሡ ጥበቃ ኃላፊ ሻለቃ የጎራው ነበር። ከሱ በላይ ኮሎኔል ዳንኤል ነው። በጥበቃ ኃላፊው ሥር ሆኖ ግቢው ውስጥ የሚሠራ እንዳለ የሚባል ነርስ ተመድቦ ነበር።ይሄ ነርስ እዚያው በቅርብ እንዲ ሆን የተመደበው ጃንሆይን ለማከም ሳይሆን አንድ የጤና መታወክ

ቢያጋጥማቸው ሐኪሞቻቸውን እንዲጠሩ፣ እንዲሁም አንድ የጊዜ ፕሮግራም ወጥቶለት በሳምንት በተወሰነ ቀን እየሄደ እንዲጎበኛቸው:: እሳቸው ጤናቸውን በሚመለከት ‹አንድ ነገር እፈልጋለሁ› ወይም ‹እንዲህ ያለ ችግር አጋጥሞኛል› ቢሉ ሐኪሞቻቸው እስኪደርሱ የሕክምና ባለሙያ የሆነ ሰው አጠገባቸው እንዲሆን ነው:: እሱውም ሁል ጊዜ ከጠባቂዎች ጋር በነሱ ሥር ሆኖ ነው የሚሠራው:: ንጉሡ ጋ ማንም አይቀርብም:: እንደነርሱ ለሥራ የተመደበ ሰው እንኳን ቢሆን ብቻውን ሊጠጋቸው አይችልም::

በመጨረሻው ላይ፣ በተለይም የጤና ችግር ካጋጠማቸው ወዲህ በደርግ ስብሰባ ላይ ስለጤንነታቸው ሪፖርት ተደርጎልናል:: የጥበቃ ክፍሎቹ የሚያቀርቡትን፣ አልፎ አልፎ ራሱ ኰሎኔል ዳንኤል ወይም ደግሞ የደርጉ የእስር ቤት ኮሚቴ ሊቀመንበር ያቀርባል::

አንዳንድ ጊዜ በእግራቸው ግቢው ውስጥ ሲንሸራሸሩ ከጠባቂ ወታደሮች ጋር የሚያደርጉት የንግግር ልውውጥ በቀልድ መልክ ሲነገር እንሰማለን:: ባንድ አጋጣሚ አንዱን ወታደር ‹እስቲ ጠመንጃህን ልየው› ይሉታል:: ወታደሩ በአክብሮት ይሰጣቸዋል:: ሳቅ ይሉና ‹ጠባቂያችን ሆነህ እንዴት መሣሪያህን ትሰጠናለህ?› ብለውት አለፉ::

ልዕልት ተናኘ፣ ጃንሆይ ሊሞቱ አካባቢ አጠገባቸው መሆናቸውን እጠራጠራለሁ:: ምክንያቱም ንጉሣውያን ቤተሰቡን በክብር ይዘናቸው በቀድሞው የልዑል መኰንን ቤት አስቀምጠናቸው በራሳቸው ጥፋት ወደ ወህኒ ከወረዱ ወዲህ ጃንሆይ ዘንድ የሄዱ አይመስለኝም::

# የመጀመሪያዎቹ ሰለባዎች

*ገነት - የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣናት የነበሩትንና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ ሌሎች የጦር አባሎችን ህዳር 14፣ 1967 የሞት ፍርድ ፈርዳችሁባቸዋል::ሕግና ፍትሕ ያለ መስሏቸው እጃቸውን በመስጠት በጥበቃችሁ ሥር የነበሩትን (በተለምዶ ስልሳዎቹ እየተባሉ የሚጠሩትን) ሰዎች አንዳቸውም ሕግ ፊት ሳይቀርቡ ጥፋተኝነታቸው ሳይረጋገጥና ሳይ ፈረድባቸው በድምፅ ብልጫ እጅ እያወጣችሁ እንዲሞቱ በይናችሁባቸዋል:: ሕይወትን ያህል ነገር ላይ እንደቀልድ ፈርዳችኋል:: በታሪካችሁ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥለው ካለፉት ነገሮች አንዱ የሆነውን ይህን ገድያ እንዴት ያዩታል?*



መንግሥቱ - የኢትዮጵያን አብዮት ሁኔታ በደንብ የተረዳሽ አይመስለኝም:: የኢትዮጵያ አብዮት ሲፈነዳና ይህ ዛሬ የምንወቀስበት የፖለቲካ ውሳኔ ሲወሰን አንቺ ራስሽ ገና ተማሪ ነበርሽ:: ነገር ግን ከአባባልሽ እንደምረዳው ስለዚህ ሁኔታ ለአንድ ወገን ብቻ አድልኦን የሚያሳይ አስተሳሰብ እያንፀባረቅሽ ነው:: ከሰዎች የሰማሽውን አስተያየት ብቻ አይደለም ያቀረብሽው:: የራስሽን ስሜት ጭምር ነው የሚያንፀባርቀው:: ብዙ ኢትዮጵያውያን ስለነዚህ ሰዎች አሟሟት የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ይመስለኛል::

መጀመሪያ ነገር የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት ምክንያት ምንድ ነው? የገዢ መደቡ አባላት ያን ሁሉ ዘመን በሕዝብ ላይ ሲሰሩ የነበረው ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ያስፈልጋል::

ባለሥልጣኖቹ እያንዳንዳቸው ፈፀሙት የተባለው ጥፋት በደንብ በሕግ ሳይመረመር፣ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን በጅምላ የተፈፀመባቸው ቅጣት በማንም ዘንድ ተቀባይነት አይኑረው እንጂ በዚህ በመረረ መልኩ እነሱን ፍፁም ንፁሐን ወይም ምንም ጥፋት የሌለባቸው አድርጎ መመልከቱ፤ እነሱን ፍፁም ንፁሐን ወይም ምንም ጥፋት የሌለባቸው አድርጎ ማቅረቡ ትክክል አይደለም:: እነሱን ምንም ኃጥያት የሌለባቸውና እንዲህ ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት በትር የተሰነዘረባቸው አድርጎ በማቅረብ እነሱ ለዘመናት ሲያጠቁትና ሲበድሉት የኖረውን ሕዝብ ሰቆቃ እንደቀላል ነገር ቆጥሮ ማለፍ ሚዛናዊ ፍርድ ሊሆን አይችልም::

የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ መለስ ብለን ብንመለከት በየትኛው የመንግሥት ለውጥ ጊዜ ነው ሠላማዊ የሥልጣን ርክክብ የተደረገው? አንዱ ንጉሥ ሞቶ ሌላው ሲተካ፣ አንዱ ገዢ ተሸሮ ሌላው ሲሾም፣ በፍቅር ተሸጋግሮ ያውቃል እንዴ? ተራኮቶ ተላልቆ ተፋጅቶ አይደለም? ለመጀመሪያ ጊዜ መልክ የያዘና ዘመናዊ በሆነ መንገድ ሥር ነቀል የሆነ የሥርዓተ ማህበር ሽግግር የተደረገው በ1966 አብዮት ነው::

ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ፣ ማለትም ንጉሥ አንስቶ ንጉሥ መተካት ሳይሆን የነበረን ሥርዓት ለውጦ አዲስ ሥርዓት ለመተካት የተሞከረው ለመጀመሪያ ጊዜ ያኔ ነው:: ይህ ታላቅ ነውጥ ያመጣና ከፍተኛ መሥዋዕትነት የተከፈለበት ነው:: በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ ምንድን ነበር የተከናወነው? በሰባ ቀን ጊዜ ውስጥ የፓሪስ ወዛደሮች ተሰብስበው ሲያበቁ ሲያላግጡባቸው የኖሩትን መሳፍንቱንና መኳን

ንቱን ስል መጋዝ በአደባባይ ተክለው አንገታቸውን በመቁረጥ ሕዝቡ ተሰብስቦ እያጨበጨበ ነበር ያሰናበታቸው:: በእንግሊዝና በጀርመን የቡርዧ አብዮት ታሪክ፣ በራሽያ፣ በነኚህ ሁሉ የተከናወነ ነው:: ከዚያ ጋር ሲነፃፀር በኛ አገር የተከናወነው፣ በውነቱ በጣም የተጋነነ ነው::

ማንም አመነም አላመነም እኔ የምናገረው እውነቱን ነው:: በበኩሌ የተወሰደውን እርምጃ አልደገፍኩትም:: ሌሎቹም የደርግ አባላት ቢሆኑ በስልሣዎቹ ግድያ ሊጠየቁ አይገባም:: ምክንያቱም በተቆጡና በተናደዱ የንዑስ ደርግ አባላት ድምፅ ተውጠን፣ በዚያ ውስጥ ተደፍቀን የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ ነው:: እኛ የተነሳንለትና ቆመንለት የነበረው ዓላማ ይሄ አልነበረም:: ያንን የመሰለ ውሳኔ ለመወሰን አላሰብንም ነበር::

የፍትሕ ሥርዓቱን አመቻችተን ከወረዳ ጀምረን እስከጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ በየደረጃው አቋቁመናል:: ሰዎቹ ለጥፋታቸው የሚመጥን ቅጣት በሕጉ መሠረት እንዲያገኙ ነበር የፈለግነው:: ደግሞም ለነሱ ብለን ብቻ ሳይሆን ለዘመናት በዳኝነት እጦት ሲንገላታ የኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬም የተሻለ ነገር አጥቶ እንዳይቸገር፣ እኛም ደግሞ የጣለብንን አደራ ተወጥተን አገሪቱን በሕዝብ ለተመረጠ አካል አስረክበን ወደግንባታውና ወደመደበኛ ሥራችን እንመለሳለን የሚል ነበረ ሃሳባችን:: ወደፊት የሚመጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖችም ሆኑ የአሁኖቹ ለጊዜው የሚጠይቀን የለም ብለው ሕዝብን ቢበድሉ አንድ ቀን በሕግ ፊት መቆም እንዳለ በማስገንዘብ ለሚመጣው ትውልድም ትምህርት ይሰጣል ብለን ነበር የምናስበው::

መርማሪ ኮሚሽን የተቋቋመ ጊዜ ቢሯቸው ድረስ ሄጄ ያደረግሁት ንግግር ነበር:: በኋላም ኃላፊነቱን ሲረከቡ ጠርተን የሰጠናቸው መመሪያ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ተላልፏል::ፍትሕ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሐቅ ሲሰራ እንዲታይ ነው የምንፈልገው ብለናል:: እነፕሮፌሰር መስፍን፣ እነበረከት፣ ለማ ጉተማና ሌሎቹም ነበሩ::

እንግዲህ ይሄን ሁሉ ካስተካከልን በኋላ ነው የያን ዕለቱ ነገር እንደዱብ ዕዳ የወረደብን:: ለዚህ ሁሉ መነሻ የሆኑት አንድ ሰው ነበሩ:: ጄኔራል አማን አንዶም::

ጄኔራል አማንን የደርጉ ሊቀመንበር አድርገን ስንሾማቸው በሠራዊቱ ተመርጠው አልነበረም:: ከቶውኑም የደርግ አባል አልነበሩም:: እንዳውም አንዳንዶች ‹አሁን ሰው ጠፍቶ ነው እሳቸውን የምትሾሙት? ያለቅጥ ካባችኋቸው እኮ› የሚሉን ነበሩ:: እኛ ደግሞ ስለኤርትራ



ጉዳይ መፍትሔ ለማግኘት ይረዱናል፣ መከላከያውን ያደራጁልናል በሚል ነው እውነትም ከበን፣ ከበን እላይ ያወጣናቸው:: አማን ብዙ ኳሊቲዎች እንዳሏቸው ግልፅ ነው:: በዚያው ልክ ደግሞ ሥልጣን ማግበስበስ የሚወዱ ሰው ነበሩ:: ከመጀመሪያው ገና ከሳቸው ጋር ቅራኔ ውስጥ የገባነው በዚህ ፀባያቸው ነበር:: «ይሄንን ተዉ» ነበር የምንላቸው:: ለምሳሌ፣ ጄኔራል ግዛው በላይነህን ለምድር ጦር አዛዥነት ገና ስናስባቸው ተቃወሙ:: ‹ምክትል ቺፍ ኦፍ ስታፍ ከሆነ አይበቃውም ወይ!?› ብለው ውልግድ አሉ:: ይሄ ማንም የሚያውቀው ታሪክ ነው::

ጄኔራል ግዛው ደግሞ ከጄኔራል አማን በችሎታ ቢበልጡ እንጂ የሚያንሱ ሰው አልነበሩም:: ችሎታ ያላቸው፣ በንግግራቸው ግልፅና ጨርሶ አድርባይነት የማያጠቃቸው የረቀቁ መኰንን ነበሩ:: በአገልግሎታቸውም የኢትዮጵያን ሠራዊት ያስተማሩ ሰው ናቸው:: ገና ጦር ትምህርት ቤት እያለን ጀምሮ ዝናቸውን እናውቃለን:: ወታደራዊ ስልትና ጥበብ የምንማርበትን መጽሐፍ ያዘጋጁት እሳቸው ናቸው::

ከዚያ አማን ጭራሽ ሊያሳስሯቸው ሞክረው ነበር:: ቅድም እንዳልኩት ጄኔራል ግዛው በንግግራቸውም ሆነ በተግባራቸው ግልፅ በመሆናቸው የሚሰማቸውን ሁሉ ፊት ለፊት የሚናገሩ ሰው ናቸው:: ለፖለቲካውና ዲፕሎማሲያዊ ንግግር ብዙም ትኩረት አይሰጡትም:: በዚያን ሰሞን ወታደሩ የደሞዝ ጭማሪው አልበቃንም ብሎ ሲያጉረመርም ሰብስበው ‹ኢትዮጵያ ትቅደም ብለህ ተነስተህ የለም እንዴ? አሁን ደሞዝም፣ ቀለብም ተጨምሮልሃል:: ሌላ ከየት መጥቶ ነው የሚጨመርልህ? እንደበፊትህ ሥርዓትና ዲሲፕሊን ይዘህ ሥራህን ቀጥል› ነው ያሉት:: እንደዚህ ነው የሚናገሩት:: ከወታደሩ መሐል በዚህ ንግግር ያልተደሰቱ እንዳሉ አማን ስለሚያውቁ ሲያልፉ ሲያገድሙ ሁሉ ‹ግዛው እኮ ድሮውንም እዚህ ቦታ ላይ መኖር ያልነበረበት ሰው ነው::ለሱ አንድ መላ ይፈለግለት እንጂ› እያሉ ነገር ጣል በማድረግ ወታደሩን ያነሳሱ ነበር:: ሊያሳስሯቸውም ሞክረዋል:: እኔ ታዲያ «ለምንድነው የሚታሰሩት? ምን አደረጉ? በመታሰር ላይ ያሉት እኮ ወንጀል ሠርተዋል ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎች እንጂ እንዲሁ አይደለም:: ወታደርን የገሰፀ፣ ዲሲፕሊን ይከበር ያለ ሁሉ ሊታሰር ነው እንዴ? ይሄማ ወታደርን ቀና ብላችሁ አትዩ ማለት ወደአናርኪ የሚመራ ነገር ነው:: ግዛው አይነቃነቁም:: እንግባባ:: ሹመቱም የሚገባቸው ነው:: ይልቁኑ የራሳችሁን ነውራችሁን አስቡበት:: የምንሠራው

ስመላው ሠራዊት ነው:: ይሄ የግላችሁ ሠራዊት አይደለም:: እና
ጤና አትንሱት» ስል ፀጥ ነው ያሉት:: በኋላ ግን ‹እንዴት ነው ይሄ
ሰውዬ ደሞ ከግዛው ጋር ከመቼ ወዲህ ነው ወዳጅ የሆነው› ማለታ
ቸውን ሰማሁ:: እኔ ግን ከጄኔራል ግዛው ጋር ልዩ ግንኙነት አልነበ
ረኝም:: እሳቸው ለኔ ምንም ያሉኝ ነገር የለም:: የእምነትና የመርሕ
ጉዳይ ነው::

ጄኔራል አማን ይህንና ይሄን በመሳሰለ ነገር ሲያስቸግሩን በትዕግ
ሥት የቆየንበት ምክንያት ነበረን:: እሳቸው ይረዱናል ብለን ስላሰብንና
እምነት ስለጣልንባቸው ከሚገባቸው በላይ ክበናቸው ነበር:: እሳቸውን
በመደገፍ ብዙ ሠርተናል:: በፕሮፓጋንዳው፣ በምኑ እዚያ ላይ አውጥ
ተናቸዋል:: «አማን ኮዳ ትራሱ» እየተባለ:: እኔ ራሴ በእጄ በተፃፈ
ፅሑፍ አማንን አንስቼ የፃፍኩት በሬዲዮ፣ በጋዜጣ ተላልፏል:: በውነ
ትም ወታደራዊ ችሎታቸውንና አቋማቸውን የምናደንቀው ብዙ
ነበርን:: ለዚህም ነው አማን ሳይሆን «ኤ ማን» ነበር የምንላቸው::
«ቁጥር አንድ ሰው» ለማለት ነው::

ሰውዬው ሁለት፣ ሦስት ጊዜ እንደልጅ እያኮረፉ ትተውን ሄደው
ነው ቤታቸው የሚቀመጡት:: ሽማግሌ እየያዝኩ እየሄድኩ ነበር
የምለምናቸው:: «ምን ነካዎት ጄኔራል? እባክዎ ይተዉ:: ይቺ ልክ
እንደእንቁላል የሆነች አገር ናት እኮ እጃችን ውስጥ ያለችው:: እኛ
ላይ ታሪክ ጥሏታል:: ብንለቃት እኮ እምቦጭ የምትል ናት:: እርስዎ
እኛን ሰብሳቢ፣ እኛን መካሪ ነዎት እንጂ እኛ እየመጣን ጠዋት ማታ
እንዴት ነው» ስላቸው፣ ‹እኔን የማንም ሃምሳ አለቃና አሥር አለቃ
አያዘኝም!› አሉ::

እኔን በበኩሌ ብዙ ጊዜ በሚያጓጓ ሥልጣን ሊደልሉኝ ሞክረዋል::
‹ብትፈልግ አንተ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ብትፈልግ መከላከያ ሚኒስትር
የፈለግህን ውሰድ:: ይሄን ሃምሳ አለቃውን፣ምናምኑን፣ግማሹን ሹመት
ስጡት:: ወረዳ ገዢ ምናምን እያላችሁ ማሰናበት ነው:: ከዚያ በኋላ
ሥራ ይሠራል እንጂ እንዴት ነው በአሥር አለቆች አገር የሚመ
ራው?› ብለውኛል::

«እንዴት ነው ነገሩ? እርስዎ ምን ቸገረዎት? እርስዎን ያመጣ
ዎት እኮ ይሄ ኃይል ነው:: ይሄ ኃይል ደግሞ የሚያገለግልበትና የሚ
ፈለግበት ወቅትና ጊዜ አለ:: ከዚያ በኋላ የራሱን ሂደት በራሱ ጨርሶ
ይሄዳል:: አሁን እስቲ በመጀመሪያ በዙሪያችን ያሰፈሰፈውን ጠላት
እንመክት:: እኚህ እኮ ደጋፊዎቻችን ናቸው:: እያንዳንዱ ወታደር ይሄ



እርሶ የሚያጣጥሉት አሥር አለቃና ሃምሳ አለቃ እኮ ከኋላው ሺ
አሥር አለቃና ሃምሳለቃ ወክሎ ነው የመጣው:: ሺ ወታደር ማስከ
ተል ይቻላል:: እንደዚህ የሚናቅ ኃይል አይደለም:: ሌላው ችግር
አንገታችን ድረስ ዘፍቆን እያለ እርስበርሳችን በመናናቅ ጊዜያችንን
ለምን እናጠፋለን? ደርጉን በሚመለከት ላለው ነገር እኔ አለሁ::
እርስዎ ሥራዎን ይሥሩ» ብዬ ስንት ጊዜ ለምኛቸው አቅተውኛል::

ለምን እንደዚህ እንዳስቸገሩ ሳይገባን ቀርቶ በኋላ ነው የተገለ
ጠልን:: ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ ነው:: ደርግን የማፍረስ ጉዳይ
ነው:: ኃላፊነት የጎደላቸው ሆነው ነው ያገኘኋቸው::

*ገነት - በመሪ ዘንድ ግን ከፍተኛ ተሰሚነት ነበራቸው::*

*መንግሥቱ* -አዎን:: ሁኔታውን ያመቻቸንላቸውም እኛ ነን:: የደ
ርግ አባል ሳይሆኑ ከበላያችን አስቀምጠናቸዋል:: ይህ እኛ በሳቸው
ላይ ያሳደርነውን እምነት ያሳያል:: በሠራዊቱ ውስጥም ተሰሚነት አላ
ቸው በሚል፣ በተለይም ለተቸገርንበት ጉዳይ «ሂዱና ጦሩን አናግሩ»
ብለናቸው በነጌሌ፣ በሐረርጌና በኤርትራ እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል::
ማለትም ሠራዊቱን እሳቸው ላሰቡት ነገር እንዲኮረኩሩት ዕድል ሰጥ
ተናቸው ነበር ማለት ነው:: እኛ ንጉሡን ከነግሳንግሳቸው፣ ጳጳሱን
ጭምር ሳይቀር ያንኮታኮትናቸው መሣሪያ በመያዛችን ነው:: ያ መሣ
ሪያ ደግሞ ነገ ጠዋት በኛ ላይም ሊዞር ይችላል::ይሄን እናውቀዋለን፤
እሳቸውም ያውቁታል:: ሁላችንም ወታደሮች በመሆናችን:: ለዚህ ነው
ጥፋታቸው እየበዛ መጥቶ የሃገሪቱን ደህንነት ለማደፍረስ ሲቃጣ ዝም
ብለን ማየት ስለማንችል ከሁሉም የጦር ክፍሎች የመጡ ተወካዮች
ባሉበት ጉዳዩን ለማሳወቅ ቁርጥ ሃሳብ ያደረግነው:: ነገ አማን አንድ
ነገር ቢሆኑ ወይም ቢያመጡ፣ ራሳችን የካብነው ካብ ተመልሶ ናዳ
ሆኖ ሊጎዳን እንደሚችል ስለተገነዘብን የሁሉም ጦር ክፍል ተወካዮች
ባሉበት አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ፈለግን:: በሻለቃ፣ በብርጌድ ደረጃ
ሳይቀር ተወካዮቻቸው መጥተው ሁሉም እዚህ ውስጥ እጁ ይግባበት
ብለን ነው እውነቱን ለመናገር «አማን እንደዚህ፣ እንደዚህ አድርገ
ዋልና ምን እናድርግ?» ያልነው:: አገሪቱንና ሠራዊቱን ለማፍረስ
ያደረጉትን ሙከራ በደንብ ተረድተው ግንዛቤ እንዲያገኙ፤ ከዚያ በኋላ
የመሰላቸውን እንዲወስኑ ነው:: በዚህ ዓይነት መጡ:: ተሰበሰብን::
ወደ600 ይሆናሉ::

*ገነት - ይሰብሰቡ እንጂ ከደርግ አባላት በስተቀር ሌሎች የንዑስ ደርግ አባላት ድምፅ መስጠት አይችሉም ነበር።*

***መንግሥቱ*** - ማነው እንደዚያ ያለው?

*ገነት - እንዴት? ውሸት ነው?*

***መንግሥቱ*** - ውሸት ነው። ሁሉም ድምፅ ሰጥቷል። አብረውን እንዲወስኑ እኮ ነው ያመጣናቸው።

*ገነት - የዛን ዕለት የሰብሰባችሁ አጀንዳ ምን ነበር?*

***መንግሥቱ*** - የዚያን ዕለት አጀንዳ የጄኔራል አማን ጉዳይ ነበር። ብቸኛው አጀንዳ እሳቸው ነበሩ። ሌላ፣ ስለቀድሞ የኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች የሚል ነገር ጨርሶ አልነበረም። አሁንም ደግሜ ላረጋግጥ የምፈልገው እኔ ሌሎቹ የንዑስ ደርግ አባላት፣የጦሩ ተወካይ የተባለ ሁሉ አንድ ሳይቀር እንዲገኝ የፈለግሁት ውሳኔው ምንም ይሁን ምን የአማን ጉዳይ ሠራዊቱ ውስጥ የሚያስከትለውን ስሜት ስለማውቅ (እኛው ራሳችን በገነባነውና ባጋነንነው ዝናቸው የተነሳ) ሁሉም እጁን እንዲያስገባ ነው። እኔ ይቺን አስቤ ነው የጠራኋቸው እንጂ ለኃይለሥላሴ ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች ምን ስብ ሰባ መጥራት ያስፈልጋል? መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል። በቃ ይሄው ነው። እርግጠኛ ነኝ ካነጋገርኳቸው የደርግ አባላት አንዱም ከስብሰ ባው በፊት ስለታሰሩት ባለሥልጣኖች መነጋገራችንን አልመሰከረም። ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ጨርሶ አልተነጋገርንም። ያነሳም የለ። በሃሳ ባችንም የለ።እኔ ሰዎቹን በሚመለከት አጀንዳ አቅርቤያለሁ? በፍፁም! ከቤቱ ነው ጥያቄው የመጣው።

*ገነት - ታዲያ እንዴት ወደነሱ ጉዳይ ሄዳችሁ?*

***መንግሥቱ*** - ነገሩን ከሥሩ ለመረዳት በሰዎቹ ላይ የተላለፈው ውሳኔ የተወሰነ ዕለት በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ የነበረው ስሜት ምን ይመስል ነበር ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ይሄ ከየጦር ሜዳው የመ ጣው ብሶት ያንገፈገፈው ሠራዊት ግጥም ብሏል።ተናጋሪ ሞልቷል። ሁሉም አሰፍስፎ ይጠብቃል። አጀንዳውን አቅርቤ ስለጄኔራል አማን ጉዳይ መሆኑን ኀስረዳ፣ ስለአንድ ጄኔራል ጉዳይ መነጋገሩ ብዙም እንዳላስደሰተ ተረዳሁ።



ትዝ ይለኛል መቶ አለቃ ከዱ ይባላል።ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ሕክ ምና ክፍል ነበር የመጣው። መቼም ተናጋሪ ነው። እሳት ነው የሚተ ፋው። ብድግ ብሎ ሲናገር ቤቱን በጭብጨባ አናጋው። ‹ዛሬ ታሪካዊ ቀን ናት። የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቀን ናት። ይቺን ታሪካዊ ቀን እንጠቀ ምባት።ይሄን ዶሮ እየተቀለበ የተቀመጠ የወሎ ሕዝብ ነፍስ ገዳይ፣ የኢትዮጵያ ነፍሰ ገዳይ አንድ ውሳኔ ሳንሰጠው መሄድ የለብንም። አይሸታችሁም እንዴ ዶሮው? ዛሬም እኮ ደማችንን እየመጠጠ በእስር ስም ተቀምጧል!›እያለ ሲል ያ ቤት በጭብጨባና በሁካታ ተናጋ።እሱ ብቻ አይደለም። ሌሎችም እየተነሱ ‹ምንድነው ስለአንድ ጄኔራል ጉዳይ የምትጠሩን?አማን አንድ ጄኔራል ነው። እሱን ምንም አይደለም በአፍታ እንሸኘዋለን። ሕዝቡ እኮ የወሎን ሕዝብ ዕልቂት ካየ በኋላ፣ ምንድነው እነኚህን አሳሞች ቁጭ አድርገው የሚቀልቡት!? እያለ ነው የሚለው። መቼ ነው ውሳኔ የሚሰጠው?› እያለ ነው። ይሄን አንድ ሳና ደርግማ አንወጣም።› የድጋፍ ጩኸቱ፣ሁካታው ይቀጥላል።

አንዱ ይነሳና ‹እነዚህ ሰዎች ምንድነው ሲሠሩ የኖሩት? በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የወሎ ሕዝብ በረሃብ ሲረግፍ ዝም ብለው ያዩ ሰዎች ናቸው። የረገፈው እኮ ፍየል ወይም ዶሮ አይደለም። በነሱ ግድየለሽነትና ኃላፊነት የጎደለው አሠራር ነው ያ ሁሉ ጭቁን በረሃብ ያለቀው። እኛም ብንሆን ጠዋትና ማታ በየጠረፉ የምንዋደቀው የነሱ ብልሹ አስተዳደር ባመጣው ዳፋ ነው› ይላል። «የለም። ለዚህማ መር ማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል። በዚያ ተጣርቶ ለፍርድ ይቀርባሉ» ሲባል፣ ‹ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እንደበላይ ዘለቀ ያለውን ለአገሩ የተዋጋ አርበኛ በስሙኒ ገመድ እያንጠለጠለ ሲሰቅል የነበረው በየትኛው መርማሪ ኮሚሽን ተጣርቶ ነው? አፈንጉሡ ይናገሩ፣እሱ ይበይናል። ከዚህ የተሻለ ፍትሕን ድሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ አግኝቶ ያውቃል ወይ?› ይላል ሌላው።

በዚህ ዓይነት ቤቱ በፍፁም ተለወጠ። እኛ መቶ ሃያ ነን። በዚያ ሁሉ የንዑስ ደርግ አባል ተዋጥን። ተደፈቅን። ጭብጨባ ነው። ቤቱ የሁካታ፣ የፉከራ ቤት ሆነ። ያመዛዛኝና የሕግ ቤት አልሆነም። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ብዙዎቻችን ምንም ማድረግ የማንችልበት ደረጃ ላይ ደረስን። ይህን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ነው ቁጭ ያልነው። ከጠረፍ፣ ከበረሃ መጥቶ ብሶት ያደነዘዘው ነው ያን ዕለት የነበረው ተሳታፊ።

በበኩሌ ሁሉም ያከብሩኛል። ያፈቅሩኛል። ተደፍሬ አላውቅም፤ ተጀምሮ እስኪጨረስ። በሕይወቴ የተደፈርኩበት ቀን ቢኖር ያን ቀን ነበር።ያን ዕለትና የመጨረሻው የሸንጎ ስብሰባ ጊዜ እነዶክተር ኃይሉ አርአያ ሲፎልሉብኝ። 17 ዓመት ሙሉ አንድ ሰው ቀና ብሎ አይቶኝ አያውቅም። ያን ዕለት ግን ‹ምንድነው ሻለቃ መንግሥቱ!? ምን ሆነው ነው ለነሱ ሽንጥዎን ገትረው የሚከራከሩት?› ነው የተባልኩት።

***ገነት - ከዚህ መሐል የሚያስታውሱት የግለሰቦች አቋም አለ? ለምሳሌ፣ «ገደሏቸው!» የሚል ወይም «ተዉ፣ጥሩ አይደለም» የሚል? እነማን ነበሩ?***

***መንግሥቱ*** - አጥናፉ፣ ‹ይሙቱ!› ነው ያለው። የመርሕ ወይም የአብዮት ወይም የፍትሕ ጉዳይ አይደለም ለሱ። የነሱን ጥፋተኝነት ከማረጋገጥ አንፃር አይደለም የሱ ክርክር። አጥናፉ ከበላይ ዘለቀ ሞት ጋር ነው ያያያዘው። ‹እነሱ የትኛው መርማሪ ኮሚሽን፣ ኮሚቴ ተቋቁሞና ተጣርቶ ነው ስንቱ ላይ ሞት ሲፈርዱ የኖሩት? በፊውዳሎች ችሎት ፈርደው አይደለም እንዴ በላይ ዘለቀን የመሰለ ለአገሩ የተዋጋ አርበኛ በአደባባይ የሰቀሉት?› ብሎ ነው ካጠገቤ ብድግ ብሎ የተናገረው።

እንደዚያ ነገሩ ሁሉ ቀውጢ ሲሆን፣ከዋናው ደርግ አባላት ድጋፍ የሰጡኝ አሉ። ከሌሎቹ ጋር ‹በለው!› እያሉ ያጋጋሉም አሉ። ሻምበል ሚካኤል ገብረንጉሥ የሚባል የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጅ የሆነ የደርግ አባል (በኋላ ወደሻዕቢያ የገባ) እሱ አሁን ከጐኔ ነበር የቆመው። ባይሆን ስለጄኔራል አማን ሲነሳ የአገር ልጅም ስለሆኑ ወደሳቸው ያደላል እንጂ በሰዎቹ ጉዳይ እኔ ያልኩትን ደግፎ ነው የተናገረው። ሌሎቹም የደርግ አባላት እንደዚሁ። ‹እነዚህ ሰዎች ሙቶች ናቸው። በቁጥጥራችን ሥር፣ በጫማችን ሥር ያሉ ሰዎች ናቸው። ትላንት ለፍርድ ይቀርባሉ ብለን ተናግረን ዛሬ ይሄን ዓይነት ውሳኔ ስንወስንባቸው ሕዝብስ ምን ይላል?› ብለዋል። የሕግ ባለሙያ የሆኑ የደርግ አባላት ብዙ ተከራክረዋል። ‹መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ፣ ዳኞች ተሰይመው እነዚህ ሰዎች የጃቸውን ያገኛሉ ብለን ለሕዝብ በይፋ ተናግረን ቃላችን እንዴት ይታጠፋል?› ሲሉ፤መልሱ ‹አብዮትና ሕግ መቼ ቀን አብሮ ሄዶ ያውቃል!?› የሚል ነው።እነአጥናፉ አባተን፣ እነእንዳለ ተሰማን ያየሽ እንደሆነ ደግሞ ‹በለው!› ነው፤ ሽለላ ነው የሚቀራቸው። አጫፋሪዎች፣ ሙዚቀኞች ናቸው። ሌላ ደግሞ አንድ



ነበረ በኋላ ጎንደር ሄዶ የሞተ ልጅ (ጥሩ ካድሬ ነበር)፤ ገዛኸኝ ወርቁ። እ ... ደጀኔ፤ አሁን እነሱን ያየሽ እንደሆነ ወጣቶች ናቸው ያኔ። የዚያን ጊዜ አልተሰማቸውም።

ሕዝቡስ ቢሆን? የዚያን ጊዜ ‹በለው!› ነበር የሚለው። ወታደሩን ይገፋፋ ነበር። አስታውሳለሁ፤ ‹አየር ኃይልና ምድር ጦር፣ ብሔራዊ ጦርና መደበኛው፣ ፖሊስና አርሚው ተጣልቷል፤ መሐንዲስና አየር ወለድ ተለያይቷል› እያሉ - ያው ጠላቶቻችን ናቸው - አሉባልታ ማናፌስ ጀመሩ።ነገሮችን እያሰፉና እያጎሉ ሊከፋፍሉን ሲቃጡ «ይሄ ወሬ እያደር ከቆየ ጥሩ አይሆንም። ሠራዊቱም፣ ፖሊሱም፣ የጦር ኃይሉ በሙሉ አንድ መሆኑን ለማሳየት ሕብረታችን እንዳለ ነው፤አልተናጋም የሚለውን መልዕክት ለማሳለፍ በአዲስ አበባ ውስጥ አንድ ሰልፍ እናሳይ»አልን። አየር ኃይሉ በአየር እየበረረ፣ፖሊሱም፣ ጦር ሠራዊቱም ሁሉም ባንድነት ተሰለፈ።እኔና ጓዶቼም ላንድሮቨር ውስጥ ሆነን (ማንነታችን ያኔ አይታወቅም)የሕዝቡን ስሜት ለማየት አብረን ወጣን። በስድስት ኪሎ አድርገን፣በጎጃም በረንዳ ዞረን፣በልደታ በኩል ተግባረዕድ ዞረን ነው የመጣነው። በየመንገዱ የወጣው ሕዝብ ቁጥሩ ይህ ነው አይባልም።በጣም ብዙ ነበር።ታዲያ ምን ነበር የሚለው? ‹በሉት ይሄን አሳማ! ምንድነው የምትጠብቁት? ሸኙት!› እያለ ነበር የሚጮኸው።

ፕሮፌሰር መስፍንና የሻዕቢያው ዶክተር በረከት አንድ ናቸው። ሁለቱም አንድ ናቸው። የመርማሪ ኮሚሽኑን መቋቋም በተመለከተ መስፍን ተቃዋሚ ነበር።ዶክተር በረከትም እንደዚያው።ኮሚሽኑን ለማፍረስ ሁለቱም ጥረዋል።ፕሮፌሰር መስፍን ዛሬ ሰብዓዊ መብት እያለ እንደሚያወራው አይደለም። በጣም መሠሪ ሰው ነው። ያኔ ያማከረን ሌላ ነበር። እሱ እንደምሳሌነት የሚያነሳው የስፔይንን አብዮት ታሪክ ነው።

የስፔይን አብዮት በሁለተኛ የዓለም ጦርነት አካባቢ ሲፈነዳ ስፔይን ውስጥ የኮሚኒስቶች ንቅናቄ ባንድ በኩል፣ የዓለም አድሀሮት ኃይሎች በሌላ በኩል ሆነው የተሠራ ታሪክ ነበር። የአውሮፓ ቡርዧዎች እዚያ ውስጥ የተነሳውን አብዮት ለመደምሰስ ተባብረው ሄደው ሲወጓቸው የየአገሩ አብዮተኞች ደግሞ ዓለም አቀፍ ብርጌድ የሚባል አቋቋመው ከራሺያ፣ ከቡልጋርያ፣ከሕንድና ከእንግሊዝ ሳይቀር ኮሚኒስቶች ተሰባስበው ሕይወታቸውን ለዚህ ክቡር ዓላማ ለመስጠት ተዘጋጁ። ልክ እንደኛ አገር ህዝቡ ተነሳና አብዮቱን ደገፈ። አብዮቱ የበላይነት ተቀዳጀ። ኮሚኒስቶቹ ቡርዧዎቹን ሰብስበው አሰሯቸው። ከዚያ

ኮሚሽን አቋቁመው ጉዳያቸውን እናያለን ሲሉ የአድህሮት ኃይሎች ገብተው ሁሉንም ፈጇቸው።

ይሄንን በምሳሌነት ጠቅሶ ፕሮፌሰር መስፍን የሚለው ምንድነው 'እናንተ ጠመንጃው ያለው በጃችሁ ሆኖ፣ ጊዜውም ሁኔታውም እየፈቀደላችሁ የኛን የብዕር በትር እንዴት ትጠብቃላችሁ? መርማሪ ኮሚሽን ምናምን እያላችሁ ስታመነቱ በስፔይን አብዮት እንደደረሰው ጎርፉ እኛንም፣እናንተንም ጠራርጎን እንዳይሄድ እፈራለሁ። ምንድነው ጠመንጃው በጃችሁ አይደለም እንዴ? እኛን በሕግ በምናምን ተብትባችሁ አስራችሁ ሰዎቹን ለፍርድ አቅርቡ ትሉናላችሁ' ብሎ ነው የተናገረው።

ዶክተር በረከትማ 'ግደሉ!' ነው ያለው። 'በሕግ መታዘዝ የግድ አስፈላጊ አይደለም። ፍትሐዊነቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የሕዝብ ድጋፍ ያለው ውሳኔ ከሆነ መወሰን ይችላሉ' እያለ ነበር የሚያማክረው። እሱ እንኳን ዓላማ ነበረው። ያው ዘር ከልጓም ስቦት ሻዕቢያው ገብቷል። እና እኛ ይህን በመሳሰለ ግፊት ሥር ነበርን። ይሄነን ብዙ ሰው የተረዳልን አይመስለኝም።

ከንዑስ ደርግ አባላት አንዳንዶቹ 'እኛ ታዛቢ ነበርን እንጂ ድምፅ በመስጠት አልተሳተፍንም' ማለታቸውን ስሰማ እታዘባቸዋለሁ። ያን ሁሉ ሰዓት ስብሰባ ላይ ቁጭ ብሎ እጁን እያወጣ ሲወስን ቆይቶ አሁን 'ታዛቢ ነበርኩ' ይባላል እንዴ? ለመሆኑ ከነጌሌ፣ ከአጋዴን፣ ከደቀ መሐሪ፣ ከአቆርዳት በአውሮፕላንና በሄሊኮፕተር ሲምዘገዘግ የመጣው እኛ የምንሰጠውን ውሳኔ ታዝቦ ለመሄድ ነው? ለምስክርነት ነው? ለዚያማ እነሱን መጥራት ምን አስፈለገ? «እማን እንደዚህ አድርጓልና ገለናል» ብሎ ማለት አይቻልም እንዴ? ደግሞ እነሱ ተወንጅለው አልተከሰሱ። የተከሰስነው እኛ የደርግ አባሎች ነን። እነሱን ማን አስዋሻቸው። እውነቱን አይናገሩም?

*ገነት - የደርጉ አባላት እርስዎ እንደሚሉት በንዑስ ደርግ አባላት ተፅዕኖ ሥር ወድቃችሁ ከሆነ ስብሰባውን ማቆም ወይም ጥሉ መውጣት አይቻልም?*

**መንግሥቱ** - የዛን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በዛሬው ዓይን ሳይሆን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ማየት ያስፈልጋል። የነበረው አደጋ ደርግን ራሱን የሚያፈራርስና አገሪቱንም እጅግ ወደከፋ ሁኔታ ሊያሸጋግራት የሚችል አዝማሚያ ነው የታየው። ያን ዕለት አንድነታችንን



ሊያናጋና የደርጉን ሕልውና ጨርሶ ሊያጠፋው የሚችል ነበር። እያንዳንዱ አባል እኮ ከዚያ አዳራሽ ወጥቶ ወደየክፍሉ ሲመለስ የየራሱን እሳት ሊጭር የሚችል ነው። ገና ነገሩ ሁሉ በቋፍ ያለና አንዱ አንዱን በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቅበት ጊዜ ነበር። ይሄ የተሰማቸው የደርግ አባላት ለጥቂት ሰዎች ሕይወት ብለን ጠቅላላ የሃገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ የምንጥልበት ምክንያት የለም የሚል ነገር እንደተሰማቸው ይገባኛል። ድምፅ ይሰጥ ሲባል እጅ እንደችቦ እየወጣ ነው ድጋፍ አግኝቶ ያለፈው።

*ገነት - እጅ እያወጣችሁ ነው አይደለ ድምፅ የሰጣችሁት?*

**መንግሥቱ** - አዎን።

*ገነት - እርስዎ ድምፅ የሰጡበት ትዝ የሚልዎት ሰው አለ? ይሙት፣ ወይ ይዳን ብለው እጅ ካወጡበት ትዝ የሚልዎት ካለ?*

**መንግሥቱ** -እንዴ እኔኮ ሰብሳቢ ነኝ። እኔ ነኝ ስብሰባውን የምመራው። በሌሎችም ስብሰባዎች እንደሚደረገውና እኔም ሳደርግ እንደኖርኩት የሰብሳቢው ሥራ ይሄ ነው። አጀንዳውን አቀርባለሁ፤ አከራክራለሁ። ይሄ ይናገራል፤ያ ይናገራል። ክርክሩ ሞቆ ሁሉም ሃሳቡን ገልጿል። የመናገር ዕድል ለሁሉም ተሰጥቷል። የምፈልገውን ተናግሬያለሁ ብሎ ረክቷል የሚለውን ነገር ስደርስበት ነገሩን አሰባስቤ «ይሄን፣ ይሄን ተናግራችኋል። አሁን ሃሳባችሁን እንቋጭ» እላለሁ። ወደድምፅ ለመሄድም እንደዚሁ «አሁን ወደ ድምፅ ትሄዳላችሁ ወይ?» ተብሎ ቤቱ ሲስማማ ነው ወደዚያ የተሄደው። ያለቤቱ ፈቃድ የሚደረግ አንዳችም ነገር አልነበረም።«እከሌ ይሙት!» የምትሉ እጃችሁን አውጡ ይባላል። ይመዘገባል።«የምትቃወሙ» ይባላል። ይሄም ድምፁ ተቆጥሮ ይመዘገባል። ድምፀ ተአቅቦም እንዲሁ። ከዚያ በኋላ የተሰጠው ድምፅ ከሃምሣ በመቶ በላይ መሆንና አለመሆኑን ቁጥሩን አይተን በውስጠ ደንቡ መሠረት የሚያስገድል ከሆነ ወይም የሚያድን ከሆነ በዚያ መሠረት ውሳኔው ይተላለፋል። የኔ ድምፅ መስጠት ያለመስጠት የሚያመጣው ለውጥ አልነበረም።

*ገነት - በዚያ ስብሰባ ላይ ተካፋይ የነበሩ ብዙ ሰዎች የሚናገሩት ስብሰባው ሙሉ በሙሉ በርስዎ ተፅዕኖ ሥር ወድቆ እንደነበረ ነው። ስለዚህም እርስዎን ብቻ ሙሉ ኃላፊ ያደርጉዎታል።*

**መንግሥቱ** - አንድ እውነት አለ። ሁላችንም ነገሩ ትክክል ያለመ

ሆኑን እናምናለን:: ያንን ትክክል ያልሆነ ነገር እዚያ ቁጭ ብለን አስፈ ፅመነዋል:: አሁን ጊዜው ካለፈ በኋላ የዚያ ውሳኔ አካል ነበርን ለማለት አልፈለግንም:: የሚያንቀን ሕሊና አለን:: ስለዚህ ከዚያ መውጫ እንፈልጋለን:: በደርግ ውስጥ በተሰጣቸው ኃላፊነት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ሁሉ ሊክዱ ይሞክራሉ:: ለምሳሌ፣ የሕግ ኮሚቴ ሰብሳቢና አባል የነበሩት ሰዎች ‹ዛሬ አናውቅም፤ አልነበርንም› ብለው ሲሉ ይገርመኛል:: ሕግን የሚመለከት እንደዚህ ያለ ጉዳይ አጀንዳ የሚጠናውና የሚቀርበው በሕግ ኮሚቴ አማካኝነት ነው:: እንደዚህ ያለ ዝግጅት እንደሌለ እነፍሰሐ ደስታ ያውቃሉ:: እኔ ደግሞ ወይ የእስር ቤቶች፣ የፀጥታ ወይም የአስተዳደርና የሕግ ኮሚቴ ሳያቀርብ በግሌ ስለታሰሩት ሰዎች የማቀርበው አጀንዳ የለም::

*ገነት - ጄኔራል አማን እንዲገደሉ በቀጥታ ትዕዛዝ የሰጡት እርስዎ ነዎት ይባላል::*

**መንግሥቱ** - ጄኔራል አማንን በሕይወት መያዝ ካቃተ ይደም ሰሱ የሚለው ውሳኔ የተላለፈው በቤቱ ነው:: በጉባኤው በቀጥታ የተላለፈ ትዕዛዝ ነው:: ‹መንግሥቱ እዚያው ሆኖ እንዲደመሰሱ ትዕዛዝ ሰጠ› የተባለው ጨርሶ ሐሰት ነው::እኔ መጀመሪያውኑ ሆነ ብዬ የሰበሰብኳቸው ለዚሁ ነው:: ጄኔራል አማንን በተመለከተ አንድም ውሳኔ በኔም ሆነ በሌላ በተናጠል እንዲሰጥ አልፈለግሁም:: ራሳቸው የፈለጉትን እንዲወስኑባቸው ነው የሰበሰብኳቸው ብዬ ደጋግሜ ተናግሬያለሁ:: ምክንያቱም ‹ሰውዬው ሥልጣን ፈልጎ አንደኛ ሲኒዬር ጄኔራል በመሆናቸው፣ ሁለተኛ የኤርትራ ተወላጅ ስለሆኑ ደርግን ይዞ እየተጠቀመባቸው ነው› እየተባለ ሐሜት ስለነበረ አሁንም እሳቸውን በተመለከተ አንድ ነገር ቢፈጠር መንግሥቱ ነው እንደምባል ስለማውቅ ነው:: እኔ ከዚህ በተቻለ መጠን ለመውጣትና ኳሱን በተሰብሳቢዎቹ ሜዳ ላይ ለማስቀመጥ ነው:: እነሱ ወደፈለጉት አቅጣጫ ሊወረውሩት ይችላሉ:: ለዚህ ነው ሁሉም ባደባባይ እንዲሆን የፈለግሁት:: አማንን ለመግደል ከሆነ ሃሳቤ ለምንድነው ጉባኤ የምጠራው? ዳንኤልን ጠርቼ ሳበቃ «ግምባሩን በለው!» ማለት ይቻላል:: ታንክስ ምንስ ምን ያስፈልጋል? ሹፌሩ ራሱ አጃቢያቸው የኛ ሰው ነው:: ማን እንደገደላቸውም ሳይታወቅ «አስተኛና ና!» ማለትም እችል ነበር::

*ገነት - ጄኔራል አማን ጦር እያስተባበሩ መሆኑ እንዴት ተደረሰበት?*

**መንግሥቱ** - ጄኔራል አማን የጦር ኃይል አባላትን ለማንቀሳቀስ



ሙከራ ሲያደርጉ መረጃ የደረሰን ከተለያየ አቅጣጫ ነው:: አንደኛ በስልክ በመጠቀም ጦሩን ሊያንቀሳቅሱ ሲሉ የልዩ ካቢኔው ግንኙነት መቆጣጠሪያ ደረሰበት::በዚህ ላይ የሳቸው ኤዲሲ የኔ ኮርስሜት ነው:: ወዲያው ለኛ ሪፖርት ተደረገልን:: እንደገና የጦር ኃይሎቹን መገናኛ ማዕከል በመጠቀም የተመሰጠረ ቴሌግራም ሩቅ ላሉ አዛዦች ሲያስተላልፉ ተሰማ::

በኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስቴር የተቋቋመ የሠራዊቱን ግንኙነት የሚቆጣጠር፣ የሚመራ አንድ የጦር ኃይሎች የመገናኛ ማዕከል አለ:: በጣም የረቀቀ መሣሪያ ያለው፣ በምስጢርም፣ በግልፅም መልዕክት የሚተላለፍበት፣ ከመላው ሠራዊት ጋር ግንኙነት የሚደረግበት የሬዲዮ መገናኛ እምብርት ነው:: የጦር አዛዦች በሥራቸው ላሉ ብርጌዶች የሚያስተላልፉትን ትዕዛዝ፣ እነኛ የሚያቀርቡትን ሪፖርት እያዳመጠ ቼክ የሚያደርገው፣ ጤናማ ነው ወይስ አንድ ነገር አለ የሚለው ይህ ማዕከል ነው:: ማንኛውንም እንቅስቃሴ የምንቆጣጠረው በዚያ ነበር:: በሲቪል ኢንጂኒዬርነት ከፍተኛ ትምህርት በተማረ ከኮሎኔል ያላነሰ ማዕረግ ባለው መኮንን ይታዘዛል::

በጃንሆይ ጊዜ ልዩ ካቢኔ የሚባል ነበር:: ልዩ ካቢኔ ማለት የንጉሠ ነገሥቱን ደህንነት፣ ጥበቃ፣ ሥልጣናቸውን መጠበቂያ ተቀናቃኝ ቢመጣ ማደኛና ማጥፊያ ማለት ነው:: በፊት በጄኔራል አበበ ገመዳ የሚመራ ነበር:: ከዚያ ቀደም ሲል ደግሞ በነኮሎኔል ሰለሞን ከድርሥር የነበረ ነው:: በታላቁ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ የተተከሉ የረቀቁ የረጅም ርቀት የግንኙነት መሣሪያዎች አሉት:: በአገሪቷ ውስጥ ከየትም ቦታ ወደየትም ቦታ የሚያደርገውን ግንኙነት መቆጣጠር ይችላል:: በስልክ፣ በሬዲዮ ሁሉ:: ይሄን የሚቆጣጠረው ይህ የልዩ ካቢኔው አካል ነው::

*ገነት -የጄኔራል አማን ስልክ ተጠልፏል ማለት ነው? «የመሣሪያ ግምጃ ቤት ዱቄት ሠፍሬ ሁላ!» ብለዎችኋል ሉ::*

**መንግሥቱ** - እኔ ዱቄት ሠፍሬ አላውቅም (እየሳቁ):: ግምጃ ቤቱም የዱቄት አልነበረም::የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት ነው:: እሳቸው ይሄንን ማለታቸው ግን እርግጥ ነው:: ከጄኔራል ግዛው በላይነህ ጋር ሲነጋገሩ ነው ይሄን ያሉት:: በተለያየ ጊዜ፣ ሌላም ሌላም ብዙ ነገር ብለው ለኛ ቀርቦልናል::ወደኦጋዴን ደውለው ምን እንዳሉ፣ወደኤርትራ ደውለው ምን እንዳሉ አንድ ባንድ ሪፖርት ተደርጎልናል::

እና ከጄኔራል ግዛው በላይነህ ጋር ሲነጋገሩ ‹ይሄ ሁሉ ለኛ ውርደት ነው:: እኔ የጄኔራሎችን ክብርና መብት ለማስጠበቅ ነው:: አንዳንድ ጨቅላ ሻለቆችና ሃምሳ አለቆች...› እያሉ ያሰቡትንና ዓላማቸውን ይነግሯቸዋል:: ጄኔራል ግዛው ‹ጌታዬ፣ እንግዲህ እየተማከራችሁ ምሩን እንጂ:: እኛ ከናንተ አመራር ተቀባይ ነን:: ማንኛውንም ነገር ከነሱ ጋር እየተማከሩ እንዳው መስማማቱ ይበጃል› ይሏቸዋል::

‹ከማን ጋር ነው የምማከረው?›

‹ከሥራ ጓደኞችዎ ጋር::›

‹ማነው የሥራ ጓደኛዬ?›

‹አብረዎት ካሉት ከነሻለቃ መንግሥቱ ጋራ::›

‹ከነዚህ ከዱቄት ሰፋሪዎች ምናምን ጋራ?!› እንደዚህ ነው የሚናገሩት::

***ገነት -ከጄነራል አማን ጋር ቅራኔ ውስጥ የገቡት በዚህ ምክንያት ነው?***

***መንግሥቱ*** - ይሄንን ስላነሳሽው ለጨዋታ ያህል ጠቀስኩት እንጂ ከጄኔራል አማን ጋራ ቅራኔ ውስጥ የገባሁት ይሄን የመሰለ ንግግር ተናገሩኝ ብዬ አይደለም:: «የአገር ጉዳይን የተሸከምንና እጅግ አጣዳፊ ሁኔታዎች ጫንቃችን ላይ የወደቁብን ሰዎች ነን:: ወንበዴዎች አሥመራን በ10 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ቀለበት ውስጥ አስገብተው ከበዋታል:: የኤርትራን ነገር እንዴት እናድርግ? ወንበዴዎች ከበዋል:: ሠራዊት ልከን እናስለቅቅ ወይስ እንዴት እናድርግ?» አልን:: እሳቸው የመከላከያ ሚኒስትር ናቸው:: ምንም ያደረጉት ነገር የለም:: እኛ አንድ ነገር ያልን እንደሆነ ‹የተሰጠኝን ኃላፊነት ወስጄ እየሠራሁ ነው:: በአንድ ወቅት እናንተን ሁላችሁንም ስመራ የኖርኩ ጄኔራል መኰንን ነኝ:: በሥራዬ ጣልቃ አትግቡ› ብለው ይቆጣሉ::

እኛ ደግሞ መላ አገሪቱን አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ሲመጣ ዝም ብለን ማየት አንችልም:: እንዴት ነው ነገሩ? እሳቸውን ላለማስቆጣት ፈርተን ዝም ስንል ብዙ ነገር እየተበላሸ ነው ብለን እሳቸው በተገኙበት ደርጉ ጉባኤ ተቀመጠ:: ‹ጦር አይሄድም› አሉ::

«አገር እንጠብቃለን ብለን ተረክበናል:: በመሪነታችን ብቻ ሳይሆን በወታደርነታችንም የአገር ዳር ድንበር የመጠበቅ ግዴታ ያለብን መለዮ ለባሾች ነን:: ወንበዴዎቹ እኮ ከዛሬ ነገ ነፃነት ሊያውጁ ትንሽ ነው የቀራቸው:: ለሕዝቡስ፣ ለወታደሩስ የገባነውን ቃል እንዴት ነው የምናደርገው:: ኃይለሥላሴ ያዋሃዷትን አገር ለሽፍታ አስረክበን ቁጭ ልንል ነው?እያንዳንዳችንን እዚህ እደጅ የቆመው ወታደር ነው መጥቶ ሆድ ሆዳችንን በሳንጃ የሚወጋው::እርስዎ ይሄንን ነው የሚፈልጉት? ደግሞም የኛ በሳንጃ መወጋት አይደለም ቁም ነገሩ:: የኢትዮጵያ መወጋት ነው:: የኛ ሕይወት ከአገራችን አንድነት ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነው:: እንዴት ኢትዮጵያ ትገነጠላለች:: አንድ ነገር መደረግ አለበት» ብዬ አምርሬ ተናገርኳቸው:: እሳቸው ፍንክችም አላሉ:: ‹ብትፈልጉ ታንክ ይሂድ፤ ጦር አይላክም› አሉ::

ታንክ ያለው የት ነው? ቀብሪደሐርና ጅጅጋ ነው ያለው:: በምን ድነው የምናጓጉዘው? ታንክ ማጓጓዣ የለንም:: በባቡር ይሂድ ቢባል የባቡር ጋሪ የለንም:: ታንኮቹም ቢሆኑ ባትሪ እንኳን የሌላቸው አሜሪካን ተጠቅሞ፣ ተጠቅሞ የጣላቸው አሮጌዎች ናቸው:: ቢሄዱ እንኳን አሰብ ሳይደርሱ የትም ተንኮታኩተው የሚቀሩ መሆናቸውን በሚገባ ያውቃሉ:: ስለዚህ የግብር ይውጣ፣ እንዲሁ እምቢ ብለዋል እንዳይባሉ ብቻ ነው እንደዛ የሚሉት:: ወታደሩ በፍጥነት ሄዶ የተፈጠረውን አደጋ እንዲያቆም ጨርሶ አልፈለጉም:: ታንክ ሄዶ ይዋጋ ሲሉ፣ መቼም እኛን ስለወታደራዊ ጥበብ ምንም የማያውቁ ደንቆሮዎች ናቸው ብለው ገምተዋል:: እኛ ያንን አሮጌ ታንክ ከቦታ ቦታ ስንጎትት እንድንከርም ነው የፈለጉት:: ከታንክ ጋር ስንጓተት ወራቶች እንዲያልፉና ወንበዴ ነፃነት እንዲያውጅ ነው የተፈለገው::

«ወንበዴዎቹ የያዙት የጎሬላ ውጊያ ነው:: ባዙቃ፣ታንክ መምቻና የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ብቻ ይዘው አድፍጠው መትተው የሚሮጡ ሰዎች ናቸው::ከአምስትና ቢበዛ ከአሥር ሰው ባልበለጠ ቡድን ሆነው ተከፋፍለው ከቦታ ቦታ እንደጦጣ እየዘለሉ የሚዋጉ ናቸው:: በብዛት ተሰልፈው እግረኛና መድፈኛ፣ታንከኛ ይዘው የሚመጡ መደበኛ ሠራዊት አይደሉም:: እኛ ከዚህ ቀደም ታንክ ያሰለፍነው ታንክ አሰልፎ በመጣብን የሶማሊያ መደበኛ ሠራዊት ላይ ነው:: እሱንም በአመቺው የኦጋዴን ሜዳ ላይ ነው:: ተራራ ላይ ከተንጠለጠለ ወንበዴ ጋር ለመዋጋት ታንክ ጨርሶ አያስፈልግም:: ለወንበዴ ፀሩ እግረኛ ነው:: እርስዎ ልምድ ያለዎት ጄኔራል መኰንን ነዎት:: እኔም በሻለቅነቴ፣ ሌሎቹም ሃምሳ አለቆች ቢሆኑም ይሄ የሚሊቴሪ ‹ሀሁ› አልጠፋንም:: እርስዎ እንዴት እንዲህ ይላሉ?» ብዬ ላስረዳ ሞከርኩ:: አሁንም ‹አይሆንም!› ብለው ድርቅ አሉ::

እንደገና በአገሪቱ አሉ የተባሉትን በልምዳቸውና በሥራቸው እውቅናን ያገኙ ምርጥ ጄኔራሎችን፣ የጦር ስልት፣ የጦር መላ አዋቂ ከፍ

ተኛ መኰንኖችን ጠርቼ አሁንም እሳቸው ባሉበት ስብሰባ ተቀመጥን:: ጄኔራል አማን እንደዚህ አሉ ሳልል በደፈናው «እንዲህ፣ እንዲህ ያለ ነገር ሲመጣ መጠቀም ያለብን ስትራቴጂ ምን መሆን አለበት?ለምሳሌ ኤርትራ ታንክ ቢላክ ምን ይመስላችኋል?» ብዬ ጥያቄውን አነሳሁ::

‹እንዴ! እንዴት ሊሆን ይችላል? እናንተስ ብትሆኑ ወታደሮች አይደላችሁም እንዴ? ይሄ እንዴት ይጠፋችኋል? ኤርትራ ታንክ ምን ያደርጋል?መጀመሪያ ነገር ታንክ ልናንቀሳቅስ ብንፈልግስ እዚያ ድረስ ማጓጓዣው አለን እንዴ? ጊዜውስ አለን እንዴ? ወንበዴው እስከዛ ጊዜ ይሰጠናል ወይ? እሱም ይሁን ተሳክቶልን ታንክ ይሂድና እዚያ ወሎ ወይም አሰብ አካባቢ ይቁምና ኩይሳ ይምሰል? የሶማሌ ሜካናይዝድ ጦር መጥቶ ቢያጥለቀልቀን ለጊዜው እንኳን በምንድነው የምንመክተው? የኦጋዴን በር ተከፍቶ ይቀመጥ ነው የምትሉት?› አሉ ሁሉም በአንድ ቃል::

እነሱ ከወጡ በኋላ ወደ ጄኔራል አማን ዞሬ «ጌታዬ፣ በወታደራዊው በኩል ሁኔታው እንደሰሙት ነው:: በፖለቲካው በኩል ያለውን በሚገባ ያውቁታል::በተጨማሪ ደግሞ ተስፋዬ ወልደሥላሴ ኤርትራ ቆይቶ ነው የመጣው:: ሪፖርት ያድርግልዎት» አልኳቸው::

ተስፋዬን እኔ ልኬው ነው የሄደው:: «በደንብ አድርገህ ግራ ቀኙን አይተህ አጣርተህ ናና ንገረኝ» ብዬ ነው የላኩት:: ሲመለስ ‹ባስቸኳይ አንድ ነገር ካልተደረገ ኤርትራ በዚህ ሁኔታ ሁለት ቀን የኢትዮጵያ አካል ሆና ከቆየች ከምላሴ ፀጉር ይነቀል› ነው ያለኝ:: እውነቱን ነበረ:: ተስፋዬ የደህንነት ሚኒስትር ለመሆን የበቃው የዚያን ጊዜ ባቀረበው ትክክለኛ ግምገማው ነው:: ቁልጭ አድርጎ ነው ያቀረበው:: ሁኔታዎችን በቅድሚያ በሚገባ የማየት ችሎታ አለው:: ያንኑ ለኔ የነገረኝን ደገመላቸው::

‹ኤርትራ በዚህ ሁኔታ ሁለት ቀን በእጃችን ከቆየች ዕድለኛ ነን::›

‹ምን አልክ?!› አምባረቁበት ጄኔራል አማን::

‹ልድገመው ጌታዬ:: ካሁን በኋላ ሁለት ቀን የዘገየን እንደሆነ አሥመራ በእጃችን አትኖርም::›

‹ከየት ነው ያመጣኸው ይሄንን?› ብለው ተስፋዬ ላይ ወረዱበት:: ስድብ ጭምር::

«ተዉ እንጂ ጌታዬ፣ ጉባኤ ላይ ነው እኮ ያለነው:: ሥነ ሥርዓት ነው እኮ የሚገዛን:: እሱም ቢሆን ታዞ ነው የሄደው:: የተላከበትን ተልዕኮ ግብ አድርሶ አሥመራ ሄዶ ያየውን፣ የተገነዘበውን፣ በሱ ሙያዊ



ግንዛቤ የደረሰበትን ድምዳሜ ነው የነገረን:: ምን ላይ ነው ጥፋቱ:: ለምንስ ይዘለፋል? እርስዎስ የራስዎን አስተያየት ይስጡን እንጂ ወደ ሌላ ለምን ይሄዳሉ?» አልኩ:: እኔ እንዲህ ስናገር በረድ አሉ::

የፖለቲካው ሁኔታ ሲተነተንና ነገሩ ሁሉ እሳቸው እንደሚሉት ያለመሆኑ በማያወላዳ መንገድ በበቂ መረጃ ተደግፎ ሲቀርብ ምን ይበሉ? ፀፀትም የተሰማቸው ይመስላል:: አሁን ደግሞ ወደነቢትወደድ አስፍሐና ወደነንቡረዕድ ዲሜጥሮስ ዞሩ:: ‹እነሱ ናቸው ነገሩን ሁሉ ለዚያ ያበቁት::እንዲታሰሩ የጠየቅሁት ለዚህ ነበር::ኤርትራን የሸጧት እነሱ ናቸው› አሉና ደግሞ ቱግ አሉ:: እነዚህ የሚሏቸው ሰዎች እኮ የታወቁ የአንድነት ኃይሎች ናቸው:: ፍፁም ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተመልሳ እንድትቀላቀል ሲታገሉ የኖሩ ሰዎች ናቸው::

«ጄኔራል ራስዎን ግልፅ ያድርጉ:: እነዚህ ሰዎች ኤርትራን እንዴት ነው የሸጧት?» ብለን ስንል፣ ሌሎቹ የደርግ አባላት ትዕግሥታቸው አለቀ:: የደርግ አባላት እንደሆነ በተለይ በአንድነት ሲሰበሰቡ ኃይለኞች ናቸው:: ቀልድ የለም:: ‹በለው!› ነው የሚሉት:: ደርግ ሲሰበሰብ ምላጭ ነው::

ያን ለትም አልቀረም:: እሳቸው እዚያው ቁጭ እንዳሉ እየተነሱ መዓቱን ያወርዱት ጀመር:: ‹እኛ በቅቶናል:: የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ በሚጥል ሰው መመራት አንችልም› ነው ያሉት:: ትዝ ይለኛል አሊ ሙሳ ነው ብድግ ብሎ ‹ሻለቃ መንግሥቱ! ኤርትራን በተመለከተ አንድ ነገር ቢፈጠር እኛ የምናውቀው አንተን ነው::እኛ ጄኔራል አማንን አናውቅም:: ኮዳ ትራሱ፤ ምንትሴ እያላችሁ በሌሉበት ቦታ እየካባችሁ አምጥታችሁ እዚህ ቁጭ ያደረጋችኋቸው እናንተ ናችሁ:: ሠራዊት አልመረጣቸው:: የደርግ አባል አይደሉ:: ካሁን ጀምሮ አማን የሚባል ሰው እኔ አላውቅም:: አንተ ነህ ያመጣሃቸው:: እኛ የምናውቀው አንተን ነው:: ካንተ ራስ ላይ አንወርድም:: የኤርትራን ጉዳይ ሁላችንም የምናውቀውና የሚያሳስበን ነገር ነው:: እነቢትወደድ አስፍሐን የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው የሚሉ ሰውዬ መሐላችን አስቀምጠን ለኢትዮጵያ አንድነት እንታገላለን ማለት ዘበት ነው› ብሎ ሲል ደርግ በሙሉ ከመቀመጫው ተነስቶ ዳር እስከዳር በጭብጨባ ቤቱን አናጋው:: ይሄን ጊዜ ጄኔራል አማን ብድግ አሉና ተነስተው ሄዱ:: አልተመለሱም::

ስለዚህ እሳቸው በስልክ ያደረጉት ንግግር መሰማቱ ብቻ ሳይሆን ደርግ ‹እናውቃቸውም› ብሎ ይህንን የመሰለ ከፍተኛ ውሳኔ በጉባኤ ወስኖባቸዋል:: ‹እናውቃቸውም:: ኃላፊነቱ የናንተ ነው› ብሎናል:: ‹ገንጣይ ናቸው!› ተብሎ በግልፅ በጉባኤ ተነግሯል:: ከዚያ በኋላ እኚህ ሰውዬ አለቀላቸው:: ልብ አድርጊ፣ከሥልጣን ማውረድና አግልሎ ማቆየት ሲቻል እዚያ መሐላችን ቁጭ ብለው ጦርነት ሊቀሰቅሱ በመ ሞከራቸው ነው በራሳቸው ላይ እሳት የጫሩት እንጂ አሁን እንደሚባ ለው ‹ለኤርትራ ፌዴሬሽን ይሰጥ› ወይም ‹ሰላማዊ መፍትሔ ይፈለግ› በማለታቸው፣ እኔ ደግሞ «የለም መፍትሔው ኃይል ነው» በማለቴ አይደለም:: ባለብኝ ሃላፊነት አገር የሚጎዳ ሥራ ሲሠራ ዝም ብዬ ማየት ስለማልችል እሳቸውንና ደርግን ፊት ለፊት አስቀምጬ አፋርጃ ለሁኝ:: ተጋልጠው ተረተዋል:: ያ ሥራዬ ነበር:: በዚህ እኮራለሁ::

አማንን ከጡረታ አምጥተን እዚያ ቦታ ላይ ለምንድነው ያስቀመ ጥናቸው? ከኃይለሥላሴ መንግሥት ጋር እጅና ጓንት ሆነው ከልጅነት እስከ ዕውቀታቸው ከአርባ አመታት ላላነሰ ጊዜ ያገለገሉ ሰው ናቸው:: እሳቸውን ከነጄኔራል ከበደ ገብሬ ወይም ከነጄኔራል አበበ ገመዳ ምን የሚለያቸው ነገር አለ? በዕውቀትስ ከሌሎቹ በልጠው ነው? አይደለም::ግና ከበፊቱ ‹የኤርትራን ነገር እመነኝ› ስላሉኝ ነው:: ገና አብዮት ሳይፈነዳ በፊት ከሳቸው ጋር በነበረኝ ዕውቀትና ግንኙነት ስለኤርትራ ጉዳይ ምን ይበጃል እያልን እንነጋገር ነበር:: ‹የኤርትራን ጉዳይ አትፍሩት:: ይሄ ሥርዓት ቢገረሰስና አንድ ዓይነት ለውጥ ቢመጣ እነሱ ከኛ ጋር መጥተው ነው የሚሰለፉት:: የሸፈቱት በኢት ዮጵያዊነታቸው ሳያምኑ ቀርተው ሳይሆን አገዛዙን ጠልተው ነው› እያሉ ይነግሩኝ ነበር::ይሄን ተማምኜ ነው ለኤርትራ ችግር መፍትሔ ያመጣሉ ብዬ ተስፋ የጣልኩባቸው:: ለኔ ወዳጄም ነበሩ:: በክፉ ቀንም ውለታ ውለውልኛል::

አንድ ብዙ ጊዜ ሲነገር የምሰማው ግድፈት አለ:: ጄኔራል አማን በ1953 የኢትዮ- ሶማሊያ ግጭት እንጂ፣ በ1956 ጦርነት አይደለም ዝናን ያተረፉት:: ጄኔራል አማን በ1954 የዳኖት ግጭት ጊዜም ጥሩ አመራር አሳይተዋል:: በ1956 ጦርነት ትልቁን ሚና የተጫወቱት ጄኔራል አበበ ገመዳ ናቸው:: ሶማሊያ በሽምቅ ውጊያ ስታካልበን የነበ ረውን ትግል የመሩት አበበ ገመዳ ናቸው እንጂ አማን አልነበሩም:: አማን ይደነቁ የነበረው ጦሩን ለማስተማር፣ ለማንቃትና ሞራልን ከፍ ለማድረግ ባደረጉት ጥረትና በጦሩም ዘንድ ተወዳጅነት በማትረፋቸው



ነው:: ጥሩ አዛዥነታቸውን፣ ወታደርነታቸውንና ጥሩ የጦር መሪነታ ቸውን ከሚያደንቁት አንዱ ስለነበርኩ እሱን አሌ አልልም::

ጄኔራል አማን የአገሪቱ መሪ ተባሉ እንጂ እሳቸው ጄኔራል መሆናቸውና እኛ ከሳቸው ያነሰ ማዕረግ መያዛችን ወሳኝ አልነበረም:: ለደርግ አባላት በሙሉ የወል ርዕሰ ብሔርነት ነው የተሰጠን::ጄኔራል አማንም፣ ከኔም፣ ከደርግ አባል የሆነው አሥር አለቃም እኩል ርዕሰ ብሔር ስንሆን፣ በግል በተሰጠን የሥራ ክፍፍል ደግሞ እሳቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ናቸው:: እኔ ደግሞ ርዕሰ ብሔር የሆነው አካል፣ ማለትም የደርግ ሰብሳቢ ነኝ::

እሳቸው ሊቀመንበር ተብለው ተቀምጠው እንደመሪ በዓለም ፊት እንዲወክሉን አስቀመጥናቸው እንጂ በሕግ የግል የሆነ ሥልጣን አልተሰጣቸውም:: ከዚያ አንፃር ጄኔራል አማን ምንም አልነበሩም:: እንዴ እኔ ጄኔራሎችን እሾም አልነበረም እንዴ?

*ገነት - ከእሳቸው ጋር የነበራችሁን ቅራኔ ለማርገብ በርስዎ በኩል ምን ጥረት አደረጉ?*

***መንግሥቱ*** - ጄኔራል አማን የተገደሉ ዕለት ፍስሐ ደስታ፣ ደበላ ዲንሳ፣አጥናፉ አባተ፣ተካ ቱሉና ሌላ አንድ ስሙን የረሳሁት ኮሎኔል (ከሁላችንም በዕድሜ ጠና ያለ የመገናኛ መኮንን ነበረ) እነኚህን ይዤ እቤታቸው ሄድኩኝ:: ሥራ መግባት ትተዋል:: ብዙ ለመንናቸው:: «እባክዎን ይተዉ:: አጥፍተንም ከሆነ እንደ አባት ይመክሩናል እንጂ እንዳው እንደልጅ እየጣሉን ሲሄዱ እኛም ሆደባሻ እንሆናለን:: ሥራ ውም ይበላሻል:: ከርስዎ ይሄንን አንጠብቅም:: ለማንም ጥሩ አይሆ ንም:: ከኛ የሚለዩበት ነገር የለም:: ብዙ ጊዜ ተደጋገመ:: ከዚህ በፊት አለመግባባት ሲኖር፣ ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር ታደርጉ እንደነበረው ቀርባችሁ በመነጋገር ቀና በሆነ መልኩ ሕዝብም ሳይሰማ መፍታት ይቻላል:: ሻለቃ መንግሥቱ ያጠፋው ነገር ካለም ተናገሩ:: ፊት ለፊት መነጋገርና ልዩነትን ማስወገድ ይቻላል»አልናቸው:: ምንም ፈቃደኝነት አላሳዩም:: ‹ደግሜ፣ ደጋግሜ ተናግሬ ሰልችቶኛል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ መቀጠል አልችልም› ብለው ዘጉ::

ሁኔታቸውን ሳያቸው ትክክል አልመሰሉኝም:: ዓይናቸውም ደፍ ርሷል:: ምናልባት ምሽቱን ሲጠጡ ቆይተው ሊሆን ይችላል:: ዱሮ የማውቃቸው አማን አይመስሉም:: «ምናለ ሌላ ጊዜ ብንመጣ?» ብዬ ነበር:: ሌሎቹ ግን በደንብም ስለማያውቋቸው በእምቢተኝነታቸውና ለኛ በጎ አመለካከት በሰጡት ምላሽ ደማቸው ፈላ::

ከዚህ በኋላ እሳቸውም መረጃ የሚያቀብላቸው ይኖራል:: ‹ደርግ ቆርጣለች:: አምርራለች› እላቸው መሰለኝ ቢሯችን ከተመለስን በኋላ ስልክ ይደውላሉ:: ‹ሻለቃ መንግሥቱ ያነጋግረኝ› ይላሉ የሚል መልዕክት መጣ:: በኛና በሳቸው መካከል ላይዘን ኦፊሰሩ ፍቅሬ ዘርጋው ነበር:: ‹ምናልባት ቅድም ራሴን አሞኝ ስለነበር በጥሩ ሁኔታ አላናገርኳችሁምና ፈቃድህ ቢሆን መጥተህ ብታነጋግረኝ ይላሉ ጄኔራል አማን› አለኝ:: «ሂድና ይሄንኑ ለደርግ ንገር» ብዬ ወደነሱ ላኩት:: ከደርግ የመጣው መልስ ‹በአክብሮት እቤታቸው ድረስ ሄደን ስንለምናቸው እምቢ ብለው መልሰውናል:: ሲፈልጉ ራሳቸው ይምጡ እንጂ አንተ አትሄድም::ደግሞስ ምን እንዳዘጋጁ ምን ይታወቃል?አትሄድም› የሚል ሆነ:: ‹እርስዎ ራስዎ ይምጡ› ብለህ ንገራቸው ተባለ:: ከዚህ ቀደም ኮሎኔል አጥናፉንና ሻለቃ መንግሥቱን ነጌሌ ያለው ጦር ሊያነጋግራቸው ይፈልጋልና ይሂዱ ብለው አዘው እዛ በተለይ እኔን ለማጥፋት የተዶለተ ነገር እንደነበር ተደርሶበት ነበርና አሁንም ወጥመድ ሊሆን ይችላል በማለት ነው ደርግ እንዳልሄድ የወሰነው:: ከዚያ በኋላ እንግዲህ ነገር ተበላሸ:: ያ ስብሰባ ተጠራ::

የዕለቱ አጀንዳችን የስብሰባችን ዋና ዓላማና አጀንዳውም የጄኔራል አማን ጉዳይ ነበር:: ጄኔራል አማን የደርጉ ሊቀመንበር፣ የመከላከያ ሚኒስትርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ናቸው:: ከዚህም በተረፈ አሁን በመፍጠር ላይ ያሉትን ችግርና በአገሪቱ ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን አደጋ አስረዳሁ:: የደህንነት ኮሚቴው የኤርትራን ጠቅላላ ሁኔታ በመዘርዘር ለተሰብሳቢዎቹ የተሻለ ግንዛቤ ለመስጠት የበኩሉን አቀረበ::በቅርቡ ጄኔራል አማን ከደርግ አባሎች ጋር በአንድነት ሆነው ሠራዊቱንም ሆነ ሲቪሉን ሕዝብ እንዲያነጋግሩ ታቅዶ አሥመራ ሄደው ጉብኝት አድርገው ነበር:: ይህንን በሚመለከት አብረዋቸው የሄዱት የደርግ አባላት ሪፖርታቸውን አሰሙ:: በዚህን ጊዜ ጄኔራሉ አብረዋቸው የሄዱትን ሰዎች አግልለው ብቻቸውን ሲሠሩ እንደቆዩ፣ ያደርጉት የነበረው ንግግር ሁሉ አፍራሽና አደገኛ አዝማሚያ ያለው እንደነበረ፣ከዚያ በፊት በሠራዊቱና በወንበዴዎች መካከል የተደረገውን ግጭት አንስተው ‹ይሄንን ሥራ የሠራው የሠራዊት ክፍል ለፍርድ ይቀርባል› እንዳሉ ቁልጭ አድርገው ሪፖርት አደረጉ:: ከዚያ በመቀጠል የኤርትራ ጦር ተወካዮች ደግሞ በፊናቸው አማን ኤርትራ ሄደው ምን እንደሠሩ፣ ምን እንዳሉና ያም በጦሩ ላይ ያሳደረውን ስሜት በበኩላቸው አጣርተው መጥተው ነበርና እነሱም ተናገሩ::



ይሄ ሁሉ ከሆነ በኋላ ደግሞ እዚያው ቢሮአቸው ሆነው ምን ይሠሩና ይሉ እንደነበር፣ በቴሌፎን እየተነጋገሩ ምን ዓይነት ሴራ ይጎነጉኑ እንደነበር ቀረበ:: በሰነድ የተያዘ የጽሑፍ ማስረጃ ቀረበ::

ከዚያ በኋላ ነው «እኚህ ሰውዬ ምን ውሳኔ ሊወሰንባቸው ይገባል?» ወደሚለው የሄድነው::«ይደምሰሱ ወይም ይገደሉ» የሚል ነገር ሳይሆን «ይሄን፣ ይሄን አጥፍተዋልና በዚህ ላይ እንወያይ» ነው:: ይሄ ሁሉ ሲሆን ብዙ ሰዓት ፈጀ:: ቀኑን ሙሉ ስንነጋገር ዋልን:: ረፋዱ ላይ ‹በአዲስ አበባ ውስጥ ጦር የማንቀሳቀስ ሙከራ እያደረጉ ሳይሆን አይቀርም› የሚል መልዕክት ከውጪ መጣ:: ከነገሌ መጥቶ ጎፋ ሠፈር ከተቀመጠው ሁለተኛ መድፈኛ ሻለቃ አካባቢ ደስ የማይል ሁኔታ ይታያል:: ምናልባትም አማን ሊያንቀሳቅሱ የፈለጉት ጦር ይሄ ሊሆን ይችላል› የሚል ሪፖርት ነው የደረሰን:: ይሄንን እንዲያጣሩ ዘለቀ በየነና ሻምበል ግርማ የሚባል ሌላ የደርግ አባል ተልከው ሄዱ:: ምንም የሚያሰጋ ነገር አለመፈጠሩንና እዚህ ግባ የሚባል እንቅስቃሴ ያለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ተመልሰው መጥተው ሰላም መሆኑን ተናገሩ::

ጄኔራል አማን እንዲታሰሩ የተወሰነውም፣ እምቢ ብለው የተታኮሱትም ማታ ነው እንጂ ቀን አልነበረም:: ይሄም ሆን ብሎ የተደረገ ሳይሆን ስብሰባው ይኼን ሁሉ ነገር ሲያጣራና ሲነጋገርበት ቀኑን ሙሉ ስለቆየ ነው:: ሁሉም የበኩሉን እንዲናገር ዕድል ተሰጥቷል:: የአብዛኛው ሰው አስተያየት ‹ይሄንን የመሰለ አገሪቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል ሲሠሩ ከተገኙ ከመሰሎቻቸው ጋር እስር ቤት ይግቡ:: ቢያውቁት ኖሮ ደርግ ባለውለታቸው ነው:: እሳቸው ከሌሎቹ ያሰርናቸው ጄኔራሎች በምንም አይለዩም:: እዚህ ከፍተኛ ቦታ ላይ አስቀምጠን አገርን የመምራት ኃላፊነት ስንሰጣቸው ከድተውን ኢትዮጵያን የሚያጠፋ ነገር ከሠሩ እዚያው ከጓደኞቻቸው ጋር ይቀላቀሉ› የሚል ነበር::

*ገነት - እዚህ ላይ ያልገባኝ ነገር ቢኖር እርስዎ እንደሚሉት ለጄነራል አማን ስትነጋገሩ ቀኑን ሙሉ ከፈጃችሁና የተገደሉት ማታ ላይ ከሆነ ሰዎቹ እንዲገደሉ የወሰናችሁት ምንጊዜ ነው? የተገደሉትስ መቼ ነው? ምስክርነታቸውን የሰጡ ሰዎች እስረኞቹ ምሽቱ ላይ ወደአንድ ሰዓት ገደማ ራታቸውን በመብላት ላይ እያሉ ተጠርተው እንደተወሰዱና እንደተገደሉ ነው የተናገሩት::*

መንግሥቱ - ማታ ነው የተገደሉት:: እነሱ ላይ ፍርዱ መስጠት

የተጀመረው ቀን ነው:: ጄኔራል አማን ላይ ከተወሰነ በኋላ እዚያ ላይ
መቆም ነበረበት:: ነገር ግን እሳቸው ላይ ብቻ ወስነን አንመለስም
ስላሉ ነው ብዬ ተናግሬአለሁ:: አማን ላይ ተወሰነ:: ከዚያ በኋላ የሳቸ
ውን ጉዳይ ትተን ወደሌሎቹ ነው የሄድነው::

የተላለፈው ውሳኔ ወዲያውኑ ተግባራዊ መደረግ ስላለበትና የደር
ጉን ውሳኔ የማስፈፀሙ ኃላፊነት የኔ ስለሆነ እዚያው ስብሰባው
እየተካሄደ እያለ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋውን አስጠራሁት:: እሳቸውን
ለመያዝ ግዳጁ ለሱ የተሰጠው የደርግ የዘመቻ ክፍል ኃላፊ ስለነበር
ነው:: ፓትሮሎችንም፣ሌሎችንም የሚያንቀሳቅሰው እሱ ነው:: የደርጉ
ውሳኔ ወደማታ ላይ ሲደርሰው ሌላ ጊዜ እንደሚያደርገው በሥሩ
ያሉትን ሰዎች ጠርቶ ለግዳጅ አሠማራቸው:: ደርጉ፣ ጄኔራል አማን
እንዲታሰሩ ስለወሰነ ቤታቸው ሄዳችሁ በቁጥጥር ሥር አውሏቸው
የሚል ትዕዛዝ ሰጠ:: ወታደሮቹ ሄዱ:: እዚያ ሲደርሱ ጄኔራሉ መሣ
ሪያ ጠምደው ተቀምጠዋል:: በሠላም እጃቸውን እንደማይሰጡ ግልፅ
ሲሆንላቸው ተመልሰው መጥተው ‹እምቢ ብለውናል፤ እንዴት እናድ
ርግ?› ይላሉ:: እኛ አሁንም እዚያው ስብሰባ ላይ ነን::

ዳንኤል መጣና ይሄንኑ ሪፖርት አደረገልኝ:: ‹ሰውዬው እጃቸ
ውን በሠላም ለመስጠት ዝግጁ አይመስሉኝም:: ቤታቸው[9] የመኖሪያ
አካባቢ ነው:: መሣሪያ ጠምደው ነው ቁጭ ያሉት:: አንድ ነገር ቢፈ
ጠርና ተኩስ ቢከፈት ሰው መውደቁ የማይቀር ነው:: ግልፅ ያለ
ትዕዛዝ ይሰጠኝ› ይላል::

ይሄንን እኔ ለቤቱ አስተጋባሁ:: «ጄኔራሉ በሠላም ወደማረፊያ
ቤት እንዲሄዱ ቢጠየቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ነው የዘመቻ መኰ
ንኑ የነገረኝ:: እና ምን ይሻላል?» አልኩ:: ‹እኛ ውሳኔውን ወስነናል፤
ካሁን ወዲያ ላለው በአፈፃፀም ሂደት ለሚደርሰው ነገር ሁሉ እየገባን
ውሳኔ አንሰጥም:: እዚያ ውስጥ ገባን ማለት ወደአስተዳደርና ወደዘ
መቻ ጉዳይ መግባት ማለት ነው:: ይሄ የሊቀመንበር ውሳኔ ነው::
እምቢ ካሉ በደንቡ መሠረት መፈፀም አለበት› አሉ:: «ጥሩ ነው:: እን
ግዲያውስ ግልፅ ነው:: በሕጉ መሠረት ትዕዛዝ አልቀበልም ካሉ ሕጉ
የሚያዘው ይፈፀማል» አልኩና ወደዳንኤል ዞር ብዬ «እንደዚህ ታደር
ጋለህ:: በድምፅ ማጉያ ውሳኔው እንዲነገራቸው አድርግ:: እምቢ ካሉ
የኃይል እርምጃ እንደሚወሰድ ማስጠንቀቂያ ስጣቸው:: ይሄንንም
እምቢ የሚሉ ከሆነ ይደምሰሱ» አልኩና ሳስበው በመቻኮል አላስፈላጊ

[9] መኖሪያ ቤታቸው ጦር ሃይሎች አጠገብ ከሆስፒታሉ አጥር ጋር ተያይዞ ነበር::



የሆነ ደም መፋሰስ እንዳይደርስ፣ በተቻለ መጠን በሠላም እንዲወጡ
ማድረግ ይቻል እንደሆነ የመጨረሻ ሙከራ መደረግ አለበት በማለት
ተስፋዬ ገብረኪዳንና አንድ ሁለት ሰዎች አብረው እንዲሄዱ አዘዝኩ::
ተስፋዬ የደርጉ የመከላከያ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነበር:: ቦታው ላይ ተገኝ
ተው የሚሆነውን እያዩ ዳንኤልን እንዲረዱት ነው::

ጄኔራል አማን ብቸኛ ነበሩ:: ቤታቸውን የሚጠብቁና አትክልት
የሚኮተኩቱ አንድ ሽማግሌ ዘበኛ ናቸው ቤታቸው ያሉት:: ከብቸኝነ
ታቸውም የተነሳ ሊሆን ይችላል ማታ፣ ማታ ቤት ሲገቡ መጠጥ
በኃይል ይጠጡ እንደነበር በኋላ ተረዳን:: ምግብ ከእህታቸው ቤት
እየመጣላቸው ነው የሚመገቡት:: ቤተሰብ የላቸው፤ ምን የላቸው::

እንደተነገረኝ መትረየሳቸውን ቤታቸው መስኮት ላይ ጠምደው
ቁጭ ብለው ሊይዟቸው የሄዱትን ወታደሮች አላስጠጋ አሉ:: አስቀድ
መው በደንብ ተዘጋጅተዋል::ጥይት ሞልቷቸዋል:: ወደቤታቸው መግ
ቢያ ያለው አንድ መንገድ ነው:: ያንን መቃረቢያውን ይዘው መሣሪያ
ቸውን ጠምደዋል:: ግራና ቀኙ በሙሉ መኖሪያ ሠፈር ነው:: ይሄን
መትረየስ ይዘው ሲለቁት በየጎረቤቶቻቸው ቤት፣ በየመስኮቱ፣ በየበሩ
ጥይቱ ይገባል::

በትዕዛዙ መሠረት በድምፅ ማጉያ እጃቸውን እንዲሰጡ ተጠየቁ::
መልስ የሚሰጡት ተኩስ በመክፈት ነው:: ጎረቤቱ ‹ኡ፣ ኡ!› ይላል::
ሠፈርተኛው ተሸብሯል:: እነተስፋዬ ተቸገሩ:: አሁን እንግዲህ ለአመ
ፅኛና በዚህ ዓይነት የሠላማዊውን ነዋሪ ሕዝብ ሕይወት አደጋ ላይ
የሚጥል ሰው ምንድነው መደረግ ያለበት? ያለው አማራጭ ታንከኛ
መጥራት ነው::ምክንያቱም ከሳቸው ጋር ተኩስ በመለዋወጥ ሠላማዊ
ሰው መሞት የለበትም:: ወታደሮችስ አስፈላጊ ያልሆነ መሥዋዕትነት
ለምን ይክፈሉ?-ታንክ መጣ:: በዚያ ቤታቸውን ደርምሰው ገቡ:: በእን
ዲህ ዓይነት ሁኔታ የአማን ፍፃሜ ሆነ:: በኋላ እንደተወራው ራሳቸ
ውን አልገደሉም:: በታንክ ነው ያጨማለቋቸው::

መንግሥቱ ነው ይገደሉ ያለው የሚለው ነገር ትክክል አይደ
ለም::እንኳን እኔ ደርጉም ቢሆን ይገደሉ አላለም:: እንዲታሰሩ በደርጉ
ተወሰነ::ያንን ማስፈፀም ኃላፊነቱ የኔ ነው:: የደርጉን ውሳኔ ተግባራዊ
እንዲያደርጉ ለተስፋዬ ገብረኪዳንና ለዳንኤል ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ::
እነሱ በሥፍራው ላይ ተገኝተው ያጋጠማቸው ነገር ሠላማዊ ሰዎች
ንም፣ ወታደሮችንም አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ አስፈላጊውን እር
ምጃ ወስደዋል:: ይሄ በማንኛውም የሚሊታሪ ግዳጅ ላይ ሊያጋጥም

የሚችል ነገር ነው:: ለአንድ ግዳጅ አንድ ሠራዊት ሲላክ በቦታው ላይ ተለዋዋጭ ነገር ሊያጋጥመው ይችላል::ያንን እንደአስፈላጊነቱና እንደሁኔታው ይከላከላል:: ይመክታል:: ይደመስሳል:: ይሄም ከዚያ አይለይም:: አንድ አመፀኛ ሲይዝ የሄደ ወታደራዊ ቡድን በሥፍራው ላይ ደርሶ በገጠመው አስገዳጅ ሁኔታ የተወሰደ ወታደራዊ እርምጃ ነው:: ቤታቸውን የጦር አውድማ ለማድረግ የመረጡት ጄኔራል አማን ራሳቸው ናቸው::

*ገነት -በዚህ ጊዜ ሁሉ እናንተ እዚያው ስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ናችሁ?*

**መንግሥቱ** - አንድ ሰው አልወጣም:: ሌሊቱ ተጋምሶ ሊነጋ አቅራቢያ ነው ከዚያ ቦታ ሁላችንም የወጣነው:: ቅድም እንዳልኩት የጄኔራል አማን ጉዳይ ካለቀ በኋላ ‹እኛ ከተሰበሰብን አይቀር የሌሎቹንም ጉዳይ ዳር ሳናደርስ አንሄድም› የሚለው ነገር መጣ:: ያ ሁሉ ሁካታ ተነሳ:: እንደገና አልመለሰበትም::

አሁን ወደሌሎቹ ጉዳይ ስንሄድ የ250 ሰው ስም ዝርዝር መጣ:: የኃይለሥላሴ ባለሥልጣኖች ብቻ ሳይሆኑ ሲቪሎች አሉበት:: ወታደሮች አሉበት::የኮንጎ ጉዳይ አለበት:: ‹ዳኝነት አንድለዋል› ብሎ ሠፈርተኛው ምኑ ሰብስቦ ያመጣቸው ሰዎች ሁሉ ነበሩበት:: ስም ዝርዝር መጣ:: ‹እንይ ከተባለ የዚህን ሁሉ ሰው ጉዳይ እንዴት ነው የምናየው? እነዚህ እኮ ባለሥልጣኖች ብቻ አይደሉም:: ከሰዎቹ ጋር በወንጀሉም ዓይነት፣መደባቸውም በጣም የተለያየ ነው:: እና እንዴት አድርገን ይሄንን በምን መልኩ ማየትና መወሰን እንችላለን?› በማለት ብርሃኑ ባየህ ተነስቶ ተናግሮ ነበር:: እሱም ተነቅፏል::

ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ‹ከደርግና ከንዑስ ደርግ አባሎች የተውጣጣ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ይየው› ተብሎ ተወሰነና ይሄ ኮሚቴ የተከሳሾቹን ቁጥር ከ250 ወደ 141 ዝቅ አድርጎ አቀረበ:: ይሄም በዛ ተባለና እንደገና በጥፋታቸው ክብደትና በነበራቸው የኃላፊነት ደረጃ መጠን፣ የጎላ ወንጀል የፈፀሙትን ዋና ዋናዎቹን ለቅሞ አመጣ:: እነዚህንም በነበራቸው የሥልጣን ደረጃ መጠን፣ በማዕረጋቸው ቅደም ተከተል ስማቸው ይዘርዝርና እኛ በዚያ ቅደም ተከተል እየሄድን ለመወሰን እንሞክር ተባለ:: በዚህ ዓይነት ዋና ዋናዎቹ ሹሞች ሲቀሩ ቁጥራቸው ወደ60 ገደማ ደረሰ::

በዚህም ቢሆን ብዙ ተወዛገብን:: ለምሳሌ፣ ‹21ኛ ተራ ቁጥር ላይ



ያለው ደጃዝማች እከሌ› ሲባል፣ ‹እንዴ 45ኛ ቁጥር ላይ ያለው ፊታውራሪ እከሌስ ለምን ይቀራል?›የሚል ይነሳል:: ‹ጄኔራል እከሌ!› የተባለ እንደሆነ፣ የአንዱ ክፍለ ጦር ተወካይ ይነሳና ‹ሲጨቁነን የኖረው ጄኔራል እከሌስ?› ይላል:: ብዙ ከተነጋገርን በኋላ መጨረሻ ላይ የቀሩት ትልልቆቹ አውራዎች፣ የጦር መሪዎች፣ መሳፍንት፣ መኳንንት እየተባሉ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ሰዎች ብቻ ቀሩ:: እንግዲህ ይበቃል አልን:: እዚያ ላይ ቆምን::

አሁን ሰዎቹ ተወስናባቸዋል:: ቀጥሎ ወደአፈፃፀም ሄድን:: እስረኞቹን ከታሰሩበት አውጥተው ወደመገደያው ቦታ የሚወስዱት ሰዎች ስም ዝርዝር ይዘው ሄዱ:: በዚህን ጊዜ ነው ‹ጄኔራል አማን እምቢ ብለዋል› የሚለው ነገር የመጣው:: ይሄ ሁሉ እስኪሆን ቀኑ መሽቷል:: እስረኞቹም የተረሸኑት፣ ጄኔራል አማንም ተኩስ ከፍተው የተገደሉት ማታ በጨለማ ነው:: ሁሉ ነገር አልቆ ከስብሰባው ቦታ የወጣነው ሊነጋጋ ሲል ነው::

*ገነት - የሰዎቹ መገደል ፀፀቶዎታል? ባናደርገው ኖሮ ብለው ቆጭቶዎታል? ምንድነው የሚሰማዎት? ከተገደሉት ውስጥ በድምፅ አሰጣጥ ጊዜ «ይሄ ሰው መሞት የለበትም» ብለው እንዳይገደል የፈረዱለት ሰው ካለ እስቲ ይንገሩኝ::*

**መንግሥቱ** - መጀመሪያ ነገር እኔም ሆንኩ ሌሎቹ የደርግ አባላት ከተገደሉት ሰዎች በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ነው የምናውቃቸው:: በበኩሌ በሠራዊቱ ውስጥ ከነበሩት ከፍተኛ አዛዦች ጥቂቶቹን ከማወቄ በስተቀር አብዛኛዎቹን ራስ እከሌ፣ ደጃዝማች እከሌ ሲባል ስማቸውን ከምሰማ በስተቀር አላውቃቸውም::ሌሎቹም እንደዚሁ:: ስለነሱ የነበረን ዕውቀት በጣም የተወሰነ ነው:: ከመካከላችን ጥቂቶቹ፣ በመረጃውና ደህንነቱ ውስጥ የነበሩ የተወሰኑትን ሊያውቁ ይችላሉ:: ቤተ መንግሥት አካባቢ ይሠሩ የነበሩ አንዳንዶቹ ስለንጉሡ፣ ስለግቢው ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያዩትንና የሰሙትን በመጥቀስ ነው ሲናገሩ የነበረው:: እኛማ ከውጪ የመጣነው ምንም የምናውቀው ነገር የለም:: መዳን አለባቸው፣ መሞት አለባቸው ብሎ ለመወሰን የሚያስችለን ዕውቀትም ሆነ ግንዛቤ አልነበረንም::

*ገነት - ስለዚህ በወሰናችሁት ውሳኔ አዝነዋል፣ ወይም ይቆጭዎታል?*

**መንግሥቱ** - ማንም ሰው በዚህ ሊደሰት አይችልም::እኔ እንደሚመስለኝ ከተወሰኑ ሰዎች፣ ምናልባትም እዚህ ውሳኔ ላይ እንድንደርስ

በመገፋፋት አስተዋፅዖ ካደረጉ ሰዎች በስተቀር «አፈፃፀሙ ትክክል አይደለም!» ብለን የተከራከርንለትና የታገልንለት ነገር ስለሆነ ደስተኛ ልንሆን አንችልም። በሕግ ፍትሐዊ አሠራር ልንሠራ መርማሪ ኮሚ ሽን አቋቁመን ለሕዝብ አሳውቀን፣ ፖሊሲ ወጥቶለትና ሥርዓት ይዞ እየተራመደ ያለን ነገር በድንገት እንዲህ ያለ ቀውጢ ሁኔታ መጥቶ ሲያዛባው ውጥናችንን ሁሉ ነው ያከሸፈብን።ሥራችንን ነው ያበላ ሸብን።

ከመካከላቸው ጨርሶ መገደል ያልነበረባቸው ሰዎች ነበሩ። አንዳን ዶቹ አለቆቼ፣በግል የማውቃቸውና ባለውለታዎቼም ናቸው።ለምሳሌ፣ ጄኔራል አበበ ገመዳን የምወዳቸው ሰው ነበሩ። አሜሪካን አገር ለሁ ለተኛ ጊዜ ለትምህርት ልሄድ ስል ከአሜሪካኖቹ ጋር ተጣልቼ ስለነበር ‹አይሄድም!› ሲሉ ሽንጣቸውን ገትረው ተከራክረው ነው እንድሄድ ያደረጉት። ትዝ እንደሚለኝ ታመው ነበር። ተነስተው በከዘራ እየተመ ረኮዙ መጥተው ‹እናንተ ናችሁ አገሪቷን የምትመሩት ወይስ እኛ?› እስከማለት ደርሰው ነው እንድሄድ ያደረጉት። ሰውዬው ጥቅም አይፈ ልጉም ነበር ወይ? ከሥርዓቱ ጋር ባላቸው ትስስር አልተጠቀሙም ወይ? ለሥርዓቱስ ታማኝ አልነበሩም ወይ? አንድ ነገር ነው። ያከናወኗቸው ፋይዳዎች ሲታዩ ቀላል ሰው አልነበሩም። ለአገርና ለሕ ዝብ የሚያስቡ ሰው ነበሩ። አገር ቢሰጣቸው ሊመሩ የሚችሉ ሰው ነበሩ። በዘመናዊ ትምህርት የጠለቀ ዕውቀት ባይኖራቸውም የበሰለ ጭንቅላት ነበራቸው። ከጣሊያን ልምድ ያካበቱ ሰው ናቸው። በኢትዮ ጵያ ልምድ አካብተዋል። በነገራችን ላይ ባንዳ ነበሩ። እስከ ሞቃዲሾ ሄደው ተዋግተዋል። ክቡር ዘበኛ ነው የተነሳባቸው። ‹አበበን ካልገ ደልን› አለ።አሁን ጄኔራል ሥዩም ገድለጊዮርጊስ እንዴት ያላግባብ በመበልፀግ ይጠረጠራሉ? ደሞዛቸውን እየፈረሙ በሞዴል ስድስት የሚወስዱ ናቸው። ሁለተኛ ክፍለ ጦር ‹በጭራሽ ካልተያዙልን› አለ። ሁሉም የየራሱ ቂም አለው። እንደበቀልም ነው። ሲጠራቀም የኖረ ቂምና በቀል በኛ ሊፈፀም የቆየ ዕዳ ሆኖ ነው የመጣብን። እኛ ላይ የመጣ የታሪክ ዕዳ ነው።

*ገነት - እስከንደር ደስታስ?*

***መንግሥቱ*** - እሱ በትውልዱ ነው እንጂ ምንም አላደረገም። ትምህርቱም እንግሊዝ አገር ነው። ባህር ላይ ነው የኖረው። የሚቀብ ጠውም፣ የሚጫወተውም፣ ምን የሚለውም እዚያው ውጪ ነው።



እሱ ብቻ አይደለም፤ ሌሎችም እንዲሁ የገቡ አሉ።

እዚያ ውስጥ ጥፋት ያለባቸው ሰዎች አልነበሩም ለማለት ሳይ ሆን በዚያ ዓይነት አሠራርና በዚያ ሁኔታ መፈፀም አልነበረበትም። በእርግጥ ጊዜው የበለው፣ በለው ጊዜ ነበር። ትንሽ በስሜት የመነዳት ሁኔታ የሚታይበት ጊዜ ነበር። በኛም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ የነበረው ስሜት አሁን ዛሬ እንደሚባለው አይደለም።እኛም ብንሆን የህብረተሰቡ አካል እንደመሆናችን የሕዝቡን ስሜት ነበር የምናንፀባርቀው።

ይሁን እንጂ እንደዚህ ያለ በሰው ሕይወት ላይ መፍረድን የመ ሰለ ነገር እጅ እያወጡ መወሰን የሚገባ አልነበረም። ሰዎቹ አገር ጠልቷቸው፣ ሕዝቡ ራሱ እያሰረ አምጥቶ ያስረከበን ሰዎች ናቸው። በሬድዮ ስማቸው ሲጠራ መጥተው እጃቸውን የሰጡ ሰዎች ናቸው። በቁጥጥራችን ሥር ውለዋል።እነሱን ለመግደል የሚያጣድፈን ወይም የሚያካልበን ም..ንም ዓይነት ጫና አልነበረብንም። በውነቱ ከመካከ ላችን ይሄንን በማድረጋችን «አበጀን፤ ጥሩ ሥራ ሰራን» የሚል ያለ አይመስለኝም። ይህ አንድ ታሪክና ጊዜ የፈጠረው አሳዛኝ ክስተት ነው። የኔን አስተያየት ሌሎቹም ይጋራሉ ብዬ አምናለሁ።

# የጃንሆይ ሞት

*ገነት - ኰሎኔል ዳንኤል በአንድ ወቅት ካንድ ነርስ ጋር ሄደው ለጃንሆይ ኪኒን እንክብል ሰጥተው ሲገሏቸው ሞክረው ሳይሳካላቸው መቅረቱ ይነገራል።እንክብሉ መሬት ወድቆ ጃንሆይም ልብሳቸው ተጨማዶ ያዩ ሰዎች አሁን እውነቱን እያወጡ ነውና ስለዚህ ምን ይላሉ?*

***መንግሥቱ*** - በንጉሡ አካባቢ በጣም ጥብቅ ጥበቃ ነበረን።በጣም መፈራራትም አለ። በዚያን ጊዜ ባንድ ትንሽ ስህተትም ቢሆን ሰው ሕይወቱን ማጣት ይችላል - የደርግ የዘመቻ ክፍል ኃላፊ የሆነው እንደ ኰሎኔል ዳንኤል ያለ ሰውም ቢሆን። ሁሉም ስለሚፈራራና ስለ ሚጠባበቅ ማንም ሳያውቅና ሳይሰማ ተንኮል ለመሥራት ብቻውን ሄዶ ጃንሆይን ለመግደል ሙከራ ያደርጋል ብዬ አላስብም። ቢሄድ እን ኳን በዚህ ዓይነት መንገድ ይከናወናል የሚል እምነት የለኝም። ሰውዬውን አለማወቅ ነው። ኰሎኔል ዳንኤል ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ምርጥ ልጆች አንዱ የሆነ ጥንቁቅና የሰከነ መኰንን ነበር። ኪኒኑን ወለል ላይ ትቶ መሄድን የመሰለ መዝረክረክ ዳንኤል ጋ የለም።

አይመስለኝም።

*ገነት - ጃንሆይ መሞታቸውን መጀመሪያ ያየው ማነው?*

***መንግሥቱ*** - ማን መጀመሪያ መሞታቸውን እንዳየ እርግጠኛ አይደለሁም። እንደዚህ ዓይነት ነገር ሆኗል ብለው ለኛ የነገሩን የጥበቃ ኃላፊ መኰንኖች ናቸው። አብረዋቸው አያድሩም እንጂ ጃንሆይ ጋር የሚገቡትና የሚወጡት፣ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያቀርቡላቸው፣ የሚያገለግሏቸው አልባሾቻቸው ናቸው። ከነሱ መሐል አንዱ ሊሆን ይችላል ያያቸው። እሱ ለጠባቂዎች ይናገራል። ጠባቂዎቹ ላለቆቻቸው ሪፖርት ያደርጋሉ ማለት ነው። እዚያ የነበሩት የንጉሡ ጠባቂ ዘቦች በቋሚነት የተመደቡ ይሁኑ ወይም በየጊዜው የሚለዋወጡ ይሁኑ አሁን በእርግጠኝነት ለመናገር አልችልም። ጊዜው ቆየ።

*ገነት - እርስዎ ጃንሆይ በሰው እጅ ተገድለዋል ብለው አያምኑም?*

***መንግሥቱ*** - በፍፁም! ታመው መሞታቸውን ነው የማውቀው። ፊኛቸውን ታመዋል ተብሎ ተነገረን። በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ኦፕራሲዮን ሆነው ከቆዩ በኋላ ነው የሞቱት።

ገና እንደታመሙ ሐኪማቸው ፕሮፌሰር አሥራት የሕመማቸው ነገር ስላሳሰባቸው ውጪ ሃገር ሄደው እንዲታከሙ ለመጠየቅ እኔ ዘንድ መጡ። ነገሩ አስቸጋሪ እንደሚሆን ባውቅም ጉዳዩን ለደርግ ለማቅረብ ቃል ገብቼ አሰናበትኳቸው።

በደርግ ስብሰባ ላይ አነሳንና ተነጋገርንበት። ብዙዎቻችን በቂ ሕክምና አግኝተው እንዲታከሙ በጎ ፈቃዱ ቢኖረንም እሳቸውን ወደ ውጪ ልኮ ለማሳከም በፖለቲካው በኩል እጅግ አስቸጋሪ ነገር ሆነብን። አንድ ንጉሥ ከሥልጣን አውርደን በጥበቃችን ስር ተቀምጠዋል። በጥብቅ ነበር የሚጠበቁት። ለምን ቢባል እኚህን ንጉሥ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚቃወማቸው አለ፣ የሚደግፋቸውም አለ። ቢጠፉ ወይም ቢሰረቁ ሊነሳ የሚችለውን የፖለቲካ አቧራና ከዚያም በኋላ የሚከተለውን ነገር በመገመት ነው።ቀላል ነገር አይሆንም። እሳቸው አንድ ነገር ቢሆኑ ኃላፊነቱ የኛ ነበር፤ እንጠየቅበታለን። ከጠባቂዎች ጀምሮ እስከ እኔ ድረስ። ሕዝቡም፣ ሠራዊቱም ይጠይቀናል። እንዴት ተደርጎ ነው አገርን ሲገዙ የኖሩ ንጉሠ ነገሥትን ያህል ነገር በጥበቃ ሥር አቆይተን አሁን ጨርሶ በማንቆጣጠረውና በማናዝበት ባዕድ አገር ልናሳክም የምንወስዳቸው? የደህንነቱና የፖለቲካው ነገር



እማይሆን ነገር ሆነብን። በእርግጥ ከደርግ አባላት መካከል ‹እሳቸው ይሄን ያህል ዕድሜ ሰጥቷቸው መኖራቸው ዕድለኛ ናቸው። ስንቱ በሕፃንነቱ ቀላል ሕክምና እንኳን እያጣ በአጭሩ የሚቀጭበት አገር ነው። ይሄን ያህል የምንጨነቅበት ነገር የለም› የሚል አስተያየት የሰጡም ነበሩ። ብቻ ዋናው ነገር ወደውጪ የመሄዳቸው ነገር የሚያስከትለው የፖለቲካ ጫና ከፍተኛ ስለሆነ በአገር ውስጥ እንዲታከሙ ተወሰነ። ለዚህም የሚያስፈልገው ወጪ ሁሉ ወጥቶ በጥሩ ሁኔታ እንዲታከሙ ተፈቀደ።

ይሄንን የደርጉን ውሳኔ ፕሮፌሰር አሥራትን ጠርቼ ነገርኳቸው። ወደውጪ ልኮ ማሳከሙ እንደማይቻል፣ ነገር ግን እዚሁ እንዲታከሙ የሚያስፈልገውን ወጪ፣ የፈለገውን ያህል ይሁን ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን አስረዳኋቸው። እሳቸውም ‹የማይቻል ከሆነ ምን ይደረጋል።እንግዲህ ቀዶ ጥገናው እዚህ የሚደረግ ከሆነ በሕክምናው በኩል የሚያስፈልገንን መሣሪያና የመሳሰለውን ነገር አጥንቼ ተመልሼ ይገልምጣ› ብለው ሄዱ። እሳቸው የሚጠይቁት ነገር እንዲቀርብላቸው ትዕዛዝ ሰጠሁ። ከዚያ ተመልሰው ሲመጡ ደግሞ አሁንም ሌላ አስቸጋሪ ነገር ይዘው መጡ። ፕሮፌሰሩ ‹ቀዶ ጥገናውን ለማድረግ የሚያስፈልገን መሣሪያና ዕቃው ሁሉ ተሟልቶ የሚገኝበት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስለሆነ እዚያ እንዲታከሙ ይፈቀድልን› የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ጥቁር አንበሳ ይሂዱ ቢባል የሚፈጠረውን ግርግር ፕሮፌሰር ያጤኑት አልመሰለኝምና ሌላ መንገድ ለመፈለግ ሞከርኩ።

«ሌላ አማራጭ የለም ወይ? እዚሁ ቤተመንግሥት ግቢ እናንተ መጥታችሁ የሚያስፈልጋችሁን መሣሪያ ሁሉ ይዛችሁ ኦፕራሲዮን ማድረግ አትችሉም ወይ? ለምንድነው ጥቁር አንበሳ ካልሆነ ያሉበት ምክንያት? ለናንተ በቅርብ ለመከታተል እንዲያመቻችሁ ነው? ወይስ እዚያ ያለ መሣሪያ እዚህ ሊመጣ አይችልም? ቴክኒካዊ ልዩነቱን ንገሩኝ» አልኳቸው።

‹መብራት የጠፋ እንደሆንስ?› አሉ።

«ጀኔሬተር መትከል አይቻልም?»

‹አይሆንም። አደገኛ ሊሆን ይችላል። ሆስፒታል ካልመጡ አስቸጋሪ ይሆናል› አሉ።

አሁንም እንደገና ለደርግ አቅርቤ፣ ሆስፒታል በግድ መግባት ካለባቸው ክቡር ዘበኛ ሆስፒታል ይግቡ ተባለ። ገቡ። በጥሩ ሁኔታ ታክ

መው ወጡ። ከዚያ በኋላ አገግመው ደህና ከሆኑ በኋላ ነው እንደገና አገርሽቶባቸው የሞቱት።

*ገነት - አሁን ከተረኩልኝ ሌላ በጃንሆይ ግድያ እጅዎን አስገብተዋል ተብሎ የቀረበብዎትን ክስ አይቀበሉትም?*

**መንግሥቱ** - በሐሰት የሚቀርብብኝን ክስ እንዴት ልቀበል እችላለሁ? ዛሬ ስለሳቸው ሞት ያልተባለ ነገር የለም። በኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በነበረው የአመራር አባላት ላይ ያልተለጠፈብን ነገር የለም። በተለይ በኔ ላይ። ከሃገር ከወጣሁ በኋላ እንደሰማሁት ‹ኰሎኔል አጥናፉና እሱ ሆነው ገብተው በመርዝ ገደሏቸው› ተባለ። የቤተመንግሥቱ ሠራተኛ ነው የተባለው ሰው ነው እሱ እንዲህ ያለው። ሌላ ወሬ ደግሞ ‹በትራስ አፈኗቸው› የሚል ነው። ዳዊት በፃፈው መጽሐፍ ደግሞ ‹አንድ ወታደር አዞ አስገደላቸው› ይላል። ወያኔ ደግሞ ‹ገድሎ ቀብሮአቸው፣ የሚቀመጥበት መቀመጫ ሥር ... ራሳቸው አፅም ላይ ነው የተቀመጠው› ብሎ አስወራ።

የሚገርም እጅግ የሚገርም ነው። እኔ ካብዮቱ በፊት በነበረው ሥርዓት የተጨቆንኩ ሰው አልነበርኩም።በግል ሕይወቴ የጎደለብኝም ነገር አልነበረም። ምናልባት አለቆቼ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ ትምህርቴን እንዳልከታተል ስለከለከሉኝ ቅሬታ ቢኖረኝ ነው እንጂ በጃንሆይ ላይ የተለየ ጥላቻ አልነበረኝም። ከሥልጣን ካወረድናቸው በኋላ የኛን መንግሥት ሊያስቸግሩ የሚችሉበት አንዳችም ፖለቲካዊ ኃይል ወይም አቅም አልነበራቸውም። ስለዚህ እሳቸውን የማስገድልበት ምንም ምክንያት የለም።

*ገነት -ሞታቸው በተሰማ ጊዜ በደርግ አባሉች ላይ ያሳደረው ስሜት ምን ይመስል ነበር?*

**መንግሥቱ** - መሞታቸውን ለኔ መጥቶ ሪፖርት ያደረገልኝ ኰሎኔል ዳንኤል ነበር። ለደርግ አባሎች ስነግራቸው፣ ብዙዎቹ ‹ግልግል› ነው ያሉት። ማንም ከቁም ነገር አልቆጠረውም። ምክንያቱም በየቦታው ሰው ይሞታል። በየቀኑ ሰው በረሃብ፣ በበሽታ ይሞታል። በየቀኑ ወታደሩ ይሞታል። ይህን ያህል ወታደር ሞተ፣ ቆሰለ፤ እከሌ ሞተ የሚለው ነገር በየዕለቱ የሚደርሰን ዜና ስለነበር እሳቸው ሞቱ ሲባል፣ ‹እና ምን ይደረግ?› ነው የተባለው።። በደስታ መጮህም የቃጣቸው ነበሩ። በሰው መሞት የመደሰቱ ነገር ትንሽ ለሕሊና የሚከብድ ነው። «ብቻ እንድታውቁት ብዬ ነው» በማለት ተናገርኩ።



*ገነት - እርስዎስ? ሞቱ ተብሉ ሲነገርዎት ምን ተሰማዎት?*

**መንግሥቱ** - በጥሩ ሁኔታ ታክመው ከዳኑ በኋላ ጥቂት ሳምንታት ቆይተው ‹ሞቱ!› ብሎ ዳንኤል ሲነግረኝ ምክንያቱ ሊገባኝ አልቻለም። «እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት ተሽሏቸው ደህና የነበሩ ሰውዬ በድንገት ሞቱ ትላላችሁ?» በማለት ዳንኤልን አፋጥጬ ያዝኩ። ነርሱም ተጠራና መጣ። እንዳጋጣሚ ሰሞኑን ለሥራ ከከተማ ወጥቼ ስለነበር ታመዋል ሲባል ስለሰማሁ ነርሱን፣ «እዚህ የተቀመጥከው ቢያማቸው ሐኪም ልትጠራ፤የሚያስፈልጋቸውን ልታቀርብ አይደለም ወይ? ለሐኪሞቹ ወይ ለባለሥልጣኖቹ ጤንነታቸው የሚያሰጋ ሁኔታ ላይ መውደቁን እንዴት ሳታሳውቅ ቀረህ?» በማለት ኃይለ ቃል ተናገርኩት። ‹እናንተ በሥራ ተወጥራችሁ ስለነበረና ከተማ ውስጥ ስላልነበራችሁ፣ እኔም ለክፉ የሚሰጣቸው ስላልመሰለኝ ለደርጉ ባስቸኳይ አላሳወቅሁም። ሆኖም ግን ለሌሎች ሐኪሞች አሳይቻለሁ› አለኝ። ነርሱ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድም፣ ለማባረርም ፈለግሁ። ሐኪሞቹ የሚሉትን ለመስማትም ፕሮፌሰር አስራትንና ሌሎቹን ሐኪሞች አስጠራሁ።

*ገነት - ግን ፕሮፌሰር አሥራት መጥተው እርስዎ አላናገሯቸውም።*

**መንግሥቱ** - ቆይ! ትንሽ መበሳጨቴን ያዩት ጄኔራል ተፈሪ ለብቻዬ ጠሩኝ። ‹አንድ ጊዜ እስቲ ወደኔ ቢሮ እንሂድ አሉኝ› እና ‹ሻለቃ መንግሥቱ! የፈሰሰ ውሃ ይታፈሳል? ምንም ሆነ ምን ንጉሡ አርፈዋል። እሳቸው ዕድለኛ ናቸው። ይህን ያህል ዘመን ገዝተዋል። በውነቱ በአብዛኛው ነገር የተሳካላቸውና ረጅም ዕድሜ ያደላቸው ሰው ናቸው። የመጨረሻ ቀኖቻቸው ባያምሩም። አሁን ደግሞ አረፉ። ሳይሰቃዩ ማረፋቸውም ዕድለኛ ናቸው። በኛ በኩል ግን አንተ እየተቆጣህ፣ በወቅቱ ለምን አልተናገራችሁም?ትላንት ደህና ናቸው ተብሎ ዛሬ ምን ሆነው ሞቱ? እያልክ ስትል ምን ዓይነት የፖለቲካ ውስብስብ ውስጥ ነው የሚከተን? የበታቾችህንም፣ እናንተ የማትረቡ ምናምን፣ ስትል ታስቀይማቸዋለህ እንጂ ምንም የምትፈጥረው ፋይዳ የለም። አሁን ሐኪም ማስጠራትንስ ምን አመጣው? ከዚህ ግቢ ውጪ ቢሰማ ጠላቶቻችንን ከማስደሰትና ውዥንብር ከመፍጠር በስተቀር ምንም አይጠቅም። ተው› አሉና መከሩኝ። «እሺ» አልኳቸው። ከዚህ

በኋላ «ሌላ ጊዜ ስንፈልጋችሁ ትመጣላችሁ» ብላችሁ አሰናብቷቸው ብዬ ሐኪሞቹ ተሸኙ።

የንጉሡን ሞት በተመለከተ በደርጉ አባላት በኩል የተለያየ አስተ ያየት ተንፀባርቋል። ‹እንዴት ሊሆን ቻለ?› የሚሉም ነበሩ። «ግልግል ነው። ታዲያ ምን ይደረግ?» ያሉም ነበሩ። ዞሮ፣ ዞሮ ግን እኛን ያጨቃጨቀንን ያህል ከሕዝቡ በኩል አንዳችም ስሜት አላየንም። ምንም ነገር! አንድም ነገር አልታየም። ይሄ አስደንቆኛል። በወቅቱ በደህንነቱም፣ በሌላም ሕዝቡ ምን እንደተሰማው ለማወቅ አስጠይቄ ነበር። ም..ንም ነገር አልተባለም። ኮር ዲፕሎማቶች አካባቢም። ምንም። ትንሽ በእንግሊዝ አገር አረፉ ተብሎ ተነገረ። በስደት ያሳለፉትን ጊዜ በመጠቃቀስ የሕይወት ታሪካቸውን ተረኩ። በቃ።

*ገነት - ከዚያ በኋላ ስለቀብራቸውስ ምን ተነጋገራችሁ?*

***መንግሥቱ -*** ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴውን ደግሞ ሰብስቤ አናግራለሁ ስል ፓትርያርኩ ቢሮዬ መጡ። ‹ፓትርያርኩ መጡ› ሲሉኝ «እኔ ጊዜ የለኝምና ኰሎኔል አጥናፉ ያናግራቸው» ስል፣ ‹አይ እኔ ከኰሎኔል አጥናፉ ጋር አልነጋገርም። እሱማ ሊያጠፉኝ ነው የሚታገለኝ። እና ሻለቃ መንግሥቱ ያነጋግረኝ። ያለዚያ ልመለስ› ብለዋል አሉኝ። ፓትርያርኩና ኰሎኔል አጥናፉ ፈፅሞ አይዋደዱም። ምክንያቱ ምን እንደሆነ አይገባኝም። «እሺ ደህና፣ አስገቧቸው» አልኩና መጡ። ብቻቸውን አልነበሩም፤ ሌሎች ሁለት ጳጳሳት አብረዋቸው ነበሩ።

‹ንጉሡ ካረፉ ሥላሴ ቤተክርስቲያን እንዲያርፉና አስፈላጊውን ጸሎተ ፍትሐት እንድናደርግላቸው ይፈቀድልን› አሉ።

ነገሩን ሳመዛዝነው ይሄ ነገር ምን እንደሚፈጥርና በሕዝብ ዘንድ በምን መልኩ እንደሚተረጎም አላውቅም። ስለዚህ «ያልጠበቅሁትን ነገር ነው የጠየቃችሁኝ። በነገሩም አላሰብኩበትም። የደርግ አባላትም እንዴት እንደሚያዩትና ምን ውሳኔ እንደሚሰጡበትም አላውቅም። እነሱን አነጋግሬ ጠይቄ የሚሉትን እነግራችኋለሁ» ብዬ መልስ ሰጧቸው።

በደርጉ ስብሰባ ላይ ይሄ ነገር ቢነሳ አቧራው እንደሚጨስ አውቃለሁ። ‹ምን ... ድ ነው እናንተ እስከዚህ ድረስ? አሁንም ንጉሡን እንደልዩ ፍጡር ከማየት እምነት አልወጣችሁም እንዴ? የሞተስ እንደሆነ? ምንድነው ሰው አይደለም እንዴ?› ብለው የሚያጣጥሉ ብዙ



እንዳሉ ስለማውቅ ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ ውስጥ ያሉትን ብቻ ሰበሰብኩና «እንዲህ ያለ ነገር ተጠይቋልና ምን ታስባላችሁ?» አልኳቸው። ያሉኝ ምንድነው ‹እሳቸውን ማየት ያለብን እንደ አንድ ተራ ሰው ነው። በሕግ በአዋጅ ወስነን ስናበቃ ከሥልጣናቸው ወርደዋል። ንጉሥ ስለነበሩና ሽማግሌ ስለሆኑ የሚያስፈልገውን ሰብአዊ እንክብካቤ እያደረግንላቸው ነው የቆዩት። በሰማኒያ ሁለት አመታቸው አረፉ። ዕድለኛ ናቸው። ከዚህ በተረፈ ሌላ ጳጳስ ምናምን ... ሥላሴ የሚባለውን ነገር ትኩረት ልንሰጠው አይገባም። ካደረግነው እርምጃ ጋር ተቃራኒ (ኮንትራዲክተሪ) ነው› የሚል ነገር ነው። እንዳውም አንዱ ተነሳና ‹እንዴ!ለመሆኑ ለምንድነው ሥላሴ የሚቀበሩት? እሳቸው እኮ አርበኛ አይደሉም። ሥላሴ የሚያርፉት አርበኞች ብቻ ናቸው› አለ።

አይ እንግዲህ አልኩና ፓትርያርኩን «ይቅርታ ያድርጉልኝ፤ ነገሩ እናንተ እንደምታስቡት አልሆነም። መልኩን ለውጦ እንዳውም ሌላ ነገር ነው ያስከተለው። ‹ንጉሡ አርበኛ አይደሉም፤ እዚያ አያርፉም። ፍትሐት ስላሉት ደግሞ ጳጳሱስ ቢሆኑ ስንቱ ወታደር በየቀኑ ሲረግፍ ምነው ለነሱ ፍትሐት ለማድረግ አልጠየቁም?› የሚል ነገር ሁሉ ተነስቷል። ከርስዎ የምደብቀው ነገር የለም። ያለው ስሜት ፍፁም እናንተ እንደምታስቡት አይደለም።አንድ የፖለቲካ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ይቅርታ አድርጉልኝ። ምንም ማድረግ አልችልም» አልኳቸውና ተሰናብተው ሄዱ።

በመጨረሻ ላይ ከሥራ አስፈፃሚው ኰሚቴ ጋር በተነጋገርነው መሠረት መመሪያ ሰጠሁ። «እንግዲህ ይሄ ፍትሐት፤ ፐብሊሲቲና የመሳሰለውን ነገር ልንፈቅድ አንችልም። ይሄ ግልፅ ነው። ሕዝብም በበጎ የሚመለከተው ነገር አይደለም። በእርግጥ የሳቸውና የዘውድ ደጋፊዎች በበጎ መንፈስም፣ በቅንነት ወይም በወዳጅነት ይህንን የመሰለ ነገር ሊጠብቁ ይችላሉ። እኛ ደግሞ ከፖለቲካችን አንፃር ችግር መፈጠር የለበትም።» በመጨረሻ «የት ይረፉ?» ሆነ ጥያቄው።

ባዕታ ተባለ። ባዕታ ገብተው ሲያበቁ ምንም ዓይነት ክበር፣ ጡሩ ምባና ጋጋታ ሳይኖር ይረፉ ተባለ። ይሄንኑ ትዕዛዝ ለእስር ቤት ኰሚቴ አስተላለፍኩ። በዚሁ አከተመ።

*ገነት - ታዲያ ትዕዛዙ መፈፀሙን አረጋገጠዋል?*

***መንግሥቱ -*** አይ ትዕዛዜ ፍንክች የማይል ነገር ነው። ይፈፀማል። አይፈፀምም ብዬ ጥርጣሬ የለኝም። ሰውዬው አርፈዋል።መሰረታዊው

የቄሶች ጥያቄ መልስ አግኝቷል:: እኔ በጣም የሚያጣድፍና ጊዜ የማይ ሰጥ ሥራ አለብኝ:: ችግር አለ:: ወደዚያ ዞሬያለሁ:: በዚህ ሁኔታ ያለፍ ነውን ታሪክ ነው አንዴ በመርዝ፣ አንዴ በትራስ ገደላቸው፣ ምናምን እየተባለ የሚወራው:: በደርጉ ውስጥ ስለሳቸው ጉዳይ ተነስቶ ምን ይሁኑ፣ ምን ብሎ ያሰበ ወይም ያሳሰበ ሰው ጨርሶ የለም:: ወደመግ ደል እርምጃ ማምራት ቀርቶ ያሰበውም የለ::

*ገነት - ጽህፈት ቤትዎ ሥር የተገኘውስ አፅም?*

**መንግሥቱ** - እኔ ምን አውቃለሁ? የማንን አፅም እንዳወጡ አላ ውቅም:: የሚገባኝ ነገር አይደለም::

*ገነት - የቀበሩበትን ቦታ የሚያውቅ ሰው እኮ ነው ተፈልጎ መጥቶ ያወጣው:: መቀበራቸውን ያየ ሰው በመኖሩ ነው አፅማቸው የተገኘው::*

**መንግሥቱ** - ማነው እሱ?

*ገነት - ስማቸውን አላስታውስም:: ግን ቤተመንግሥት ይሠሩ የነበሩ ኢንጂነየር ናቸው:: ያ ቦታ ተቆፍሮ በብዙ ድካም ነው የተገኘው:: እንግዲህ ብዙ ነገር አለ ...*

**መንግሥቱ** - ቀጣፊ በይው:: ያ ኢንጂኒየር የቤተመንግሥት መሐንዲስ የነበረው በኮራፕሽንና በሌብነት ተይዞ ‹ቤት አሳድሳለሁ፤ ምናምን› እያለ ብዙ ነገር አድርጎ - ይሄንን ጠይቆ ማረጋገጥ ይቻላል- ገና እንደገባን ነው የታሰረው:: እንዳውም እንደማስታውሰው የሱ ልጅ ካናዳ ተማሪ ነበረች:: ደብዳቤ ሁሉ ጽፋልኝ «አይ አባትሽ አንድ ትልቅ ስህተት ላይ ወድቋል:: እኔ ከሕግ በላይ አልፌ ምንም የማደርገው ነገር የለም::ነገር ግን ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንዲሰጠው ይደረጋል» ብዬ በውነቱ ለስሜቷ ስል መልሼ በእጄ ደብዳቤ ጽፌላታለሁ:: ከዚያ ከእስር ቤት ሲወጣ ወዴት እንደሄደ አላውቅም እንጂ እሱ እኛ እንደገባን ተወንጅሎ እስር ቤት ነበር:: እንዴት አድርጎ ነው ያወቀው? ደግሞስ እሳቸውን ለማሳረፍ (ለመቅበር) ለምንድነው መሐንዲስ ያስፈለገው?

*ገነት - ለመቆፈር ነው እንጂ፤ የተቀበሩበት ቦታ፣ ቦታ ነው እንዴ? ቢሮዎ ሥር አይደለም እንዴ?*

**መንግሥቱ** - ለመቆፈርስ ቢሆን መሐንዲስ ያስፈልጋል?



*ገነት - አምና! ቢሮው ሥር፣ በሽንት ቤት ቱቦ ውስጥ አልፎ አይደለም እንዴ?*

**መንግሥቱ** - እንዴት?

*ገነት - አሀ! ስለሁኔታው አያውቁም ማለት ነው? ምስክርነታቸውን የሰጡ ሰዎች እንዳሉት ከሆነ መጀመሪያ ስልዑል ሣህለሥላሴ ተዘጋጅቶ በኋላ እሳቸው በሌላ ሣጥን ስለተቀበሩ በቤተመንግሥት የሚገኝ ሣጥን መጥቶ በዚያ ዳንሆይ ሲቀበሩ ሲዘጋጅ፣ «እሱን ሁሉ ተዉ!» ተብሎ ሣጥኑ ቀርቶ እንዲሁ እንዲ ቀበሩ ሆኗል:: አፅማቸው ሲወጣ ሣጥን የለው፣ ምን የለው፤ እንዲሁ ከአፈሩ ውስጥ ነው ተቆፍሮ የወጣው:: እንደዚያ ነው::*

**መንግሥቱ** - በውነቱ እኔም ሆንኩኝ ሌሎቹ የደርግ አባላት ስለዚህ ነገር አናውቅም:: በውይይታችን መጀመሪያ ላይ እንደነገርኩሽ የምና ገረው የኑዛዜ ያህል ነው:: እኔ ካገሬ የወጣሁ ስደተኛ ነኝ:: የምኖር በትን ዕድሜ፤ የቀረኝን ጊዜ አላውቅም - እንደማንኛውም ሰው ሁሉ:: የኔ ጥረት በተቻለ መጠን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እውነቱን አስጨብጬና ለራሴም የሕሊና እርካታ አግኝቼ የማለፍ ጥያቄ ነው:: አንደኛ ነገር እሳቸው በጣም ሸምግለዋል:: ሁለተኛ ነገር ‹ሌባ! ሌባ!› እየተባሉ በዚያ ዓይነት ሁኔታ ሲሄዱ፣ እኛ እንኳን «አይ ሰው» ብለን ራሳችንን በደፋንበት ሁኔታ ከሥልጣን የወረዱ ሰው በምንም መልኩ ለኛ ፖለቲካ፣ ለኛ ሕልውና፣ በምንም ነገር ንጉሡ ጠንቅ ይሆናሉ የሚል ሥጋት ጨርሶ አልነበረንም:: ደግሞ ምንም ከሥልጣን ቢወርዱ በብዙ መልኩ እያንዳንዳችን በግላችን ጥፋታቸውንም ሆነ ልማታቸውን እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ የምናመዛዝንበት መንገድ አለን:: እኔም ሆንኩ የደርግ አባላት በዚህ ነገር እንዳው ትዝ ብሎንና አስበንበት ወደዚህ እቅጣጫ ያመራንበት ጊዜ፣ ይህንንም አንስተን የተወያየንበት ጊዜ አልነበረም:: እርግጥ ካረፉ በኋላ ቀብራቸው እንዴት ይሁን የሚለው ጉዳይ ላይ ተነጋግረናል:: ለመሆኑ እሳቸውን የምንገለው ለምንድነው? ከሞቱስ በኋላ ቢሮዬ ሥር አርቄ ጉድጓድ ቆፍሬ የምቀብራቸው ተነስተው እንዳያንቁኝ ነው? መሐንዲስ የቀየሰው ፉካ ይሁን ጉድጓድ ወይም አላውቅም፣ ግምብ የማስራው እንዳይነሱ ነው? እኔኮ በጣም ነው የሚገርመኝ:: ደግሞ እኮ ሰው ይሄን እውነት ብሎ መቀበሉ::

*ገነት - አፅሙ ሲወጣ በቴሌቪዥን ታይቷል::*

**መንግሥቱ** - ያሳዩአ! ሊያሳዩ ይችላሉ:: ማሳየት ይችላሉ::

ገነት - ታዲያ የማን ሬሳ ነው የወጣው ከርስዎ ቢሮ ሥር?

መንግሥቱ - እንዴ፤ እዚያ አካባቢ ስንት መቃብር አለ:: የማንን እንዳወጡ? እኔ ምን አውቃለሁ ብዙ መቃብር አለ::

ገነት -ከቤተመንግሥቱ ሥር እኮ ነው የወጣው:: ከፅህፈት ቤትዎ ሥር::

መንግሥቱ - ተባለ:: ሰምቻለሁ:: ነገር ግን ዋናው ጥያቄ ቤተ መንግሥቱ ሥር የሚያስቆፍርና የሚያስቀብር ጉዳይ ምንድነው ነው? ሬሳው ተነስቶ እንዳይወጋን፣ እንዳይቃወመን ነው ወይ ነው ጥያቄው:: እኔኮ ግርም ያለኝ ሎጂክ ነው:: አንደኛ ነገር ያ የተባለው መሐንዲስ በወቅቱ እዚያ አልነበረም:: እስር ቤት ነበር:: ሁለተኛ ነገር ላንድ ሰው መቃብር መሐንዲስ የሚያስፈልግበት ምክንያት አይገባኝም:: ደግሞስ ለምንድነው እዚያ ሥር የሚቀበሩት? መሞታቸው በገሃድ ተነግሯል:: ‹በፍትሐትና በአገራችን የክርስቲያን ደንብ መቅበር ይፈቀድልን› ብለው ጥያቄ ላቀረቡት ፓትርያርክ ተገቢው መልስ ተሰጥቶ እኔ ራሴ «ከአቅሜ በላይ ነው» ብዬ መልስ ሰጥቻቸዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ግንብ ተገንብቶ፣ ፉካ ተሠርቶ፣ ሲሚንቶ ተደርጎ፣ መሐንዲስ ተፈልጎ የሚባ ለው ነገር ሲነገር በውነቱ በጣም አዝናለሁ::

እንዳው ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሰብ አይችልም ብለው ነው እንዴ ይሄ ሁሉ ቅጥፈት? እንኳን እንዲህ ያለ አይን ያወጣ ቅጥፈት፣ እኔን ለማስጠላት የተደረገ ይቅርና ስንቱን ተንኮል አይቶ የራሱን ግንዛቤ አንጥሮ የሚያወጣ ሕዝብ ነው:: ለምንድነው እንደዚህ የማደርገው? ምን ለማግኘት? ይሄ ወደፊት ታሪክ የሚገልፀው ነገር ነው:: ምናልባትም ታሪክ ይለወጥና ዛሬ እዚህ ያለን ሰዎች በሕዝብ መካከል እንገኝና «እስቲ የዐፄ ኃይለሥላሴን አፅም ያላችሁትን አምጡ:: እስቲ ያ መሐንዲስ ይምጣ:: መቼና እንዴት? በማን ትዕዛዝ ነው የቆፈረው?» የሚባልበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል:: ሊመጣ ይችላል:: እኔ መቼም በዚህ ረገድ ከምንም በላይ ደግሞ ያቺን የምወዳትን አገርና በጣም የምወደውና የማከብረውን ሕዝብ፣ አሁንም ቢሆን... ወያኔ በፈ ጠረው ቲያትር ውስጥ እዚህ ውስጥ ሕዝቡን መቀላቀል አልፈ ልግም::

ገነት - የጃንሆይን መኪናዎች እዚህ ሐራሬ አምጥተዋቸዋል ይባላል:: የት ናቸው?

መንግሥቱ - የማን መኪና?



ገነት - የጃንሆይ መኪናዎች::

መንግሥቱ - ጃንሆይ ምን መኪና አላቸው?

ገነት - እንዴ! የዱሮው ነዋ፤ እሳቸው ይሄዱባቸው የነበሩት ቤተመንግሥት የነበሩት መኪናዎች

መንግሥቱ - እንዴ! የቤተመንግሥቱ መኪና እዚያው ቤተመንግ ሥት አይደለም እንዴ? እኛ እንገለገልበት የነበረውን ነው የምትይው? እይው ልንገርሽ:: ጃንሆይ ይሄዱባቸው ከነበሩት አንድ አሮጌ የአሜሪካን ሾቭረሌት ነበረች:: ሌላ ደግሞ በጣም የወደቀች የእንግሊዝ መኪና - እሷውም አትሠራም:: ሁለቱም እዚያው ግቢ ነበሩ:: ሌሎች የቤተመንግሥቱ መኪኖች አሉ:: አሁን መለስ የሚሄደው በምንድነው? ሐራሬ ደግሞ መኪና እንዴት አድርጌ ነው ጭኜ የመጣሁት ልጄ? በምንድነው ሐራሬ ድረስ የሚመጣው?

ገነት - አስቀድመው ባውሮፕላን ማስጫን አይችሉም?

መንግሥቱ - ምን ማስረጃ ይዘሽ ነው እንደዚህ የምትይው?

ገነት - በጄ ማስረጃ የለኝም::

መንግሥቱ - ታዲያ ወሬ ነው?

ገነት - እና መኪና አላመጡም?

መንግሥቱ - ው ... ሸት ነው:: ጄኔራል ፍሬሰንበትን ጠይቂ:: ‹የጃንሆይን ውሾች ወሰዱ› ተብለናል:: እኛ ቤት የነበሩ ውሾች የልጆ የትዕግሥት ናቸው::እነሱንም ደመቀ ባንጃው ነው ከድሬዳዋ ያመጣላት::

ገነት - ሐምሌ፣ 1968 በተረሸኑት የደርግ አባላት በነሻለቃ ሲሣይ ሀብቴ ተጀምሮ በነሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌና ሞገስ ወልደሚካኤል የቀጠለው እርስዎን ከሥልጣን የማገለል ሙከራ ግቡን ሊመታ ትንሽ ሲቀረው ከሸፈ:: እንደሚያስታውሱት ደርጉን እንደገና ለማዋቀር በወጣው እቅድ እርስዎ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢነቱን ብቻ ሲይዙ የተቀረው ሥልጣን በሙሉ ለጄኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ለሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌና ለኮሎኔል አጥናፉ አባተ ተሰጥቶ ነበር:: በዚህም ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ርዕሰ ብሔርነቱን፣ የጦር ኃይሎች አዛዥነቱንና ሌሎቹንም የርስዎ የነበሩትን ሥልጣኖች ደርበው ሲይዙ፣ ሻምበል ዓለማየሁ ደግሞ የደርጉ ዋና ፀሐፊ በመሆን ትልቅ ኃላፊነት ሲሰጣቸውና ኮሎኔል አጥናፉም እንደዚሁ የሕዝባዊ ሠራዊቱን የማደራጀትና የመሳሰለው በእጃቸው ሲገባ ታስቦ ነበር:: በአንፃሩ የርስዎ ሥልጣን መቀነስ ብቻ ሳይሆን ደጋፊዎችዎም በሥራና በትምህርት ስም ወደውጪና በየክፍለሃገሩ እንዲሄዱ

*ታቅዶ ነበር:: በመጨረሻ ጥር፣ 1969 ታሳቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ ተኩስ ተከፍቶ ተቀናቃኝም የነበሩት በአብዛኛው ተገደሉ:: እስቲ ስለዚህ ትንሽ ይንገሩኝ::*

***መንግሥቱ*** - በዚያን ወቅት የሆነው እንደዚህ ነው:: ደርግ ሁሉን ነገር የሚወስነው በጠቅላላ ጉባኤ ነበር:: የድርጅት ጽህፈት ቤትና የፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን ለማቋቋም አስበናል:: ‹ፓርቲው እንዴት ይፈጠር?› ለሚለው ዕቅድ ነድፈናል:: ደርግ ከሞላ ጎደል አንድ ቦታ ተሰብስቦ የሚሰጣቸውን ጠቅላላ ውሳኔዎች ጨርሰናል:: መሠረታዊና ዋና፣ ዋና የሆኑትን አብዮታዊ ርምጃዎች ከወሰድን በኋላ ያንን በሥራ ላይ ማዋልና ከሕዝቡ ጋራ በቅርብ ተሳስሮ የአብዮቱን ደህንነት እየጠበቁ ቀሪ ሥራዎቹን የማራመዱ ጥያቄ የሚለው ላይ ነበርን:: ከሁሉ በፊት የሕዝብ ድርጅት ጽህፈት ቤትን ፈጥረን ቀጠናዊ የሆነ የድርጅቶች መዋቅር ስንዘረጋ፣ የሌላ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያቋቁሙ ብቻ ሳይሆን ደርግም በበኩሉ ከነሱ ጋር ተቀናጅቶ የፖለቲካ ሥራ መሥራት እንዲችል ነው::

ለዚህ ሁላችንም አዲስ አበባ መሰባሰባችን ቀርቶ የሥራ ክፍፍል ወጥቶ በየገጠር መሄድ አሰብን:: በክፍለ ሃገር፣ በአውራጃ፣ በወረዳ ሥራ የምንከፋፈልበትን መንገድ ፈጥረን በየዘርፉ የራሳችንን ሚና የምንጫወትበት መንገድ መፈጠር አለበት:: ከተቀሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሕብረታችንን የምናጠናክርበትን መንገድ ለመፈለግና እንደደረስንበት የእድገት ሁኔታ አሠራራችንን ለመለወጥ ነው::ይሄንን ሃሳብ በደርግ ስብሰባ ላይ ያቀረብኩት እኔ ነኝ እንጂ እነሱ አልነበሩም:: ችግሩ በተሰብሳቢዎች ዘንድ በከፊል ግንዛቤ ሊያገኝ አልቻለም:: የንቃት ማነስ ጉዳይ ነው:: ሰውዬው ሃሳቡ እኛን በየገጠሩ ለማባረር ነው የሚል ስሜት አድሮባቸዋል::

እስካሁን እንግዲህ ሁሉም ነገር በደርጉ ጠቅላላ ጉባኤ ነው የሚወሰነው:: ‹እዚህ ቁጭ ብለን መወሰን ቀርቶ ሥልጣኑን ለሱ ሰጥተን ልንሄድ ነወይ?› የሚል ሃሳብ ነው የመጣባቸው:: ሌሎች ደግሞ ‹እዚህ ታጉረን የምንቀመጠው ለምንድነው? የመሬት አዋጅ አውጀናል:: የጭቁኖች መብት ተከብሯል:: አስተዳደራዊ መዋቅሮች አውጥተናል:: ባንድ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ሊሆኑ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ በሕጋዊ መልካቸው ታውጀዋል:: አሁን እዚያ ቦታው ላይ ተገኝቶ ወደተግባር የሚተረጉማቸው ኃይል ያስፈልጋል::



ሌላ ሰው በውክልና ልከን አብዮቱን ማራመድ አንችልም:: በቦታው ላይ መገኘታችን ወሳኝነት አለው› የሚሉ ተራማጆች ነበሩ::

ይሄንን ለምን እንደምናደርግ ዝርዝር አድርጌ አስረዳሁ:: አብዛኛዎቹ ገብቷቸው አመኑበት:: በመሐከላችን የተሰገሰጉት እነዓለማየሁ ኃይሌን የመሳሰሉ የኢሕአፓ ሰዎች ግን አልዋጥላቸው አለ:: ከዚያ ቀደም ሲል ተወያይተንበት ተስማምተን አብረን የነደፍነው ሃሳብ ነው:: «ሕዝቡ ውስጥ እንግባ» የሚለውን ነገር በመርሕ ደረጃ ተቀብለውት ነበር:: በኋላ ግን ነገሩን ሲያሰላስሉት የሚሰጠውን ውጤትና አዝማሚያውን ሲመለከቱት ነገሩ ግልጽ በሆነበት ጊዜ ‹መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ያለተቀናቃኝ ሥልጣኑን ሊይዝ ነው:: ሲያባርራችሁ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ እንዴ?› የሚል ቅስቀሳ ጀመሩ:: ቅራኔ እንዳይፈጠር ያላደረጉት ነገር የለም:: ከዚያ ቀጠል ያደርጉና ‹ሌላ ለውጥ የሚያስፈልገው ነገር አለ› ብለው ተነሱ:: ‹ሥራና ኃላፊነት ተሰባስቦ መንግሥቱ ኃይለማርያም እጅ ገብቷል::የሱ ሥራ ተከፋፍሎ ለሌሎች ሰዎች መሰጠት አለበት:: ጄኔራል ተፈሪ ሊቀመንበርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ተብለው ቁጭ ብለዋል:: ባሁኑ ሰዓት እሳቸው አሻንጉሊት ናቸው:: ሥልጣኑ ሁሉ ያለው መንግሥቱ ኃይለማርያም እጅ ነው:: ስለዚህ እሳቸው እውነተኛ ሊቀመንበር መሆን አለባቸው:: ርዕሰ ብሔርነታቸው በሕግ መረጋገጥ አለበት::ሁለተኛ ነገር መንግሥቱ ወይ የጠቅላይ ሚኒስትር ቦታ መያዝ አለበት ወይም የደርግ ምክትል ሊቀመንበር ይሁን እንጂ ሁሉ ቦታ እሱ ብቻ መሆን የለበትም› አሉ:: ባጭሩ መንግሥቱ አሁን የሚያራምደውን ሁሉ ከማድረግ ይገታ ማለታቸው ነው:: ይሄንን የምትለው እንግዲህ ኢሕአፓ ነች:: እነዓለማየሁ መሐከላችን ቁጭ ብለው የኢሕአፓ አባላት ኖረዋል::

የኔ ደጋፊዎች የሆኑት ደግሞ «እንደዚህ ያሉ ቁልፍ ቦታዎች በእጁ እንዲሆኑ እምነት የምንጥልበት ሰው መንግሥቱ ኃይለማርያም ነው:: ጠሩ እምነት ያሳደረው በሱ ነው:: አብዮቱ አልጠነከረም:: እኛ የግቢውን ጦርም ሆነ የሌላውን ጦር አዛዥነት ከመንግሥቱ ሌላ አምነን የምንሰጠው ሰው የለም:: ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሄደው እዚያው ይቀመጡ እንጂ ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ከኛ ሌላ ማን እንዲሠራው ነው? የኛን ጣጣና ችግር ሁሉ ማን እንዲያየው ነው? በሌላ በኩል ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ አንዳንድ ነገር ለማስፈፀም እስከፈለግን ድረስ በደርግ ውስጥ የተወሰነው ደግሞ እዚያ በተግባር ላይ መዋሉን ለመቆጣጠር አልፎ

አልፎም ቢሆን ስብሰባውን መካፈል ያስፈልጋል:: በእንዳልካቸው ካቢኔ እንኳን የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ስብሰባ እንካፈል ነበር:: ይሄ ምን ያስከተለው አፍራሽ ነገር አለ?!» አሉ::

አሁን እንግዲህ ተከፋፈልን:: ቅራኔው ሰፋ::ኩዴታ ነገር እንዳሰቡ ግልፅ ነው:: የነዓለማየሁ ቡድን እኛን ሊመታ ተዘጋጅቷል:: እኛም ራሳችንን ለመከላከል መፋጠጥ፣ መጠባበቅ ሆነ:: እነዓለማየሁ ይጠባበቁናል:: እኛም እንደዚያው:: በፊት ደርግ ስብሰባ ላይ መሣሪያ መታጠቅ ትተን ነበር:: አሁን መሣሪያ እየያዙ መምጣት ጀመሩ:: ውጥረት ሰፍኗል:: ጥያቄው ማን ነው የሚቀድመው የሚል ሆነ:: ለማንኛውም አንድ ነገር ቢፈጠር አልንና ለጥበቃው ክፍል ማን ከማን ጋር እንደ ሆነ የሚገልፅ የስም ዝርዝር ሰጥተን ነበር:: እነከሌ፣ እነከሌ የኛ ጎራ ውስጥ ናቸው:: እነከሌ እነከሌ ደግሞ የዚያ ጎራ ናቸው የሚል ነበር::

ከዚያ ጥቂት ቀደም ሲል የእድገት በሕብረት ዘመቻ ኃላፊ ሆኖ የተመደበው ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁን (የደርግ አባል አልነበረም) ስንገመግመው ለአብዮቱ ታማኝ ሆኖ አላገኘነውም:: በተማሪዎቹ አኳያ የሚከናወኑት የፖለቲካና ድርጅታዊ ሥራዎች አጥጋቢ ስላልሆኑና የሚፈጠሩ ችግሮችን በሚገባ ካለማስተናገድ የተነሳ ከተማሪው ጋር ቅራኔ ውስጥ እንድንገባ ምክንያት ሆኖ ነበር:: በዚህ ምክንያት ንቃት ያለው ታማኝ የሆነና ፖለቲካዊ መሥመራችንን በሚገባ የሚያራምድ፣ ተማሪውን በእርጋታና በመግባባት ወደኛ የሚያመጣ ሰው ያስፈልጋል ተብሎ ጓድ ፍቅረሥላሴን እዚያ መድበነው እድገት በሕብረት ዘመቻ መምሪያ ውስጥ ነበር የሚሠራው::

ፍቅረሥላሴ ሥራ ስለሚበዛበት ከኛ ጋራ የሚሰበሰብበት ጊዜ እያነሰ መጥቶ በጣም ትልቅና ወሳኝ የሆኑ ስብሰባዎች ሲደረጉ ብቻ ነበር የሚመጣው:: የዚያን ዕለት ለስብሰባ ቤተመንግሥት መጥቷል:: ግን ለጥበቃ ክፍሉ በሰጠነው ሊስት ውስጥ በሁለቱም ጎራ ውስጥ ስሙ የለም:: ወታደሮች የሚረሽኑትን መጥተው ሲወስዱ የሱን ስም ከኔ ወገኖች ዝርዝር ውስጥ ስላላገኙት ከሌሎቹ ጋር ቀላቅለው ወስደውት ከሚገደሉት ጋራ አብሮ ምድር ቤት ገብቷል:: በውነቱ ያዳንኩት እኔ አይደለሁም:: ኰሎኔል ዳንኤል ነው:: እዚያ ውስጥ ሲያየው ስሙ የለም:: እዚህ ውስጥም ሲያየው የለም:: እየሮጠ መጣና ‹ጓድ ፍቅረሥላሴ ከማን ጋር ነው?› አለኝ:: «እንዴ! ከኛ ጋራ ነዋ!» አልኩት:: ‹በስሕተት እዚያ ገብቷል› ብሎ በሩጫ ሄዶ አወጣው:: ዳንኤል



ጠንቃቃና ብልህ ሰው በመሆኑ መጥቶ ባይጠይቀኝና ዝም ብሎ አብሮ ቢመታው ኖሮ ፍቅረሥላሴ አልቆለት ነበር::

ሻለቃ ዮሐንስ የሚባለው በደርጉ ደህንነት ውስጥ የሚሠራ የፖሊስ መኰንን የኢሕአፓ አባል ነበር:: እሱ ከኛ ጋር ከነበሩት ውስጥ ዶክተር ሰናይ ልኬንና ኰሎኔል ዳንኤልን ገደላቸው:: ከነሱ ወገን ደግሞ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ፣ ሻምበል ተፈራ ደነቀ እና አንድ አሥር አለቃ ኃይሌ በላይ የሚባል በጠቅላላው ሰባት ሰዎች ተረሸኑ:: ሌላ የደርግ አባል ሙሉጌታ የሚባል ነበረ:: እሱም እንደዚሁ የኢሕአፓ አባል ነበር:: እኛን ለመግደል ካሴሩት ወገን ሆኖ ሳያውቀው በድንገት ነው ወደምዕራብ አፍሪካ እንዲሄድ ሚሽን ተሰጥቶት የሄደው:: ሲመለስ ተረሽኗል:: የተቃዋሚዎቹ ደጋፊ ነበር::

***ገነት*** *- «ለምሳ ሲያስቡን ቁርስ አደረግናቸው» ያሏቸው ናቸው?*

***መንግሥቱ*** - ባንቀድማቸው ኖሮ በነሱ ቦታ እኛ እንሆን ነበር::

# ቀይ ሽብር

***ገነት*** *- ወደ ሌላ ጥያቄ እናምራ:: ቀይ ሽብር እንዴት ተጀመረ? ማን ጀመረው?*

***መንግሥቱ*** - ባሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች ስለቀይ ሽብር እንጂ ስለነጭ ሽብር ማንሳት አይፈልጉም:: እኔ ስለሁለቱም መናገር እፈልጋለሁ:: የነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር ታሪክ ከኢትዮጵያ ግራ ኃይሎች ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ከየካቲት፣ 1966 በፊት በተማሪው ማህበር ውስጥ ወጣቱ የሃገር ውስጥና የውጪ ሃገር እንቅስቃሴ በማድረግ በመጠኑ ያደረገውን አስተዋፅዖ ብጠቅስ ጠቃሚ ይመስለኛል::

የ1953 የነጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ የዐመፅ ሙከራ (ሌሎች ሕዝብ ሳያውቃቸው የተዳፈኑ ሙከራዎች ቢኖሩም) በገሃድ ሕዝብና ወታደር ተንቀሳቅሶ በግልፅ የኢትዮጵያን ፊውዳል ሥርዓት ገበና ዘክዝኮ በማውጣት የዐፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት የተዳፈረበት የመጀመሪያው ክስተት ነበር::

ጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ ሠራዊቱን ማንቀሳቀስ እንደጀመሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ለውጥ ፈላጊነት ስለሚያውቁ በሳቸው ካምፕ ውስጥ እነሱንም ለማካተት ቀርበው አነጋገሯቸው:: ‹እኛ የተነሳሳነው ለግል ጥቅም ሳይሆን የሃገራችንን ሁኔታ አሳስቦን እንጂ ለራሳችን ሕይወት ተንደላቀን የምንኖር ሰዎች ነን› በማለት ያንን ተማሪ በነበረው

የሃገር ፍቅር ስሜትና ትኩስ ኃይል ቀስቅሰውት ነበር:: ተማሪው መሣሪያ የታጠቀ ባይሆንም ለለውጡ ድጋፉን ሰጥቷል:: በዚህም በንጉሡ ዘንድ ጥላቻን አትርፏል::

እነጄኔራል መንግሥቱ ባደረጉት ሙከራ ግባቸውን ሳይመቱ ቀርተው መሥዋዕትነት ቢከፍሉበትም ድካማቸው ፍሬ አልባ ሆኖ አልቀረም:: የታህሣሡ እንቅስቃሴ ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ሕዝብም ዓይን መግለጫ ሆኖላቸዋል:: ‹ለካ የኃይለሥላሴ መንግሥት ይደፈራልና!› የሚለውን ሃሳብ በሕዝቡ አእምሮ አስርፆ አልፏል:: ይሄን ማስታወስ እፈልጋለሁ::

የተማሪው እንቅስቃሴ እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው እየጎለበተ የመጣው:: ተማሪው በማህበር ተደራጅቶ በመንቀሳቀስ የማርክሲዝምን ጽሑፎች በማጥናት የዓለም አብዮቶችን ጅምርና ሂደት፣ ያሉበትን ሁኔታና ፋይዳ መገንዘብ ጀምሮ ነበር::

በዚህ ዓይነት በውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ቅስቀሳዎች አብዛኛው ተማሪ ሥርዓቱን በግልፅ መቃወምና የመሬት ላራሹንና ሌሎች የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን ማንሳት ያዘ:: በዚህን ጊዜ ከሕዝብም ዘንድ ድጋፍና ተደማጭነትን ማግኘት ጀመረ:: እነኚህ ወጣቶች ሁሉንም ገላልጠው አደባባይ የወጡት ቢሮክራሲው ውስጥ ተሰግስጎ በአድርባይነት የራሱ ግላዊ ፍላጎት መሟላቱን የሚከታተለው ንዑስ ከበርቴ አድፍጦ በተቀመጠበት ጊዜ ነው:: በፀረ-ፊውዳልና በፀረ-ኃይለሥላሴ ትግል የተጀመረው ነገር ቀስ በቀስ የተለያየ ቅርፅና ይዘት እያየዘ መጣ:: ባንድ በኩል በጣም ግራ ቀደምና ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም ተከታይ የሆኑ ወጣቶች ተፈጠሩ:: ወደግራ አስተሳሰብ ተማሪው እንዲያዘነብል የማድረግ ኃይላቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ ጠንክሯል:: ተማሪዎች በግራ ቀደምት ኃይሎች ደጋፊነት በአንድ ወቅት በሶቭዬት ውስጥ ከፍተኛ ጭቅጭቅና ሽኩቻ ያስከተለውን «የራስን ዕድል በራስ የመወሰን» ጥያቄ ይቀሰቅሳሉ::

በሌላ በኩል የብሔረሰብ ጥያቄን በመደብ ትግል ከመፍታት አኳያ ራሱን የቻለ ቀዳሚ ነገር አድርገው ያነሳሉ:: ይህንንም የሚያራግቡት «የራስን ዕድል በራስ መወሰን» የሚለው ጥያቄ የተማሪውን ትግል የሚከፋፍልና የሚያዳክም፣ የኤርትራንም መገንጠል የሚያበረታታ ነው ከሚል ሃሳብ ተነስተው ነው:: ይህንን ተንኩል የነቁበት ክፍሎች ‹ይህ ጥያቄ ተማሪውን ይከፋፍላል› ብለው ሲቃወሙት፣ ሌሎች ደግሞ ‹የለም ትክክለኛ መርህ ነው› በማለት ይሰለፋሉ:: ይሄ ብቻ ሳይሆን ያንን ያለሙትንና የሚመኙትን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ ሲነሱ የኤርትራ ተወላጅ የሆኑት የለየለት ግልፅ የመገንጠል አቋም ይዘው ባንድ ጎራ ይከታሉ:: ወያኔዎቹም ‹ትግራይን ነፃ እናደርጋለን› በማለት ሌላ ጎራ ይይዛሉ:: ኦሮሞቹም እንደዚሁ:: ኦሮሞዎቹ ስል፣ የኦሮሞን ሕዝብ ሳይሆን አወቅን፣ ነቃን ብለው ሊነግዱበት የተነሱት ደካማ ፍጡራንን ማለቴ ነው::



የቀሩት ከብሔረሰብ አመለካከትና የክልል ጠባብነት ውጪ ብሔራዊ የሆነ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ናቸው:: የነሱ አካሄድ ሥር ነቀል የሆነ አብዮታዊ ለውጥ ያስፈልጋል የሚለው ነው:: ጉልታዊው ሥርዓት መወገድ እንዳለበት ሲያምኑ ይሄንን በተግባር ለመተርጎም ከፖለቲካና ከወታደራዊ ስልት አኳያ፣ እንዲሁም ደግሞ ከተማሪዎቹ ሥነ ልቦና ሁኔታ በነበረው ልዩነት ወደድርጅታዊ ዘርፍ ሲመነዘር ኢሕአፓና መኢሶንን ይወልዳል::

የተቀረው፣ ተማሪው ደግሞ ‹ጠቅላላ የኢትዮጵያን አብዮት አቀጣጥሎ አንድ መሪ ድርጅት ተመሥርቶ በዚያ መሪነት ትግሉን ደረጃ በደረጃ በማካሄድ አቅጣጫ ከመያዙ በፊት ከፊረሱ ጋሪውን በማስቀደም በጣም መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች በመጀመሪያ ሊነሱ አይገባም:: እነኚህን ጥያቄዎች ወደሕዝቡ መወርወር ለገንጣዮችና አገሪቱን ለመበተን ለተነሱ ኃይሎች መሣሪያ መሆን ነው› ብሎ ይቃወመዋል:: በአውሮፓና በአሜሪካ የነበሩት የተማሪው እንቅስቃሴ አባላትም በዚህ የተለያየ አቋም በመያዝ የነዚህን ሁለት ድርጅቶች አስኳል ይፈጥራሉ::

ሌላውም በያለበት እንዳቅሙ ይንቀሳቀሳል:: ሁሉም እንዳቅሙ የፖለቲካ ቡድን አይሉት፣ ምን አይሉት ፕሮግራምና ርዕዮተ ዓለም የለው፣ እድር አይሉት፤ብቻ የየራሱን ቡድን ያቋቁማል:: ትግሬው፣ ኦሮሞው፣ አማራውም:: ለምሳሌ፣ የጎንደር ቡድን፣ የጎጃም ቡድን፣ አደሬ፣ አፋር እየተባባሉ እንዳቅማቸው ዳከሩ:: ሁሉም በየፊናው አንዳንድ ነገር ለመወጠን ይሞክር ነበር:: ይሄ በጉልህ የአገሪቱን የወደፊት ሁኔታና የወደፊት እድል አሳሳቢነት አንፀባርቋል::

አብዮቱ ሲፈነዳ ከወሰድናቸው ቀዳሚ ውሳኔዎች አንዱ የፖለቲካ እስረኞችን መልቀቅና በፖለቲካ ምክንያት ከሃገራቸው ወጥተው በስደት የሚንከራተቱ ኢትዮጵያውያን ያለምንም ሥጋት ወደአገራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግ ነበር:: ከዚያ ሌላ የጀመርነው አብዮት ከተሳካ ተሳካ ባይሆንልን ግን ይሄንን እንኳን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አድርገን እንለፍ ብለን ቅድሚያ የሰጠነው የመሬትን ጥያቄ ነው:: ገና አራተኛ ክፍለ ጦር እንደገባን ወዲያውኑ የመሬት ጥናቱ ተገባዶ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት ማድረግ አለብን እያልን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተነዋል:: ምንም ዓይነት አገልግሎትና ኢንዱስትሪ ባልተስፋፋበት ኢትዮጵያን በመሰለ አገር ውስጥ የመሬት ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ነው::ያንን ለመመለስ አቋም መያዝ የወቅቱ ጥያቄ ነበር::

ለረጅም ጊዜ ‹መሬት ላራሹ!› እያለ ሲወተውት የነበረውን ወጣት ሰብስበን ከመምህራንም፣ ከሠራዊቱም የተጣመረ ኃይል በኢትዮጵያ የተለያዩ ክፍሎች ሄዶ ሲያበቃ ገበሬውን እንዲያነቃና እንዲያደራጅ የመሬት አዋጁን ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስተባበር አለብን ብለን ተነሳን:: በመንግሥት በኩል በኃላፊነት ላይ የነበርነውን ሁሉ የሚያስጨንቅ ሁኔታ ነበር:: አንዳንዶቹ ‹እነኚህ ልጆች ሄደው ገበሬውን ቢያ

ሳስቱ፣ ለዐመፅና ለሽብር ቢያዘጋጁት፣ ያሻቸውን ቢያደርጉ፣ ኃላፊነቱ
የማነው? እነሱ የሚነግሩትና የሚያንቆረቁሩለትን ሁሉ ተቀብሎ
መልሶ ቢያስተጋባ ለዚህ መልሱን የሚሰጠው ማነው?› የሚል ነገር
አነሱ:: ይሄ ሁሉ ከሥጋት የመነጨ ነው:: ሌሎቻችን ደግሞ፣ «ፍላጎ
ታችን ገበሬው እንዲያውቅና እንዲነቃ ነው:: ስለጠየቀ፣ ስለነቃ ደግሞ
የሚያስከትለው አደጋ የለም:: ተገቢውንና የሚያረካውን መልስ መስ
ጠት መቻል አለብን» እንላለን:: በዚህ ዓይነት ተማሪው ወደገጠር
ዘመተ:: ከዚያ በኋላ የሆነው ሁሉ የሚታወቅ ነው::

ለነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች ሲታገል የነበረው ወጣቱ የሕብረ
ተሰብ ክፍል ምኞቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህ የተሻለ ጊዜ አይገ
ኝም በሚለውና ይሄንን በሥጋት በሚመለከቱ ወገኖች መካከል የተደረ
ገው ሙግት እንዲህ ቀላል አልነበረም:: ይሄንን መላው የደርግ አባላ
ትና የአካባቢ አባላትም ስለደገፉት፣ ያው ሥምሪቱ ቀጥሎ የማይናቅ
አስተዋፅዖ አደረገ:: በዚህ ሂደት ግን እነኚህ የራሳቸው የብሔረሰብ
ዓላማ ያላቸው ከኛ የተለየ ፖለቲካ የሚያራምዱ ቡድኖች ጭምር
በሙሉ ስለተሠማሩበት እግረ መንገዳቸውን በሕብረተሰቡ ውስጥ
ለመስረግ ሁኔታው ተመቻችቶላቸዋል::ባገኙት አጋጣሚ በመጠቀምም
ሕብረተሰቡንም ወደሽብርና ሥርዓተ አልበኝነት በሚያመራ መልኩ
ሊቀሰቅሱት ሞከሩ::

እዚህ ላይ የረዳን ነገር ቢኖር የሕዝቡ እርጋታ፣ ብስለትና ትዕግ
ሥት ነበር:: ከዚህም በላይ መለዮ ለባሹና አብዮታውያን በመተባበር
ንጉሡንም፣ጉልተኞችንም አስወግደው እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ ብስራት
ለማብሰር በመብቃታቸው ፅኑ እምነት አሳድረው ነበር:: በዚህ ምክ
ንያት ብዙም ባይቀበሏቸውም ሕዝቡን አብዮታዊ መንግሥት ላይ
በማስነሳት የራሳቸውን ፖለቲካዊ መሠረት ለማስፋት የተደረገው
ጥረት ሌላው የወቅቱ ክስተት ነበር:: በዚህ ዓይነት ነው ኢሕአፓ
ባጭር ጊዜ ውስጥ እየተስፋፋች ወጣቱን፣ የተወሰነ የምሁራኑን
ክፍልና ገበሬውንም ወገኗ ልታደርግ የሞከረችው:: መኢሶንም እን
ደዚሁ ለማድረግ ሞክሯል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ሌሎችም የፖለቲካ
ቡድኖች ተፈጠሩ:: የወዛደር ሊግ፣ አብዮታዊ ሰደድ፣ የኢትዮጵያ
ጭቁኖች አንድነት (ኢጭአት) የሚባለው ቡድን እነኚህ ሁሉ ተፈጠሩ::
ሁሉም ‹ፀረ-ፊውዳል ፀረ-ኤምፔሪያሊስት ፀረ-ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም
የሚለውን ፕሮግራም እንቀበላለን› አሉ::

እንግዲህ ይሄንን እስከተቀበሉ ድረስ በፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔ
ሪያሊስት ግምባር ተሰባስበን ስናበቃ አብዮቱን በጋራ እናራምድ የሚል
ጥሪ በኛ በኩል ተደረገ:: ግልፅ በሆነ መልኩ የፕሮግራሙ ብስራት
መሠረት ተደርጎ እኔ ወጥቼ ለመላው የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች፣
ለገንጣዮችም ሳይቀር ዝርዝር ባለና ፍርጥርጥ ባለ ሁኔታ አስረድቼ
ጥሪ አስተላለፍኩ:: የዘመናት ታሪክ ዳስሼ፣ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና
ጉልታዊ ሥርዓት የፈጠራቸውን ሁኔታዎች ለማስወገድና በአንድነት
ለመሥራት የኢትዮጵያ ተራማጆች እንሰባሰብ የሚል ጥሪ ነበር::



ጥሪዬ አዎንታዊ ምላሽ አግኝቶ መኢሶን፣ ወዝ ሊግ፣ ኢጭአት፣ አብ
ዮታዊ ሰደድ፣ እነሽመልስ ማዘንጊያ የነበሩበት ኢኮፓ፣ እንዲሁም
የአፋር ነፃ አውጪ ንቅናቄ ጥሪውን በመቀበል መጡ:: አንዳንድ ግለሰ
ቦችም አብረውን ለመሥራት መጥተዋል::

የኤርትራን ችግር በተመለከተ ተጨባጭ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግ
ራም አውጥተናል::«ከግለሰብ፣ ከቤተሰብ፣ ከብሔረሰብ ሽኩቻ አገሪቱን
ነፃ የሚያደርግና ከተራማጅ ዓለም ጋር የሚያሰልፈን ተራማጅ የሆነ
የእድገት አቅጣጫ ቀይሰናል:: በእርግጥ በሥርዓቱ ላይ ጥላቻ ያላቸ
ውና ለኢትዮጵያ በጎ ሃሳብ ያለን ነን የሚሉ አብዮተኞች ካሉ ሠልፋ
ቸውን ማስተካከል ያለባቸው ዛሬ ነው» ብለን ለሠላም እጃችንን ዘረጋ
ንላቸው:: የሰሜነኞቹ ምላሽ አሉታዊ ነበር:: ‹እኛ ኢትዮጵያውያን
አይደለንም:: የራሳችንን አብዮት ስናካሂድ ቆይተናል:: የናንተ አብዮት
እኛን አይመለከተንም:: አብዮተኞች ነን ካላችሁ የራስን ዕድል በራስ
የመወሰን መብት የሚለውን አክብሩና ነፃነታችንን አስረክቡን› የሚል
ነበር::

ሌሎቹ ግን ክሪቲካሊ አንዳንድ ሃሳቦቻቸውን በነፃነት ለማቅረብና
ውስጣዊ ድርጅታቸው ነፃነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሞላ ጎደል ለአብዮቱ
ድጋፍ የመስጠት አዝማሚያ ስለታየ ከደርግ ጉባኤና ከሚኒስትሮች
ምክር ቤት መክረን በተሰጠን ማንዴት እኔ፣ ልጅ ሚካኤልና አንድ
የደርግ አባል መኮንን ሆነን ባልሳሳት ወራቶች ያስቆጠረ ኢንተርቪው
አደረግን:: እያንዳንዱን ሰው ከውስጥም ከውጪም እየጠራን በግል
አነጋግረናል::

ከዚያ በኋላ እኔ የመራሁት ስብሰባ ተካሂዶ «ፕሮግራማችን ይህን
ይመስላል:: ዓላማችን ይህ ነው:: ያለንበት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግር
ይሄ ነው:: ‹ድር ቢያብር፣ አንበሳ ያስር› እንደሚለው እንዳው ሁላች
ንም በየፊናችን የመሰለንን ነገር ይዘን ከመሮጥ ኃይላችንንና ችሎታች
ንን አስተባብረን የኢትዮጵያን ሕዝብ በእግሩ ማቆምና በአንድ አቅጣጫ
መጓዝ የወቅቱ ጥያቄ ነውና ይሄን እንዴት ትመለከቱታላችሁ» አል
ኳቸው::

በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ቅድመ ሁኔታዎችን በማቅረብ አቀራረ
ቡን በጎ በሆነ መንገድ ተቀበሉት:: ብዙ ጥያቄዎችን አቀረቡልኝ:: ብዙ
ተፈታተኑኝ:: በውነቱ በቂ ዝግጅት፣ ጥናትና መሠናዶ ስለነበረኝ እኔን
ምንም የገደደኝ ነገር አልነበረም:: እነሱ ስለኔ የነበራቸውን አስተያየ
ትና አስተሳሰብ ፍፁም ነው የቀየርኩት፤ እንዲያምኑ ያደረግሁት::

በዚህ ዓይነት አምስቱ ድርጅቶች ፈቃደኛ ሆኑ:: ሁለቱ የብሔ
ረሰብ ድርጅቶች በፓርቲ መልክ ራሳቸውን ባይለውጡም መስለው
ቀረቡ:: የአፋሩና የኦሮሞው ማለቴ ነው:: እነኚህን ማሰባሰብ ቀላል
አልነበረም:: ትልቅ ድል ነበር:: የኤርትራዎቹን ግን መሳብ አልተቻ
ለም:: እነሱ ነገሩን ያዩት በተለየ መልኩ ነው::

የነሱን ይሁንታ ካገኘንና የሰዎቹን ብስለትና ንቃት፣ ያላቸውን
ያመለካከት ኮሚትሜንት ከተገነዘብን በኋላ ከዚህ ውስጥ ከብዙ ሰዎች

መካከል የመረጥናቸውን ሰዎች እንዴት አድርገን እናሰባስብ? እንግዲህ ድርጅት ለድርጅት በመቀራረብ፣ በመወያየትና በመተማመን እንደጠየቁትም የራሳቸው ውስጣዊ የድርጅት ሕልውና እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮግራሙም መድብለ ፓርቲን የሚፈቅድ ሆኖ፣ ግን ያ መድብለ ፓርቲ እርስ በርስ ተቃራኒ ሳይሆን አንዱ የአንዱ ደጋፊ ሆኖ በዓላማ ግምባር ይፈጠር?እንድ ምን ዓይነት ነገር እናድርግ? የሚል ውይይት ለብቻችን አደረግን::

እኔ የታየኝ ነገር ቢኖር ለምን ጊዜያዊ ሕዝባዊ ድርጅት እናቋቁምም የሚል ሲሆን፣ ይሄ እንግዲህ የመጣው ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ ብለን ካቋቋምነውና ኃይለሥላሴ ከሰየሙት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ውድቀት በኋላ በተተካው ሸንጎ ዓይነት አሁንም ደግሞ «ጊዜያዊ የሕዝብ ማንቂያና ማደራጃ ተቋም» ብለን በሕግ የሆነ ተቋም ከፍተን ባንድ በኩል የሕዝብ ማንቂያ ተቋም መሥርተን የሕብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች እየመጡ የፖለቲካ ትምህርትና ንቃት የሚያገኙበት፣ ሁለተኛ ነገር ደግሞ በዚህ ብቃት ያላቸው ምሁራን መድረክ ይዘው ሲያበቁ ንቃት የሚሰጡበት፣ ደግሞ ሕዝቡ የፖለቲካ ባህሉን እንዲያዳብር፤ አብዮት ማለት ምን ማለት ነው? የመደብ ትግል ማለት ምን ማለት ነው? ኢምፔሪያሊዝም ምንድነው? ሥር ነቀል ለውጥ ማለት ምን ማለት ነው? ወዘተ በማለት ብሮሸሮችና ጽሑፎች እየጎረፉ በመንግሥት የሥራ ጊዜ ሕዝቡ እየተሰባሰበ የውይይት ክበቦችን አቋቁሞ እንዲወያይበት፣ ጋዜጦች ይሄን እየተቀባበሉ በማስፋፋት የሕዝቡን ንቃተ ህሊና የሚያዳብሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ነበር:: ከዚያ በተጨማሪ ተራማጆች በሃገሪቱ ክልሎች ተሠማርተው በገፅ እየቀረቡ ትምህርትና ንቃት የሚሰጡበት፣ የሚያደራጁበት፤ በአንፃሩ አብዮቱን የሚያጠናክሩበት፤ የመሬት አዋጁንም በተጨማሪ የሚያጠናክሩበትና አብዮቱን የሚጠብቁበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነበር የተፈለገው::

በዚያን ጊዜ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ዙሪያውን ተከባለች:: ምንም አደረግን ምን፣ የኛን በጎ የሚመኝ በአካባቢው የለም:: በጣም አፍራሽና ሆስታይል በሆነ ጂኦ-ፖለቲካዊ አካባቢ የምንኖር ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን የመገዝገዙ ሁኔታ፣ ማጥቃቱ፣ መቦርቦሩ ተጀምሯል - ዙሪያውን::ጠላት ደግሞ ለለየለት ግልፅ ወረራ አሰፍስፏል:: በውስጥም ያለው ሥርዓቱ የከዳው የጉልታዊው ሥርዓት ርዝራዥ ደግሞ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም:: «የይሁዳ አንበሳ» የሚባል ድርጅት ተቋቁሟል::ሌሎችም፣ ሌሎችም::በላስታ፣በጎንደር፣ በጎጃም፤ በሸዋ እነመርዕድ ብሩ፣ እነቀኛዝማች ትርፌ፤ እነመንገሻ ሥዩም፤ እነአሊ ሚራህ፤ እነኚህ ሁሉ ይገዘግዙን ነበር:: ከዚህ ሁሉ አኳያ ይሄንን ከማድረግ የተሻለ አማራጭ አልነበረም::

ሃሳባችንን ያቀረብንላቸው፣ በጥንቃቄ የመረጥናቸው በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ አንጋፋ ሚና ሲጫወቱ የነበሩ በሳል ምሁራን ነበሩ-ሁሉም:: ቅድመ ሁኔታ ብለው ያቀረቡት ‹ሁሉንም እንቀበ ላለን:: ነገር ግን የፖለቲካ ፕሮግራሙ ላይ ጥያቄ አለን› የሚል ነበር:: ‹ሥር ነቀል ለውጥ ብለን ከተነሣን «ኢትዮጵያ ሶሻሊዝም» የተባለው ነገር ትንሽ ለየት ያለ ፍልስፍናና ባዕድ ነገር ነው:: ከዓለም ተራማጅ ኃይሎች ጋር የሚያስልፈንና ግልፅ የሆነ ፕሮግራም ስለሚያስፈልገን ይህን የጠመጠማችሁትን ሻሽ አውልቁና በግልፅ ውጡ› አሉ::

በይዘቱ አንድ ነው:: የወል ይዞታን ያራምዳል:: የሠራተኛውንና የሰፊውን ሕዝብ ሥልጣንና መሪነት ይቀበላል:: ይሄ ቀረሽ የማይባል አብዮታዊ ይዘት አለው::ግን የሃይማኖትን ጠንቅ፣በአገራችን የሕብረተሰቡን ማሕበራዊ ንቃት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለው አሰላለፍም የምንገባበትን ቅራኔ ማሰብ ያስፈልጋል:: ከምሥራቁ ብንሆን ምዕራቡ ይሰለፍብናል:: ከምዕራቡ ብንሆን ምሥራቁ ይሰለፍብናል:: ስለዚህ እነኚህን ሲሆን ማራቅ፣ ያለበለዚያም ወዳጅ ማድረግና አንፃራዊ የሠላም ጊዜ ለመግዛትና አብዮቱን ለማጠናከር የሚያስችለንን ሁኔታ መፍጠር አለብን::

በሌላ መልኩ ደግሞ ጦርነቱ የቀንና የሰዓት ጉዳይ እንጂ አይቀሬ እንደሆነ ተረድተናል:: የጦር ኃይላችን ፍፁም የተዳከመና የተዝረከረከ ስለነበር እንኳንስ መቶ ሃምሳ ሺ የታጠቀ የሶማሌን ሠራዊት ቀርቶ ወንበዴን እንኳን መቋቋም ተስኖት ነበር:: ሠራዊታችን ደግሞ ለዘመናት በአሜሪካን ሚሊቴሪ ዶክትሪንና ቴክኖሎጂ የሰለጠነ በመሆኑ በዚህ አጭር ፋታ በሌለው ጊዜ ውስጥ ለውጥ አድርገን የሚመጣብንን ጠላት ለመመከት እንደማንችል በመረዳታችን ካሜሪካ ጋር የነበረንን የግንኙነት ገመድ ለመበጠስ አልፈለግንም:: እንደምንም ብለን ካሜሪካኖች በርዳታ እንኳን ባይሆን ገንዘባችንን ከፍለን መሣሪያ አግኝተን ይሄንን መመከት መቻል አለብን በሚል በደንብ መከርንበት::

በነዚህ ምክንያቶች ወደሶሻሊስቱ ካምፕ መግባታችንን ገልጦ መናገር ታክቲካል አይደለም በማለት፣ ፕሮግራማችን የነበረው የሶሻል ዴሞክራት ሲስተም ነበር:: በሌላ አነጋገር የሠራተኛውን ሕልውናና ጥቅም በሚገባ ያስከብራል:: ለሰፊው ሕዝብ ይወግናል:: ነገር ግን በመደብ ትግሉ ላይ አንዱ የሌላው ደጋፊ ወይም ኮምፕሊመንተሪ እንዲሆን እንጂ እርስ በርሳችን በተቃራኒነት ቆመን አስፈላጊ ያልሆነ ትግል እንዳይስፋፋ ለጊዜው ልዩነታችን እንዲለዘብና እንዲገታ፣ በውጪም ለምናራምደው ዲፕሎማሲ የራሱ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለን «የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም» አልነው:: በስያሜው በግልፅ አናስቀምጠው እንጂ ሶሻል ዴሞክራቲክ ሲስተም ነው::

እነኚህን የጠራናቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች አብረን ለመታገልና የጋራ ግምባር ፈጥረን ኢትዮጵያን ወደለውጥ ለማሸጋገር ጥሪ ስናቀርብላቸው ‹ይሄንን ፕሮግራም፣ የሸፈናችሁትን ሻሽ ግለጡ› ማለታቸው በግልፅ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራምን እንንደፍ ነው:: ‹ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙ እናንተ ካላችሁ ዓላማና ስልት የተለየ አይደለም:: የሚያስከትለው ጉዳት የለም:: ብሔራዊ ከበርቴውን ያቅፋል:: ንዑስ ከበርቴውን፣ ገበሬውንና ሠራተኛውን ያቅፋል:: ደረጃ በደረጃ ግን የሠራተኛውን መደብ ማሕበራዊ መሠረት እያሰፋ

ጥቅሙን እያጎለበተ የሕዝቡን የበላይነት የሚያረጋግጥ መሪ ፓሪቲ ወደማደራጀት ያመራል:: ይሄንን በሚመለከት በዓለም ላይ ከተከና ወኑት አብዮቶች አኳያና ከታሪክና ከመደብ ትግል ትንተና ስንነሳ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚለውን ነገር መቼም መግደፍ በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው:: ታሪካዊ ስሕተት ሊሆን ይችላል:: ይሄንን ኤክስፔክት አድርጉ:: ሕዝብ በዚህ አይቸገርም› አሉ::

እኔ መቼም በዚህ መሐል ሳንድዊች ነው የሆንኩት:: በደርጉ ውስጥ፣ በመስተዳድሩ ውስጥ ያሉት የተወሰኑት የኔ ጓደኞች ‹የለም:: ወደዚህ ረቀቅ ወዳለ ፍልስፍናና የርዕዮተ ዓለም ጥያቄ ውስጥ በመግባት ከሃይማኖት መሪዎችና ከምዕመናን ከመጋጨት፤ አንዱን ወገን በመያዛችን ከሌላው ወገን ጋር ቅራኔ ውስጥ ከመግባት ይሄ ነገር ለጊዜው ቢዘገይ› የሚለውን ሃሳብ አራማጆች ነበሩ:: ሌሎቹ ደግሞ ‹አይ እኛ ይሄንን ፕሮግራም ለማራመድ ዝግጁ አይደለንም:: ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የተባለውን ነገር ከሞላ ጎደል በይዘቱም አብዛኛው የሕብረተሰቡ ክፍል የሚያውቀው በመሆኑ ሳይንሳዊ ርዕዮት በሚለው ምክንያት ባናልፈው ይሻላል› ባይ ናቸው::

እንግዲህ ነገሩን አውጥቼ አውርጄ፣ ጥቅምና ጉዳቱን ገማግሜ በዚህ ሂደት ውስጥ ሌሎች የሚሠሩ ተጓዳኝ ሥራዎች ነበሩ:: ከአሜሪካኖቹ ጋር መሣሪያ እንዲሰጡን ጥረት ስናደርግ ‹እናንተ እነማናችሁ?ለምንድነው መሣሪያ የምንሰጣችሁ? በቬትናም ጦርነት ተዳቀን ስለወጣን ለራሳችን ችግር ላይ ነው ያለነው:: የናንተን ጥያቄ ለማሟላትና ለማርካት አቅሙም ችሎታውም የለንም› የሚል አዘናጊና የሚያመነታ መልስ ተሰጠን:: ጊዜ እየሸሸን ነው:: ሥጋታችን ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ ሄደ:: እና እነኚህ ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ገብተው፣ ከዚህ ላይ ደግሞ ተገንጣዮች በሶሻሊስቱ ሥርዓተ ማሕበር፣ ‹አብዮት ወጋችሁ› ተብለው እንዳይወገዙ ‹ይሄ ዝም ብሎ ነው:: ፎኮ የሆነ ማጭበርበሪያ::ጭራና ቀንዱ የማይታወቅ ነው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ይሄ አስተሳሰብ የለም› እያሉ ፕሮፓጋንዳ ያካሂዱብን ስለነበር እኔ አንዱን ወገን መረጥኩ:: አቋም ወሰድኩ - ከሌሎች የደርግ አባሎች ጋር:: ይሄውም ምንድነው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን መቀበል ነው:: በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ የሕዝባዊ ድርጅት ፅህፈት ቤት የተቋቋመው::

«ዓላማው ምንድነው?» ያልን እንደሆነ ከጓዶች ጋር ቁጭ ብለን በመተማመንና በመተዋወቅ ተወያይተን፣ ተሳስበን ስልትና ስትራቴጂ ቀይሰን ከዚያ በኋላ ከግምባር ወደአንድ ወጥ ፓርቲ አምርተን ሕዝቡን አስተማማኝ የሆነ ድርጅት በሚኖረው ጊዜ ገበሬው መሬቱን፣ ሠራተኛው መብቱንና ዳቦ ካገኘ፣ ወታደሩ ሠላም ካገኘ የሚኖረን ተወዳጅነትና ፖፕላሪቲ ወሰን አይኖረውም:: እኛ መድብለ ፓርቲ ብለን ብንል የሚቃወመን ማነው? የብሔረሰብ ጠባብነት የሚያራም



ዱት ፓርቲዎች ናቸው የሚታገሉን ወይስ ገንጣዮች? ዘውድ የሚያፈቅረው ነው ወይስ መሳፍንቱ? በዚህ በኩል ሥጋት ሊኖረን አይገባም::

*ገነት - ለብዙኃን ፓርቲ ነበር ማለት ነው?*

*መንግሥቱ* - አዎን:: እንዴ ነው እንጂ! ፕሮግራሙን እኮ ብዙ ሰዎች ልብ አይሉትም እንጂ ዛሬ እኛ የምንወቀስበትና ምዕራባውያን እንደገና እንደ አዲስ ነገር «ሀ፣ ሁ» ትምህርት ሊሰጡን የሚሞክሩት እኛ ያን ጊዜ እኮ መድብለ ፓርቲን ከነተልዕኮው፣ ከነዓላማው፣ ከነጥቅምና ጉዳቱ ቁልጭ አድርገን አስቀምጠነዋል::

*ገነት - ታዲያ መቼ ነው ወደሶሻሊዝም የሄዳችሁት? የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ከሆነ . . .*

*መግሥቱ*- የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም መድብለ ፓርቲን ይፈቅዳል እኮ:: ነገር ግን መድብለ ፓርቲ ሲባል፣ ያው ተራማጁ የግራ ኃይል እጅግ በጣም ሰፊና ማሕበራዊ መሠረቱ ዶሚናንት ስለሆነ ከአብዮቱ ርምጃ የሚገታ ምንም ዓይነት ጠንካራ ተቃዋሚ አይፈጥርም:: ነገር ግን እንግዲህ የዓለምን የፖለቲካ ሚዛን በመመልከት አንድ ቅራኔ ውስጥ ገብተን ራሳችንን ከምንቀረቅርና የአብዮቱ እርምጃ የሚደናቀፍበትን የማያስፈልግ የትግል ጎራ ከምንከፍት ይልቅ ከዚያ የምናመልጥበትን ሁኔታ የመፍጠር ስልት እንጂ ባጠቃላይ ይዘቱ ሶሻሊዝምን የሚያራምድ ነው::: እንዴ! በሱ ነው የመሬትንም አዋጅ፣ የገንዘብ ድርጅቶችንና የማምረቻ ድርጅቶችን፣ ምኖችን ሁሉ፣ በዚህ ፕሮግራም ነው ለሕዝብ ያደረግነው::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ እንግዲህ አሁን ኢሕአፓን የኛ ጥንካሬና አብዛኛው ተራማጅ ኃይሎች ከጐናችን መሰለፋቸው በጣም ነው ያንገበገባት:: ‹ግምባር ቀደምና ብዙ ደጋፊ ያለኝ፣ ሕዝባዊ መሠረት ያለኝ ነኝ› ብላ ራሷን ያኩራራች ፓርቲ ነበረች:: ይሄ አንዱ ችግሯ ነው::

ሁለተኛው ችግር እነሱን ከመጀመሪያው ጀምሮ ከሌሎቹ የለያቸው ነገር ቢኖር ከኤርትራ ከሰሜኑ ጀምረን ወደመሐል ኢትዮጵያ ድረስ፣ ከዚያም እስከዳር እንደ ማኦኢስቶች ሠፋ ያለ መጠን ያለው ሕዝባዊ ጦርነት አድርገን ይሄንን መንግሥት እንጥላለን የሚል ሕልም ነበራቸው::ማንንም ከማን ሳንለይ ሠራዊቱንም፣ ተቃዋሚውንም ጠርገን ስናበቃ መሄድ ነው ብለው ነው ያቀዱት:: ለዚህ መንደርደሪያችን የሰሜኑ የባህር ድንበር ነው:: ሻዕቢያና ጀብሃ የፈጠሩት መሠረትና የትግል ልምድ አለ:: ‹ትግራይም ለትግላችን መንደርደሪያ ነው› ብለው ከወንበዴዎች ጋር ሕብረት ሲፈጥሩ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ለድርድር አቀረቡ:: ትልቁ ስሕተታቸውና ልዩነታቸው እዚህ ላይ ነው::

ስለዚህ «የራስን ዕድል በራስ መወሰን» በሚለው መርህ መሠረት ‹የኤርትራ ሕዝብ ከፈለገና ከወሰነ መገንጠል መብቱ ነው› የሚለውን

ነገር ነው የሚቸሩት:: እነኛ ደግሞ የትግል ልምዳቸውንና መሣሪያ የማቀበል፣ ነፍሰ ገዳዮችን ማዘጋጀትና ማሰልጠንን የመሳሰለ ነገር ይረዷቸዋል:: እዚህ ላይ ነው በኢሕአፓና በሌሎች ድርጅቶች መካከል ልዩነት የተፈጠረው:: ይሄ ነው የኢሕአፓ መሪዎች የሠሩት ትልቁ ስህተት::

ማርክሲዝም ራሱ አንድ አብዮት ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ያለው እንደመሆኑ መጠን ሰዎችን በጎሣና በቋንቋ የሚከፋፍል ሳይሆን «ዓለም የሠራተኞች ናት» የሚለውን መርህ የሚያራምድ ነው:: ያለጊዜውና ያለቦታው ባልነቃ ሕብረተሰብና መሪ አልባ በሆነ አብዮት ውስጥ ይሄንን ይዘው ለኤርትራ መገንጠል ድጋፍ ሰጡ:: እና ይሄን ይዘው የፖለቲካ ክርክር ከፈቱ:: ጋዜጦች፣ መጽሔቶች የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ በራሪ ወረቀቶች ይበትኑ ጀመር:: እኛም አጸፋውን መለስን::

ልብ በይ እንግዲህ፣ ያኔ ዱላ አልነበረንም:: ጥይት አልነበረንም:: የዚያን ጊዜ አንድ ሰው ላይ አንድ ጥይት አልተኮሰንም:: የሚፈለገው ምንድነው? አንድነት ነው ወይስ ልዩነት? አብዮት ወይስ ሥርዓተ አልበኝነት? በሚልና የሌሎችን ታሪክ በመዘርዘር፣ የወደፊቱንም በመጠቆም ሰፋ ያለ ውይይት በሚካሄድበት ጊዜ በርዕዮተ ዓለም ትግል፣ ለሕዝቡ በሚቀረቡ ጽሑፎችና ማስረጃዎች፣ መንግሥት በከፈታቸው የውይይት መድረኮች ኢሕአፓ ራቁቷን ቀረች:: እንግዲህ በዚህ ስትሸነፍ ከኛ ጋር ያበሩትን አብዮታዊ ድርጅቶች ሁሉ ‹ባንዳዎች!› እያለች ስም ሰጠች:: ደርጉን ደግሞ ‹የምርጥ መኮንንኖች መንግሥትና ፋሺስት› ብላ ሰየመች:: እኛ በውነቱ ይሄን ሁሉ ታገሥን:: በውነት ታገሥን::

ከዚያ በኋላ እንግዲህ እኔ በግልፅ አደባባይ ወጥቼ መናገር ጀመርኩ:: እየዞርኩኝ የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ማድረግ ጀመርኩ:: ለጦሩ አባሎችም፣ለሲቪሉም የኢሕአፓን ማንነት በማጋለጥ፤ በተለይ ከኤርትራ ተገንጣዮች ጋር ያላትን ትብብር ይፋ አወጣሁ::

በወረቀት ከሚደረገው የርዕዮተ ዓለም መፋጨት፣ በጋዜጦች ከሚደረገው ክርክር፣ በየውይይት ክበቦች ከሚሰለቁት ውይይቶች ሌላ የሕብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች እየሄድኩኝ ማስረዳት ጀመርኩኝ:: የተማሪውን እንቅስቃሴ ታሪክ፣ እንዴትና መቼ እንደተጀመረ፣ በውስጡ የነበረውን ልዩነትና አንድነት ተነተንኩ:: የራስን ዕድል በራስ መወሰን በማለት ጥራዝ ነጠቅ መርሆ ያለቦታውና ያለወቅቱ ደንቅረው በሰሜኑ ግንጠላ ላይ የያዙትን አቋም አደገኝነት አጋለጥኩ:: ለሕዝቡና ለሠራዊቱ እየዞርኩ አስረዳሁ:: በዚህ ዓይነት በኢሕአፓ ላይ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ፣በተገኘው ሚዲያ ሁሉ የማጋለጡ ዘመቻ ሲፋፋምባት እኔን ለማጥፋት ቆርጣ ተነሳች:: የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ነው የከፈትንባት:: የኢሕአፓን አደገኛ አቋም እየተነተንን፣ በጽሑፍ እየፃፍን፣ በቴፕ እየቀረፅን፣ በሬዲዮና በጋዜጣ፣ ባለው ሚዲያ ሁሉ አንዴ ስናዘንብ ለዚህ ግምባር ቀደም የነበርኩት እኔ ስለሆንኩኝ ኢሕአፓ



ዎች ጥቃቱ ተሰማቸው መሰለኝ መጀመሪያ በኔ ጀመሩ:: የመጀመሪያ ዒላማቸው ሆንኩ - መስከረም 13፣ 1969 ላይ:: እንግዲህ አይተሽ እንደሆነ አላውቅም ያኔ . . .

*ገነት - አዎን፤ በቴሌቪዥን አይቻለሁ::*

*መንግሥቱ* - በጥይት ተደበደብኩኝ:: አሁን ሳስበው ይገርመኛል:: ከዚያ መዓት እንዴት እንደዳንኩኝ:: ከዚያ በተረፈ ሕይወት ዛሬ መነጋገር መቻሌ! ያም ሆኖ ለጠቅላላው የአብዮቱ ወገኖች ባደረግሁት ጥሪ «እኔ ድኛለሁ:: አሁንም ቢሆን ልብ አድርጉ:: ለአንድ ሰው፣ ለአንድ አነስተኛ ነገር ተብሎ የሚፈጠረው አምባጓሮ ለብዙ ሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አትዘንጉ:: እንዳትሳሳቱ» ብዬ ሆስፒታል እያለሁ ተናገርኩ:: ሦስት ሰዓት የፈጀ የቀዶ ጥገና ሕክምና ነው የተደረገልኝ:: ሦስት ሰዓት የፈጀ የቀዶ ጥገና ሕክምና ነው የተደረገልኝ:: የተመታሁበት ቦታ በጣም አደገኛ ነበር:: እዚህ እንዳው መጋጠሚያዬ ላይ የሰጡኝ ጥይት...እንዳው የሚገርም ነገር ነው...እንግዲህ ከላድሮቨሩ የኋላ መቀመጫ ላይ ነበርኩ:: ጥይቷ የላንድሮቨሩን መቀመጫ በስታ ቀዝቅዛ ስለመጣች እንጂ ነርቭና አጥንቴን በጣጥሳ ብትወጣ ኖሮ ሕይወቴ ቢተርፍ እንኳን ዘላለም ሽባ ሆኜ ነበር የምቀረው:: ለዚያውም አንድ አጉል ቦታ ተቀርቅራ ሦስት ሰዓት የፈጀ ኦፕራስዮን ተደርጎልኝ ነው የወጣችው:: ሕዝብ ተሰብስቦ፣ ሆስፒታሉ ሁሉ ታውኮ፤ አንድ ሰው፣ ሁለት እየመሰለኝ፣ ዝሆን የሚያክል አድጎ እየታየኝ አንደበቴን እያያዘኝ «ጓዶች ድኛለሁ:: ሰው ይሞታል እንጂ አብዮቱ አይሞትም:: በስሜት ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳትወስዱ:: በትዕግሥት ቆዩ» ብዬ ተናግሬ ሁኔታውን አረጋጋሁ::

ከዚያ በኋላ ኢሕአፓን ወደኛ ስበን ለማምጣት ያደረግነውሙከራ ከንቱ እንደሆነ ተረዳን:: እሷም በእንቢተኛነቷ ፀንታ ንፁሐንን መግደሏን ቀጠለች::

*ገነት - የኢሕአፓ መሪዎች ከነበሩት አንዱ ብርሃነመስቀል ረዳ ነበር:: ከመሞቱ በፊት ከርስዎ ጋር ይተዋወቅ ነበር?*

*መንግሥቱ* - ብርሃነመስቀል[10] ራሱ ከሚያዋጋው ሠራዊት ጋር በገባበት ጣጣ፣ኋላም ደግሞ ሻዕቢያና ወያኔ ባደረሱባቸው ውርጅብኝ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ ካለው አመራር ጋር በገባው ቅራኔ ተቸግሮ ነበር:: አዲስ አበባ ሲመጣ ሁሉም አድመው ይጠብቁታል:: ‹ኣምባገነን ሆነሃል:: ይሄን አድርገሃል:: ሂስህን ዋጥ› ይሉታል:: ከኃላፊነትም ለጊዜው ገሸሽ አድረገውት ሁኔታቸው ቢያሳዝነውም ‹እሺ› ብሎ ወርዶ ሲሠራ፣ የከተማውን ጦርነት የማስፋፋቱ ውሳኔ በነሱ ማዕከላዊ ኮሚቴ ይወሰንና ያ ሰፊ የነጭ ሽብር ርሸና ይጧጧፋል::

[10] ስለኢሕአፓ የሚያውቀውን በሪፖርት መልክ እንዲጽፍ አስገድደውት ከፃፈ በኋላ እንደገደሉት ይነገራል::

እኛም አፀፋውን መልሰን ኢሕአፓ በደንብ ስትመታ ብርሃነመስቀል ውልቅ ብሎ ይወጣል:: ከነሚስቱ በየቦታው ሲንከራተት ይቆያል:: «የት ነው ያለው» ብዬ ስል፣ አንድ ጊዜ ‹ወሎ ነው› ይሉኛል፤ አንድ ጊዜ ሌላ ቦታ ሲባል፣ በመጨረሻ ላይ ገበሬዎች እጅ ይወድቃል:: መቱት:: ሲያዩ አብራው የነበረችው ባለቤቱ ነፍሰጡር ነች::

እኔ ያን ጊዜ ድሬዳዋ ነበርኩ:: መልእክት ደረሰኝ:: ‹ብርሃነመስቀል እንዲህ፣ እንዲህ ያለ ቦታ ላይ ተገኝቶ ተመታ› የሚል:: «ለመሆኑ ተዋግቶ ነው? ሠራዊት አለው?» ስል፣ ‹አይ እንዳው ብቻውን ነው ያገኘ ነው› ተባልኩ::

እንግዲህ እሱ በዚያ በከተማው ትጥቅ ትግል የነበረው አቅም ምን እንደነበረ፣ ወይም በኔ ሕይወት ላይ ስለመፍረድ አለመፍረዱ በውል አላውቅም:: ምክንያቱም አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ ነጭ ሽብርን በመንዛት ግድያውን የሚያስፈፅመው ተስፋዬ ደበሳይ ነበር:: ብርሃነመስቀል ሠራዊቱን እንዲመራ ተልኮ ትግራይ ነው ያለው:: ትግራይ ውስጥም ሊሠራ አልቻለም:: ሠራዊቱ ውስጥ ጥብቅ ዲስፒሊን አራምዳለሁ፤ ወሳኝ ውጊያም አካሂዳለሁ ሲል ወነጀሉት እንጂ አልደገፉትም:: ግማሾቹም ከዱት:: ከዚያ በኋላ ነው ብቻውን የቀረው::

እና ድሬዳዋ ሆኜ የመያዙ ዜና ደረሰኝ:: ባለቤቱን[11] እኔ አላየኋትም እንጂ ‹ትንታግ የሆነች፤ምንም ከሱ ባላነሰ ሁኔታ የምትታገል ናት› አሉ::ሎያል ናት:: እንደፍቅረኞች አብረው ከመኖር ባሻገር በትግል እንደዚህ አድርጎ መማሰን ሁልጊዜ የሚታይ ነገር አይደለም:: የሚደነቅ ነገር ነው:: እኔ መቼም በጣም ተሰምቶኛል::

ልጁ (ብርሃነመስቀል) የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ትቶ ቁጭ ብሎ ሕይወቱን ሙሉ ይቺኑ ፖለቲካ ሲያሽከረክር የቆየ ነው:: ግን የቆመለት ዓላማ ኅጠኝነትን የሚደግፍ ይሁን አይሁን፣ አላውቅም:: ኅጠኛ ነበር? በብሔራዊ ስሜት የሚታገል አብዮተኛ? ያራምደው የነበረውና ያከናወናቸው ተግባሮች ለውነት የሚታገል፣ የሆነ ለውጥ ለመምጣት ነበር ወይስ ሌሎቹ እንዳደረጉት ታክቲካል የሆነ ያንን መንግሥት የማዝረክረክና የኅጥ ዓላማ ነው? ይሄንን ለታሪክ ብንተወው:: እኔ መናገር አልችልም:: ግን የማውቃቸው ጓደኞቹ፣ በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች ግትርና በዓላማው ጽኑ፣ ኅበዝ እንደነበር ነግረውኛል::

በበኩሌ ከዚያ ቀደም ሲልም ብዙ የሚነገርላቸውንና ድርጅቱን (ኢሕአፓን) ያሽከረክሩታል የሚባሉትን ሰዎች በግል በመፃፃፍ ላገኛቸው ሞክሬአለሁ:: ብርሃነመስቀል ከፃፍኩላቸው አንዱ ነው:: ያን ጊዜ ትግራይ ነበር:: ደብዳቤ ፃፍኩለት::

*ገነት - ለብርሃነመስቀል?*

---

[11] የብርሃነ መስቀል ረዳ ባለቤት የነበሩት ወይዘሮ ታደለች ኃይለሚካኤል ለብዙ ጊዜ በእስር ሲማቅቁ ቆይተው ኢሕአዲግ አዲስ አበባ ሲገባ ተፈተዋል:: ቀደም ሲል የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በኮት ዲቯር የኢትዮጵያ አምባሳደር ናቸው::



***መንግሥቱ*** - አዎን:: ራሴ በጄ::

*ገነት - ምን ብለው?*

***መንግሥቱ*** - ወደአብዮቱ ካምፕ ግባ ለማለት ነበር:: «ና!» ነው ያልኩት «አንተና ጓደኞችህ ተሳስታችኋል:: ይሄ ወርቃማ ጊዜ ተመልሶ አይመጣም:: ዛሬ ኢትዮጵያ እንዲህ በሕዝብ የተደገፈ አብዮት አግኝታ እያለች በጥቂት ድርጅታዊ ጠባብነትና የትግል ስልት ምክንያት አግባብነት የሌለው መሥዋዕትነት ከምንከፍልና የማይፈፀም ተስፋ ጨብጣችሁ እርስበርስ ከምንፋጅ በመተማመን ቁጭ ብለን በጠረጴዛ ዙሪያ እንነጋገር:: ሠራዊቱ የራሱ የሆነ ልዩ የተደበቀ አጀንዳ የለውም:: ዓላማችን ለሕዝቡ የሥልጣን ኅዳና ለመጥረግ ነው:: ፕሮግራማችን ግልፅ ነው:: ለዚህ ትንፋሻችን እስካለ የምንታገልለት አላማ ነው» የሚል ነበር:: መልስ አልሰጠኝም:: እኔ በ1967 ለፃፍኩለት ደብዳቤ በ1970 መለሰልኝ:: ፍጥጫው ካለቀና እሱም ከኢሕአፓ ተነጥሎ ብቻውን ከቀረ በኋላ ማለት ነው:: ለኔ የደረሰኝ ከሞተ በኋላ ነው::

*ገነት - እና ከመሞቱ በፊት እርስዎ አላገኙትም?*

***መንግሥቱ*** - አላገኘሁትም::

*ገነት - እሱ ግን ከመሞቱ በፊት እርስዎን ሳገኝ እያለ ሲል ነበር የተገደለው ይባላል::*

***መንግሥቱ*** - እንደዚህ ሲባል ሰምቻለሁ:: ቅድም እንዳልኩት ገና በ1967 ደብዳቤ ጽፌለት ነበር:: በወቅቱ እንደደረሰው አረጋግጫለሁ:: የሰጠኝ መልስ የለም:: በኋላ ደብዳቤ ጽፎልኝ ኖሯል::

*ገነት - እስር ቤት እያለ?*

***መንግሥቱ*** - አይደለም:: በፊት ነው:: በ1970 ውስጥ ‹ብርሃነመስቀል የፃፈው ደብዳቤ ነው› ብለው በቢጫ የተፃፈ አንድ አራት ገጽ የሚሆን ወረቀት ከሞተ በኋላ ደረሰኝ::

*ገነት - ምን ይላል?*

***መንግሥቱ*** - ራሱን ዝቅ ሳያደርግ፣ክብሩን ዝቅ ሳያደርግ፣ ጌታዬ ምንትስ ሳይል በውነቱ ትንሽ በኩራትና በራሱ መተማመኑን በሚያንፀባርቅ የሥነ ጽሁፍ ዘይቤ ብዙ ነገሮችን አትቶ መጨረሻ ላይ ‹ይቅርታ ይደረግልኝ› ይላል:: የተፈጠረው ደም መፋሰስና እልቂት፣ ኢሕአፓ የሰራችው ስህተት ያሳዘነው ይመስለኛል:: ደብዳቤው ከሞተ በኋላ ሲደርሰኝ በዚያን ጊዜ ሁኔታ በጣም ተናደድኩ::

*ገነት - ማነው የገደለው? ማነው ትዕዛዙን የሰጠው?*

***መንግሥቱ*** - እኔ እንጃ:: የመንግሥት እጅ የለበትም::

***ገነት- እንዴ ታስር እስር ቤት ውስጥ አይደለም እንዴ የሞተው?***

**መንግሥቱ** - አይደለም:: የገደሉት ገበሬዎች ናቸው:: የዚያን ጊዜ ሚሊሺያ ተቋቁሟል - በየቦታው:: ወሎ ውስጥ ነው:: ‹ማነህ? ምንድነህ?› ብለውት በደንብ ደርሰውበታል፤አውቀውታል:: እና ገደሉት:: ሴትዮዋስ ,ምናምን ሲባል፣ ‹እይ ሴትዮዋማ ሁለት ነፍስ ናት:: እረ እሷንም ሳይገሏት መትረፏ! ኃይለኛ ነች› ነው የሚባለው::

ከኢሕአፓ አባሎች መካከል ግማሾቹ ‹ምን ነበር የምንፈልገው? የመሬት አዋጅ ታወጀ::እኛ ብቻ ተገልለን ቀረን:: በዚህ ላይ በኤርትራ መገንጠልና በሌሎችም በየውይይቱ መድረክ ያለን አቋም ደካማ ነው:: እና ይሄ ነገር መገምገም አለበት› የሚሉ ተነሱ:: ይህን/ያሉት ግማሾቹ በኢሕአፓ በራሷ ተመቱ:: የተረፉት እየከዱ መጥተው ከኛ ጋር ተቀላቀሉ:: ሌሎቹ ደግሞ «የእርምት እርምጃ» በሚል ሲለዩ ኢሕአፓ ለሁለት ተከፈለች::

የነብርሃነመስቀል ቡድን ‹በተማሪ እንቅስቃሴ ወቅት በነበረን ተሳትፎና በአብዮቱም ባደረግነው ትግል የተጋለጥንና መንግሥት በውል የሚያውቀን ሰዎች በአደባባይ ወጥተን የምንሰራበትና ከተማ ገብተን የምንንቀሳቀስበት ሁኔታ በጣም አደገኛ እየሆነ ስለመጣ እኛ ከኤርትራ፣ ከትግራይ ጀምሮ የትጥቁን ትግል እናራምዳለን› በማለት እየተሰባሰበ ትግራይ ላይ ሲከት፣ እነኚህ ስውር የሆኑትና ያልተጋለጡት እነተስፋዬ ደበሳይ ደግሞ አዲስ አበባ ተቀምጠው የድርጅት መረባቸውን ዘርግተው የትጥቅ ትግል የሚሉትን በከተማ ጀመሩ:: እነኛ ደግሞ ከገጠር ገበሬውን እየነዱ ማሲቭ የሆነ ሕዝባዊ ጦርነት ለማራመድ ፈለጉ:: ወያኔና ሻዕቢያ ይሄ መቼም ለነሱ ፋሲካ ነው ‹አይዟችሁ፤ በርቱ!› ይሏቸዋል::

በመሐል ሃገር ያለው የኢሕአፓ የበላይ አካል የሚሰጠው አመራር፣ በወቅቱ የሚወስደው ርምጃ፣ለነኛ ጫካ ላሉት ግልፅ አይደለም:: ግን በውጤቱ አፍራሽ መሆኑን ይረዳሉ:: ብርሃነመስቀል ደግሞ አብዮታዊ ዲስፕሊን ጠንከር በማድረግና ‹ለማዕከላዊ አመራር ተገዢነታችሁን ማስመከር አለባችሁ› በሚል የኢሕአፓ ሠራዊት ላይ የሚወስደው እርምጃ ጠበቅ እያለ ሲመጣ፣ በዚህ የሃሳብ አለመጣጣም ይፈጥርና ብርሃነመስቀልን እየከዱ የሚከሱት ሰዎች ይመጣሉ:: የራሳቸውን ስብሰባ ያደርጋሉ:: ከዚያ ብርሃነመስቀልን ከቦታው ያነሱታል:: እሱም የራሱን አንጃ ይዞ ሲያበቃ በሌላ መልኩ ትግሉን ለመቀጠል ይወስናል:: ከዚያ በኋላ የትጥቅ ትግሉ ይፋፋማል::

ቀጠሉና ሌላውን አብዮተኛ የመኢሶን አባል ሠንጋተራ አካባቢ ጠብቀው ገደሉት:: ፍቅሬ መርዕድ ይባላል:: እንዴት ዓይነት ግሩም ልጅ ነበር:: ከዚያ ቀጠሉና የምኒልክ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበረውን መኰንን ሽገኔን ገደሉ:: ይህ ሰው አንድ እግር፣ አንድ እጅ የሌለው የታወቀ ምሁርና አብዮተኛ ነበር:: ቀጠሉ:: ቀን በቀን አብዮተኞችን እያሳደዱ መግደሉን ተያያዙት::በአዲስ አበባና በየክፍለ ሃገሩም



አብዮተኞችን እያሳደዱ መግደሉን ተያያዙት:: በአዲስ አበባና በየክፍለ ሃገሩም ጭምር በየቀኑ ባማካይ አሥራ አምስት ሰው ይገድሉ ነበር:: መጨረሻ ላይ ትዕግሥት አስጨራሽ ሁኔታ የተፈጠረው ሁለት ጊዜ ያስመረጥነውን የሠራተኛ መሪ ቴዎድሮስ በቀለን ሲገድሉ ነው::

ይሄን ጊዜ ሕዝቡ ንቅል ብሎ ሲያበቃ ‹እንዴ! ምንድነው የምትጠብቁት? ባዶ እጃችንን አታስገድሉን፣ አታስፈጁን፤ አስታጥቁን› ብሎ ተነሳ:: አብዮት አደባባይ በራሱ አነሳሽነትና ቀስቃሽነት፣ ዱላና ፍልጥ እየያዘ መጥቶ እንደደመራ ችቦ ከመረና ‹በዚህ እንድንከላከል ነወይ የሚፈለግው? ጠመንጃና ሽጉጥ ስጡን› አለ::

በዚህ ጊዜ እኛ ከፍተኛ ፈተና ላይ ወደቅን:: እኔ ደግሞ የደርግም፣ የሕዝብ ድርጅትም ሰብሳቢ ነበርኩ:: እና ቁጭ አልን:: «አይ ኢሕአፓ ገደቡን አልፋለች:: ብዙ ጓዶቻችንን አጣን:: አልፎ ተርፎ ሠራዊቱም ውስጥ እየሠረገች እየገባች ነው:: የኤርትራንም መገንጠል፣ የሶማሌንም ወረራ በመደገፍ ላይ ነች:: ሕዝቡ በፍርሃት ወደ መንበርከኩ ነው:: በኛ ላይ ተስፋ የማጣት አዝማሚያ እየታየ ነው:: የአዛውንት ሴቶች የኡኡታ ኰሚቴ እስከማቋቋም ተደርሷል:: እና ምን እስከምንሆን ነው መጠበቅ የያዝነው» አልን::

***ገነት - ከዚያ በፊት ግድያ አልነበረም ነው የሚሉት? ደርግ ከዚያ በፊት አልገደለም?***

***መንግሥቱ*** - ግድያ አይደለም፤በጥፊ የተመታ ሰው አልነበረም:: አንድ ሰው የታሰረ የለም::

***ገነት - ከመስከረም፣ 1969 በፊት የኢሕአፓን አባሎችም ሆነ ሌሎች ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት በደርግ ግድያዎች ተፈጽመዋል::***

***መንግሥቱ*** - እኛ እነዚህን ሰዎች እንፈልጋቸዋለን:: ለምንድነው የምንገላቸው? በአብዮቱ ውስጥ እንፈልጋቸዋለን:: ተስፋዬ ደበሳይ፣ እነዓለምአንተ፣ ብንያም አዳነና ሌሎችም የኢሕአፓ አባሎች መሬት ይዞታና ግብርና ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው:: ከእኛ ወገን፣ ከሌሎችም ተውጣጥተው በአንድ ኮሚቴ ተዋቅረው የመሬት ሥሪቱን ሁኔታ አጥንተው ያቀረቡልን እነሱ ናቸው:: እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሕዝብ ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ የጋራ መሰስተኛ ብሔራዊ ፕሮግራም ወጥቶ የሁሉም የራሱ ሕጋዊ ሕልውና ታውቆ፤ ነገር ግን ባንድነት ተሰልፈን ፀረ-ፊውዳል ግምባር በመፍጠር የኢትዮጵያን አብዮት ከግብ ለማድረስ ምኞት ነበረን:: ያለመታደል ሆነና ኢሕአፓዎች በተሳሳተ ስሌት የማይሆን ነገር ውስጥ ገቡ:: በየከተማው እኛንና የኛን ደጋፊዎች እያደኑ በመግደል ሽብር ነዝተው ሥልጣን ለመያዝ የሚችሉ መሰላቸው:: ወደደም መፋሰሱ ሄድን:: እንግዲህ የኢሕአፓ ትልቁ ስሕተት ይሄ ነው:: ያ ባይሆን ኖሮ ኢሕአፓ ውስጥ የነበሩ ከኛ ጋር ሆነው አገራቸውን ለማገልገል የሚፈልጉና በቀላሉ የማይተኩ ሰዎች የማያስፈልግ መሥዋዕትነት ከመክፈል ይልቅ የአብዮቱን

ጎራ ያጠናክሩልናል የሚል ጽኑ እምነት ነበረን:: ኢሕአፓዎች ደርግ ውስጥም ነበሩ:: አብረናቸው እንሠራ ነበር::

በኛ በኩል ኢሕአፓዎች ደንበኛ የከተማ ሽምቅ ውጊያ ጀምረው አዲስ አበባና በየከተማው ግድያ ሲቀጣጠል እንኳን ተስፋ አልቆረጥንም:: ምንድነው ምክንያቱ? የምንነጋገረው አንድ ቋንቋ ነው:: በተማሪው እንቅስቃሴ ፍላጎታቸው ይሄ ነበር:: መሬት ላራሹ ሆኗል:: ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ዓላማችን ሆኗል:: እና ምንድነው የሚፈልጉት? ምንድነው ልዩነታችን? በምን ምክንያት ነው ወደዚህ አቅጣጫ የሚገፋን? በማለት ረጂም ጊዜ የፈጀ ስብሰባ አድርገን ተነጋገርንበት::

በስብሰባችን ከተሰነዘሩት ሃሳቦች ግንዛቤ ያገኘነው ነገር ቢኖር የነሱ ችግር የሚመነጨው ካመራራቸው መሆኑን ነው:: አመራሩን የያዙት ለሻዕቢያ ድጋፍ የሚሰጡ የሰሜን ሰዎች ናቸው:: የችግሩ ዋነኛ ምክንያት አመራሩን የሰሜን ጠባቦች ስለያዙት ነው:: ለምሳሌ፣ ብርሃነመስቀል ዱር በነበረበት ጊዜ፣ አዲስ አበባ ቁጭ ብሎ በኔም፣ በሌሎቹም ላይ የሚያስተኩሰውና ያንን ሁሉ ሰው የሚያስፈጀው ተስፋዬ ደበሳይ ነበር:: የሻዕቢያ ነፍሰ ገዳዮች ከኢህአፓ ጋር በቅንጅት ይሠሩ ነበር:: እነጎይቶም ለባሲን መጥቀስ ይቻላል:: እነሱ የራሳቸው የሆነ የተለየ አጀንዳ ነበራቸው::

እኛ ደግሞ የዚያን ጊዜ ስለወያኔ የነበረን መረጃ በጣም፣ በጣም ደካማ ነበር:: በኋላ ነገሩን ስንረዳው ትግራይ የራሱን ነፃ አውጪ እያቋቋመ ነው:: ኤርትራዎቹ ምን እንደሚፈልጉ ያደባባይ ምስጢር ነው::ሃሳባቸው ትግራይ ተደራጅቶ ከኤርትራ ጋር ተቀናጅቶ ኢሕአፓን የነሱ መሣሪያ በማድረግ ባንድነት ሆነው መላ ኢትዮጵያን ለመጠራረግ ነው:: እንደዚህ ያለ ጆብደኛ ዓላማ ይዘው ሲነሱ እኛ ነገሩን አቃለን ማየት አይገባንም:: እነዚህ ሰዎች መልስ ያስፈልጋቸዋል:: ነገሩ ከእጃችን ከመውጣቱና ሕዝቡ በእኛ ላይ ጨርሶ እምነት ከማጣቱ በፊት በግድ መልስ መስጠት አለብን የሚለው ውሳኔ ላይ ደረስን::

ብዙዎቹ የመኢሶን ጓዶች እነነገደ ጎበዜና ሌሎቹም ጓደኞቻቸው ስለተመቱባቸው በጣም አዝነዋል::ተበሳጭተዋል:: ስሜታዊ ሆነዋል:: ሕዝቡ ደግሞ ‹አታስፈጁን› እያለ ያንን ዓይነት ሰልፍ ካሳየ በኋላ «ዝም በልና ሙት» ማለት ስለማይቻል እርምጃ ለመውሰድ ተገደድን:: ያንን ባናደርግ በፖለቲካ ራስን እንደመግደል ይቆጠራል:: የሚገርመው ነገር ምንም መሣሪያ የለንም:: ሕንድ አገር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ እንግሊዝ የሠራው ዲሞትፈር በቀላል ዋጋ አግኝተን ገዛንና በየቀበሌው ከአሥር፣አሥር ጥይት ጋር «ራስህን ተከላከልበት» ብለን ሕዝቡን አስታጠቅን:: አሁን እንግዲህ መመላለስ ተጀመረ::

እዚህ ደረጃ ላይ ከደረስን በኋላ ሕዝቡ ራሱ በየቀበሌው፣ በየጓዳ ጎድጓዳው አስፈላጊ የመሰለውን ማድረግ ጀመረ:: የያንዳንዱን ቀበሌና የየግለሰቡን ድርጊት በሕግ ፋይል ከፍቶ ፖሊስ ጣቢያ ምርመራ አድርጎ ለመለየትና በተለመደው ሕጋዊ አሠራር ተጠቅሞ ለማስተናገድ በፍፁም የሚቻል አልነበረም:: ዛሬ አሁን የተደላደለ መሬት ላይ ቆሞ



መፍረድ ቀላል ነው:: በሌላው ዓለም በተመቻቸ ሁኔታ ሲደረግ የሚያየውን ሁሉ ለምን ያኔ አልተደረገም በማለት አፉ እንዳመጣለት፣ ከጥርሱ ሳያላምጠው መናገር ቀላል ነው:: በጊዜው የነበረውን ሁኔታ በጥሞና ማየትና መገንዘብ ያስፈልጋል::

በዚያን ጊዜ እኛ በአራቱም ማዕዘን ጦርነት ተከፍቶብን ተወጥረናል:: ሠራዊቱ መቼም (ይሄ ግልፅ ነው)፣ ቀይ ሽብር ውስጥ እጁ የለበትም:: ሠራዊት የሚባል ከተማ ውስጥ የለንም:: ወታደር የለን:: ፖሊስ የለን:: ፖሊሱንም ድምበር እንዲያስከብር ግምባር ልከነዋል:: ለምሳሌ፣ በነገሌ በኩል ያለው የኢትዮጵያ ፖሊስ ተጠራርጎ ሲያበቃ ሱማሌን እንዲገትር ተልኳል::

በከተማው የጦር ሠራዊት የሚባል የለንም:: ለራሳችን እንኳን ጠባቂ የለንም:: በጣም ጥቂት ሰው ነው አጠገባችን ያለው:: ጦሩ ያለው ግምባር ነው:: ያለው ምሥራቅና ሰሜን ነው:: ሽማግሌውን፣ ጡረታ ያወጣነውን ሳይቀር ሰብስበን «አባት ጦር» ብለን ጦር ግምባር ልከነዋል:: በዚህ ላይ ጦሩ ባንድ ፊት ከጠላት ይዋጋል:: እየተዋጋ ከውስጡ ደግሞ ኢሕአፓዎች ተሰግስገው ‹ለማነው የምትዋጋው?› ይሉታል::

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ስንገኝ ሕዝቡ ራሱን እንዲከላከል ማስታጠቅ የግድ ሆነብን:: ያለዚያ ሕዝቡ ራሱ በኢሕአፓ ምክንያት በምሬት እኛ ላይ የሚነሳበት ደረጃ ላይ ተደርሶ ነበር::

ለነገሩ እኛ «ቀይ ሽብር» የሚለውን ቃሉን ራሱ ሰምተነው እናውቅም:: «ቀይ ሽብር» ከቃሉ ጀምሮ መሠረቱ የሩስያ አብዮት ነው:: ራሽያኖቹ በአብዮታቸው መጀመሪያ ላይ እንደዚህ ያለ ታሪካዊ አጋጣሚ ደርሶባቸው በሃገራቸው ቅልጥልጥ ያለ ሽብር ተካሂዷል::ያውም በፀረ-አብዮት ካምፕ ሳይሆን በአብዮቱ ካምፕ ውስጥ:: ቀይና ነጭ ሽብር እየተባለ ሜንሼቪኮችና ቦልሼቪኮች ተዋግተዋል::

ይሄንን ታሪክ እንግዲህ ከወዲያም ከወዲህም ያሰባሰቡ ጓዶች፤ ኢሕአፓዎች ጓዶችን መግደል ሲጀምሩ ‹ይሄ ነጭ ሽብር ነው:: መልሱ እንግዲህ ቀይ ሽብር ነው› ይሉና ይሄ በውይይት ደረጃ ሕዝቡ ውስጥ ይሠርፃል:: በጋዜጦች ይወጣል:: ፓምፍሌቶች ይነዛሉ:: ውይይት ይደረጋል:: አቋም ይወሰዳል:: እነሱ የሚሰነዝሩትን ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር መመከት የወቅቱ ጥያቄ ሆነ::

*ገነት - ግን መልሱ እኩል ነወይ ነው ጥያቄው:: በዚህ የቀይ ሽብር የመልስ ምት የአንድ ትውልድ [illegible]ቶች ናቸው ያለቁት ...*

*መንግሥቱ* - (በማጣጣል) ብፍ ...

*ገነት - ... ሁለተኛ ነገር ደግሞ የአገዳደሉ ሁኔታ አሰቃቂ ነው:: ከሰብአዊነት ውጪ ልጅን ከገደሉ በኋላ አምጥቶ ወላጆች በር ላይ መጣል፣ የሞተበትን ቤተሰብ የጥይት ዋጋ ማስከፈል:: ይሄን የመሳሰለው ነገር በእውነቱ ቀይ ሽብርን እጅግ አሰቃቂ ያደርገዋል:: ይሄ ደግሞ «ነፃ እርምጃ»*

*እየተባለ ከአንድ ቤተሰብ አራት፣ አምስት ልጅ የሚያልቅበት ሁኔታ ነበር:: ስለዚህ ምን ይሰማዎታል?*

*መንግሥቱ* - ጥሩ ጥያቄ ነው:: በዚያን ወቅት የነበርንበትን ሁኔታ በዓይነ ሕሊና ዞር ብሎ ማየት ያስፈልጋል:: በዚያን ጊዜ የሃገር መሪዎች ሆነን ተቀምጠናል:: ለስሙ መንግሥት ነበረ እንበል:: ግን ምን ዓይነት መንግሥት? የተዳከመ፣ ከየአቅጣጫው የተወጠረ መንግሥት ይዘን ነው የተቀመጥነው:: በተለያየ የሃገሪቱ ማዕዘን የተረባረበብንን ጠላት መመከት ተስኖን የሃገሪቱ ሕልውና እጅግ አደገኛ ሁኔታ ላይ የወደቀበት ወቅት ነበር:: መደበኛው ሠራዊታችን አልበቃ ብሎን የ70ና የ80 ዓመት አዛውንቶች ጦር ሜዳ እየሄዱ የሚፋለሙበት ወቅት ነበር:: ስሜታችን ከቁጥጥር ውጪ አልሆነብንም:: በተቻለን ሁሉ የአብዮቱ አቅጣጫ ለማስተናገድ የሚቻለውን ጥረት አድርገናል:: ከአቅማችን በላይ ሲሆን ግን ምንም ማድረግ አልቻልንም::

በኢሕአፓ ላይ ሕዝቡ እኮ ነው የተነሳው! ጎርፍ ነው! የሕዝብ አመፅ ነው! ነውጥ ነው! በምን ምትሃት፣ በምን ተአምር ነው ያንን ሕዝብ ማቆም የምንችለው?አብዮት እኮ ነው::የሕዝብን አመፅ ማቆም የሚቻል ከሆነ ገና ከመጀመሪያው አፄ ኃይለሥላሴ ለምን አላቆሙትም? እነአክሊሉ ሀብተወልድ፣ እነእንዳልካቸው ለምን አልገቱትም? ይሄም እንደዚያው ነው::

ኢሕአፓ የምታካሂደው ግድያ ከትዕግሥት በላይ ሲሆን ሕዝቡ ግልብጥ ብሎ መጣ:: የየቀበሌው ነዋሪዎች ናቸው ‹አስታጥቁን!› ብለው የመጡት:: ማዕበል ነው! ጎርፍ ነው! አንዴ ቤተመንግሥቱን ወረሩት! ዘብ አላቆማቸው፣ ምን አላቆማቸው:: ወይም ሕዝብ ላይ አንተኩስ:: ግቢውን እንዴ አጥለቀለቁት:: ፍልጥ እንጨት ከምሬው ሲያበቁ ‹በዚህ ልንከላከል ነወይ?! አስታጥቁን አታስፈጁን› አሉ:: በደም ፍላት:: መፈክሩ ምኑ፣ ...ፖለቲካሲ ስናየው የሕዝቡን ብዛት፣ የቁጣውን መጠን ስንመለከተው፣ ምን ማድረግ ነበረብን? የኛን አቅም ውሱንነት፣ የነበርንበትን ቦታና ሁኔታ መለስ ብሎ ማየት ያስፈልጋል:: የተማርን ነን የሚሉት ምሁራን ተብዬዎች እንኳን ዛሬ ይሄን ማገናዘብ ተስኗቸው እኛን ሲከሱ ይገርመኛል:: እኛ የሕዝቡን ትርታ አዳምጠን አስተካካይ ነው የሆንነው እንጂ፣ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበርና ሕብረተሰቡን ለመቆጣጠር አቅሙ ፈፅሞ አልነበረንም:: ትልቁ ችግር ይሄ ነው::

ሁለተኛ፣ የተነሳንበት ዓላማና የሚያስፈልገንን የሕዝብ ድጋፍ ስንመለከተው መንግሥት ያለ ሕዝብ፣ ሕዝብ ያለ መንግሥት የለም:: ኢሕአፓ በምትወስደው ጀብደኛ ርምጃ በየቀኑ የሚቀሰፈውን ሰው ስናይ፣ ሕዝቡን ሳይጠይቁትና ምረጠኝ ሳይሉት ይበጁኛል ብሎ የመረጣቸውን የሕዝብ ተመራጮች እየነጠሉ ሲገነጥሉ ዝም ብሎ ማየት ይቻላል?የትኛው መንግሥት ነው ይህ ሲደረግ ዝም የሚለው? ካለው አገር አቀፍ ውጥረት ጋራ የሕዝቡ በቁጣ መገንፈል ሲጨመርበት የመቆጣጠሪያ መካኒዝም አልነበረንም:: አቅማችን ውሱን ነበር:: እነ



ዚህን የመሳሰሉ ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ማግባት ያስፈልጋል እንጂ ዝም ብሎ መፍረድ ትክክል አይደለም::

ያም ሆኖ ያንድ ትውልድ ወጣት ጠፋ የሚባለው ነገር፣ ያለምንም ማወላወል መናገር እችላለሁ ዓይን ያወጣ ቅጥፈት ነው:: ለመሆኑ ኢሕአፓ የአንድ ትውልድ ወጣት መልምላለች እንዴ? መጀመሪያ ነገር የኢሕአፓ አባላት ቁጥር ስንት ነው?

*ገነት - በወጣቱ መሐል መቼም ከፍተኛ እንደነበር ግልፅ ነው::*

*መንግስቱ* - በፍፁም! ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ወጣቶች በሙሉ አላሰባሰበችም:: እኛም ወጣት ነበረን:: መኢሶኖችም ወጣት ነበራቸው:: ኢሕአፓ ስንት ሺህ ሰው መልምላለች:: የኢሕአፓ አባሎች ቁጥር ጠቅላላ ቢደመር ከአራትና አምስት ሺህ አይበልጥም:: እኛ መንግሥት ሆነን እየተንቀሳቀስን፣ በገፍ ምልመላ እያደረግን ‹ሁሉ በደጄ› የነበረው ኢሠፓ ከ17 ዓመታት ትግል በኋላ ቋሚና ተለዋጭ አባሎች በአንድነት ተደምረው ቁጥራቸው 70 ሺህ ገደማ ነበረ:: ከ60 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ 70 ሺህ ብቻ ነበርን:: አንድ ትውልድ ጠፋ ከማለት በፊት ‹የአባላቷ ቁጥር ስንት ነው?› ብሎ ለማወቅ የሚሞክር የለም:: የኢሕአፓ አባል የነበረው ሁሉ እንኳን ቢያልቅ እንዴት የአንድ ትውልድ ወጣት ጠፋ ይባላል? ለመሆኑ በሰሜኑስ፣ በምሥራቁስ ጦር ግምባር አንድ ትውልድ ጠፍቷል? ያ ሁሉ ታንክና መድፍ፣ ሮኬትና ሚግ የሚያጓራበት የጦር አውድማ እንኳን የአንድ ትውልድ ወጣት አልጠፋበትም:: አንዳንዴ የኛ ሰው እያጋነነ ለማውራት፣ ‹የግራኝ ቁመቱ 80 ክንድ ነው፤ ሰይፉ 40 ክንድ ...› እንደሚለው ማለት ነው:: እንደዚያ ካልሆነ በስተቀር የኢሕአፓ አባላትም ሆኑ የተቀሩት ቡድ ኖች ያሰባሰቡት የሰው ኃይል ፓርቲ ነው የሚሰኝ አይደለም:: አስኳል ነው:: እንጭጭ ነው:: ሙከራ ነው:: ቡድኖች ናቸው:: ፓርቲ አይደ ሉም:: ሁሉም!

እኛም ብንሆን ወጣት ነበረን:: ማነው የገጠሩን አዋጅ ተግባራዊ ያደረግልን? ወጣቱ አይደለም እንዴ? እውነት ኢሕአፓ የወጣቱ መሪ ከሆነች መልሶ ያጠፋት ማነው? የደመሰሳት ወጣቱ ነው::

*ገነት - እርስዎ በዚያን ወቅት ያለቁት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ስንት ይሆናል ነው የሚሉት?*

*መንግሥቱ* - ነገሮችን ለያይቶ ማየትና መገንዘብ ያስፈልጋል:: ባብዮቱ መባቻ ላይ ብዙ ሰው ሞቷል:: ሁሉም ግን በኢሕአፓ ጎራ ወይም በመኢሶን ጎራ አልነበረም:: ገበሬዎች ከመሬት ባለቤቶች ጋር ያደረጉት ትንቅንቅ፣ ጠባብ ብሔረተኞችም በባሌ፣ በሲዳሞ፣ በአርሲ፣ በሐረርጌ ሲረሽኑ ነበር:: ይሄንን ሁሉ አንጥረን ስናወጣው ፖለቲካዊ ይዘት ባለው ምክንያት በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል «ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር» በሚለው ቅንፍ ሥር የወደቀው ሰው ቁጥር በጣም ትንሽ ነው::

በቁጥር ብዙ ሰው የሞተው አዲስ አበባ ነው። ተቆጥሮ ተነቅሶ በፎቶግራፍ ተደግፎ የወጣው አኃዝ ከሦስት መቶ በላይ ነው። ማዘጋጃ ቤት ይገኛል። በየክፍለ ሃገሩ ደግሞ አምስት፣ አሥር፣ ሃያ እየተባለ እንደዚያ ተቃርሞ የተገኘው አኃዝ በጣም ትንሽ ነው። እኔ እንደሚመስለኝ ቀይ ሽብር የሚለውን ነገር ሊያናፍስ የፈለገው ለፖለቲካ ዓላማ ሊጠቀምበት የፈለገው ወያኔ ነው። ለዚህ ደግሞ አጫፋሪ የሆኑለት የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍሎች ጊዜና ወቅት ስላላመቻቸውና ወጥመዱን ስለነከሱለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የነጭ ሽብሩን ሰለባ ደግሞ ጊዜና ሁኔታ እንደዚሁ ጠብቆ የሚመጣበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ስንት ሰው ነው ቢነግሩት የሚያምነው? ባላዩት ባላወቁት ነገር፣ ባልተጨበጠ ነገር፣ ይሄን ያህል ደፍሮ ሰውን መኮነን አለ እንዴ? ከየት አምጥተው ነው ይሄን የሚያወሩትና የሚፅፉት?

*ገነት - ሁሉም ተደምሮ ስንት ይሆናል?*

*መንግሥቱ* - ባብዮቱ መጀመሪያ ላይ በአገራችን ስለደረሰው ደም መፋሰስ ሲነሳ በቀይና በነጭ ሽብር ሰለባ ሆነው በነበረው ትንቅንቅ ሕይወታቸው ለጠፋው ኢትዮጵያውያን በማዘን ከሚመነጨው ስሜት ይልቅ ወደኋላ በዚህ በፖለቲካ ተጠቃሚ ለሆኑትና በዚህ ካርድ ለመጫወት ለፈለጉት ሰዎች መሣሪያ የመሆኑ ነገር ነው ጎልቶ የሚታየኝ። ኢሕአፓ ምንድነው? በተቃራኒው የተሰለፉት እነማናቸው? መንስኤው ምንድን ነበር? ማን ከማን ጋር ተሰልፎ ነበር? ከሁሉም በላይ ደግሞ ስንት ሰው ተገደለ? የሚለውን ነገር ጠልቆ ለማወቅ የሚፈልገው የተወሰነ ሰው ነው። የሚገርመው ነገር አንቺም ብትሆኚ ካጠያየቅሽ ትስማሚያለሽ ብዬ አላምንም። ማንም ላያምን ይችላል። ለመሆኑ የተገደለው ሰው ብዛት ስንት እንደሆነ በትክክል ይታወቃል? ግማሹ መቶ ሺ ያደርገዋል። ግማሹ አሥር ሺ ይላል። የወያኔ አቃቤ ሕግ ተብዬ ደግሞ አምስት ሺ እና ስድስት ሺ አድርሶታል። እኔ ከሁለቱም ጎራ የሞተው ሁሉ ቢደመር ሁለት ሺ ይሞላል ብዬ አላምንም።

ብዙ ሰው ሞተ የሚባለው እንግዲህ አዲስ አበባ ነው። በ1969 ለሦስት ወራት ያህል ሽብሩ ተፋፍሞ ነበር። በዚያ ወቅት ከሁለቱም ወገን በቀን ቢያንስ አሥራ አምስት ሰው ይሞት ነበር። ከአዲስ አበባ ቀጥሎ ብዙ ሰው የሞተው ከፋ፣ በተለይ ጂማ ከተማ ውስጥ ነው። እዚያም ኢሕአፓ ጠንክሮ ያለ ቡድን ስለነበራት በየቀኑ ሰው ትገድል ነበር፡፡ እኛ የሚመታ ኃይልም አልነበረን። እሷ ናት የሰው ሕይወት እንደቅጠል በየሜዳው ስታረግፍ የከረመችው። በሰሜን ምዕራብ ባሕርዳር ውስጥ እንደዚሁ የጎላ እንቅስቃሴ ነበራት። ሐረርጌ፣ በተለይ ሐረርና ድሬዳዋ ትንቀሳቀስ ነበር። ጎንደር ውስጥ ሰው መግደል የጀመሩት በኋላ ነው። ሌሎች ከተማዎችን ያየን እንደሆነ ናዝሬት አካባቢ እንደዚሁ ሰው ሞቷል። ከነዚህ ውጪ በደቡብም፣ በሰሜንም፤



በትግራይ፣ በኤርትራ ቢባል በቀይና በነጭ የተገደሉ ሰዎች ጥቂት ናቸው። ከፖሊስ፣ ከክፍለ ሃገራት፣ ከደህንነት ከየአቅጣጫው የሚመጣውን ሪፖርት እናያለን። አንድም ይሄን አሁን የማወራውን ቁጥር የሚያሳይ ነገር የለም።

ወታደሩ ጨርሶ እጁ የለበትም። ያለው በየግንባር ነው። እነማን ነበሩ ቀይና ነጭ ሽብር የሚያካሂዱት የተባለ እንደሆነ ቀበሌና የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። እነሱ ናቸው ይደባደቡ የነበሩት። እያንዳንዱ ድርጅት በየበኩሉ ያደረሰው ጥቃትና የደረሰበትን ጉዳት ያውቃል። ይሄ ተሰባስቦ እኛ ጋ ይቀርባል።እኛ የምናውቀው አኃዝና አሁን የሚነገረው የምድርና የሰማይን ያህል ይራራቃል። ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ውስጥ ዓይነተኛ ቦታ ተሰጥቶት ለባለሥልጣኖቹ ዋና መክሰሻ ሆኖ የመቅረቡ ጉዳይ አንድ ቀን ታሪክ እውነቱን ሲገላልጠው ብዙ ሰዎች አንገታቸውን የሚደፉበት ሁኔታ ይፈጠራል።

*ገነት - በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ የገቡ ብቻ ሳይሆኑ ምኑም ውስጥ ያልነበሩ ንፁሐን ሰዎች እኮ በርስዎ ወታደሮች ተገድለዋል።*

*መንግሥቱ* - ወታደሩ ጨርሶ እጁ የለበትም። ያለው በየግንባሩ ነው። እነማን ነበሩ ቀይና ነጭ ሽብር የሚያካሂዱት የተባለ እንደሆነ ቀበሌና የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። አብዮት በሚፈነዳበት ጊዜ ትንሽ የሥርዓት መላላት የታየ እንደሆነ፣ አንዳንዶቹ የሚፈጠረውን አገጭ አጋ ተጠቅመው የፈለጋቸውን የሚሠሩበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይሄ በሌሎችም አገሮች ታይቷል። በአጋጣሚው ተጠቅመው የመሰላቸውን የሰሩ አሉ። ለምንና በማን እንደተገደለ በውል ሳይታወቅ በአብዮት ስም የተረሸነ ምልቷል። ዱሮ አጥር የተጋፋውን ሁሉ በግል ቂሙን ለመበቀል አጋጣሚውን ተጠቅሞ የገደለ ይኖራል።

*ገነት - በርሶ ስባባል በዚያ ወቅት የደረሰው ደም መፋሰስ የማን ኃላፊነት ነው? ማነው ተጠያቂው?*

*መንግሥቱ* - ለዚህ ኃላፊው ማነው? የተባለ እንደሆነ፣ እኔ መጀመሪያ የማቀርበው ኢሕአፓን ነው።ስሕተቱ የመጣው ከኢሕአፓ ነው። ለምን ቢባል የኢሕአፓን ታሪክ ከሥር ጀምሮ ማየት ያስፈልጋል። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ «አዞ» የሚባል ሕቡዕ ቡድን ተቋቁሞ ጥቂት ታጋይ ተማሪዎች ማርክሲዝምን ለማጥናትና በተማሪው መሐከል አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመፍጠር ተነሱ። ከዚያ በኋላ የተማሪው ንቅናቄ ሕዝባዊ ወገናዊነትና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም አቋም ያዘ። ቀስ በቀስ የግራ ፖለቲካ ማራመድና በፊት ለፊት ደግሞ ከፊውዳሉ መንግሥት ጋር በመጋፈጥ ትግሉን በተያያዘ ጊዜ መንግሥት ተማሪውን በተለያየ መልክ መቶታል- በእስራትም፣ በግድያም። በዚህ ከተጠቁት መካከል አንዳንዶቹ ወደሰሜን አሜሪካና ወደአውሮፓ የተሰደዱ ተማሪዎች ነበሩ። እነዚህ በነበረው መንግሥት ላይ የመረረ ቂም ይዘው ነበር። ከመካከላቸው ያንን መንግሥት በትጥቅ ትግል መጣል አማራጭ የለውም ብለው ያመኑ ነበሩ።በወቅቱ ከነሱ የትግል

መሥመር ጋር የሚቀራረብ፣ ጠመንጃ አንግቦ መንግሥትን የመፋለም ነገር የሚታየው በኤርትራ ስለነበር ‹ለኤርትራ የትጥቅ ትግል ድጋፍ መስጠት አለብን› ማለት ጀመሩ:: በዚህ ዓይነት ከኤርትራውያኑ ጋር ተባብረን ብንታገል የኃይለሥላሴን መንግሥት ውድቀት ያፋጥንልናል የሚለው አቋም በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ መንሰራፋት የጀመረው ገና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር::

ይህ የሁሉም አቋም አልነበርም:: ‹የፊውዳሉን መንግሥት ለመጣል ብለን የአገርን አንድነት ከሚጋፋ የውጪ እጅ ካለበት ተገንጣይ ኃይል ጋር ተባብሮ መገኘት በፖለቲካ ዓለም ራስን መግደል ነው:: በኤርትራ የመገንጠል ትግል ከሚያደርጉ ጋር መሰለፍ የለብንም› በማለት አጥብቀው የተቃወሙ ነበሩ::

እነዚህ የተለያየ አቋም የያዙ ቡድኖች አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ የጀመሩትን ቅራኔ ይዘው ነው እንግዲህ በኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ ጊዜ ወደኢትዮጵያ የመጡት:: እጅግ አሳዛኙ ሁኔታ ይህ ነው:: ‹ተምረናል፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሩኅ ተስፋን እንገነባለን› ብለው የመጡት እነዚያ ወጣት ምሁራን ሕዝቡ መካከል መጥተው እርስ በርሳቸው መጨፋጨፍ ጀመሩ:: ማርከሻ ሊያገኙለት ያልቻሉትን መርዛቸውን ከውጪ ይዘው መጥተው ሕዝብ መሐል ረጩት:: ያለ አግባብ ያሰፉትን ቅራኔያቸውን ሊያቆሙት ካለመቻላቸው ሌላ ከጠላት ጋር አብረው በመገኘት ከኛ ጋርም መቆራቆስ ጀመሩ:: እኛ ወታደሮች ነን:: የአገርን ድንበርና አንድነት ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ ነገር መደራደር አንችልም:: ድርብ ኃላፊነት ነው ያለብን:: ወይ መለዮአችንን አስቀምጠን መውጣት፣ ኃላፊነታችንን ማውረድ ነው ያለብን፤ ወይም ላገራችን አንድነት መዋደቅ አለብን:: ሦስተኛ አማራጭ የለንም::

ኢሕአፓ ጦርነቷን «ሀ» ብላ የከፈተችው እኔን ለመግደል ሙከራ በማድረግ ነው::ሊገድለኝ አዲስ አበባ ድረስ የመጣው ኤርትራ ውስጥ የሰለጠኑ የኢሕአፓዎችና የሻዕቢያ ነፍሰገዳዮች በአባልነት የሚገኙበት ቡድን ነው:: ከዚያ በኋላ እነሱን የተቃወመና አብዮቱን የደገፈውን ንፁሑን ነዋሪ ሁሉ እየገነጠሉ መግደል ጀመሩ:: የቀበሌ ተመራጮችን፣ የደርግ አባሎችን፣ ምንም ውስጥ የሌሉ ንፁሐን ዜጐችን፣ ወንድ ሴት ሳይለዩ ‹ጠላት ነው› ብለው የፈረጁትን ሁሉ ይረሽኑ ጀመር::

***ገነት - የጥይት ዋጋ መከፈሉንስ አያውቁም?***

***መንግሥቱ*** - አላውቅም:: ይሄንን እኔ እዚህ ከመጣሁ የሰማሁት ነው::እንደዚህ ያለ ነገር ስሰማ ለመሆኑ «ይሄንን ነገር ሰምታችኋል?» እያልኩ ባካባቢዬ ያሉትን ሰዎች (አሁን) እጠይቃለሁ:: ሰው ተገድሎ ሬሳ የሚሰጠው በጥይት ዋጋ ነው የሚባለውን ነገር... እኔ እንዳው ... በጠቅላላው ያኔ በሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ቢጠየቁ ማወቃቸውን እጠራጠራለሁ:: ለኔም ባዕድ ነው:: እንደዚህ ያለ መመሪያ ከኛ አካባቢ ይወጣል ብዬ አላምንም:: አንቺ ራስሽ እስር ቤት ላሉት ለኛ ባለሥልጣኖች ቃለ መጠይቅ አድርገሽላቸዋል አይደለም? እንዳው በዚያ



ካየሻቸው ሰዎች እንዲህ ያለ መመሪያ ይወጣል ብለሽ ታምኚያለሽ? እንዴ! አብዮቱ ካምፕ ውስጥ የነበሩት ሰዎች እኮ አረመኔዎች አይደሉም:: ለሃገርና ለሕዝብ መብት ለመዋደቅ ቁርጥ ዓላማ አድርገው የተነሱ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው:: እነሱ የጥይት ዋጋ እንዲከፈል አድርገዋል የሚለው ነገር መታሰቡ ራሱ ይገርመኛል:: ከኛ መካከል ይሄንን የመሰለ ግፍ የፈፀመ ይኖራል ብዬ አላስብም:: ሊሆንም አይችልም:: ምን ዓይነት ሕሊና ነው?

*ገነት - አይ እሱ እንኳን በትክክል ተደርጓል::*

*መንግሥቱ* - ቀበሌዎቹ ናቸዋ! ምን ይደረግ? እንግዲህ ማነው የሚከሰሰው?

*ገነት - ደርግ ነዋ::*

*መንግሥቱ* - አይ...ይ ይሄ እንኳን ትክክል አይደለም:: እኛ ለራሳችን ያኔ ከሻዕቢያና ከሶማሌ ጋር እየታገልን ነበር::

*ገነት - ሬሳ የሚጣለውንስ አያውቁም ነበር ወይ?*

*መንግሥቱ* - አዎ፣ ሬሳ ይጣል ነበር:: የታሪካችን ጥቁር ነጥብ ነው:: መካድ አይቻልም:: ግን እነሱ ስላደረጉት እኛም አድርገናል ለማለት ሳይሆን ይሄ በሁሉም ወገኖች ተደርጓል::ኢሕአፓም ብትሆን ከገደለች በኋላ መፈክሯን ጽፋ እየለጠፈች ሬሳ ጥላለች:: ከወዲህም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጥሏል:: የዚያን ጊዜ የተያዘው እኮ እብደትና እልህ ነው:: በጣም የተጫጫሰ ሁኔታ ውስጥ ነው የነበርነው:: ወጣቱ፣ አዛውንቱ የየቀበሌው ነዋሪ ሁሉ በውነቱ በተፈጠረው ነውጥ ሰክሯል:: አሮጊቱ፣ ባልቴቱ ሁሉ ዘፈን እያጠና ‹ማን ይፈራል ሞት!› እያለ እየዘፈነ ሲወጣ! የኡኡታ ኮሚቴ በሚል እየታቀፉ የአዲስ አበባ ሴቶች ወገን ለይተው ወጥተዋል::

አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል በዚያን ወቅት የአሜሪካን ኮንግሬስ አባሎች መጥተው ስለዚህ አነሱብኝና ቁጭ ብዬ አስረዳኋቸው፤ «በውነቱ ያለብንን ችግር፤ ያለውን ሁኔታ ተረዱልኝ:: በኛ ፍላጎትና ፈቃደኝነት የሚካሄድ ሳይሆን በእንደዚህ ያለ ለውጥ ውስጥ የሚፈጠር ችግር ነው:: ከቀን ወደቀን እየቀነሰ፣ እየሰከነ፣ እየተረጋጋ ይሄዳል፤ እና ችግራችንን ተረዱልን» ብዬ አሳምኛቸው ያን ለታውኑ ወደኤርፖርት ሲሄዱ ሬሳ ወድቆ ያያሉ::

እንግዲህ ሕዝቡ አብዮቱን ለመጠበቅ በየከተማው፣ በየገጠሩ ሲደራጅና የአብዮት ጥበቃ ጓዶችን ሲያቋቁም በአንዳንድ ቦታዎች ይሄን ቦዘኔውንም፣ ዱርዬውንም ምናምኑን ሰብስበው፣ ‹ና! ገንዘብ እንሰጥሃለን:: በሳምንት ይሄን ያህል ታገኛለህ› ብለው ሲያበቁ ጠመንጃ እንዲያነግት ያደርጉታል:: ታዲያ ከንደዚህ ያለ ሰው ምን ይጠበቃል?

***ገነት - በቀበሌ አካባቢ የነበሩት ማለትም ነው?***

**መንግሥቱ** - እዎን።

*ገነት - እና እናንተ ምን ይደረግ እንደነበር አታውቁም ማለት ነው?*

**መንግሥቱ** - እኛ ምን ፋታና ጊዜ አለን?

*ገነት - እርስዎ ከተማ ውስጥ ይካሄድ እንደነበር አያዩም ነበራ?!*

**መንግሥቱ** - እኔ ምን ጊዜ አግኝቼ ነው ከተማ የምወጣው። ይልቅስ ለዚህ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገ የደርግ አባል ነበረ። አዝናለሁ፤ ዛሬ በሕይወት የለም። የደርጉ የደህነት ኃላፊ ጓድ ተካ ቱሉ። ከተማውን ይዞርና የሆነውን ሁሉ አይቶ ሲያበቃ ስብሰባ ላይ እጁን ያወጣና ‹ጎበዝ! ይሄ ነገር እንዴት ነው? በፀረ-አብዮተኛ አታስፈጁን ስለተባለ፤ ራስን ለመከላከያ ቀበሌውን ሁሉ ጠመንጃ አስታጠቅን። አሁን እየተሠራ ያለው የሚያሳዝን ነገር ነው። በቂም በቀል፤ መኪናውንም ለመንጠቅ፤ ሚስቱንም ለመቀማት፤ አጥርም በመጋፋት የተጣላውን ሁሉ ጊዜና ሁኔታ ያመቸው እየተነሳ የፈለገውን የሚያደርግበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሄ ከሆነ ምኑን አብዮት ተካሄደ። ካለፈው ሥርዓትስ በምን እንሻላለን? ምን እያራመድን ነው?› በማለት አምርሮ ከተናገረ በኋላ ‹እንዲህ፤ እንዲህ ያለ ነገር እየተካሄደ ነው?› ብሎ ዝርዝር ያለ መረጃ አቀረበ። ተካ ቱሉ ፖሊስ ነው። ከደህንነትም፤ ከፖሊስም መረጃ አሰባስቦ ነው ይሄንን የደረሰበት።

ከዚያ በኋላ እንግዲህ ሁሉንም ሰበሰብንና መኢሶኖቹንም፤ ሌሎችንም «አይ! ገደብ አልፋችኋል። ኢሕአፓ መጨረሻ ላይ እርቃኗን የቀረችውና ሕዝቡ ተፍቶ የጣላት በተግባሯ ነው። አሁንስ እናንተ ምን እያደረጋችሁ ነው? ይሄ ነገር መቆም አለበት። ካሁን በኋላ ማንም ሰው ቢሆን ወንጀለኛ አገኘሁ ሲል ለአጥቢያው ፖሊስ ማቅረብ እንጂ ራሱ እርምጃ መውሰድ አይችልም» ብለን ወሰንን። አከታትለን ወዲያውኑ ማሻሻያ ሕግ አወጣን። ለየቀበሌው ሁሉ ካሁን በኋላ በፍፁም በሰው ሕይወት ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት እንደሌላቸው በመግለፅ ኃላፊነታቸውን የሚወስንና የሚያከናውኑትን የሚያብራራ ሕግ አውጥተን ይፋ አደረግን። እነሱ ማድረግ የሚችሉት በበቂ ማስረጃ እጅ ከፍንጅ ከያዙም ለፖሊስ ወስደው ማስረከብ አለባቸው። ፍርድ ቤቶች ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ ማስተናገድ ስለማይችሉ ለቀበሌዎች ለተወሰነ ጊዜ የማሰር መብት ሰጥተናቸዋል።

*ገነት - ሬሳ መንገድ ላይ መጣሉን ያስጣሏቸው ፊደል ካስትሮ ናቸው የሚባለው እውነት ነው?*

**መንግሥቱ** - አይ ውሸት ነው። ይሄ ሁኔታ ባንድ ወቅት የተካሄደ ጉዳይ ነው። ሦስት ወር ያህል ነው እንደዚህ ትርምስምሱ የወጣው። ከዚያ በላይ አልሄደም። ከዚያ በኋላ ከውጪም ጫጫታ ሲበዛና በአብዮቱ ላይ ጠባሳ እየጣለ ሲመጣ የደርጉ የደህንነት ኃላፊ ተካ ቱሉ ተንቀሳቀሰ። በአዎንታዊ መንገድ፤ በነቃ ሁኔታ የሚጓዝ በጣም የሰከነ



ሰው ነው። ሁኔታውን ዞሮ አይቶ ካጣራና ከገመገመ በኋላ ‹□ረ ትንሽ ከመሥመር የወጣ ነገር ሳይካሄድ አልቀረም። በአብዮቱ ስም ማንም እየሄደ የፈለገውን የሚገልበት፤ መኪና የሚቀማበት፤ ባጠቃላይ የፈለገውን የሚያደርግበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነውና አንድ ነገር መደረግ አለበት› አለ። የእኛን በሥራ መወጠርና የኛን ድክመት በማየት አጋጣሚውን የሚጠቀሙ ሰዎች መፈጠራቸው ገባን። እንደገና የቀበሌ መዋቅር ተገምግሞ ተለወጠ። አዲስ ሕግ ወጣ። የአብዮት ጥበቃ ጓዶች ንቃተ ሕሊናቸው ተገምግሞ በቂ ሥልጠና ከተሰጣቸው በኋላ መሣሪያ እንዲያነግቡ ተደረገ። ከዚያ በፊት በተፈጠረው አጣዳፊ ሁኔታ ጠመንጃ ተቀብሎ ያሻውን ያደርግ የነበረው ቀረ።

*ገነት - ያም ቢሆን በቀይ ሽብር ጊዜ ስህተት እንደተሠራ ያምናሉ?*

**መንግሥቱ** - ሥጋ መሬት ላይ ወድቆ አፈር ሳይነካው ይነሳል እንዴ? የምንሠራው እኮ እንዲህ በተዝናና ሁኔታ አልነበረም። አበሻ ሲተርት ‹እዬዬ ሲዳላ ነው› ይላል። አብዮት እኮ ነው ያካሄድነው። በጣም ሥር ነቀል የሆነ የሕዝብ አመፅ ነው። ነውጥ ነው። ስንት አገርና መዋቅር እንደፈራረሰ ታውቃላችሁ? ስንት ትርምስ ነበር? ስንት መዋደቅና መጣል ነበር? ስሕተት አልተሠራም ማለት አይቻልም።

*ገነት - አንዳንድ የደርግ አባላት በፈፀሙት አሠቃቂ ወንጀል ስማቸው ጎልቶ ይጠራል። ለምሳሌ፣ እነመላኩ ተፈራን የመሳሰሉ ሰዎች በጎንደር ብዙ ወጣቶች ጨፍጭፈዋል። እንዳውም ሰው በገደል ሁሉ ይጥሉ ነበር ይባላል። ስለዚህ ምን ይላሉ?። ይሄንን በፊትም ያውቁ ነበር፤ ወይስ አሁን ነው የሰሙት?*

**መንግሥቱ** - የለም። በገደል መጣልና የመሳሰለ ነገር አንደኛ አልሰማሁም። ተደርጓል ብዬም አላምንም። መላኩ ተፈራ በርግጥ ኃይለኛ ልጅ ነው። ትዕግሥቱ ውሱንና ወደወታደራዊ ባህርይ የሚያደላ ነው። ይሁን እንጂ እሱ የነበረበት የጎንደር ክፍለ ሃገር ለኢሕአፓ፣ ለሻዕቢያና ለወያኔ ቤዝ ከነበረው ከሱዳን ጋር ይዋሰናል። እንዲሁም ለትግራይ፣ ለኤርትራ ባለው ቀረቤታ ትልቁ ምሽጋቸው ነበር። ባንድ ወቅት ጎንደር በጣም አስቸጋሪ የሆነ ከፍተኛ ሽብር ተካሂዶበታል። ትምህርት ቤቶች ነደዋል። ክሊኒኮች ተቃጥለዋል። ሕዝቡ ተዘርፏል። ተገፏል። እዚያ የነበሩ የፀጥታ አስከባሪዎች በሙሉ እንዳሉ ተጨፍጭፈዋል። አንድ ፖሊስ ለወሬ ነጋሪ የተረፈ የለም። የክፍለ ሃገሩን አስተዳዳሪ የጓድ ካሣ ገብሬን ወንድም በሚያሳዝን አኳኋን በጦር ጨቅጭቀው ገደሉት። በየቦታው የታረደው ሰው ቁጥር አይወሳም። ስንት ታጋይ ሞተ? ስንት ሰው በጎንደር ከተማ ውስጥ ወደቀ? ስለነሱ ጠይቃችኋል?

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ «አንተ ትወለድበታለህ። የሕዝቡን ባህል ታውቃለህ።ሂድና ታገል» ብለን ነው የላክነው።ስለዚህ መከላከል ነበረበት። ወያኔ አለ። ሻዕቢያ አለ። ኢዲዩ አለ። ኢሕአፓ አለ።

ከተማው ትብትብ ብሎ ግራ የተጋባ ሁኔታ ውስጥ ነው የላክነው
መላኩን:: እንዴ! አንድ ኮር ሠራዊት እኮ ነው ለመላክ የተገደድነው::
ከኤርትራ እኩል:: ከዚያ በፊት እሱ ብቻውን ነበር የሚታገለው:: ከሱ
ምን ነበር የሚጠበቅበት? መሞት? እጅ መስጠት? ጥቃት የደረሰባ
ቸው ሰዎች ቤታቸውን እየለቀቁ እየመጡ በደርግ መሥሪያ ቤት
ዙሪያ መሬትና ሲሚንቶ ላይ እያነጠፉ ሲተኙ ምንድነው ማድረግ
የነበረበት? እና እሱ ተዋግቷል:: በኃይል! ልክ እነሱ እንደሚያደርጉት
እሱም ቆራጥ እርምጃ ወስዷል:: ነገር ግን ቁጥሩ እነሱ ከፈጁት ጋር
ይተካከላል ወይ? ነው መሆን ያለበት ጥያቄው:: በጋይንት ያለቀውን
ሕዝብ ደግሞ በደሴ ኮታ በር ያለቀውን ብቻ ብንቆጥር ባጠቃላይ
የኢትዮጵያ አብዮት በፀረ-ሕዝቦች ላይ በወሰደው እርምጃ ከተመቱት
ቁጥሩ እጥፍ ነው:: እጥፍ:: ይሄንን እቦታው ላይ ሂጂና ጠይቂ::
ስንት ሰው ነው ያለቀው? ስንት ቤት ነው የፈረሰው? በይና ጠይቂ::
እንዳው ባጠቃላይ አብዮቱ እንኳን መጣልን፣ የመሬት አዋጁን
እንደግፋለን ያለውን ሁሉ እኮ ነው የጨፈጨፉት:: መላኩ ተፈራን
እኮ እዚያ እሳት ውስጥ ነው የጨመርነው::ዛሬ ያም እየተነሳ መላኩ፣
ያም እየተነሳ መላኩ ይላል:: መላኩ ምን ያድርግ?

*ገነት - አሊ ሙሳስ?*

*መንግሥቱ* - በባሌ ብትይ እንደዚያ ነው:: ኢሕአፓው፣ የኦሮሞ
ነፃ አውጪ ነኝ የሚለው፣ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ነኝ የሚለው
ሠርጎ እየገባ ጠቅላላ ሃገሩን በቁጥጥር ሥር ባዋለበት ጊዜ አሊ
ሙሳን ላክን:: አሁን እሱ እዚያ ሄዶ የከፈለው መሥዋዕትነት፣ ያደ
ረገው ተጋድሎ ኢትዮጵያን አድኗል:: በዚያን ወቅት አንዳንዶቹን እን
ኳን ይሄንን የመሰለ ኃላፊነት መውሰድ ቀርቶ «ኑ ሚኒስትር እናድር
ጋችሁ፣ ኑ እንሹማችሁ» ብለን ስንጠይቃቸው ፍርሃት እንደወባ በሚ
ያንቀጠቅጣቸው ጊዜ «ሂድ!» ነው ያልነው አሊ ሙሳን:: ወታደር
የለን:: ምን የለን:: የነፍስ ወከፍ ጠመንጃ አስይዘን «ሂድና ሙት»
ነው ያልነው:: ታግሎ አታግሎ አገሪቱን ካዳነ በኋላ ዛሬ በየድራፍት
ቤቱ ቢራቸውን እየጠጡ ግለሰቦች ላይ የሚዘምቱ ሰዎች የሚያስወ
ሩት ወሬ ገኖ ይሰማል እንጂ፣ ‹ይህ ሰው ያን ጊዜ በምን ዓይነት
ኃይል ተከቦ ነበር? እሱስ ምን ኃይል ነበረው?በምን ዓይነት ቆራ
ጥነትና ወኔ ነው የተዋጋው? ከወዲያ ስንት ሰው ሞተ? ከወዲህስ?
ሕዝቡ ምን ተስፋ ነበረው?› ብሎ ማንም አይጠይቅም:: ይሄን የሚያ
ወሩት መጀመሪያ ነገር ቦታውንም አያውቁትም:: አዲስ አበባ ቁጭ
ብለው ነው ይሄን ሁሉ ወሬ የሚፈበርኩት:: የተከፈለውን መሥዋዕት
ነትም አያውቁትም:: ያ ባይሆን ኖሮ የሃገሪቱ እድል ምን ይሆን
ኖሯል? የሚለውንም ማገናዘብ አይፈልጉም::

በከፋ በኩል የነበረው ጓድ ተሰማ በላይ፣ በወለጋ የነበረው ጓድ
ንጉሤ፣ ጓድ ካሣዬ በሐረርጌ፣ በኋላ ደግሞ ጓድ ዘለቀ በየነ እነኚህ
ሁሉ በዚያን ቀውጢ ወቅት የነበረባቸው ፈተና በጣም አስቸጋሪ



ነበር:: ሕዝቡ ነው እየተነሳ የሚጮኽባቸው:: ‹አስጥሉን› እያለ እንቅ
ልፍ የሚነሳቸው:: ‹በዚህ በኩል እገሌን ገደሉት:: በዚህ በኩል እገሌ
ወደቀ:: መንግሥት ምንድነው የሚጠብቀው? አለቅን:: ለማን አቤት
እንበል› ሲሏቸው? ያለውን ሰው ይዘው ሄደው ሲያበቁ ታግለዋል::

ስለመሆኑ እነዚህ ሁሉ የዛሬ ተወንጃዮች፣ የደርግ አባላትም፣
ሌሎች አብዮተኞች ሰው በመግደል ምንድነው የሚያገኙት? የገደ
ሉትን ይበላሉ እንዴ? ታሪክና ጊዜ ለዚህ ቦታ ዳርጓቸው ነው እንጂ
መጀመሪያ ከቤታቸው ሲወጡ ለዚህ ዓላማ መሰለፋቸውን፣ ከነማንስ
ጋር እንደሚፋለሙ አስቀድመው ያውቁ ኖሯል እንዴ? ዛሬ የሚወ
ነጅሏቸው እያንዳንዳቸው እነሱ ቦታ ቢቀመጡ ኖሮ ምን ያደርጉ
ኖሯል? የነበራቸው አማራጭ እጃቸውን መስጠት ወይም ደረታቸውን
ለጥይት ሰጥተው መጋተር::ይሄው ነው:: ሌላ አማራጭ አልነበረም::
የሠሩትም ይሄንኑ ነው:: ይሄ ደግሞ እነሱ የፈጠሩት ሁኔታ ሳይሆን
የኢትዮጵያ የዘመናት ታሪክ ውጤትና የአብዮቱ ባህርይ ያመጣው
ነገር ነው::

እነኚህ «መክቱና አድኑ» ብለን የላክናቸው፣ የነፍስ ወከፍ ጠመንጃ
እየሰጠን የላክናቸው ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነበር የሚጠበቅባቸው?
ሌላው ቦታ ሩቅ ቢሆንባቸው አዲስ አበባ የነበረውን ሁኔታ አያውቁም
እንዴ? እንዴት ነበር ሁኔታው? እንዴ በቴሌቭዥን የታየው ትዝ
ይልሻል? ቴዎድሮስ በቀለ የሠራተኛው መሪ በሞተ ጊዜ የወጣው
ሕዝብ? የሕዝቡ እንባ! የሕዝቡ ቁጣ! አዝናለሁ:: እነሱ እነሱን የመ
ሳሰሉ ነገሮች ዛሬ በእጄ የሉም:: የማንንም ልቦና ይሰረስራል- ለቅሶና
ቁጣው ...

የምኒልክ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበረውን መኰንን ሸገኔ
የሚባለውን (አካለስንኩል ነበር) በአንድ ጥይት እንኳን አይደለም፣
በስንት ጥይት ወንፊት አድርገው ጥለውት ነው የሄዱት...

ይሄ ሁሉ ሆኖ ሲያበቃ በኛ በኩል በደህንነታችን አማካኝነት እየፈ
ለግን መሪዎቹን ለማደን ከተደረገው ሙከራ በስተቀር ሠራዊቱ እጁ
የለበትም:: በሕዝብና በሕዝብ መካከል የተፈጠረ ፍልሚያ ነው::

*ገነት - እናንተ ናችሁ ደጋፊዎቻችሁን አበረታታችሁ ነፃ እርምጃ እንዲ
ወስድ የፈቀዳችሁት::*

*መንግሥቱ* - እሺ፤ እኛስ እንዲህ ተባልን:: ሌላውስ ምን ሲያደ
ርግ ነበር? ለምን የሌላው ወገን ስሕተት አይታይም? ኢሕአፓ በየ
ትኛው ሕግ ተመርታ ኖሯል ሰውን በጠራራ ፀሐይ እየደፋች ስትሄድ
የነ በረው? በየትኛው ፍርድ ቤት ብይን አግኝታ ነው ሰው ላይ እር
ምጃ ስትወስድ የነበረው?

*ገነት - እናንተኮ መንግሥት ናችሁ::*

*መንግሥቱ*- ብንሆንስ:: እኛ ቀድመን አንድ እርሳስ አላጮህንም::
በኔ ጀምረው ሹብሩን ለወራት ሲያካሂዱ ነበር - በተለይ ጄኔራል ተፈሪ

ከመጡ በኋላ:: ነገሩ ወደበኋላ ነው የተከሰተው:: የሳቸው ልጅ የኢሕአፓ አባል ሆኖ ተገኝቷል - ያይንእሸት ተፈሪ ይባላል:: እኔ ከል ጅነቱ ጀምሮ አውቀዋለሁ:: እሳቸው ‹ግድየለም መንግሥቱ አንድ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ትቅደም ብለሃል፤ ኢትዮጵያን አስቀድም እና ግድየለም› ሲሉኝ፣ እኔም በቅንነት ሌሎቹንም እያስታገስኩ፣ ነገሩን እያቃለልኩ እያለሁ እነሱ ከመሃላችን እየገነጠሉ መምታት ጀመሩ::

ተመስገን የሚባል የደርግ የፕሮፓጋንዳ ማሺን! እንዴት ዓይነት ልጅ! የፈጠራ ችሎታው፣ ፖቴንሻሉ እጅግ የሚገርመኝ እንዴት ያለ ልጅ! ... ገደሉት::

ገበያው ተመስገን ይባላል:: እዚያው በራችን ላይ ደፉት:: ንጉሤ ነጋሣ ይባላል:: እንዴት ዓይነት ልጅ! ገደሉት:: መሃከላችን ገቡ:: ሚኒስትሮቻችን ሥራ መሄድ አቃታቸው:: ሥራ የሚሄድ ጠፋ:: ግቢ ውስጥ ማደር ተጀመረ:: ፀጉር ለመስተካከል ከተማ ውስጥ አደገኛ ሆኖ ደርግ ግቢ ውስጥ ፀጉር አስተካካይ እስከማምጣት ደረስን:: ሻይ እንኳን ለመጠጣት ወደከተማ ጎራ ማለት በጣም የሚያሳስብበት ደረጃ ላይ ተደርሶ ካፍቴሪያ ግቢ ውስጥ አቋቋምን:: ምን ዋስትና አለ? ለእያንዳንዱ ሰው ቤት፣ መኪና፣ጠመንጃ መስጠት ነበረብን:: ራሳቸው መኢሶኖች ሁሉ:: ሁሉን በዘብ መጠበቅ አይቻል:: ወታደር የለን:: እንዴት እንሁን? በዚያ ሰዓት ኢሕአፓ አዲስ አበባን ከሞላ ጎደል ተቆጣጥራዋለች ማለት ይቻላል::

ከዚህ ለመውጣት በሕዝቡ ባጠቃላይ በተወሰደው እርምጃ ኢሕአፓን ለመግታት ተሞክሯል::በዚህን ጊዜ መሪያቸው (የኢሕአፓን) ተስፋዬ ደበሳይ አዲስ አበባ ፊሊፕስ ሕንፃ ላይ ተደብቆ ቁጭ ብሎ በኮሚኒኬሽን ነፍሰገዳዮቹን ከቦታ ቦታ እያንቀሳቀሰ ማስገደሉን ራሳ ቸው ኢሕአፓዎች ነገሩን:: ወታደር ልከን ሲከበብ፣ ከፎቁ ላይ ዘሎ ተፈጥፍጦ ሞተ::ከዚያ በኋላ የአዲስ አበባ ሁኔታ ተለወጠ:: ሕዝቡም እፎይ ብሎ ተነፈሰ::

እዚህ ላይ ሁልጊዜ የማይነሳ ወይም ሆን ተብሎ የሚዘለል ጥያቄ አለ:: ኢሕአፓ ሠርጎገቦችና ከሞላ ጎደል የከተማ ትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ፣ለዚያውም በሚሰጣቸው ሊስትና ጥቆማ ዒላማ የሚመቱ የተወሰኑ ወጣቶችን በከተማ ውስጥ ስታስማራ ከተከታዮቿ የሚበል ጠው ኢትዮጵያን ለማጥለቅለቅና መንግሥትን ለመገልበጥ የተሰበሰ በው ኃይሏ የሄደው ትግራይ አሲምባ ነው:: የት ሄደ? ያ ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣት የት ደረሰ? ማን ፈጀው? ይሄንን የጠየቀ ሰው አለ? የኢሕአፓ ዋናው ሠራዊት የነበረው ትግራይ ነበር:: አሲምባ የከተ ተው ያ ሁሉ የት ደረሰ?

ልጆቹ የኢሕአፓን ዓላማ ለማራመድ ትግራይ ሲሄዱ ያልገባቸው ነገር አለ:: እነሱ አብዮት የሚያካሂዱ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታ ገሉ ነው የመሰላቸው:: ብሔራዊ ስሜት የነበራቸው ናቸው:: እዚያ ሲደርሱ ግን ያጋጠማቸው ጀብሃና ሻዕቢያ ነበር:: ኢትዮጵያ ብሎ ነገር በአጀንዳቸው የሌለ ፍፁም ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ አቋም ያላቸው



ገንጣዮች:: እንዴ? ምንድነው ይሄ ነገር? የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ‹እሃ! ይቺ ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቆረጠምም› ተብሎ በወያኔ ሠራዊት ተጨፍጭፈዋል:: እተኙበት ቦታ... ሰ... ሽ ብለው እንደተኙ ሌሊት በደንብ በተዘጋጀ ሠራዊት ጭፍ ... ጭፍ አድርገው ፈጅተዋቸዋል:: በዚህ ዓይነት በግፍ ያለቁት ቁጥር ስንት ነው? ይህን ያነሳ አለ? መለስ ዜናዊ ኢሕአፓ እያለ ተቆርቋሪ ሆኖ ሲናገር ግርም ነው የሚ ለኝ:: ወደደም ጠላም ሕሊና ካለው ዛሬ ለሕሊና ፍርድ፣ ነገ ደግሞ ለሕዝብ ፍርድ መቅረቡ የማይቀር ነው:: የትግራይ ሕዝብ ይሄንን ያውቃል:: ኢሕአፓዎች ሁሉም አላለቁም፤ ቢጠየቁ ይናገራሉ::

*ገነት - እና እርስዎ የሚሉት ወያኔ ነው የፈጃቸው ነው?*

*መንግሥቱ* - ታዲያስ! ወያኔና ሻዕቢያ ባንድነት ነው የፈጇቸው:: ‹እኛ አሰልጥነንና አስታጥቀን ለዚህ ስናበቃቸው የኢትዮጵያን አንድ ነት ይጠይቃሉ እንዴ?› ብለው ነው ሙልጭ አድርገው ያጠፏቸው:: እኛ እንደሆነ መጀመሪያ ነገር አሲምባ ሠራዊት የሚባል አልነበረ ንም:: እዚያ ሄደንስ እናውቃለን እንዴ? የኛ ሠራዊት የዚያን ጊዜ ያለው ምፅዋና ባሬንቱ ነበር::

*ገነት - በቦታው ካልነበራችሁ እንዴት አወቃችሁ?*

*መንግሥቱ* - ከብዙ ድካም በኋላ መጥተው በቀጥታ እኛ ጋ ነው የገቡት:: አንዳንዶቹ ከሠሩት ሥራና ከገቡበት ጣጣ አንፃር ምህረት አናገኝም ብለው በመጠራጠር ብቻ በየጫካው ሲናውዙ ከቀሩት በስተቀር በቀጥታ መጥተው እጃቸውን ሰጡ:: ‹እኛ አብዮተኞች ነን:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብለን ነው የተነሳነው:: የተሳሳተ አመራር ሥር ነው የወደቅነው:: ተረሸንን:: ተጨፈጨፍን:: ለዚህ አልነበረም እዚያ የሄድነው:: ተሳስተናል:: የአመራራችን ስሕተት ከሕዝብም አጋጭቶ ናል:: ከናንተም አጋጭቶናል:: ይቅርታ ይደረግልን› ብለው ወደኛ ገቡ:: እነኚህ ሰዎች ተመልሰው የአብዮቱን ካምፕ ተቀላቅለዋል:: ከመካከላቸው ከፍተኛ ሥልጣን ድረስ የደረሱ አሉ:: አንዳንዶቹ እን ደውም ዛሬ በወያኔ ታስረው ከሚገኙት ውስጥ አሉ:: ለማጠቃለል እኔ ስሕተት አልተሠራም አልልም:: በሁሉም በኩል ጥፋት አለ:: ነገር ግን ነገሩ ለምን ካንድ ወገን ብቻ ይታያል? ነው የምለው:: ለምን ታሪኩ፣ ወቅቱ አይመረመርም? ለምን የሕዝቡ ስሜትና በዚያን ጊዜ የነበረው ሁኔታ አይገመገምም? በምን ዓይነት ኃይል ነው የተከበ ብነው? እኛ ስንት ነበርን? ያንድነት ፀሮች ቀደም ሲል በመደራጀታ ቸውና መሣሪያ በመታጠቃቸው ምን ያህል ጥቃት ነው በሕዝቡ ላይ ያደረሱት? ይሄን ሁሉ ማገናዘብ ያስፈልጋል::

*ገነት - ኃይሌ ፊዳስ? በነሐሴ፣ 1970 ተይዞ ከአንድ ዓመት በኋላ ነገር ከበረደ፣ ሁሉ ነገር ከተረጋጋ በኋላ ነው የተገደለው:: በዚያን ጊዜ የኃይሌ ፊዳ በሕይወት መኖር መንግሥትን ያሠጋ ነበር?*

መንግሥቱ - መቼ ነው የሞተው ኃይሌ ፊዳ?

ገነት - በሐምሌ፣ 1971 ነው::

መንግስቱ - ማነው የገደለው?

ገነት - እኔ ምን አውቃለሁ:: አስከሬኑ ከቀድሞው የራስ እሥራተ ካሣ ግቢ ነው ተቆፍሮ የወጣው:: እዚያ ነው የተገኘው::

መንግሥቱ - ኃይሌ?

ገነት - አዎን:: ኃይለ ፊዳ::

መንግሥቱ - እዚያ ምን ሲሰራ?

ገነት - እዚያ ነው አስከሬኑ የተገኘው::

መንግስቱ - እኔ አላውቅም::

ገነት - መሞቱንም አያውቁም? እሱንም እዚህ ከመጡ ነው የሰሙት?

መንግሥቱ - መኢሶኖች እኮ ጥለውን ሄደዋል:: የሶማሊያ ጥቃት መንግ አይሎ ሲመጣ የሻዕቢያዎች ጎራ ስለጠነከረ 'ከዚህ ከደከመ ሥት ጋር ምን እንሠራለን?' ብለው አይደል እንዴ ጥለው የነጎዱት:: በነሱ ሃሳብ እኛ በመዳከማችን ወደፊት ከኛ ጋር በመቀጠል የሥልጣን ጥማታቸውን የሚያረኩበት መንገድ ስለማይኖር ልዩ፣ ልዩ ምክንያት ሲያቀርቡ ቆይተው በመጨረሻ ፈርጥጠዋል:: በዚህን ጊዜ እነመስፍን ካሡ ወደሲዳሞ፣ እነኃይሌ ፊዳ ወደወለጋ ሲሄዱ አግኝቶ ገበሬ ነው የከለከላቸው::

ገነት - እዚያ ነው የተገደሉት?

መንግስቱ - በሙሉ!

ገነት - ዶክተር ንግሥት አዳነስ?

መንግስቱ - እሷም፤ ሁሉም::

ገነት - ከእሥራተ ካሣ ግቢ ነው እኮ ሬሳቸው ተቆፍሮ የወጣው::

መንግሥቱ - ያሥራተ ግቢ የመድኃኒት ግምጃ ቤት ነው እኮ:: እዚያ ግቢ ምን ሊያደርጉ ይሄዳሉ? ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከውጪ ሃገር የሚያመጣቸውን መድኃኒቶች ለማስቀመጫ ጠይቆ ተሰጥቶት ለዚህ እንደሚገለገልበት ነው እኔ የማውቀው:: ሰው አይኖርበት፤ ምን የለበት::

ገነት - አባይ ሺየሱስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ያለውን ነው እኮ የምልዎት::

መንግሥቱ - አንድ አይደለም እንዴ የአሥራተ ካሣ ቤት? ቤቱን እኔ ቦታው የት እንደሆነ አላውቀውም:: እኔ የማውቀው የአሥራተ



ካሣ ቤት ለመድኃኒት ግምጃ ቤትነት ተጠይቆ መፈቀዱን ነው:: አሁንም ሄደሽ መጠየቅ ትችያለሽ::

ገነት - እንዴ! እኔ ሠፈሬ ነው:: በደምብ አውቀዋለሁ:: ሬሳቸው ከዚያ ወጥቷል::የአቡነ ቴዎፍሎስም፣ የነኃይሌ ፊዳ፣ የዶክተር ንግሥት፣ የነደጃዝማች ሐረጎት፣ የደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ...

መንግሥቱ - (በማቋረጥ) የለም፤ ግዴየለም እሱን ተይው:: አንቺ በግምትሽ ኃይሌ ፊዳን እዚያ ምን ይወስደዋል? የሱን አፅም እዚያ ምን ይወስደዋል?

ገነት - ታስሮ ነዋ! ያቡነ ቴዎፍሎስም፣ የሱም፣ የሌሎችም...

መንግሥቱ - የአሥራተ ካሣ ቤት ማሠሪያ ነው?

ገነት - አ - ዎን

መንግስቱ - ስንት ግቢ ነው ያላቸው?

ገነት - አባይ በግብፅ ኤምባሲ አድርገው ወደኢየሱስ ቤተክርስቲያን ዳገቱን ከወጡ በኋላ የኦሜጋ ዋና ፀሐፊ መኖሪያ የነበረው አጠገብ የሚገኝ ትልቅ ቤት ነው:: ያቡነ ቴዎፍሎስ እንዲያውም በጥቁር የተክህና ልብሳቸውና አድርገውት በነበረው ነጠላ ጫማ ተሰይተ፤ ይሄ ሁሉ ተገኝቶ ነው ወጥቶ የተቀበረው::

መንግሥቱ - የራስ አሥራተ ቤት ለዚህ ተግባር መዋሉን አሁን ገና ካንቺ አንደበት መስማቴ ነው:: ወኅኒ ቤት አለ:: ማሠሪያ አለ:: እዚያ የሚሄድበት ምክንያት አይገባኝም::የአሥራተ ቤት ለጤና ጥበቃ እንዲሰጥ ዶክተር ተፈራ ወንዴ ነው የጠየቀው:: ለዚህ መዋሉ ነው ትዝ የሚለኝ:: ኃይሌ ብቻ ነው ወይስ ሌሎቹም?

ገነት - ሌሎቹም ቅድም ስማቸውን ልጠቅስልዎት የሞከርኩት ሰዎች ሁሉ::

መንግሥቱ - እንግዲህ ይሄንን ሊያውቅ የሚችለው ተስፋዬ ወልደሥላሴ ነው::

ገነት - እርስዎ የሚያውቁት ኃይሌ ፊዳ በገበሬዎች መገደሉን ነው?

መንግሥቱ- አዎን:: መኢሶኖች ተያይዘው ጠፉ:: ሰው እንዲያውቅና እንዲይዛቸው ስማቸውንና ፎቷቸውን መበተን ያስፈልጋል ተባለ:: ተበተነ:: በየሄዱበት አቅጣጫ ያሉ ገበሬዎች በየቦታው ያዟቸው:: 'እንከላከላለን እያሉ ሲፍጨረጨሩ ተገደሉ' ተብሎ ነው የተነገረኝ:: ጠረፍ ድረስ የደረሱም ነበሩ:: ለምሳሌ፣ ዳንኤል በወለጋ በኩል ከነኃይሌ ጋር ነው የሄደው:: በሲዳሞ በኩል ደግሞ እነተረፈ፣ እነመስፍን ካሡ ናቸው የሄዱት:: የአመራር አካሉቹ ሁሉም አልተሰወሩም:: እነዶክተር ወርቁ፣ ዶክተር ዓለሙ አበበ፣ ዶክተር ያየህይራድ ቅጣውና ሌሎቹም የኢሠፓ አባላት ሆነው ከኛ ጋር እስከመጨረሻው ዘልቀዋል:: እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ከመኢሶን የሄዱት ኃይሌ ፊዳ፣ ከበደ መንገሻ፣ ዳንኤል ታደሰ፣ መስፍን ካሡና ንግሥት አዳነ ናቸው::

***ገነት - ይዋሹዎታል ማለት ነው እነተስፋዬ ወልደሥላሴ?***

***መንግስቱ*** - እነኃይሌ ፊዳ ብዙ ጠላት እንዳላቸው መዘንጋት የለበትም:: አንደኛ የምዕራቡ ዒላማ ናቸው:: ይሄንን የሶሻሊዝምን ጣጣና አብሮት የመጣውን ነገር ሁሉ ያመጡ እነሱ ናቸው እየተባሉ የሚጠላቸው ሞልቷል:: ኢሕአፓው ጠላታቸው ነው:: ከእኛም መሐል ቢሆን እነሽመልስም፣ እነዓለሙ አበበ፣ «ዘ ጋንግ ኦፍ ፎር» የሚባሉት ሁሉ አሉ:: በውነቱ የሠሩቱም ሥራ አስቀያሚ ነው:: ሌላው ግልፅ ነው:: የሶማሌያን ወረራ ፈርተው ነው::

መኢሶንና ኢሕአፓ የተለያዩ ናቸው:: በጣም! ኢሕአፓዎቹ ለሚያምኑበት ነገር ተዋጊዎች ናቸው:: ለዓላማቸው ይሞታሉ:: መኢሶኖቹ ደግሞ የፖለቲካ ሰዎች ነን ይላሉ እንጂ የትግል ስሜታቸው ደካማ ነው:: ግምጋሜያቸው ከመጀመሪያውም ቢሆን ትክክል አልነበረም:: በጣም የተማሩ፣ብዙ ያነበቡ ምሁራን አሉባቸው:: ለምሳሌ እኔ ለኃይሌ ፊዳ ትልቅ አክብሮት አለኝ:: ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም:: የሰከነ፣ ያነበበ፣ ጥሩ ማርክሲስት ነበረ:: ጥሩ ጭንቅላት ያለው፣ በጽሑፍ፣ በንግግር ቢባል ጥሩ የፓርቲው ምሰሶ ነበር:: በሁሉም መንገድ እንከን አይወጣለትም:: ከድርን ያየሽው እንደሆነ በኢኮኖሚክስ ዶክትሬት አለው:: የኢሉባቡር ልጅ ነው:: አብዮቱ በፈነዳ ጊዜ ሱዳን፣ ካርቱም ዩኒቨርስቲ ያስተምር ነበር:: ሱዳን የነበሩትን ሰዎች ያሰባሰበ እሱ ነው:: ጣጣ የማያበዛ፣ ተግባቢና ጥሩ ኮሚኒስት ነበር:: ሰናይ ልኬ እንደዚሁ ነበር:: እነኚህ ሁሉ በጣም በቅርብ የማውቃቸው፣ የምወዳቸውና የማከብራቸው ሰዎች ነበሩ:: ለወደፊቱ ላብዮቱ መጎልበት አለኝታ የሚሆኑ ናቸው ብዬ እተማመን ነበር:: ኃይሌ በሌሎቹ የተዋጠና የተወሰደ ይመስለኛል:: ከመካከላቸው ኖቶሪየስ የሆኑና ሥልጣን የጠማቸው በጣም ከ... ላቦች ነበሩባቸው:: ቀንድ የሚነክሱ ችኩሎች አብረዋቸው ነበሩ:: አሁን ይሄ ዳንኤል ቅዥቅዥ ያለ ነው:: ከበደ እንደዚሁ ነው:: ተረፈ እንደዚሁ ነው:: ሴትየዋ የለየላት እብድ ነች - ንግሥት አዳነ የምትባለው:: ቢንያም አዳነ የሚባለውን የኢሕአፓ አባል ወንድሟን ከቢሮው ጐትታ አውጥታ ያስገደለች እኮ ነች! የገዛ ወንድሟን አስገድላለች:: ታዲያ ይቺ ጤነኛ ነች? ልጁ ግብርና ሚኒስቴር ነበር የሚሠራው:: እኔን ራሴን ልትገለኝ ነበር:: ወደኋላ ላይ መኢሶን ‹ቀኝ መንገደኛ› እየተባለ በድርጅት ውስጥ በሥነ ጽሑፍ መወራወር ተጀምሮ ነበር:: እኔ ታዲያ በጋራ ሰብስቤ እንዲሁ በደፈናው እገሌ፣ እገሌ ሳልል «ተዉ!» ብዬ አነጋግሬያቸው ነበረ:: ‹እረ ሰውዬው ወደኛም ዞር ሳይል አይቀርም› ሲባባሉ፣ ‹መንግሥቱን መደምሰስ ካስፈለገ እኔ ግዳጁን መውሰድ እችላለሁ› ብላ ፈቃደኛ ሆና ትቀርባለች:: ‹ከፈለጋችሁ ቢሮው ገብቼ አጥፍቼው እጠፋለሁ› ትላቸዋለች:: ይሄንን እኛ ወዲያው ደረስንበትና ወደኔ ቢሮ ዝር እንዳትል አደረግን::



***ገነት - ማነው የነገረዎት?***

***መንግሥት*** - ‹ይቺን ሴትዮ ቢሮህ አታስገባ› አሉኝ:: እነሰናይ ልኬ ዱሮ አውሮፓ እያሉ ያውቋታል:: በደምብ ይተዋወቃሉ:: ደግሞ በኔ ጨክነው አይጨክኑም:: እኔን አምነው ነው ብዙዎቹ የመጡት:: እኔ ነኝ ያነጋገርኳቸው:: እኔ ነኝ የጠራኋቸው:: ‹አንድ ነገር እንጭ እን ቢል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሌለ ሌላው ወታደር ያርደናል ነው› የሚሉት:: አብረውኝ ያሉት ሚሊቴሪዎች ደግሞ ‹ሁሉንም አድ ፈጥፍጦ በብረት ቡጢ መምራት ሲቻል፣ እነዚህን ሰብስቦ ምንድነው የሚያደርገው?› እያሉ ከጀርባዬ ይሙኛል:: ይሄንን ሁሉ እነሰናይ ልኬ ያውቃሉ::

ከኤርትራ የተመለሰች የጀብሃ አባል የነበረች ማስታወቂያ ሚኒስቴር የምትሠራ ሣራ መኰንን የምትባል ነበረች:: ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ለሻዕቢያ አሳልፎ ሰጥቶ አስገደላት:: ታዲያ ያኔ ሣራ ከጀብሃ ከድታ ወደኛ ገና መምጣቷ ነው:: ንግሥት ሆዬ በሷ አካባቢም ወጣ ገባ ስትል ታይታለች:: እና ደህንነቶቹ ‹ይቺን ሴትዮ አናምናትም› ይላሉ::

እኔ ደግሞ ወደፊት ሴቶችን የማደራጀቱን ኃላፊነት ወስዳ እንድትሠራ አስቤ ነበር:: ሴቶችን በሚመለከት ብዙ ሥራ መሠራት ነበረበት:: እና እሷ በዚህ በኩል ትሯሯጣለች:: ‹እንደዚህ ብናደርግስ?› እያለች ሃሳብ ታቀርባለች:: አስተያየታችንን ትጠይቃለች:: ስለዚህ ሴቶችን ስለማደራጀት በቅርብ ስታናግረኝ እረዳት ነበር::: የምትፈልገውን ነገር አመቻችላታለሁ:: በዚያ መቀራረብ ተጠቅማ በመጨረሻ ላይ ያው እንዳልኩት እኔን ለመግደል እንደማትመለስ ሲታወቅ እንዳታቀርባት አሉኝ::

የመኢሶን አባላት በጠቅላላው የሚወነጀሉ አይደሉም::አብዛዎቹ፣ ዘጠና በመቶው ማለት ይቻላል፤ ከአብዮቱ ጋር እስከመጨረሻው የተራመዱና ብዙ አስተዋፅዖ ያደረጉ ናቸው:: ኢሠፓን ከመሠረቱት ነባር አባሎች ውስጥ አሁን በወያኔ እስር ቤት የሚማቅቁ የቀድሞ የመኢሶን አባላት ሞልተዋል::

ኃይሌ ፊዳ እዚያ ውስጥ መገኘቱ በጣም የሚያሳዝን ነው:: ሶማሌ በወረረን ጊዜ እንዴት ጥለው ይሄዳሉ በማለት የሕዝቡም ዒላማ በመሆናቸው በየገጠሩ እየተመቱ ወድቀዋል:: እኔ የማውቀው ይሄንን ነው:: አሥራተ ካሣ ቤት ለምንና እንዴት እንደተወሰዱ አላውቅም:: ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን መስማቴ ነው::

***ገነት - ዕውቁ ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ ከቤቱ እንደወጣ የት እንደደረሰ ሳይታወቅ እንዲሁ ቀርቷል:: ከጠፋ ከጥቂት ቀናት በኋላ መኪናው መንገድ ላይ ቆማ ተገኝታለች:: "ኦሮማይ" በተባለው መጽሐፉ የተነሳ እንደተገደለ ይገመታል:: ስለዚህ ምን ይላሉ?***

*መንግሥቱ* - በዓሉ ግርማን የማውቀው ከአብዮቱ በፊት ነበር:: እኔ ከአሜሪካን አገር እንደመጣሁ ወደሐረር ከመሄዴ በፊት ለጥቂት ቀናት አዲስ አበባ አንድ ሆቴል ውስጥ አርፌ ነበር:: ቦታው ትዝ ይለኛል:: ራስ መኰንን ድልድይ አጠገብ ወደሰባ ደረጃ የሚወስደውና ወደናዝሬት ትምህርት ቤት የሚታጠፈው መንገድ አለ:: ልክ እዚያ ጋ ዞር ስትይ በቆርቆሮ የተጋረደ ግቢ አለ:: ይሄ ግቢ በዚያን ጊዜ ሆቴል ነበር:: የሆቴሉ ባለቤት አሥራት የምትባል ሴት ነበረች:: የአበሻ ምግብ በጥሩ ሁኔታ ትሠራለች:: አሥር፣ አሥራ አምስት የሚሆኑ መኝታ ክፍሎች አሏት:: ወራቱ ክረምት ስለነበር አጎቴ ከሚኖርበት ከተማ መጥቶ እሱም እዚያ አርፏል:: አብረን ለመጫወት ተቀጣጥረን ነው ካሜሪካን በምመጣበት ቀን እዚያ መጥቶ የጠበቀኝ:: እንዳጋጣሚ ድምፃዊቷ ብዙነሽ በቀለም ከሥራ ስትመለስ ቡና ለመጠጣት እዚያ ጎራ ትላለች:: አንዳንድ የሚያውቋት ሰዎች ‹እባክሽን ዝፌኝልን› እያሉ ሲያስቸግሯት እሷም ስትዘፍንላቸው፣ ያንን ለማየት ሁላችንም እንሰበሰባለን:: እዚያ ቦታ ነው በዓሉ ግርማ፣ ብዙነሽ በቀለና እኔ የተዋወቅነው:: እሱም እዚያ ለመዝናናት ሲመጣ፣ በተለይም ብዙነሽ ስትጫወት ለማየት ማታ፣ማታ ስንሰበሰብ እንገናኛለን:: ቀንም ምሳ ላይ እንገናኛለን:: በዓሉ አሜሪካን አገር በጋዜጠኝነት የማስተርስ ዲግሪውን ይዞ መምጣቱ ነበረ:: ማስታወቂያ ሚነስቴር ውስጥ እንደሚሠራ አጫወተኝ::

አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ አዲስ አበባ ስመጣ እንደዚሁ ሰላምታና ሃሳብ ለመለዋወጥ ተገናኘን:: በበኩሌ ኃላፊነት የሚሰማው ሰው መሆኑን፣ ለአብዮቱ ያለውን አመለካከት ለማጥናት ሞከርኩ:: በዚህም ሰዎች ለሱ መልካም ግምት እንዳላቸው ተረዳሁ::

ከዚያ ጥቂት ቀደም ሲል እኔ ወደሐረር እንደሄድኩኝ የመንግሥትና የተማሪዎች ቅራኔ ተባብሶ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በጠቅላላ በተማሪዎቹ ላይ ዘምቶ ከፍተኛ ፀረ-ተማሪ ፕሮፓጋንዳ የሚካሄድበት ወቅት ነበር:: በዚያን ጊዜ በዓሉ ግርማ እንደሌሎቹ የመንግሥት ጋዜጠኞች ይሄንን አራማጅ ነበረ:: ለነገሩ ያኔ በግል የተያዘ ወይም ነፃ የነበረ ጋዜጣ ወይም ሬዲዮ አልነበረም:: እና ይሄን የሚያስታውሱ ሰዎች ‹በዓሉ ግርማ ኀበዝ ጋዜጠኛ ይሁን እንጂ የፊውዳሉን ሥርዓት ፕሮፓጋንዳ በማራመድ ለመንግሥት መሣሪያ ሆኖ እንዲህ፣እንዲህ እያለ ሲፅፍ የነበረ ሰው ነው:: የአብዮቱ ደጋፊ ሊሆን አይችልም› የሚል አስተያየት ይሰነዝሩ ነበር:: «እሱ ጋዜጠኛ ነው:: ጋዜጣው የመንግሥት ነው:: የታዘዘውን ካልሠራ ወይ ሥራውን በፈቃዱ ለቆ መሄድ አለበት እንጂ እሱ የሚያምንበትን ብቻ በሐቅ ለመፃፍ ነፃነት የለውም:: በዚህ መውቀስ አይቻልም» ተባለ::



መቼም ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ነበር:: በኋላም ቢሆን ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሁሌ ችግር ነው:: ተጀምሮ እስኪጨረስ:: መንግሥት እንደሚሰጠው በጀት፣ በአመራሩ ጥንካሬ፣ በመሣሪያም፣ በሰው ዓይነትም፣ በውነቱ የተሟላ ሆኖ አያውቅም:: ከሚኒስትሮቹ ጀምሮ ታች ድረስ ችግር አለ:: እና በመጀመሪያዎቹ ወራት ሰው ለማግኘት ተቸግረን ነበረ:: የቴሌቪዥን ኃላፊ ማን ይሁን? የሬዲዮስ? እያልን እንዲሁ ስናገላብጥ ነው የከረምነው:: ነባሮቹን፣ የዱሮዎቹን ያየሽ እንደሆነ አስ...ቸጋሪዎች፣ ሞገደኞች ናቸው:: በመጠጥ የነበዙ ናቸው::

በዓሉን ስንመርጠው የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ያኔ ጓድ ግርማ ነበር:: እሱ ለአብዮቱ ያለው ታማኝነት አስተማማኝ ነው:: ጨዋና ከሰው ጋር ተግባብቶ መሥራት የሚችል ሰው ነው:: ፖለቲካውን በተመለከተ ሚኒስትሩ ይቆጣጠራል:: በዓሉ ደግሞ በሱ ሥር ሆኖ በሙያው ይረዳል በማለት ሾምነው::

በዚህ ዓይነት ሲሠራ ከቆየ በኋላ ችግር የመጣው በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ነበር:: ከዚያ በፊት በምሥራቁ ዘመቻ ጊዜ በሶማሊያ ላይ ያን የመሰለ አኩሪ ድል ስንቀዳጅ በሚገባ ለታሪክ ተመዝግቦ እንዲቆይ የተቀነባበረ ሥራ ስላልተሰራ እንቆጭ ነበር:: በዚያ ወቅት ተወጥረን ስለነበረና በደንብ ስላልተደራጀን ያመለጠን አጋጣሚ ነበር:: በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ይሄ እንዳይደገም በዓሉ ግርማ በሽመልስ ማዘንጊያ ሥር ሆኖ ጋዜጠኞችን እንዲያስተባብርና የፕሮፓጋንዳውን ሥራ እንዲያቀናጅ አሥመራ ከኛ ጋር ተንቀሳቀሰ:: የተሰጠውን የሥራ መመሪያ በእጁ ጽፌ ያረቀቅሁት ራሴ ነኝ:: ይሄውም ምንድነው የመንግሥት ፖሊሲና የፖለቲካውን አካሄድ በተመለከተ ከሽመልስ ማዘንጊያ መመሪያ እየተቀበለ እንዲሠራ፣ ጋዜጠኞቹን እንዲያሰማራ፣ ለነሱ የሚያስፈልጋቸውን የሎጂስቲክ፣ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ እየተከታተለ እንዲሰጥ የሚል ነው:: የኤርትራው አስተዳደር ደግሞ በክልሉ በኩል የፕሮፓጋንዳ ሥራ የመሥራት ኃላፊነት ስላለበት ከነሱ ጋር በቅንጅት መሥራትም ይጠበቅበት ነበር:: የነዚህ ሁሉ ሥራ ተካብቶና በአንድነት ተጠርዞ ሲያበቃ ለፓርቲው እንዲቀርብ፣ ማለትም ባንድ በኩል ያብዮቱን ታሪክ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኤርትራ የተደረገውን ትግል እንዲሁም ደግሞ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ምን ይመስል ነበር የሚለውን መዝግቦ እንዲያቆይ ነው::

***ገነት - ስለዚህ እርስዎ ቀይ ኮከብን በተመለከተ በዓሉ ግርማን መጽሐፍ ፃፍ ብለውታል የሚባለው እውነት ነዋ!?***

*መንግሥቱ* - አላልኩትም:: እሱ የፕሮፓጋንዳውና የሥነ ጽሑፍ ዘመቻው አካል ነው እንጂ በግሉ እንዲፅፍ የታዘዘው አንድም ነገር የለም:: ለቀይ ኮከብ ዘመቻ ብዙ ሰው ነው ይዤ የሄድኩት:: ከበዓሉ ጋር የቅርብ የሥራ ግንኙነት የነበራቸው ዳዊት ወልደጊዮርጊስ፣ ሽመልስ ማዘንጊያ፣ የጦር ሃይሎች የፖለቲካ መምሪያ ምክትል

የነበረው ፊለቀ የሚባለውና ሌሎችም ነበሩ። የሥነ ጽሑፍና የደራሲዎችም ቡድን ነበረ። እነዚህ ሁሉ የሚያሰባስቡት የዚያ ዘመቻ ውጤት መረጃ፣ ከፖሊሱ ክፍል የሚመጣ መረጃ አለ። የሕዝቡን አስተያየትና አዝማሚያ የሚያሰባስብ አለ። በሚሊተሪው ፖለቲካ ክፍል የሚቀርብ ዘገባ አለ። ካመራር፣ ከሰሜን ዘመቻ ደግሞ የጦሩ ስልት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የተገኘው ውጤት ወይም ውድቀት ተጠናቅሮ ተሰብስቧል። ዓላማው ይሄ ሁሉ በጋራ ተጣምሮ ቀርቦ ለታሪክ እንዲቆይ ማድረግ ነው።

በዓሉ ግርማ ይሄንን በሚያስደስት ሁኔታ በሚገባ ሠርቶ አቀረበ። በሁለት፣ በሦስት ኮፒ አሠርቶ አንዱን ለኔ አቀረበ። ለፓርቲውና ለርዕዮተ ዓለም መምሪያው ሰጠ። ምናልባትም ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ሳያቀርብ አይቀርም። ለራሱም ኮፒ ይኖረዋል። በጣም ጥሩ። እስከዚህ ድረስ ምንም ችግር አልነበረም።

አሁን ይሄን ሁሉ ይይዝና «ኦሮማይ»ን ፃፈ። መጽሐፉን ጽፎ ሲጨርስ ሊያሳትም ይሄዳል። ይሄንን የተመለከቱ ‹ለርዕዮተ ዓለም መምሪያው አሳይተህ ከዚያ ፈቃድ ሳታገኝማ ይሄን እንዴት ታሳትማለህ? ወታደራዊ ጉዳይ አለበት። የፖለቲካ ጉዳይ አለበት። ትንሽ አስቸጋሪ ይመስላል› ይሉታል። ኮፒውን ይዞ ፍቅረሥላሴ ጋ ይሄዳል።

*ገነት - የርዕዮተ ዓለም ኃላፊው ሽመልስ ማዘንጊያ አይደሉም እንዴ?*

***መንግሥቱ*** - ነው። ከሱ በላይ ፍቅረሥላሴ ነው። በዓሉ በቀጥታ እሱ ጋ ሄዶ እንዲያይለት ይሰጠዋል።አሁን ነገሮችን ወደኋላ ተመልሼ ሳገናዝብ የዚያን ጊዜ ፍቅረሥላሴ በሥራው ላይ ትንሽ ዳተኛነት ይታይበት ነበር። ‹ምን ሆኖ ነው? ስንፍና ነው ወይስ ምንድነው?› ስል ለካስ ውስጥ፣ ውስጡን በሕመም ይሰቃይ ኖሯል። በኋላ ውጪ ሄዶ ታክሞ ከመጣ በኋላ ነው የዳነው። እና በዚያ ወቅት በዓሉ የሰጠውን የኦሮማይ ኮፒ አላነበበውም። ቀን ሥራ ይበዛበታል። ማታ እቤቱ ሲገባ ስለሚደክመው፣ ሕመሙም ስላለ ዝም ብሎ ራስጌው አስቀምጦት ሳያነበው ቀርቷል። በኋላ ቆይቶ ኩራዝ ማተሚያ ቤት ላለው ቦርድ ይልከዋል።

ይህ ቦርድ ከዩኒቨርሲቲና ከሌላም በሙያው ችሎታ ያላቸው ምሁራን ተመርጠው በሥነ ጽሑፍ ወጥ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን ሠርተው ለሚያመጡ ሰዎች ድጋፍ ለመስጠት የተቋቋመ ነበር።

*ገነት - ሳንሱር የሚያደርግ ማለት ነው?*

***መንግሥቱ*** - የመጽሐፉን ይዘት አይቶ ቴክኒካል ድጋፍ የሚሰጥ ነው። የቋንቋውን ውበትና ጥራት ይመለከታል። የመከላከልና የማገድ ነገር ሳይሆን፣ የሚታረም፣ የሚስተካከል ካለ እንዲሻሻል ምክር መስጠት ነው። ከዚያም ሌላ ቦርዱና ኩራዝ ማተሚያ ቤቱ እየተባበሩ ደራሲያን በቀለለ ገንዘብ ማሳተም እንዲችሉ ድጋፍ የሚሰጥ ነው።



በዚህ በመበረታታት በርካታ ደራሲያን ባነስተኛ ዋጋ ሥራዎቻቸውን ለሕዝብ በብዛት አቅርበዋል። መጽሐፍት በብዛት ተሰራጭተዋል።

ኩራዝ ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ ማተሚያ ቤት አልነበረም። ይሁን እንጂ «ራሱን ችሎ ለመንቀሳቀስ ወጪውን መሸፈን መቻል ስላለበት በመጠኑም ቢሆን የንግድ ባሕሪ የተከተለ አንድ የሕትመት ስርጭት ተቋም እንፍጠር፣ በቴክኒክ በኩል በምሁራን እንደግፈው» ብለን ያቋቋምነው ድርጅት ነው።

ፍቅረሥላሴ እንግዲህ ለዚህ ቦርድ ነው የበዓሉን ሥራ የላከው። ከፅሑፉ ጋር አያይዞ የላከው መመሪያ ግልጽ አልነበረም። ‹እኔ ለማንበብ ጊዜ አላገኘሁምና እናንተ አንብባችሁ ያለውን እንከን አውጡ› አይልም። በደፈናው ‹አንብቡና ውሳኔ ስጡት› ይላል። እነሱ ደግሞ በወጣላቸው መመሪያ መሠረት ሥራቸው ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት ነው። ይቺን እዚጋ ብታርማት፣ ይቺን ብታስተካክላት ብለው በጣም ጥቃቅን ነገር አርመው ይሰጡታል። በዓሉ ወስዶ ያሳትማል።

እዚህ ላይ ጥፋቱ የማነው? ፍቅረሥላሴ አላነበበውም። የቦርዱ አባላት ‹ከሳቸው (ከፍቅረሥላሴ) ጋ ከመጣ› በማለት ፖለቲካዊ ፋይዳውን አላገናዘቡም። ሥራቸውም አይደለም። በዓሉ ለሚመለከተው ሁሉ አሳይቷል። አልፎልኛል ብሎ አሳተመ። ተሰራጨ።

የሆነ ሰው መጣና ‹የቀይ ኮከብ ዘመቻን ታሪክ በዓሉ ግርማ ጽፏል። ትንሽ አጨቃጫቂ ይመስላል› አለኝ። «መጽሐፉን አምጡልኝ» አልኩ። አንድ ሳምንት ፈጀብኝ። ማታ፣ ማታ ነው የማነበው። ጭቅጭቅ እንዳስነሳ ስለተነገረኝ በደንብ አድርጌ አንብቤ ጨረስኩት።

እኔን እንዳውም አመሰገነኝ እንጂ አልነቀፈኝም። ሌሎች ብዙ የተበሳጩ ሰዎች ነበሩ። ምክንያታቸው ይለያያል። የሚገርመው ነገር የሚበልጡት የተበሳጩት በይዘቱ ሳይሆን፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች ያሰባሰባቸው እሱ አይደለም በሚል ነው። ብዙ ጋዜጠኞች በጦር ሜዳ ጥይት እየዘነበባቸው የቃረሙት መረጃ ነው። ከሲቪሉ፣ ከወታደሩ፣ ከፓርቲው ከያለበት ተውጣጥቶ የቀረበ ነው። ‹ይሄንን በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን ነገር አቀናብሮ መጽሐፍ አድርጎ እንደራሱ ፈጠራ ሊያቀርብ አይችልም› ብለው ነው የከሰሱት።ሌሎችን በመልካቸው፣ በቁመናቸው፣ በባሕርያቸው ተሳልቆባቸዋል። እንግዲህ ደራሲዎች ጽሑፋቸው ተነባቢ እንዲሆን ወዝ ለመስጠት የሚሰጡት ቅባት፣ የሚቀቡት ቀለም የተለያየ ነው። እንደሰዎቹ አመለካከት። እሱ እንደቅባት የተጠቀመባቸው ሰዎች የሚያሳድሩትን ስሜት አላጤነውም። ወይም ስቀው የሚያልፉት መስሎት እንደሆነ እንጃ። ከሰዎቹ ጋር በነበረው ቅርበትና ከጓደኝነት አንፃር ለቀልድ ያደረገው ሊሆን ይችላል። የኛ ሰው ይሄን ለመሰለ ቀልድ የተዘጋጀ አይደለም። ባለጉዳዮቹ ችላ ቢሉት እንኳን ሌላው ሰው ተረቡን ሁሉ የምር አድርጎ መውሰዱ አይቀርም።

እነአማኑኤል፣ እነፈለቀ፣ እነፍስሐ ገዳ፣ እነፍስሐ ደስታ ... ማን ቀረ:: እነዚህን ሁሉ ወርፏል:: ተስፋዬ ወልደሥላሴንም ደህና አድርጎ ጠራርቦታል (እየሳቁ):: እኔን ምንድነው ያለኝ? ‹ሲቆጡ፣ ዓይናቸው ሲደፈርስ አንበሳ ነው ነብር ይመስላሉ› ነው ያለው? (እየሳቁ) ስለኔ አንድም ቦታ ላይ የመንቀፍ ነገር አልፃፈም:: ለኔ ሳይሆን ለሌሎቹ አላሳቃቸውም:: ብዙ ሰው አገንግኗል:: በተለይ ተስፋዬ ወልደሥላሴ:: ጥያቄው አሁን በዓሉ ይሄን ሲፅፍ ዓላማው ምንድነው? ለምን ግብ ነው የፃፈው? ይሄ አጠያያቂ ነው::

መጽሐፉን ካነበብኩ በኋላ መጀመሪያ ፍቅረሥላሴን አስጠራሁ:: ፍቅረሥላሴ በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ለመዝጊያው ሥነሥርዓት እንኳን አሥመራ አልተገኘም:: ምክንያቱም ከኔ ቀጥሎ ሁለተኛው ሰው እሱ ስለሆነ ሁለታችንም ባንድ ጊዜ አዲስ አበባን መልቀቅ የለብንም:: ከሁለት አንዳችን አዲስ አበባ መሆን አለብን:: ሆኖም ኤርትራ እያለን የተደረገውን ያውቃል:: የፕሮፓጋንዳ ክፍሉ የተሰጠውን ኃላፊነት ያውቃል:: መመሪያውን ያውቃል:: «ይሄ መጽሐፍ እንዴት ታተመ? ከመታተሙ በፊት አይተኸዋል ወይ?» አልኩት:: ‹አላነበብኩትም:: ለቦርዱ ነው ያስተላለፍኩት› አለኝ:: ‹ፋታ ስላላገኘሁ፣ ጊዜ ስለሌለኝ እናንተ ተመልከቱት› ነው ያልኩት ነው የሚለው:: አብሮ የላከውን ማስታወሻ አሳየኝ:: በደንብ የተፃፈ ደብዳቤ ሳይሆን፣ አነስተኛ ማስታወሻ ነገር ጽፎ እዚያው ኮፒው ላይ አያይዞ ነው የላከላቸው::

የቦርዱ አባላት ደግሞ ከፍቅረሥላሴ ቢሮ ሲመጣላቸው ያው የተለመደው ቴክኒካል ድጋፍ ስጡት የሚል ነው በማለት ነው የተገነዘቡት:: የይታተም፣ አይታተም ጥያቄ ሊሆን ይችላል ብለው አልወሰዱትም:: የቦርዱን ሊቀመንበር አስጠርቼ ስጠይቀው የነገረኝ ይሄንኑ ነው:: ‹እኛ ቴክኒካል ጥራቱን ነው ያየነው:: ይሄንንም ከራሱ ከበዓሉ ጋር ሆነን አብረን ሠርተን ሠጥተነዋል:: መጽሐፍ ይታተም አይታተም ብለን የመወሰን ኃላፊነት አልተሰጠንም:: ቦርዱም የተቋቋመበት ዓላማ ይሄ አይደለም› ብሎ መልስ ሰጠ:: በነሱ ላይ ለመፍረድ አስቸጋሪ ነው::

ይሄን በመሰለ ድንግዝግዝ ያለ ሁኔታ ነው «ኦሮማይ» የታተመው:: ዋናው ነገር ማንም ሰው ወደኋላ የሚመጣውን ነገር ይሆናል ብሎ እንዳላሰበውና እንዳላጤነው ግልፅ ነው::

ከዚያ በኋላ በዓሉን ራሱን አስጠራሁት:: «የቀይ ኮከብ ዘመቻ የፕሮፓጋንዳው ክፍል ሁለተኛ አመራር ሰጪ ሰው ሆነህ አሥመራ ስትሄድ አንተ ምንድን ነበር የገባህ? ከተራ ሲቪል ሠራተኛ እስከ አመራሩ፣ ከተራ ወታደር እስከ ጄኔራሎቹ ድረስ በተለያየ ሙያ በብዙ ሺ የሚቆጠር ሠራዊት ተሰልፎ አንድ ግብ ለመምታት ተረባርቦ የተሠራ ሥራ መሆኑን ታውቃለህ:: የብዙ ሰው ደም፣ የብዙ ሰው ላብ፣ የብዙ ሰው ትግል ውጤት ነው:: ያንተ የብቻህ የሥራ ውጤት አይደለም:: ይሄ የኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ አካል ስለሆነ ይሄንን



አቀናጅተህ ለታሪክ እንዲቀመጥ ማድረግ ነው እንጂ አንተ በስምህ ባለቤት ሆነህ እንደራስህ ሥራ አገጣጥመህ እንዴት በመጽሐፍ ልታወጣ ቻልክ?» አልኩት:: ‹ይሄ አልገባኝም ነበር:: እንደዚህ ይሆናል ብዬም አላሰብኩ:: አሁን ነገሩን ሳሰላስለው ምን ያህል ስሕተት እንደሰራሁ ተረድቻለሁ› አለ:: አመነ:: በውነቱ የተሠራው ስሕተት እኮ ቀላል አይደለም:: መጽሐፉ ታትሞ ለገበያ ውሏል::

አንድ በአንድ የስሕተቱን ከባድነት ነገርኩት:: «አንደኛ የአገርን ታሪክ የራስህ ፈጠራ አድርገህ ማቅረብህ ነው:: ወደመጽሐፉ ይዘት ስንገባ ደግሞ ብዙ ጉድ አለ:: የብዙዎች ደም የፈሰሰበት፣ ስንቶች እየተዋደቁ ያሉበት ገና ሞት ሽረታችንም ያለየለት፣ሂደቱም ያላለቀበት ሁኔታ ውስጥ እያለን ያን ያህል ፌዝ፣ መቀለድና መሳለቅ፣ ያስፈልጋል እንዴ? ከሴቶቹ ጋር መዋዛቱ፣ መዳራቱ፣ መሳከሩ፣ ያ ሁሉ ነገር ከያዝነው ትግል ጋር አብሮ ይሄዳል እንዴ? ዘመቻው እንዲህ ቀልድ ኖሯል ማለት ነው? የሄድነው ከሴት ለመዳራትና መጠጥ ለመጠጣት ነው? በኤርትራ ለአንድነታችን ደም እየፈሰሰ፣ አጥንት እየተከሰከሰ ያለበትን ሁኔታ እንዴት እንደዚህ ዓይነት ሥዕል ሰጥተህ ታቀርበዋለህ? እንግዲህ አንተ አልተኛህ፣ አልሰከርክ:: ከሕሊናህ ጋር መምከር እንዴት ተሳነህ? ሁላችንንም እኮ ችግር ውስጥ አገባኸን:: መጽሐፉ ታትሞ ተሰራጭቷል:: አሁን ምንድነው የሚደረገው?» አልኩት::

በሙሉ ስሕተቱን አመነ::‹አጥፍቻለሁኝ::እርስዎ እንዳሉት አንዴ ታትሟል:: የሚወሰነብኝን ቅጣት እቀበላለሁ:: ጥፋተኛ ነኝ› አለ::

ሰውዬው አብዮት ለመቀልበስ ወይም ሆን ብሎ ሰው ለመጉዳት ብሎ እንዳላደረገው መረዳት ችያለሁ:: ምናልባት ለራሱ ዝናና ስም ለማግኘት ከመነጨ ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር ያንን በመጻፉ የሚመታው የፖለቲካ ግብ የለም:: ባንፃሩ ደግሞ ያስነሳው አቧራ ቀላል አይደለም:: ምን እንደማደርግ ቸገረኝ:: ነገርን ካመዛዘንኩ በኋላ «ስሕተት መሥራትህን አምነሃል:: አብዮቱን ለመጉዳት የሠራኸው አለመሆኑን እረዳለሁ:: ይሁን እንጂ አሁን ባለህበት ኃላፊነት ቦታ የምትቆይበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ብዙ ጠላት ነው የገዛኸው:: እኛንም ውስብስብ ችግር ውስጥ ነው የጣልከን:: ለማንኛውም አሁን ወደቤትህ ሂድ» ብዬ አሰናበትኩት:: ከዚያ በኋላ ከኃላፊነቱ እንደተነሳ የሚገልፅ ደብዳቤ ተፃፈለት:: ከኃላፊነቱ ተነሳ:: ከሥራ ግን አልተባረረም:: ከዚያ በኋላ እሱ ራሱ ‹በሙያዬ በግሌ ብሠራ ይሻለኛል› አለ:: «ፍላጎትህ ይሄ ከሆነ በግል ሥራ ብትሠማራ የሚከለክልህ የለም» ተባለ:: ‹እንደሱ ይሻለኛል› አለ:: በዚህ ዓይነት በሱና በኛ መካከል የነበረው የሥራ ግንኙነት ተቋረጠ::

ትንሽ ጊዜ ቆይቶ ‹በዓሉ ግርማ ጠፋ› የሚል ነገር ተነገረኝ:: ተስፋዬ ወልደሥላሴ መጥቶ ‹በዓሉ ጠፋ› አለኝ:: እኔ ከአገር ጠፍቶ የሄደ ነው የመሰለኝ:: «ወዴት ነው የሄደው?» ስል፣ ‹እኛ አናውቅም::

ብቻ ጠፍቷል› አሉኝ:: መሄዱ አልገረመኝም:: አልፈረድኩበትምም:: ምክንያቱም ከብዙ የፓርቲ አባላትና ባለሥልጣኖች ጋር ተጣልቷል:: በዚህ ሁኔታ በግል እየሠራ ለመኖርስ ይችላል ወይ? ከእንግዲህ እዚህ አገር ቦታ የለኝም:: ከዚህ ወጥቼ ገለል ብዬ ልኑር ቢል አያስደንቀንም:: ስለዚህ ለምን ሄደ አላልኩም:: በዚህ ነገሩ ቆመ::

እኔ ግን እጠብቅ ነበር:: ከሄደ አሜሪካን ይሆናል የሚሄደው:: የትም ቢሄድ ደግሞ ስለኛ መናገሩ አይቀርም:: ባንዱ ሬድዮ ጣቢያ ሲናገር እንሰማዋለን ወይ አንድ ነገር ይጽፋል የሚል ግምት ነበረኝ:: ባይ፣ ባይ ምንም ወሬ የለም:: ምንም አይሰማም:: በመካከሉ ጭምጭምታ ነገር ደረሰኝ:: ‹በዓሉ የት እንደሄደ አይታወቅም:: ቤተሰቦቹም ሊያገኙት አልቻሉም› የሚል ነገር መጣልኝ:: ቀጥሎ ደግሞ ውባንቿ ራሷ ስምታ ‹እረ እንደዚህ እየተባለ በከተማው ይወራል› አለችኝ::

ሰውዬው የት ሊገባ ይችላል? ጨረቃ ላይ አይሄድ:: ከጠፋ አንድ ቦታ መድረስ አለበት:: ሌላው ቢቀር ለቤተሰቡ ድምፁን ሊያሰማ ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው? አልኩና ተስፋዬ ወልደሥላሴን አስጠራሁ:: «ይሄ ሰውዬ ጠፋ ነው ያላችሁት አይደለ? መጥፋቱን ያወቅሽው እንዴት ነው? መቼ ነው ከዚህ የሄደው?» ስለው፣ ‹መጥፋቱንማ ከቤቱ ባለመኖሩ ከከተማ በመሰወሩ ነው ያወቅነው:: ቤተሰቦቹ እየፈለጉት ነው:: የትና መቼ እንደሄደ ግን እኛ አናውቅም› አለኝ:: ይሄንን ለመቀበል አቃተኝ:: እሱ በደህናው ሆኖ ተደብቆ ባለቤቱ እሱን ፍለጋ በየቦታው ትንከራተታለች? ለባለቤቱ፣ ለልጆቹ እናት እዚህ ቦታ ነኝ ሳይል፣ ምንም ነገር ሳይናገርና ሳያሳውቅ ይሄን ያህል ጊዜ ከቤት ወጥቶ ጠፋ ማለት አንድ ነገር ደርሶበታል ማለት ነው:: ይሄን በእርግጠኝነት ለመናገር ደግሞ የጨበጥኩት ማስረጃ የለም::

«ተስፋዬ! ይሄ የምትለው ነገር እውነት ነው?»

‹አዎን፤ እውነት ነው::›

«እሺ፤ ወደፊት እንደርስበታለን» ብዬው ከቢሮዬ ወጣ::

ብዙ ተጠበቀ:: አንድም ‹በዓሉን አየሁ› የሚል ሰው የለም:: በየትም አካባቢ ዱካው ጠፋ:: አሁን ‹ተመቷል› የሚል ነገር ተሰማ:: በእርግጥ ሁሉም ጥርሳቸውን ነክሰውበታል:: ለሱ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ነው:: ሁ...ሉም:: እነዚህ ሰዎች ከኛ ጀርባ በዚህ ሰውዬ ላይ ርምጃ ሳይወስዱበት አይቀሩም:: መቼም አደረግን ብለው አያምኑም:: በምን ዓይነት ማረጋገጥ ይቻላል? ስል ስዊድን አገር አምባሳደራችን የነበሩት ጄኔራል ታዬ ጥላሁን ከድተው ሄዱ:: እንደተለመደው ጥለው የሄዱበትን ምክንያት በጋዜጠኞች ሲጠየቁ ዋና ነገር አድርገው ያቀረቡት የበዓሉ ግርማን መገደል ነበር:: በራሴ መንገድ ለማጣራት ሞከርኩ:: የምጠይቃቸው ሁሉ ‹ሰውዬው ብዙ ጠላቶች አፍርቷል:: በትክክል ስለሆነው ነገር የምናውቀው ነገር የለም:: የየራሳችን ጥርጣሬ አለን:: የተጨበጠ መረጃ ግን የለንም› የሚል መልስ ነው



የሚሰጡኝ:: ምን ማድረግ ይቻላል? ከዚያ በኋላ በከተማ ውስጥም ‹በዓሉ ተገድሏል› በማለት መወራቱን ቀጠለ:: ሕይወትም ቀጠለ:: ሥራም ቀጠለ::

አሁን ከምንወነጀልበት አንዱ የበዓሉ ሞት ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በግል ቂምም ሆነ በፖለቲካው መንግሥት ሳያውቀው ሕይወታቸውን የጠፉ ሰዎች ሞልተዋል:: በዓሉ ግርማ ከነሱ አንዱ ነው::

# የጦሩ መሸነፍ

*ገነት - በሥልጣን ዘመንዎ ካጋጠሙዎት ችግሮች ዋነኛው ጦርነቱ ነው ማለት ይቻላል::አንድም ጊዜ አቋርጦ አያውቅም:: ይህም በሰው ሕይወት ላይ ካደረሰው እልቂት በተጨማሪ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የደረሰው ውድቀት አንድና ሁለት የለውም:: አገሪቱን ከድህነት ለማውጣት በተደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳደረሰ ግልፅ ነው:: በመጨረሻም በአሸናፊነት አልወጡም:: በእርስዎ አስተያየት ሠራዊቱ ሲሸነፍ የበቃው በምን ምክንያት ነው?*

***መንግሥቱ-*** ‹በጦርነት ለምን ተሸነፋችሁ?!› ብሎ ማለት ቀላል ነገር ነው:: እዚያ ቦታው ላይ ተገኝቶ ጦርነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማየትና ማሸነፍ ደግሞ ሌላ ነገር ነው:: ጨው ውሃ እየጠጡ፣ አሸዋ ላይ እየተኙ፣ ድንጋይ እየተንተራሱ፣ ቆስለው፣ ደምተው፣ ጦርነትን ፊት ለፊት የተጋፈጡ ብቻ ናቸው ቀላል ጨዋታ አለመሆኑን የሚረዱት:: በታሪክ አጋጣሚ ወደሥልጣን ከመጣን ጀምሮ ባላቋረጠ ጦርነት ውስጥ ተዘፍቀን ቆይተናል:: ይሄ የሆነው ጦረኛ በመሆናችን ሳይሆን ለሠላም ያደረግነው ጥረት ቀደም ብዬ እንዳልኩት ሳይሳካ በመቅረቱ ነው:: ከዚያ በኋላ ጦርነቱን መቀጠልና የሃገራችንን አንድነት ለመጠበቅ መዋጋት ነበረብን:: ለምን አላሸነፍንም? መልሱ ቀላል አይደለም:: ነገሩን ከሥሩ ጀምሮ መረዳት ያስፈልጋል::

«ጦርነቱ» ብለን ስንል ምናልባት ብዙ ሰው የሚገነዘበው መደበኛ በሆነው በአብዮት ፀሮችና በሕዝቡ፣ በገንጣዮችና በሠራዊቱ መካከል የተደረገውን ጦርነት ብቻ ይመስለኛል:: ጦርነቱ የተለያየ መልክና ፈርጅ ነበረው::

ባንድ በኩል ከውጪ ኃይሎች፣ ማለትም ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳሳረ ነው:: እነኚህ ለዘመናት ለኢትዮጵያ ውድቀትና ድክመት ያለማቋረጥ ሲጥሩ የነበሩ ኃይሎች ሁኔታ በታሪካችን የታወቀ ነው::ለዘመናት ሲያደርጉት የነበረው ጥረት በኢትዮጵያውያን አልበገሬነት ባለመሳካቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ ንቅናቄና ሥር ነቀል የሆነ ማህበራዊ ለውጥ በሚከናወንበት ጊዜ ከዚህ የተሻለ ጊዜ አይገኝም ብለው ሁሉም የተሰባሰቡበት ጊዜ ነበር:: የነሱን ፍላጎትና ጦርነት በእጅ አዙር ተወክለው ወይም